በዶ/ር ቶማስ ሞካይቲስ

# ሰውዬው ማን ነው?



የኦሳማ ቢን ላደን ታሪክ
(አወዛጋቢው የሞቱ ሂደት የተካተተበት)

(ትርጉም፡- መሐመድ ኢብራሂም ሲራጅ)

# ሰውዬው
## ማን ነው?

### የኦሳማ ቢን ላደን
### እውነተኛ የሕይወት ታሪክ
### (አወዛጋቢው የሞቱ ሂደት የተካተተበት)

*Osama Bin Laden-A biography*

በዶክተር ቶማስ ሞካይቲስ

ትርጉም፡- መሐመድ ኢብራሂም ሲራጅ

© 2003 ዓ.ም.
መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው።

የመጀመሪያ ዕትም፡- ሰኔ 2003 ዓ.ም.

**ዋና አከፋፋይ**
ዩኒቲ መጻሐፍት መደብር
አድራሻ፡- ከሰም ሆቴል ወደ ሾላ በሚወስደው መንገድ
100 ሜትር ያህል ገባ ብሎ
ስልክ፡- 0912 02 87 94
፡- 0911 66 99 46
የመ.ሳ.ቁ.፡- 4143
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

# ስለ ደራሲው

ዶክተር ቶማስ ሞካይቲስ በቺካጎ ኢሊኖስ ዲፖል ዩኒቨርሲቲ የታሪክ ፕሮፌሰር ነው።የመጀመሪያ ዲግሪዉን በታሪክ ከአሌጋኒ ኮሌጅ፣የማስትሬትና የዶክትሬት ዲግሪዉን ደግሞ ከዊስኮንሲን ዩኒቨርሲቲ አግኝቷል። የመጀመሪያ መጽሐፉ *British Counterinsurgency, 1919–1960* (Macmillan, 1990) በእንግሊዝ ወታደራዊ ታሪክ የምርጥነት ቴምፕላር ሜዳሊያ አሸናፊ ኾኖለታል። በቅርቡ ካሳተማቸውና ተወዳጅነትን ካተረፉለት መጻሕፍት መካከል *The "New" Terrorism: Myths and Reality* (Praeger, 2008) ፣እና *Iraq and the Challenge of Counterinsurgency* (Praeger, 2008) ተጠቃሽ ናቸው።

# ማውጫ

**አርእስት** **ገጽ**


በኦሳማ ቢን ላደን ሕይወት ውስጥ
የኾኑ ዐብይ ክስተቶች ..................................V-XI

ምዕራፍ አንድ
ሰውዬው! ኦሳማ ቢን ላደን ---------------------------12

ምዕራፍ ሁለት
ኦሳማ ቢን ላደን ስለዓለም ያለው አመለካከት--------------------- 36

ምዕራፍ ሶስት
ኦሳማ በአፍጋኒስታን ------------------------------ 48

ምዕራፍ አራት
አል ቃኢዳ ---------------------------------------68

ምዕራፍ አምስት
ታላቁን ሰይጣን መፋለም ----------------------------87

ምዕራፍ ስድስት
ቢን ላደን እና አል ቃኢዳ ከ9/11 በኋላ -----------------121

ቅጥያ
አወዛጋቢው ቢን ላደንን የመግደል ዘመቻ ---------------- 205

ኦሳማ ቢን ላደንን በፎቶ ---------------------------214

# በኦሳማ ቢን ላደን ሕይወት ውስጥ የኾኑ ዐብይ ክስተቶች

1913፡- አብዱል አዚዝ ኢብን ሳሁድ አብዛኛውን የአረብ ባህረ ገብ መሬት አሰባስቦ የሳውዲ አረቢያን ግዛት መሰረተ።

1948፡- ነፃነቷን ያወጀችው እስራኤል አምስት የአረብ አገራትን በጦርነት አሸነፈች።

1956፡- በሁለተኛው የአረብ እስራኤል ጦርነት እንግሊዝ፣ ፈረንሳይና እስራኤል ትብብር ፈጠሩ። እንግሊዝ የስዊዝ ካናልን በድጋሚ ስትቆጣጠር እስራኤል ደግሞ የሲናን ሰላጤ ያዘች። በዩናይትድ ስቴትስ የተመራ ዓለም አቀፍ ጫና ሁለቱ አገራት ይዞታቸውን እንዲያስረክቡ አደረገ። በቀጣዩ ዓመትም የተባበሩት መንግሥታት የመጀመሪያውን ሰላም አስከባሪ ወደ ሲና ላከ።

1958፡- ኦሳማ ቢን ላደን በሳዑዲ አረቢየያዋ ሪያድ ተወለደ።

1966፡- ሰይድ ቁጥብ በፕሬዚዳንት ጋማል አብዱል ናስር ግብፅ ውስጥ በሞት ተቀጣ። የእስላማዊ እንቅስቃሴውም መስዋዕት ሆነ።

1967፡- የኦሳማ ቢን ላደን አባት ሞሃመድ ቢን ላደን ሳዑዲ አረቢያ ውስጥ ባለው አንደኛው የሥራ ቦታው የግል አውሮፕላኑ ተከስክሳ ሞተ። ቢን ላደን በሊባኖስ ቤይሩት ውስጥ ከነበረበት አዳሪ ትምህርት ቤት ተመልሶ ትምህርቱን ሳዑዲ አረቢያ ውስጥ አጠናቀቀ። በስድስቱ ቀን ጦርነት እስራኤል የግብፅ፣ ሶሪያ፣ ጆርዳን እና ኢራቅ ጦርን አሸነፈች። የጐላን ተራሮችን፣ ጋዛን፣ የሲና ሰርጥን፣ ዌስት ባንክን እንዲሁም የእስላም ሶስተኛው

ቅዱስ ቦታ ዶም አፍሮክ የሚገኝበትን ምስራቃዊ እየሩሳሌምን ተቆጣጠረች፡፡

1973፡- እስራኤል በዩም ኪፑር ጦርነት ግብፅና ሶሪያን አሸነፈች፡፡ ለእስራኤል ማሸነፍ ዩናይትድ ስቴትስ ከፍተኛ እገዛ አድርጋለች፡፡

1979፡- በኢራን የአያቶላህ ኮህሚኒ እስላማዊ አብዮት ተሳካ፡፡ አክራሪ ሙስሊሞች የመካውን ታላቁን መስጊድ ተቆጣጠሩ፡፡ የሶቪየት ኃይሎች ኮሚኒስት አመራሩን ለመደገፍ አፍጋኒስታንን ወረሩ፡፡

1979-89፡- የአፍጋን አማፅያን በዩናይትድ ስቴትስና ሳዑዲ አረቢያ እየታገዙ ሶቭዬቶችን ለማስወጣት ቻሉ፡፡ ኦሳማ ቢን ላደን አማፅያኑን ለመርዳት ሙጆሃዲንን ተቀሳቀሰ፡፡

1984፡- ኦሳማ ቢን ላደን ከአብዱላህ አዛም ጋር የአፍጋን አገልግሎት ቢሮን በፓኪስታን ፓሽዋር ከፈተ፡፡ ቢሮው አማፅያኑን ለመቀላቀል ወደአፍጋን የሚገቡ የውጭ ሙጆሃዲኖችን የሚረዳ ነበር፡፡

1986፡- ኦሳማ ቢን ላደን የራሱን አረብ አፍጋን ተዋጊ ቡድን መስርቶ በአፍጋን ፓኪስታን ድንበር "የአናብስት ጉሬ" የተሰኘ ማሰልጠኛ ከፈተ፡፡

1987፡- ኦሳማ ቢን ላደን በአፍጋኗ ኮስት ከተማ አስቃቂ ዘመቻ መራ፡፡

1988፡- ኦሳማ ቢን ላደን፣ አብዱላህ አዛምና ሌሎች አልቃኢዳን የጦር ሰፈሩን መሰረቱ፡፡

1989፡- ቀዝቃዛው ጦርነት በምስራቅ ጀርመኖች የበርሊንን ግንብ መከፈት ተጠናቀቀ፡፡

1990፡- የኢራቁ ሳዳም ሁሴን ኩዌትን በመውረር ሳዑዲ አረቢያንን አስፈራራ። ኦሳማ ቢን ላደን ወራሪዎችን የሚያስወጣ የአረብ ሙጅሃዲን ጦር ለማቋቋም ጥሪ አቀረበ።

1991፡- ዩናይትድ ስቴትስ መራሹ 500,000 ጦር ኢራቅን ከኩዌት አስወጣ። ከጦርነቱ በኋላ የዩናይትድ ስቴትስ ጦር ሳዑዲ አረቢያ ውስጥ መቆየት ኦሳማ ቢን ላደንን አስቆጣ። ሶቭየት ህብረት ፈራረሰች።

1992፡- ፓኪስታንን በጥልቀት ከጉበኘ በኋላ ኦሳማ ቢን ላደን በፈቃደኝነት ወደ ሱዳን ተሰደደ።

1993፡- ራምሴይ ዩሱፍ እና ዐይነስውሩ ሼህ አብዱል ራህማን በኒውዮርኩ የዓለም የንግድ ማዕከል ስር ያፈነዱት ቦምብ ስድስት ሰዎችን ገድሎ 1042 አቆሰለ። የሶማሊያውን ጦረኛ መሃመድ ፈራህ አፍዲድን ለመማረክ ባደረጉት ያልተሳካ ጦርነት የዩናይትድ ስቴትስ የጦር አበጋዞች ሞቃዲሾ ውስጥ ተገደሉ። አልቃኢዳ በቀጥታ በጦርነቱ ተሳትፎ ባያደርግም በኋላ ላይ ቢን ላደን ሶማሊያዊያንና አጋዥ ሙጅሃዲኖችን አድንቋል።

1994፡- ሳዑዲ አረቢያ የኦሳማ ቢን ላደንን ዜግነት ሰረዘች።

1996፡- ዩናይትድ ስቴትስና ሌሎች አገራት ሱዳንን አሳልፋ እንድትሰጥ ጫና መፍጠር ጀመሩ። ወደአፍጋኒስታን ተዛውሮ በፅዮናውያን እና በመስቀል ጦረኞች ላይ ፋትዋ (ጦርነት?) አወጀ። ሂዝቦላህ በሪያድ የከባር ግንቦች ላይ ባፈነዳው ቦምብ 19 የዩናይትድ ስቴትስና አንድ የሳዑዲ ዜጎች ሲገደሉ ሌሎች 372 ሰዎች ቆሰሉ።

1998፡- ኦሳማ ቢን ላደን በዓለም እስላማዊ ግንባር ስም ለአምላካቸው ያደሩ ሙስሊሞች አሜሪካዊያንን በአገኙበት ቦታና ጊዜ ሁሉ እንዲገድሉ ጥሪ አስተላለፈ። በነሐሴ የአልቃይዳ መልዕክተኞች በታንዛኒያ ዳርኤሰላምና በኬንያ ናይሮቢ የሚገኙ የዩናይትድ ስቴትስ ኤምባሲዎችን በቦምብ አጋዩ። ዩናይትድ ስቴትስ አፍጋኒስታን ውስጥ በሚገኝ የአልቃኢዳ ማሰልጠኛ ጣቢያ እና ሱዳን ውስጥ በሚገኝ የመድሃኒት ፋብሪካ ላይ በክሩዝ ሚሳኤሎች ጥቃት ሰነዘረች። ፋብሪካው የኬሚካል ጦር መሳሪያ ማምረቻ እንደ ሆነ ተገምቶ ነበር።

2000፡- የአልቃኢዳ አጥፍቶ አጥፊዎች በዩኤስኤስ ኮል መርከብ ላይ በኤደን ወደብ በፈፀሙት ጥቃት 19 የዩናይትድ ስቴትስ ባህረኞች ሲሞቱ መርከቧ ከፍተኛ ጉዳት ደረሰባት። የሚሊኒየም ዋዜማ ዝግጅት ጋር እንዲገጣጠሙ የታሰቡ የሽብር ጥቃቶች የሎስ አንጀለስን ዓለማቀፍ አየር ማረፊያ በቦምብ ማጋየትን ያካተቱ የዩናይትድ ስቴትስ መንግሥት ማክሸፉን አሳወቀ።

2001፡- መስከረም 11 የአልቃኢዳ አሸባሪዎች በአራት ቡድን ተከፋፍለው አራት የዩናይትድ ስቴትስ አይሮፕላኖችን ጠለፉ። ሁለት አይሮፕላኖች በመንታዎቹ የኒውዮርክ የዓለም የንግድ ማዕከል ህንፃዎች ሲከሰከሱ ሶስተኛውን በቨርጅኒያ አርሊንግተን ከሚገኘው የፔንታጐን ህንፃ ጋር አላተሙት። ወደ ዋሽንግተን በማምራት ላይ የነበረው አራተኛው አይሮፕላን መንገደኞች ከጠላፊዎች ጋር ባካሄዱት ግብግብ ፔንሲልቫኒያ ውስጥ በሚገኝ ሜዳ ተከሰከሰ። በዩናይትድ ስቴትስ ታሪክ አስቃቂው የተባለለት

የሽብር ክስተት አስራ ዘጠኙን ጠላፊዎች እና የ2998 ሰዎችን ሕይወት ቀጠፈ። ፕሬዚዳንት ጆርጅ ቡሽ ዓለማቀፋዊ የፀረ ሽብር ዘመቻ አወጁ። የዩናይትድ ስቴትስ ልዩ ዘመቻዎች እና ሲአይኤ በዩናይትድ ስቴትስ አየር ኃይል እየታገዙ ዘ ኖርዘርን አሊያንስ የተሰኘው ጥምረት ታሊባኖችን አስወግዶ በአፍጋኒስታን ስልጣን እንዲይዝ አደረጉ። በሃሚድ ካርዛይ የሚመራውን አዲሱን መንግሥት ለመርዳት የኔቶ ጦር አገሪቱን ተቆጣጠረ።

2002፡- በመጋቢት ከተካሄደው የአናኮንዳ ኦፐሬሽን ያመለጠው ኦሳማ ቢን ላደን በፓኪስታን ድንበር አካባቢ አመለጠ። በሕዳር ከአልቃኢዳ ጋር ትስስር ያለው ጀማህ ኢስላሚያ የተሰኘ በኢንዶኔዥያ የሚገኝ አሸባሪ ድርጅት በኢንዶኔዥያ ባሊ በሚገኝ የምሽት ክበብ ላይ ባደረሰው የቦምብ ጥቃት 202 ሰዎች ሲገደሉ ከመቶ በላይ የሚሆኑ ቆሰሉ።

2003፡- በዩናይትድ ስቴትስ የተመራ ጥምር ጦር የኢራቁ አምባገነን ሳዳም ሁሴን ጅምላ ጨራሽ መሳሪያዎችን እያመረተ እና አሸባሪ ድርጅቶችን እየረዳ ነው በሚል ሰበብ በመጋቢት ኢራቅን ወረረ። የዩናይትድ ስቴትስ ኃይሎች በጥቂት ሳምንታት ውስጥ ባግዳድ ደረሱ። መደበኛውን ዘመቻ ተከትሎ ጥምር ኃይሉንና ኢራቃዊ ደጋፊዎቹን የሚቃወሙ አማፅያን ትግል እያደገ ሄደ። ህዳር 21 ከአልቃኢዳ የተሳሰሩ ኃይሎች በቱርክ ኢስታንቡል በሚገኙ ሁለት የአይሁድ ቤተ መቅደሶች ላይ የቦምብ ጥቃት አደረሱ። ከአምስት ቀናት በኋላ የኤች ኤስ ቢሲ ባንክንና የእንግሊዝ ቆንስላን በቦምብ አጋዩ። በጥቃቶቹ 57 ሰዎች ሲገደሉ ከ700 በላይ ቆሰሉ።

2004፡- በመጋቢት 11 አቡ ሃፍዝ አልማስሪ ብሪጌድ የተሰኘው የአልቃኢዳ ክንፍ በስፔን ማድሪድ ባደረሰው የባቡር ጣቢያ የቦምብ ፍንዳታ 191 ሰዎች ሲገደሉ ከ600 በላይ ጉዳት ደረሰባቸው፡፡ የኢራቁ አመፅ በሺ እና ሱኒ ሙስሊሞች መካከል በሚፈጠሩ ግጭቶች የተነሣ እየተባባሰ ሄደ፡፡

2005፡- በሐምሌ 7 አራት አሸባሪዎች በእንግሊዝ መጓጓዣዎች ላይ በጀርባ በሚታዘሉ ቦርሳዎች በተያዙ ቦምቦች ጥቃት አደረሱ፡፡ ሶስቱ አሸባሪዎች የመሬት ውስጥ ባቡሮች ላይ ጥቃት ሲያደርሱ አራተኛው ቦምቡን ያፈነዳው አውቶቡስ ውስጥ ነበር፡፡ በጥቃቱ 52 ሰዎችን ገድሎ ከ770 የሚልቁትን አቆሰለ፡፡ በሐምሌ 21 ሌሎች አራት አሸባሪዎች ለንደን ውስጥ ተጨማሪ ጥቃት ለማድረስ ሞከሩ፡፡ ጥቃቱ የከሸፈ አሸባሪዎች የቦምቦቹን ቁልፎች ማላቀቅ ስላቃታቸው ነበር፡፡ የእንግሊዝ የፀጥታ ኃይሎች አሸባሪዎችን ከነደጋፊዎቻቸው ለመቆጣጠር ቻሉ፡፡

2006፡- የእንግሊዝ ባለስልጣናት አትላንቲክን በሚያቋርጡ አይሮፕላኖች ላይ ጥቃት ለማድረስ የተዘጋጅ 26 ተጠርጣሪ ሽብርተኞችን በመያዝ ሽብሩን አከሸፉ፡፡ ኢራቅ ውስጥ ሕይወታቸው ያለፈ የዩናይትድ ስቴትስ ወታደሮች ቁጥር የ9/11 ሰለባዎችን በልጦ 3000 ደረሰ፡፡ መልሰው የተቋቋሙት ታሊባኖችና አልቃኢዳ ከፓኪስታን ምሽጐች እየተነሱ በሚያደርሷቸው ጥቃቶች የተነሣ የአፍጋኒስታን ፀጥታ እየተባባሰ ሄደ፡፡ ኋይት ሃውስ የጦሩን ቁጥር በ30,000 በማሳደግና ጀነራል ዴቪድ ፔትሮስን በኢራቅ የሚገኘውን የዩናይትድ ስቴትስን ጦር እንዲመራ በመመደብ

ተልዕኮውን ለማጠናከር ቃል ገባ። "የአንባር መነሣሣት" የተሰኘ ቡድን አማፅያኑን የመደምሰሱን ጥረት ተቀላቀለ። በኢራቅ የአልቃኢዳ መሪ የነበረው አቡ ሙሳብ አልዛርቻዊ በዩናይትድ ስቴትስ የቦምብ ጥቃት ተገደለ።

2007፡- የህክምና ዶክተሮችን በመጠቀም በለንደን የምሽት ክበቦች ላይ አልቃኢዳ ሊያደርስ ያቀደው የቦምብ ጥቃት ከሸፈ። በመኪና ላይ የተጠመዱ ቦምቦች ሳይፈነዱ ቀሩ። አንደኛው አሸባሪ በመኪናው ላይ የተጠመደውን ቦምብ ይዞ የግላስኮን አየር ማረፊያ አቋርጦ ለመግባት ሞክሮ ነበር። በሙከራው ምንም ጉዳት ሳይደርስ በእርሱ ላይ ብቻ ቃጠሎ ደረሰበት።

2008፡- በሕዳር ላስካርኤነታይባ የተሰኘ በአልቃይዳ የሰለጠነ ፓኪስታን ውስጥ የሚገኝ አሸባሪ ቡድን በህንድ ሙምባይ ሆቴሎች ላይ ጥቃት አደረሰ። የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ኾነው የተመረጡት ሴናተር ባራክ ኦባማ ኢራቅ ውስጥ አልቃኢዳን ለማዳከም ጠንክረው እንደሚሰሩ ቃል ገቡ።

2009፡- ፕሬዚዳንት ኦባማ ጦሩ ከኢራቅ የሚወጣበትን የጊዜ ሰሌዳ ይፋ አደረጉ። የማጠናከሪያ ጦር ወደ አፍጋኒስታን እንደሚላክም ገለፁ። በሰኔ ወር የፓኪስታን ጦር በስዋት ሸለቆ በሚገኙ ታሊባኖች ላይ ጥቃት ከፈቱ። ሐምሌ ደግሞ 4,000 የዩናይትድ ስቴትስ ባህር ኃይል አባላት ከአፍጋኒስታን መንግሥት ጋር በመተባበር ሄልሞንድ ግዛትን ከታሊባኖች የማጥቃት ዘመቻ አካሄዱ።

# ምዕራፍ አንድ

## ሰውዬው፤ አሳማ ቢን ላደን

አሳማ ቢን ላደን የማይጨበጥ ሰው ነው፡፡ የምድራችን ልዕለ ኃያል አገር ከአስር ዓመታት በላይ እርሱን ለመማረክ ያደረገችውን ጥረት ከማምከኑ በተጨማሪ የሕይወት ታሪኩን ለመከተብ የተጉ ፀሃፊዎች የሚያደርጉትን ማሳደድ ተቋቁሞ የሕይወቱን ሙሉ ምስል ማግኘት እንዳይችሉ አድርጓቸዋል፡፡ ከዝነኛነቱ በተፃራሪ በተለይ እስከ 21 ዓመት ዕድሜው ስለ አሳማ ያለው መረጃ በጣም ውስን ነው፡፡ የአልቃኢዳው መሪ የልጅነትና ታዳጊነት ዓመታት ታሪክ ለመሰወሩ ዐብይ ምክንያቱ የትውልድ አገሩ ተፈጥሮ ነው፡፡ በ1960ዎቹና 70ዎቹ ሳዑዲ አረቢያ በፈጣን የለውጥ ሂደት ውስጥ ነበረች፡፡ የነዳጅ ትርፍ አብዛኛውን ንጉሳዊ ቤተሰብ በሃብት ሲያጥለቀልቅ በአብዛኛው የሳዑዲ ዜጋ ዘንድ ግን ትርጉም ያለው ለውጥ አላስከተለም፡፡ የመሃይምነት ወለሉ ካለመቀነሱም በላይ የመሰረተ ልማት ለውጡ ዝቅተኛ ነበር፡፡ በበርካታ ምዕራባዊ አገራት እንደተደረገው ዐይነት የአገር ምስረታው ሂደት ገና አልተጠናቀቀም፡፡ ሳዑዲ አረቢያን ያስተዳድሩ የነበሩት የውሃቢ እስልምና አራማጆች ልደትን ማክበርንም ሆነ ፎቶግራፍን አለማበረታታቱ የአሳማ የሕይወት ታሪክ ሊሆን ከሚችለው እንዲቀጥን ምክንያት ሆኗል፡፡

በእነዚሁ ምክንያቶች የተነሣ የታሪክ ተመራማሪዎች ለምርምር የሚፈልጓቸው ማህደሮች ጠፍተዋል፡፡ ለምሳሌ አሳማ የልደት ማስረጃ የለውም፡፡ መሰል ማስረጃዎቹ በሌሉበት ሁኔታ የሕይወት ታሪኮች በቃለ

ምልልሶች ላይ ያተኩራሉ፡፡ ቢን ላደን በጣት የሚቆጠሩ ቃለ ምልልሶችን ያውም ሁሉንም አልቃኢዳን ከመሰረተ በኋላ ሰጥቷል፡፡ እነዚያ ቃለ ምልልሶች ስለአመለካከቱ ጠቃሚ መረጃዎችን የማይሰጡ ቢሆኑም ስለቀደምት ሕይወቱ ግን የሚናገሩት ውስን ነው፡፡ ቢንላደን ስለ እነዚያ ዓመታት የተናገረው ጥቂት ከመሆኑም በላይ ሲናገር በሐይማኖታዊ መነፅር ተመልክቷቸው ነው፡፡ እንደ አብዛኞቹ የርዕዮተ ዓለም መሪዎች እርሱም ሕይወቱን የሚያነበው ወደኋላ የሚያውቁት ሁሉ ስለቢን ላደን የተወሰኑ መረጃዎችን ሰጥተዋል ይሁንና መረጃዎቹ የተሰበሰቡት ከመስከረም 11ዱ ጥቃት በኋላ ነው፡፡ የሚያራምደው አቋም ከበርካታዉ ዓመት የዳበረ መሆኑን ገልጿል፡፡ በመሆኑ በጤናማ ጥርጣሬ መታየት አለበት፡፡ የቢንላደን ቤተሰቦች ከሰውዬው ለመራቅ በቂ ምክንያት ይኖራቸዋል፡፡ ጓደኞቹና የሚያውቁት ሰዎች ግን ለመዋሸት ሳይገደዱ አይቀሩም፡፡ ከዓመታት በፊት የሚያውቁት ሰዎች የሚያስታውሱትን ሁሉ አይናገሩም፤ ወይም የተወሰነውን ይረሱታል፡፡ ከቢንላደን ዐይናፋርነት ጋር ተያይዞ ከሚያውቁት በርካቶቹ ከመገረማቸው የዘለለ የሚናገሩት መረጃ የላቸውም፡፡

ከማስረጃዎቹ አጥረትና ከቃለ ምልልሶች መገደብ የተነሣ የሕይወት ታሪክ ፀሃፊዎች በዋና ዋና የልጅነቱ ዘርፎች ላይ ግምቶችን ማንሸራሸራቸውን ቀጥለዋል፡፡ ስለአስተዳደጉ ለማብራራት ያደገበትን ማህበረሰብ ማዕቀፍ በመበርበር ላይ ያተኩራሉ፡፡ የሆነ ሆኖ ስለአንድ ሰው ስነ ልቦና ጠልቆ ለመመርመር በተሞከረ መጠን ነገሮች ይበልጥ የመወሳሰብ አዝማሚያ ያሳያሉ፡፡

# ሳዑዲ አረቢያ

ቢን ላደን ተወልዶ ያደገበት ምድር ጥንታዊ ቢሆንም መንግሥትነቱ አዲስ ነው:: በ1905 የአረቢያን ሰላጤ በልዑላን የሚተዳደሩ በርካታ ግዛቶች እና የቤድዊን ጐሳዎች የተሞላ ነው:: የዘመናዊዋ ሳዑዲ ግዛት የኾነው መሬት ሁለት የስልጣን ማዕከሎች ነበሩት:: በስተምዕራብ የሃሽማይት ቤተሰብ የመካና መዲና ቅድስት ከተሞችን እንዲሁም የጂዳ ከተሞችን ያስተዳድራል:: በሰሜን ምስራቅ ደግሞ አብዱል አዚዝ ኢብን ሳዑድ በሪያድ አካባቢ ያለውን ክልል ያስተዳድራል:: በመጀመሪያው የዓለም ጦርነት ወቅት እንግሊዞች በኦቶማን ቱርኮች ላይ ያመፁትን ሃሽማይቶች ይደግፉ ነበር:: ጦርነቱ ሲያበቃ ግን ድጋፋቸውን ለወጡ:: በጦርነት ዋና ፀሐፊው ዊንስተን ቸርችል በተመራው የ1920ው የካይሮ ኮንፍረንስ ላይ እንግሊዞች ኢብን ሳዑድን ለመደገፍ ወሰኑ:: ሳዑድ ግዛቱን በፍጥነት በማስፋፋት ጀበል ሻማርን በ1921፣ መካን በ1924 እንዲሁም መዲናን በ1925 ተቆጣጠረ:: በ1932 የአዲሱን መንግስቱን ስም ወደ ሳዑዲ አረቢያ ቀየረው:: ኢብን ሳዑድ ወደሥልጣን የመጣው ኢክወሃን ተብለው የሚታወቁትን ጦረኛ የወሃቢ ቤድዊኖችን ኃይማኖታዊ ፅናት በመጠቀም ነው:: ይሁንና ወደ ሥልጣን ከመጣ በኂላ እነዚህን ጦረኞች አገሪቱን ለማሰልጠን ጫና ያደርግባቸው ነበር::

አብዛኛው የግዛቱ ክፍል ባዶ በረሃ በመሆኑ በቅኝ ግዛት ያስተዳድሩት የነበሩት አውሮፓዊ ኃይሎች እምብዛም ትኩረት አይሰጡትም ነበር:: ይኸው ሁኔታ በ1930ዎቹ የነዳጅ ዘይትን መገኘት ተከትሎ ወዲያውኑ ተቀየረ:: በግዛቱም ስር የ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ቀዳሚው

ስትራተጂካዊ ሃብት ተገኘ። ከዚህ ውጪ ግን ሳዑዲ አረቢያ ኋላ ቀር ስለነበረች በውጭ አገር ኢንጂነሮች፣ ነጋዴዎች እና ኤክስፐርቶች ተጠቅማ ነዳጁን ማውጣት ግድ ይላት ነበር። እንዳለመታደል ሆኖ አብዱል አዚዝ እና ተከታዮቹ መሰረተ ልማትን ከማስፋፋት እና የምስኪኑን ሳዑዲ አረቢያዊ ሕይወት በማሻሻል ፋንታአብዛኛውን የነዳጅ ሃብት ያፈሰሱት ዘመናዊ ቤተመንግሥቶችን ለመገንባት እና የተቀናጣ ሕይወት ለመኖር ነው። ይኸው ሁኔታም የአሳማ ቢን ላደን የልጅነት ዘመን እስከሆኑት 1960ዎቹ ድረስ ሳይቀየር ቆይቷል።

በአረብ አገራት ዘንድ ዘመናዊነት እየመጣ የነበረ ቢሆንም ፈጣኑ ሂደት ለወግ አጥባቂው ህዝብ የተመቹ አልሆነም። አጥብቀው ከፈለጉት የምዕራባዊያን ዕውቀት ጋር የማይፈልጉትና በኋላም የተፀፀቱበት የምዕራባዊያን ባህልና ተፅኖ መጣ። የለውጡ ሂደት የማዛቱን ወግ አጥባቂነት በመጠበቅና ሐይማኖታዊ ንቅናቄን አመጣ። እንደዚህ ዐይነቱ ንቅናቄ አሳማ ቢን ላደን በትውልድ አገሩና በዩናይትድ ስቴትስ ላይ የሽብር ጥቃቶችን እንዲቃጣ ሳያበረታታው አልቀረም።

## የቢን ላደን ቤተሰብ

የቢን ላደን ቤተሰቦች ወደሰፊ ሀብትና ስልጣን መምጣት የሳዑዲ አረቢያ ዘመናዊ ግዛት ከመመስረት ጋር ጐን ለጐን የኾነ ነው። የቢን ላደን አባት መሃመድ ቢን ላደን የተወለዱት በ1905 በየመኗ ሃድራሙት ክልል ነው። በ1925 (ያልተረጋገጠ) በምዕራብ ሳዑዲ አረቢያ ወደ ምትገኘው ጂዳ ከተማ አመሩ። በዚያውም ጥሩ እመርታ ያሳዩበትን የግንባታ ዘርፍ ንግድ

ጀመሩ። በ1931 የራሳቸውን ኩባንያ አቋቋሙ። ቤቶችን በመገንባት ጀምረው አረቢያን አሜሪካን ኦይል ካምፓኒ ለተሰኘ ድርጅት ጡብ የመደርደርን ኮንትራት ከመንግሥት ተቀበሉ። ከውጭ ባለሃብቶችና ከንጉሣዊያን ጋር የመስራት ችሎታቸው ለመሐመድ ቢን ላደን ባለፀጋነትን አተረፈላቸው።

ለንጉሣዊያኑ ገንዘብ የማበደር ፈቃደኝነታቸው ንግዳቸው ያለምንም ሳንካ እንዲንቀሳቀስ መንገድ ከፍቷል። በሂደትም የቢን ላደን ድርጅት የመዲናውን የነብዩን መስጊድናየ መካውን ታላቁን መስጊድ መልሶ ለመገንባት ትልቅ ረብጣ የሚያሳፍስ ኮንትራት ተፈራረመ።

እንደአብዛኞቹ የሳዑዲ ሀብታሞች መሐመድ ቢን ላደንም ከብዙ ሚስቶች በርካታ ልጆችን ወልዷል። በአብዛኞቹ መዝገቦች ላይ እንደሰፈረው መሐመድ ቢን ላደን ከ22 ሚስቶች 54 ልጆችን አፍርተዋል። ሁሉንም ሚስቶቻቸውን በጥሩ ገቢ እንደላቆ በማኖር ጥንካሬያቸው ይታወሳሉ።

መሐመድ በ1967 አይሮፕላን ተከስክሶ ሲሞቱ ሃብታቸውን ንጉሣዊው አስተዳድር በአደራ አስቀመጠው። ለቤተሰቡ እንደመልካም አጋጣሚ ሆኖ የመጀመሪያ ልጃቸው ሳሌም ከአባቱ ያልተናነሰ ነጋዴ ሆኖ ብቅ አለ። ከሳዑዲ ንጉሣዊያን ጋር ያለውን ትስስር አጠናክሮ ሳዑዲ ቢን ላደን ግሩፕ የተሰኘ ዓለማቀፍ ኩባንያ መሰረተ። በ1986 በአይሮፕላን አደጋ ሕይወቱ ስታልፍ ንግዱን መልካም አስይዞት ስለነበር ታናሽ ወንድሙ ባክር የቤተሰቡን ንብረት ያለምንም መንገራገር ወደፊት ለማስቀጠል ችሏል።

# የሕይወት ጉዞ

የማያጨቃጭቁት የኦሳማ ቢን ላደን የሕይወት ክፍሎች ጥቂት ናቸው። ትክክለኛው ወር ባይታወቅም የተወለደው በ1957 በሪያድ ሳዑዲ አረቢያ ውስጥ ነው። ከ1968 በጂዳው አል ታግር ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ገባ። የመጀመሪያ ሚስቱን ያገባው በ1974 ሲሆን በዚያው ዓመትም የኪንግ አብዱል አዚዝ ዩኒቨርሲቲን ተቀላቅሏል። በዚያም የኢኮኖሚክስ ትምህርቱን ቀጥሎ የነበረ ቢሆንም ዲግሪውን ግን አላገኘም።

የቢን ላደን እናት አሊያ ጋዛነም ከደሃ ሶሪያዊ ቤተሰብ የተወለዱ ሲሆኑ መሐመድ ቢን ላደን በ50ዎቹ ዕድሜው እያለ በ14 ዓመታቸው ነበር በ1956 የተጋቡት። ከዓመት በኋላ ቢን ላደንን ወለዱ። ሌላ የጋራ ልጅ ስለሌላቸው ምናልባትም ልጁን እንደወለዱ ከቢን ላደን ሳይፋቱ አልቀረም። በኋላ ሌላ አግብተው ከአዲሱ ባለቤታቸው በርካታ ልጆችን ወልደዋል።

ቢን ላደን የመሐመድ 16ኛ ወይም 17ኛ ልጅ መሆኑና በእናቱ ሌላ ማግባት የተነሳ ከቤተሰቡ ቅጥር ርቆ የሚኖር ቢሆንም የጉደለበት አንዳች ነገር የለም። ይሁንና ቢን ላደን ካደገ በኋላ በመግለጫዎቹ ላይ አንድም ጊዜ ጠቅሶት አያውቅም። ቢን ላደንን በልጅነቱና በእድገቱ የሚያውቁትም ሰዎች ስለቢን ላደን የእንጀራ አባት ምንም ብለው አያውቁም። በልጁ እድገት ላይ የነበረው ተፅዕኖ በጣም ትንሽ ወይም ምንም ሳይሆን አይቀርም።

ከአባቱ ሞት ዘጠኝ ዓመታት ቀድሞ የተወለደው ቢን ላደን የተዋከበ የንግድ ሕይወት ከሚመራው አባቱ መሐመድ ጋር የነበረው ግንኙነት የተገደበ እንደነበር ይነገራል፡፡ መሐመድም የነበራቸውን ትርፍ ጊዜ ለ54 ልጆቻቸው ማከፋፈል ነበረባቸው፡፡ ልጆቹ ባደጉ ጊዜ በግንባታ ንግድ ድርጅቱ ውስጥ ስራ ይቀጥራቸው ነበር፡፡

ከወንድሞቹ ሲነፃፀር ከታናናሾቹ የሚደመረው ቢን ላደን አባቱን የማግኘት ዕድሉ ከታላላቁ በእጅጉ ያነሰ ነበር፡፡ አባቱ ሲሞቱም የዘጠኝ ዓመት ልጆች እንደሚያደርጉት አባቱን ከልክ በላይ አሞግሶል፡፡ "አባቴ በአንድ ቀን በሶስቱም መስጊዶች (በመካ፣ መዲናና እየሩሳሌም) መስገድ መቻሉ በአላህ ፈቃድ የሆነ ነው፡፡" ብሏል ቢን ላደን ሲያጠቃልል፡፡ መሐመድ ጥብቅ እምነት የነበረው ቢሆንም ከመስጊዶቹ መራራቅ አንፃር የተባለውን ለማድረግ በእጅጉ መቸገሩ አይቀሬ ነው፡፡

የዚያኑ ያህል ቢን ላደን ከእናቱ ጋር ስላለው ግንኙነትም የሚታወቀው ትንሽ ነው፡፡ በሳዑዲ አረቢያ ካለው የሴቶች መገለልና ፖለቲካዊ መብት ማጣት አንፃር የእናቱ ዝምታ የሚጠበቅ ነው፡፡ የቢን ላደን ጐረቤትና የልጅነት ጓደኛ የነበረው ካሀሊድ ባታርፊ "ፊታ ያለች ሙስሊም ናት፡፡ ቴሌቭዥን ትከታተላለች፡፡" ሲል ይገልፃቸዋል፡፡ በተጨማሪም ቢን ላደን ከሌሎች ልጆች በተሻለ የእናቱን ትዕዛዝ እንደሚጠብቅ ጂሃድን ብቻ ግን እምቢ ብሎ እንደገፋበት ይገልፃል፡፡ ከምንም ነገር በላይ ሙስሊማዊ ግዴታውን መወጣትን እንደሚያስቀድምም ይናገራል፡፡ ቢን ላደን በተሰደደባቸው እና በተደበቀባቸው ዓመታት ሁሉ ከእናቱ ጋር ይገናኝ ነበር፡፡ ቢን ላደን በተወሰነ ደረጃ ከቤተሰቡ ጋር ጊዜ ማሳለፉ እርግጥ ቢሆንም ልዩ የሚባል ቁርኝት ግን ያለው አይመስልም፡፡

# የቢንላደን ቤተሰብ ሕይወት

ቢን ላደን ያደገው ከእናቱ ጋር በመሆኑ አብዛኞቹ እህቶቹና ወንድሞቹ ከሚኖሩበት ቅጥር ርቆ ነው። ይሁንና ወንድሞቹ በእንቅስቃሴዎቻቸው ሁሉ ያካትቱት ነበር። ይኸው ተቀባይነቱ ቢን ላደን የበለጠ ሐይማኖታዊ እየኾነ በሄደ ጊዜም የተለወጠ አይመስልም። እንደ የካቶሊክ ቤተሰብ አንደኛው ልጅ ቄስ ወይም መነኩሴ እንዲሆኑ የሚያበረታቱን ያህል ሰፊና ሐብታም የሆነው የቢን ላደን ቤተሰብም ሃይማኖቱን ማጥበቁን ሳይወዱለት አልቀሩም።

ኦሳማ ቢን ላደን ከሌሎች የቤተሰቡ አባላት ጋር ጉዞ አካሂዷል። በ1970 ከአዲሱ የቤተሰቡ ንግድ ኃላፊ ታላቅ ወንድማቸው ሳሌም ጋር ወደ ስዊድን ሄዷል። በቀጣዩ ዓመትም ሳሌምን ጨምሮ 22ቱ ወንድሞቹና እህቶቹ በተሳተፉበት የቤተሰብ ጉዞ ላይም ተሳታፊ ነበር። ከፍተኛ ተግባቢነት የነበረው ቢሆንም ባረፉበት ሆቴል ባለቤት የተሰጠው ትኩረት አናሳ ነበር። በቀን ጨዋታዎች ዋንኛ ተሳታፊ ቢሆንም ወደ ምሽት ክበቦች ግን ዝር አላለም። የቅርብ ጓደኛው እንደተናገረው ቢን ላደን በ12 ዓመቱ ወደ ለንደን ጉዞ አድርጓል። ወደሌሎች የአውሮፖ አገራትም ሳይጓዝ አልቀረም።

# የልጅነት ዘመን ጠባሳዎች

ተመራማሪዎች በቢን ላደን የልጅነት እና የወጣትነት ዘመናት በጉልማሳነቱ ላሳየው የፅንፈኝነት ባህሪ መገለጫ የሚሆኑ አጋጣሚዎችን ለማግኘት ብዙ ቆፍረዋል። በዚያ ዕድሜው አባቱን ማጣቱ አስደንጋጭ መሆኑ ባይካድም ሌሎች በርካታ ልጆችም ያውም መሐመድ በልጁ ዘንድ

ከነበረው ትስስር በላይ የነበራቸውን ወላጆቻቸውን አጥተዋል፡፡ ቢን ላደን አካባቢውን በቅጡ ማወቅ በጀመረበት ወቅት እናቱ አግብታ ስለነበር አባት የሌለው ልጅን ስሜት ማስተናገዱን የሚገልፅ ምንም ዐይነት ማስረጃ አልተገኘም፡፡ ከፍቼ በኋላ መሐመድ ያጋባት ባል በራሷ ማግኘት የማትችለው ከመሆኑም በላይ ኑሯቸው የተንደላቀቀ እንደነበር መረጃዎች አሉ፡፡

ቢን ላዲን "ዐይናፋር፣ በጣም ጥሩና ሩህሩህ እና ሁልጊዜም ተባባሪ ልጅ ነበር፡፡" ሲሉ እናቱ ይህንን ግምት በማረጋገጥ ቢን ላደንን ይገልፁታል፡፡ አክለውም እንዲህ ይላሉ "ፈሪሃ አላህ ፍቅር በውስጡ ይሰርፅ ዘንድ፣ ለቤተሰቦቹ፣ ለጉረቤቶቹና ለመምህሮቹም አክብሮት እንዲኖረው ለማድረግ ጥሬያለሁ፡፡" የቅርብ ጓደኛው የሆነው ካሊድ በተረፈ እንደሚለው ከሆነም ቢን ላደን ለእናቱ ከፍተኛ ፍቅርና ቀረቤታ ነበረው በተለይም ከአባቱ ሞት በኋላ፡፡ "እናቱ ሁሉንም ነገር ነበረችው፡፡" ሲል ይናገራል፡፡ "እሱ ለእሷ በጣም ታዛዥ ነበር፡፡ ምናልባትም ለአባቱ ቅርብ ስላልነበር ይሆናል፡፡" ገና በአፍላነቱ አባቱን ባጣው ልጅና በእናቱ መካከል የነበረው እንዲህ ያለ ቅርርብና ዘላቂ ወዳጅነት በጣም ያልተለመደ ዐይነት ይመስል ነበር፡፡"

እጅግ አሰቃቂ ክስተቶች ምናልባትም አላማ ቢን ላደንን ቀርፀውት ሊሆን ይችላል የሚል መላምታዊ ማጠቃለያዎች አሉ፡፡ ምናልባትም የ ዘጠኝ አስራ አንዱን አውዳሚ ጥቃት ለተመለከቱ

አሜሪካኖች ለመቀበል አስቸጋሪ የሚሆንባቸው ነገር በልጅነት ወቅት የሚከሰት እጅግ አስቃቂ ገጠመኝ እና ስነ ልቦናዊ በሽታ አሸባሪ ለሆኑና እንዲህ ዐይነት አስቃቂ ድርጊት ለሚፈፅሙ ሰዎች የግድ የጀርባ ምክንያት ሊሆን ይችላል የሚለው ነው። የአሸባሪዎች እንቅስቃሴ ተከታይ የሆኑት ወታደሮች በኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሁኔታዎች ከተጎዱ ቡድኖች የመጡ ቢሆኑም እንኳ መሪዎቻቸው ግን እንደዚህ አይሆኑም። እነሱ ለዓላማ እንዲሞቱ ከሚያዟቸው ተከታዮቻቸው በበለጠ የተማሩና ሀብታም የሆኑ ናቸውና።

በጅምላ ውጊያ ዙሪያ ዕውቀቱ እንዳላቸው ተሰሚ ሰዎች ድምዳሜ መደዴ ሰዎች ያልተለመዱ ጭካኔያዊ ድርጊቶችንና ውድቀቶችን በተገቢው ሁኔታ ውስጥ ሊፈፅሙ ችሎታው ያላቸው ናቸው።

## ትምህርት

መሐመድ ቢን ላደን በርካታ ልጆቹን ለትምህርት ወደ ውጭ ልኳቸዋል። በ1950ዎቹ እና በ1960ዎቹ ውስጥ ሳውዲ አረቢያ በጣም ጥቂት ጥሩ የሁለተኛ ደረጃ እጅግ በጣም ጥቂት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ብቻ ነበሯት። በመሆኑም አብዛኞቹ የቢን ላደን ልጆች በእንግሊዝ፣ በሊባኖስ፣ ወይም በሶሪያ አዳሪ ት/ቤቶች ውስጥ የነበሩ ሲሆን ዩኒቨርስቲ ትምህርታቸውን ደግሞ በአውሮፖና በአሜሪካ ውስጥ ቀጥለዋል። ከእነሱ መካከል ለውጭ ዕድል ያልበቃው ኦሳማ ቢን ላደን ነው በ1967 በሊባኖስ በሚገኘው የቋከር

አዳሪ ትምህርት ቤት ከአንድ ዓመት ላነሰ ጊዜ ከመቆየቱ በስተቀር ሙሉ በሙሉ የተማረው ሳዑዲ አረቢያ ውስጥ ነው። ምናልባትም ይህ ሁኔታ ለጥልቅ አክራሪ አመለካከቱ አስተዋጽኦ ያደረገ እውነት ሳይሆን አይቀርም።

ወደ ሳዑዲ አረቢያ እንዲመለስና ወደዚያ ት/ቤትም ተመልሶ እንዳይሄድ ያደረገው የአባቱ ሞት ሳይሆን አይቀርም። አጥኚዎች ምንም ዐይነት የት/ቤት መረጃ ስላላገኙ የመጀመሪያ ደረጃ የትምህርት ሕይወቱን ለማውሳት አስቸጋሪ ነው። እናቱ እንደሚሉት "እሱ ተማሪ አልነበረም። ፈተና የሚያልፈው በመካከለኛ ውጤት ነበር። ይሁንና በክፍል ባልደረቦቹና በሰፈሩ ልጆች ዘንድ የሚፈቀርና የሚከበረ ልጅ ነው።"

የቢን ላደን የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት በተሻለ የተደራጀ ቢሆንም በዚህ ደረጃ ያለው የሕይወቱ ታሪክ ግን የተሟላ አይደለም። በ1967 ወደ ቤቱ ከተመለሰ በኋላ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ወደአጠናቀቀበትና ጂዳ ውስጥ በሚገኘው የአልታጋር የሞዴል ት/ቤት ውስጥ እናቱ አስመዘገበችው። እንዳብዛኞቹ የአልታጋር ተማሪዎች ቢን ላደንም ከእናቱ ቤት እየተመላለሰ ነበር የሚማረው። ሀብታሞች የሚማሩበት ይህ ት/ቤት ከአክራሪነት በራቀ መልኩ ተማሪዎቹን በእንግሊዝ ውስጥ እንዳሉ የመሰናዶ ት/ቤቶች ዐይነት ዩኒፎርም የሚያለብሳቸውና ትምህርቱን የምዕራባውያንን ትምህርታዊ ዘዴ በተከተለ ካሪኩለም አማካይነት የሚሰጥ ነው በማንኛውም ጉዳይ

ላይ ቢን ላደን ተናጋሪ የሆነ ተማሪ አልነበረም የሚያገኘው መካከለኛ ውጤት ነው፣ ሲጠየቅ ካልሆነ እንጂ በራሱ ተነሳሽነት መልስ የሚመልስም አልነበረም "በአጠቃላይ ተነሳሽ አልነበረም" ሲል ያስታውሳል የእንግሊዝኛ መምህሩ። "ብዙ ተማሪዎች የቱን ያህል ጉበዝ እንደሆኑ ሊያሳዩህ ይፈልጋሉ። እሱ ግን ስለ አንድ ነገር መልሱን ቢያውቅ እንኳን እውነታውን አያሳይህም። ከጠየቅከው ብቻ ነው የሚያናግርህ።"

በአልታጋር እያለ፣ ከግብጾች አክራሪ የእስላም ወንድማማችነት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት የሌለው የእስላማዊ ተደጋግፎ (ተዛዘኖ) አመለካከት ባለውና የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት መምህሩ በሆነው ሶሪያዊ አስተማሪ ተፅዕኖ ስር ወድቆ ነበር። ወጣቱ መምህር እስፖርትንና የተጨማሪ ሰዓት ትምህርቶችን እንደማበረታቻ በሚሰጥ አነስተኛ የእስላማዊ ጥናት ቡድን ጋር እንዲቀላቀል ግብዣ አቀረበለት።

መምህሩም፣ ልጆቹን በጣም አክራሪ ለሆነ አመለካከት እንዲጋለጡ የሚያደርግ፣ የትውፊታዊ እስልምና እሴቶችን መመለስ፣ እና የፖለቲካንና የሃይማኖትን መቀላቀል በይፋ የሚደግፉ ነበሩ። እናም እነዚህ አመለካከቶች ቢን ላደንን ለወግ አጥባቂነት እንዲወስን አደረጉት። ኋላም ስመጥር ሚና ወደተጫወተበት የት/ቤቱ የሃይማኖት ኮሚቴ ውስጥ ተቀላቀለ ፂሙንም በማሳደግ ማስረዘምና

ኢ-ብልጭልጭ የሆነ አለባበስ መልበስ ጀመረ። በእግር ኳስ ሜዳ ላይ እንኳን በአጭሩ መታጠቅን ይቃወም ነበር።

በ1976 ጂዳ ውስጥ በሚገኘው አብዱል አዚዝ ዩኒቨርሲቲ ገባ። እዚያ ኢኮኖሚስት ማጥናት ቢጀምርም ከጥቂት ዓመታት በኋላ ድግሪውን ሳይቀበል ለቆ ወጣ። በወቅቱ የቅርብ ጓደኛው እንደነበረው ሰው አባባል ቢን ላዲን በጣም ጥብቅ ሃይማኖተኛ ነበር፣ በእስልምና ሕግ መሠረት የተከለከለ ወይም ሀራም እንደሆነ አድርጐ ይወስድ ስለነበር ፊልም ማየትና ሙዚቃ ማዳመጥን እንኳን ይቃወም ነበር። ይኼው ጓደኛው እንደሚለው እሱና ቢን ላዲን፣ ሁለቱም በዩንቨርስቲው ውስጥ ከፖለቲካዊ እስልምና ጋር ይጋፈጡ ነበር። የሰይድ ቀተስ 3 "ወሳኝ ታሪካዊ ጊዜ /Milestone/" እና "በቁርአን ጥላ ስር /In the shade of the quran/ የተሰኙ መፅሐፍትን አንብዋል። በተጨማሪም በዩኒቨርስቲው ውስጥ የሚያስተምረውና የሰይድ ወንድም የሆነውን የመሐመድ ቀለበን ንግግሮች ተከታትለዋል።

## ሥራ

እንደ ሁሉም ወንድሞቹ ሁሉ ቢን ላዲንም በቤተሰቦቹ ቢዝነስ ውስጥ ሰርቷል። የአባቱን ሞት ተከትሎ ንጉሡ የመሐመድን ንብረት በታማኝነት አቆይቶለታል። ይሁን እንጂ በጥቂት ዓመታት ውስጥ የመሐመድ ታላቅ ልጅ የሆነው ሳሌም የቤተሰቦቹን ንብረት መልሶ የመቆጣጠርና የማስተዳደሩን ሥራ እስከ 1986 ዕለተ ሞቱ ድረስ ሲያከናውን ቆይቷል። ውጤታማ ማናጀር የነበረው ሳሌም ከንጉሣዊ አስተዳደሩ ጋር ያለውን ግንኙነት በማበልፀግ አባቱ በፍላጐታቸውና በችሎታቸው መሠረት ያከፋፍልላቸው ነበር። እንዲያውም ከካምፓኒው ትርፍና ኢንቬስትመንት፣ ለመኖር የሚያስችላቸውን ከበቂ በላይ የሆነ ገንዘብ ያገኙ ነበር። አብዛኞቹ የቢን ላዲን ወንድ ልጆችም ለሥራ የሚነሳሱ ዐይነት ነበሩ።

እንደ አብዛኛው ሕይወቱ ሁሉ የቢን ላዲንን የሥራ ሕይወት አስመልክቶ ያሉት ነገሮች ግልጽ አይደሉም። ሳዑዲ አረቢያ ውስጥ ወደሚገኙ የግንባታ ስፍራዎች ጋር ይጓዝ እንደነበር ይናገራል፣ ወደ የትኞቹ የግንባታ ጣቢያዎች እንደሄደና እንደምንስ እንደጐበኛቸው የሚያብራራ ዝርዝር ጉዳይ ግን አያቀርብም።

ከሶቪየት ጋር በነበረው የአፍጋን የጦርነት ወቅት የነበረው የቢን ላዲን ውስብስብ የዋሻና የካምፕ ግንባታ እንዲሁም በሱዳን የነበረው የመንገድ ሥራ ስለ ኮንስትራክሽን ንግድ ምን ያህል ከፍተኛ

እውቀት እንዳለው የሚገልፁ ናቸው፡፡ ዩኒቨርሲቲ ለቆ በወጣበትና ወደ አፍጋኒስታን እስከሄደበት ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ለቤተሰቡ ኩባንያ ጥቂት የግንባታ ፕሮጀክቶችን ሳይመራ አልቀረም፡፡ በመምራት ዘይቤው በኩል ደግሞ የአባቱን የማኔጅመንት አቅጣጫ የተከተለ ይመስላል፡፡ የቅርብ ጓደኛው እንደሚያወሳው ቢን ላዲን ከወንድሞቹ ጋር በሚሰራበት ወቅት "ወደ ቡልዶዘሮቹ ይሄድና ሹፌሩን ካስወረደው በኋላ እራሱ መንዳት ይጀምራል፡፡"

## ጋብቻና ቤተሰብ

ምንም እንኳን አባቱን የሚያወድስ ቢሆንም በመሐመድ የተቀነባበረው ጋብቻዊ ድርጊት ግን ቢን ላዲን ይህ እስላማዊ ሕግ ሳይሆን የእስላማዊ ሕግን መንፈስ የሚፃረር ብሎ ስለሚያስብ የኢኮኖሚ ችግር ከሌለበትና ለሁሉም እኩል ማቅረብ እስከቻሉ ብሎ ነቢዩ በፈቀደው መሠረት ራሱንም በአራት ሚስቶች ወስኗል፡፡ ቁጡ ሆርሞን እንዳለው እንደማንኛውም ወጣት ሰው በወሲባዊ ተራክቦ ብርቱ መሆን ቢመኝም ከወንድሙ ከሳሌም በተለየ ግን ከጋብቻ ውጭ ወሲብ መፈፀምን አይፈቅድም ነበር፡፡ በመሆኑም ገና በወጣትነቱ አገባ፡፡ ቢን ላዲን የ14ዓመቱን የአክስቱን ልጅ ነጅዋ ጋኔምጣን ሲያገባ ገና 17 ዓመቱ ነበር፡፡

በልማዳቸው መሠረት እሷም የታላቅ ልጇን ስም በመውሰድ "ኢሞ አብዱላሂ ተብላ መጠራት ጀመረች በአረብኛ "ኢሞ" ማለት እናት ማለት ሲሆን "አቡ" ማለት ደግሞ አባት እንደማለት ነው ቢን ላደን በመቀጠልም ሌሎች ሶስት ሚስቶችን አገባ ኡሞ ሀምዛን፣ ኡሞ ካሊድንና ኡሞ አሲን። (የሀምዛን እህት፣ የካሊድን እናትና የአሲን እናት እንደ ማለት ነው።)

ከህዝባዊው እምነት በተለየ መልኩ፣ የሳዑዲ አረቢያው የእስላም ወግ አጥባቂነት ሴቶችን ከመማርና ከባለሙያነት የሚነፍጋቸው አልነበረም። በመሆኑም ከቢን ላዲን ሚስቶች ሁለቱ የተማሩና የራሳቸው ሙያ ያላቸው ናቸው። ኡሞ ሃምዛ የህፃናት ስነ ልቡና ፕሮፌሰር ስትሆን፣ ኡሞ ካሊድ ደግሞ የአረቢኛ ሰዋሰው መምህርት ናት። አራቱም ሴቶች ከቢን ላዲን ልጅ የወለዱለት ሲሆን፣ ወጣትዋና የመጀመሪያው የሆነች ሚስቱ የብዙዎች እናት ናት።

እንደ አንዳንድ ታማኝ ምንጭ ከሆነ የወለደው ከመጀመሪያ ሚስቱ አስራ አንድ ልጆችን ሲሆን፣ ከሁለተኛ ሚስቱ አንድ፣ ከሶስተኛ ሚስቱ አራት፣ ከአራተኛ ሚስቱ ደግሞ ሶስት በማፍራት በድምሩ የአስራ ዘጠኝ ልጆች አባት ለመሆን በቅቷል።

አራቱም የቢን ላዲን ሚስቶች አንድ የጋራ መኖሪያ ቤት ስር የተጠለሉ አልነበሩም፡፡ እሱ ሳዑዲ አረቢያ፣ በኋላም ሱዳን ይኖር በነበረበት ጊዜ በአንድ ህንፃ ላይ ያሉ የተለያዩ አፓርታማዎችን ይዘው ነበር፡፡ እሱ ወደ አፍጋኒስታን በተንቀሳቀሰበት ወቅት ደግሞ የጋራ ግድግዳ ባለችው የአንድ ቅጥር የተለያዩ ጎጆዎች ውስጥ ኖረዋል፡፡ ቢሆንም አልፎ አልፎ በመካከላቸው ውጥረት መንገሱ አልቀረም፡፡ ከቢን ላዲን ጋር በአንድ ሃገር በአንድ ቅጥር ውስጥ ይኖር ከነበረው ተከታዩ ልጅ የሆነው ዘይነብ አህመድ ከድር አገላለፅ ቢን ላዲን ለኡሞ ሀምዛ ያደላና በእሷም ይተማመን ነበር፡፡ በሰባት ዓመት የምትበልጠውና የዩኒቨርስቲ ፕሮፌሰር የሆነችው ኡሞ ሃሞዛ እሱ የሚያደንቀው ዐየነት ጥበብና ብስለት ሳይኖራት አልቀረም፡፡ ይህ ልዩ ትኩረት የመጀመሪያውና የሁሉም ፈተና የሆነችውን ሚስቱን ኡሞ አብዱላሂን በጣም ቀናተኛ አደረጋት፡፡ እሷ ከቢን ላዲን በሶስት ዓመት የምታንስ፣ እጅግ በጣም ቆንጆ ግን በትምህርቷ እስከዚህም የሆነች ሴት ናት፡፡ እሷና ቢን ላዲንም ዘወትር መጋጨት ጀመሩ፡፡ የተንቀሳቃሽነት ሕይወቱ እስከፈቀደለት ድረስ እሷን ለማረጋጋት ሲጥር ቆይቷል፡፡ እንዲያውም የእሱ እምነት የሚጠላውን የምዕራባውያን ሰላማዊነትን እንኳን ሳይቀበለው የአሜሪካኖችን የሴቶችን የውስጥ ልብስ እንኳን እንድትገዛ ፈቅዶላታል፡፡

በጋብቻ የፀና እምነት ከመኖሩ የተነሳ ቢን ላዲን ከየትኛዋም ሚስቱ ጋር ለመፋታት ተነሳስቶ አያውቅም ይሁንና አራተኛ ሚስቱ ልትተወው ፈለገች፡፡ መከፈሉ የተፈጠረው የሳዑዲ ዜግነቱን ከተነጠቀና መላው ቤተሰቡ ሱዳን ውስጥ መኖር ከጀመረ በኋላ ነው፡፡ እናም ኡሞ አዲና ቢን ላዲን አብረው ረጅም ርቀት ሳይጓዙ ቀሩ፡፡ ከወላጆቿ መነጠሉ፣ በሱዳን ያለው ዝቅተኛ የኑሮ ጥራት፣ ተመልሶ ወደ ሳዑዲ አረቢያ የመመለሱ ተስፋ አጠራጣሪ መሆን ደስተኛ ላለመሆንዋ ተጨማሪ ምክንያት ሆንዋት እናም ቢን ላዲንን እንዲፈቱ ጠየቀችው፣ እሱም ተስማማላትና ሶስት ልጆቿን ይዛ ወደ ቤቷ ተመለሰች፡፡ ከዚያ እሱ ደግሞ ቢያንስ አንድ ተጨማሪ ልጅ የወለደችለትን የመናዊት ሴት አገባ፡፡

ፍቺን ከመቃወሙ በተጨማሪነት ቢን ላዲን ለሚስቶቹ ታማኝ ነበር፡፡ ከጋብቻው ውጪ ዕቁባት ማስቀመጥና በወሲብ ዘና ማለትን አይሻም፡፡ ከአንዳንዶቹ ሃይማኖታዊ አክራሪዎች በተለየ፣ ወሲብን ዝም ብሎ ለፍላጐት ማርኪያ ብቻ የሚውል የሰው ልጅ ተፈጥሮ ውስጥ ያለ ተራ ነገር አድርጐ አይወስድም በጋብቻ ውስጥ የሚፈፀም እንጂ፡፡ ለዚህም ይመስላል ለጤናማ ወሲባዊ ግፊት ማብረጃያ ሲል ገና በአፍላ ጉረምሳነቱ ሙሽሪትን የወሰደው፡፡ ከቤት ውጭ ከወሲባዊ ተራክቦ ለመራቅ ይጠነቀቃል የወሲባዊ ሀሳቦችን ግድድር ለመቋቋም እንኳን አንድ ሴት ወደ ክፍል ስትገባ ዐይኑን ይነቅል ነበር፡፡

በሁሉም ረገድ ቢን ላዲን ጥብቅ ቢሆንም በተቻለው መጠን ጊዜውን ከልጆቹ ጋር ማሳለፍ የሚወድ አፍቃሪ አባትም ጭምር ነው። ለካምፕ ጉዞ ወደ በረሃ ይወስዳቸዋል፣ የቤት ስራቸውን በመስራት ረገድ ዕገዛ ይሰጣቸዋል፣ ስፖርትና የተለያዩ ጨዋታዎችን አብሮአቸው ይጫወታል። ዋነኛ እስላማዊ እምነቱን እንዲፈፅሙ የሚያደርጋቸው ቢሆንም ቢን ላዲን ከራሱ ፅንፈኛ ድንጋጌ በተቃረነ መልኩ ልጆቹን አያቀርባቸውም ነበር። እሱም ቢሆን በእስልምና ሕግ መሰረት እንደሀራም የሚወገዘውን ሙዚቃ ይዝናናበታል። በተጨማሪም ወንድ ልጆቹ ናይንቴንዶ እንዲጫወቱ ይተዋቸው ነበር። ይህ አስተያየት የእንጀራ እህቱ እሱ ሳዑዲ እያለ ከሰጠችው አስተያየት በጭራሽ የሚቃረን ነው። እሷ እንዳስቀመጠችው ቢን ላዲን "ሙዚቃ ማዳመጥና ቴሌቪዥን ማየትን አይወድም ልጆቹንም ይህን ከማድረግ ይከለክላቸዋል። ምናልባትም ባንድ በኩል ጊዜያት አላዝበውት ሊሆን ይችላል አልያም ደግሞ በዚያ በአፍጋኒስታን አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ለልጆቹ ጥቂት የቅንጦት ኑሮ ፈቅዶላቸው ሊሆንም ይችላል።

# ባህርይና ስብዕና

የቢን ላዲንን ሕይወት ዝርዝር ነገሮች መልሰን ለመገጣጠም ብንሞክር የጥብቅ ፍላጎቶቹን፣ ተፈጥሮውንና ስብዕናዊ ዕድገቱን፣ እንዲሁም የባህሪውን ሁኔታ፣ በይበልጥ ደግሞ የተፈጠሩትን ነገሮች ማስቀመጥ ይቻላል። በአብዛኛው ህብረተሰብ ዘንድ እንደተለመደው የአንድን ሰው አብዛኛውን የሕይወት ክፍል የሚያውቁት የቅርብ ቤተሰብና ጥቂት ታማኝ ጓደኞች ናቸው። በዚህ ረገድ ተሳስሮ በተንሰራፋው የሳዑዲ አረቢያ የቤተሰብና የዝምድና ተቋም ውስጥ ቁጥሩ ከፍ ያለ ሊሆን ቢችልም የቤተሰብ አባላቶች ግን ለውጭ ሰው ስለአንድ ዘመዳቸው ለማውራት ፈቃደኛ አይሆኑም። ዝምድናቸው በቤተሰብና በአገር ደረጃ የታወቀ ከሆነ የዝናቸውን ደረጃ የበለጠ ያጠናክሩታል። የልደት ቀናትን ማክበርና ፎቶ ግራፍ ማንሳትን እንደሚቃወሙት አብዛኞቹ የዋሃቢስቶች አንጃ ሁሉ የግዛት አዔው ዝግና ምስጢራዊ ተፈጥሮ መረጃን ለመሰብሰብ ሁኔታዎችን ይበልጥ አስቸጋሪ አድርጉአቸዋል። ከዚህ በተረፈ አብዛኞቹ ታሪኮች በሕይወት ታሪኩ ሔደው የተለቃቀሙ እፍኝ ቁርጥራጮች፣ የሰውየው ዝና ጣሪያ ከነካ ታሪኩ እንደጥንታዊ ታሪክ ይታይ በጀመረበት ወቅት ከተደረጉ ቃለ መጠይቆች የተውጣጡ ናቸው።

እንደ ወጣት ኦሳማ ቢን ላዲን በዙሪያው በነበሩት ላይ ጥቂት ተፅዕኖዎችን አሳርፏል። ባልተለመደው ርዝማኔው ጥቂት ትኩረት

ሳይሰብ አይቀርም። መምህራኑና ጓደኞቹ ከሰው የማይደባለቅና ዝምተኛ፣ ጉብዝ ግን ብቻውን በት/ቤቱ ስራ ላይ የማይሳተፍ እንደሆነ ያስታውሳሉ። ጥልቅ አፍቃሪ ሃይማኖተኛነቱም ከአባቱ ሞት በኋላ እያደገ የመጣ ይመስላል። እንዲያም ሆኖ ግን እንዲህ ዐይነቱ ሁኔታ በሳዑዲ አረቢያ የተለመደ አይደለም። ወደ አክራሪ ገዳይነት እንዲያድግ ስላበቃው የልጅነትና የአቅመ አዳም ዕድሜው ባህሪይ ምንም የሚታወቅና ሀሳብ የሚሰጥ መረጃ የለም።

በተፈጥሮው በቁርጠኝነት ራቅ ባለ መልኩ ፊት ለፊት መጋፈጥን ያስቀድም ነበር። አንድ ጓደኛው ቢን ላደንን ለፀብ ሊያነሳሳው ፈልጎ ቢገፈትረው ቢን ላዲን ደግሞ ያን ጓደኛውን ከመግፋት ትቶታል "እየሮጥኩ ወደ ልጅ ሄድኩ ከዚያም ከኦሳማ አላቀቅሁት እናም ችግሩ በዚህ መንገድ ተፈታ።" ሲል ከሊድ በታሪክ ያስታውሳል "ከዚያ ደግሞ ኦሳማ ወደ እኛ መጣና "ታውቃለህ? አንተም ባትመጣ ኑሮ እኔ ችግሩን በሰላማዊ መንገድ እፈታው ነበር አለኝ።"

እማኞች በእሱ መሪነት ላይ አይስማሙም። አብዛኛው ግርማ ሞገሳዊ ማንነቱ ሊመጣ የቻለው በምዕራብ ዓለም ከታወቀና በሙስሊሙም ዓለም ከተወሰደ በኋላ ነው እንደ ወጣትና ላቅመ አዳም እንደደረሰ ሰው በቀላሉ የሚያምንና አንዳንዴም በልጅነቱ በሞት የተነጠቀውን የአባቱን ምስል የሚፈልግ ነበር። ከቅርብ ጓደኞቹ አንዱ ቢን ላዲንን ሲገልፀው "ጥሩ ወታደር ነው የትም

ላከው ትዕዛዛትን ይከተላል::" ይላል:: ይሁን እንጂ ይኸው ጓደኛው "ከቀጥታ ትዕዛዛት ይልቅ በምሳሌዎችና በምክሮች የሚጠቀም ተፈጥሯዊ መሪ" ሲልም ይገልፀዋል:: ሆኖም በዩናይትድ እስቴትስ ኦፍ አሜሪካ የቀድሞ አምባሳደር የነበሩት ልዕልት ባንደር ቢን ሱልጣን በቢን ላዲን የመሪነት ችሎታ ላይ የወረደ አስተያየት ነው ያላቸው:: "ስምንት ዳክዬዎችን በመንገድ ላይ መምራት የሚችል አይመስለኝም::" ይሉታል::

ቢን ላዲን ጠንካራ ስብዕና ባለውና እሱን ወደ ሃይማኖተኛነት የበለጠ እንዲለወጥ ባደረገው ሰው ተፅዕኖ ስር በቀላሉ ወደቀ:: ሶሪያዊው የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የስውነት ማጎልማሻ መምህሩ ለጥናት ቡድኑ ከመለመለው በኋላ ወደ ጅሃድ በሚወስደው መስመር በወንድሙ በሰይድ አስተምሮዎች ያነሳሳዋል:: አብዱላሂ አዛም ደግሞ ወደ ፓኪስታን በመሄድ ገቢ እንደያሰባስብና ሶቭየትን በመቃወም አፍጋኒስታን ውስጥ በሚደረገው ጦርነት እንዲያደራጅ ያግባባዋል:: ኋላም በግብፃዊው አክራሪ በዶክተር መይማን አል ዘዋሪ ውዝዋዜ ውስጥ ገባ:: አላምና ዘዋሪ የቢን ላዲንን የግል ሀብት በሽልማት መልክ ለማሽነፍና ለየግል የስራ መደባቸው የሚሰጣቸውን ገንዘብ ለማግኘት የሚፎካከሩ ነበር:: አንዳንዴ እነዚህ ሰዎች እሱን ከእነሱ ጋር እኩል እንደሆነ ሰው ሳይሆን እንደ አንድ ጠቃሚ ንብረት አድርገው ነው የሚመለከቱት::

## ዝንባሌና ፍላጐት

ኦሳማ ቢን ላዲን ለዓለማዊ ድርጊቶች ያለው ጥላቻ በጥቂት ዝንባሌና የጊዜ ማሳለፊያ እንዲገደብ አድርጐታል። ይሁን እንጂ ፈረሶችን የማደለብና የመጋለብን ልዩ ፍቅር ነበረው። ማሬም ባለድል ጋላቢም ነበር። ሶብየቶችን በመቃወም ለሚደረገው የአፍጋን ጦርነት ከመሄዱ በፊት በሳዑዲ አረቢያው የእርሻ ስፍራ ላይ ፈረሶችን ያደልብ ነበር። ወደ ሱዳንም ከሄደ በኋላ የፈረስ እሽቅድምድሙን ቢያከናውንም በምላሹ ትርፍ ለማግኘት ሲል ገንዘብ ግን አያስይዝም ነበር። በወጣ በገባው የአፍጋኒስታን መልክዐ ምድር፣ ሶቭየቶችንና አሜሪካኖችን በመቃወም በሚደረገው ትግል ውስጥ ፈረሶች የትግሉ አካል ነበሩ።

## ፅንፈኛ ሰበብ ፍለጋ

በማንኛውም የሳዑዲ አረቢያ መለኪያና እሱም በሚኖርበት ማህበራዊ መደብ ኦሳማ ቢን ላዲን ከማንም የተለየ ሰው አልነበረም። በሃይማኖታዊ አገዛዝ በሚመራ ማህበረሰብ ዕቅፍ ውስጥ ይሁን እንጂ ከዘመነኞቹና ከሐይማኖተኞቹ በላቀ ሁኔታ ሃይማኖተኛ ነበር። በማንኛውም መስፈርት ሀብታም ቢሆንም እንደታላቁና ያንድ ወገን ወንድሙ እንደምሳሌም የዓለም አቀፍ ኘሌይቦይ ዐይነት ሕይወት አልነበረውም። ምንም ነገር ሳያምረው አለአንዳች ቅንጦታዊ ሕይወት ነበር ያደገውም። ከዩኒቨርሲቲ ዲግሪ የማግኘት ችሎታው ቢኖረውም ይህን ለማድረግ ፍላጐቱን ያጤን ነበር። በክፍሉ ውስጥ

ንቁ እንቅስቃሴ የማድረግና የጥሩ ባለሙያነት ምርጫው ነበረው። ከእነዚህ ሁሉ ነገሮች ይልቅ እጅግ በተንቦረቀቀው የቢን ላዲን ቤተሰብ ውስጥ እዚህ ገባ የማይባል፣ የጥብቅ ሃይማኖተኛና በቤተሰቡ ውስጥ ምስኪናዊ አኗኗርን ነበር እሱ የመረጠው። በተጨማሪም ከእሱ ችሎታና ከትሁት ሃይማኖተኛ አስተጣጠቁ (አለባበሱ) ጋር የሚሄድ የሥራ ሀላፊነት ነበርም የተሰጠው።

ቢን ላዲን ያደገበት የታሪካዊ አጋጣሚ ድባብም የተለየ ነበር። እሱ ልጅ የነበረበት ጊዜ በዓረቡ ዓለም የልሽቀትና የመንኮታኮት ወቅት ነበር። የ1967ቱ የአረብ እስራኤል ጦርነት የአረቡን ዓለም ለውርደት የዳረገውና ዓለማዊውን የአረብ ብሔርተኝነት አንድነትን ዋጋ ቢስ ያረገበት ጊዜ ነው። በ1979 የተከሰቱት ሁለቱ ክስተቶች ማለትም በኢራን የነበረው የእስላማዊ ንቅናቄ ውስጥ በገራንድ መስጊድ ላይ የደረሰው ጥቃት፣ ጥቃቅን ግን ወሳኝ የሆኑ ፅንፈኛ ቡድኖችን ያነሳሳበት ወቅትም ነው። በ1979 የሶቭየት አፍጋኒስታንን መውረር ጭምር ይቺን የእስላም አገር ከአምላክ የለሽ ኮሚዩኒስቶች ጥቃት ለማዳን፣ ለሙስሊሞች በቅዱሱ ጦርነት የመሳተፍ ዕድል ከፍቶላቸዋል። ቢን ላዲን በአፍጋን ጦርነት ውስጥ እምነቱን በተግባር የሚተረጉምበት ዕድል አስተውሎ ነበር። ግጭቱ በተግባሩ ላይ ዕረፍት የለሽና ፍላጐቱ የሚያስፈልገውን ትኩረት ያደርግ ዘንድ አበቃው። ዓለም ታሪክ የሚነግርለት ጉድ ሆነ።

# ምዕራፍ ሁለት

# ኦሳማ ቢን ላደን ስለዓለም ያለው አመለካከት

በዓለም ላይ የሚኖረን እምነት፣ ግምት፣ አመለካከትም ሆነ አቋም የሚፈጠረው ቀስ በቀስ በጊዜ ሂደት ነው። በማህበረሰቡ የይሁንታ ክልል ተሸብቦ በቤተሰብና ጓደኞች ቅርፅ ተሰጥቶት አመለካከት በግለሰባዊ ገጠመኞችም ይወሰናል። በኋላ ላይ ሰውዬው ከግለሰባዊ ስነ ልቦናው አንፃር ሊለውጠው ወይም እንዳለ ሊያስቀጥለው ይችላል። ወደ ኦሳማ ቢን ላደን ሕይወት ስንመጣ አጋጣሚዎች ሐይማኖታዊ ታማኝነቱን ወደ አደገኛ ፅንፈኝነት ቀይረውት ከዕድሜው ጋር እየጨመረ ሄዷል።

## ከማህበረሰባዊና ታሪካዊ ዳራ አንፃር

ኦሳማ ቢን ላደን ሕይወቱን የጀመረው ስለዓለም አቋም ይዞ አይደለም። እንደማንኛውም ሰው ተወልዶ የተቀላቀለው ጥንታዊ ባህልና እምነት ያለውን ቤተሰብ ነው ። እነዚህ ኃይሎች በወግ አጥባቂው የሳውዲ አረቢያ ግዛት ውስጥ የቢን ላደንን ሕይወት ቅርጽ አስይዘውታል። ወደትምህርት ቤት ከገባ በኋላም አስተማሪዎች እና ጓደኞች በቀጥታ ከሬዲዮና ከቴሌቭዥን ከሚያገኛቸው ሃሳቦች ጋር ተዳምረው ተጨማሪ ተፅዕኖ በአመለካከቱ ላይ አሳርፈዋል። በዕውቀት ዘመኑም እንዴት መኖር እንደሚገባ የሚቃረኑ ገለፃዎች አጋጥመውታል። የቢን ላደንን አመለካከት ለመገንዘብ የተወለደበትን ማህበረሰብ ባህላዊ ዳራ እና ካደገ በኋላ አመለካከቱ ላይ ተፅዕኖ የፈጠሩ አጋጣሚዎችን መመርመር ይገባል።

ኦሳማ ቢን ላደን የተወለደው አገሩ ሳዑዲ አረቢያም ሆኖ በአጠቃላይ መካከለኛው ምሥራቅ በፈጣን ለውጥ በሚናጡበት ወቅት ነበር፡፡ የሳዑዲ አረቢያ ከመካከለኛው ዘመን ግዛትነት ወደ ዘመናዊ መንግሥትነት መለወጥ የቢን ላደንን ቤተሰብ ከድህነት ወደ ቱጃርነት ቀየረው፡፡ መሐመድ ቢን ላደን ከጉልበት ሰራተኛነት ተነስቶ የገነባውን የግንባታ ድርጅት ልጁ ሳሌም ወደ ዓለማቀፋዊነት አሳደገው፡፡ ኦሳማ ያደገው የነዳጅ ሃብት ተፅዕኖ በሳዑዲዎች ዘንድ መታየት በጀመረበት ወቅት ነው፡፡

## ወሳኝ አጋጣሚዎች

ከወሳኝ አጋጣሚዎች መካከል በስድስቱ ቀን ጦርነት እስራኤል አራት የአረብ አገራት የማሸነፏን ያህል ቢን ላደንና መሰሎቹ ላይ ተፅዕኖ ያሳረፈ የለም፡፡ በሰኔ 1967 እስራኤል የግብፅን ጥቃት ደመሰሰች፡፡ በቀጣዩ ሳምንት ዳግሞ የጆርዳን፣ ሶሪያና ኢራቅ ኃይሎችን አሸነፈች፡፡ የእስራኤል ማሸነፍ የሲናይ፣ ጋዛ፣ ዌስት ባንክና ጐላን ተራሮችን በቁጥጥር ስር እንድታውል ሲያደርጋት በርካታ ፍልስጤማውያንን አፈናቀለ፡፡ ከሁሉም በላይ ምስራቃዊ እየሩሳሌምን ማጣት የሙስሊሙን ዓለም የሚያንገበግብ ኾነ፡፡ ምስራቃዊ እየሩሳሌም የዳዊትን ጥንታዊ ከተማ እንዲሁም የጁዲዝምና ክርስትና ቅዱስ ከተሞችን የሚያጠቃልል ነው፡፡ "The Dome of the rock" ተብሎ የሚጠራውን የእማር መስጊድም ይዟል፡፡ በሙስሊሞቹ ዘንድ ሶስተኛ ቅዱስ ከተማ እንደሆነ ይታመናል፡፡ የሰለሞን መቅደስ በነበረበት ተራራ የቆመው መስጊድ ነብዩ መሐመድ ወደ ጀነት ሲያመሩ የተነሣበት ቦታ እንደሆነ ይታሰባል፡፡ የስድስቱ ቀን ጦርነት

ለአረብ አገራት ሶስተኛው ነው፡፡ የከፋው ሽንፈት የደረሰባቸው በ1948 እስራኤል አምስት የአረብ አገራትን አሸንፋ በመንግሥትነት ስትመሰረት ነበር፡፡ አረቦች በ1973 ደግሞ በዮም ኪፐር ጦርነት ሽንፈት ደረሰባቸው፡፡ አክራሪ ሙስሊሞች ለዚህ ሽንፈት ኃይማኖታዊ ምክንያት ይሰጡታል፡፡ ምዕራባዊ ሃሣቦችን በቀና የማየትን የነብዩን ሱና ባለመከተላቸው አምላክ ፊቱን አዙሮ የቀጣቸው መሆኑን ይናገራሉ፡፡

የፍልስጤማውያን መፈናቀል፣ የዶም አፍ ll ሮክን ማጣት እና በዋናነት ደግሞ የእስራኤል መኖር ኦሳማ ስለ ዓለም ያለውን አመለካከት ለመወሰን ዋነኛ መንስዔዎች ናቸው፡፡ "ዕዩናዊት የመስቀል ጦረኛ" አገር ለመፈጠሯና በመካከለኛው ምስራቅ ስለመስፋፋቷ ኦሳማ ቢን ላደን ጣቱን የሚቀስረው ወደ አሜሪካ ነው፡፡ የሁለቱ አገራት ግንኙነት ግን የየአገራቱ ህዝብም ኾነ የአረቡ ዓለም ነዋሪዎች ከሚያስቡትም በላይ ውስብስብ ሆኖ የቆየ ነው፡፡ ምንም እንኳን ዩናይትድ ስቴትስ በርካታ አይሁድ ስደተኞች በፍልስጤም መሬት ላይ እንዲሰፍሩ እንድትፈቅድ በእንግሊዝ ላይ ጫና ያደረጉት በ1948 እስራኤል መንግሥትነቷን ስታውጅ ቀድማ ዕውቅና የሰጠቻት አገር ብትሆንም ከዚያ በኋላ በነበሩት ሁለት አስርት ዓመታት ያደረገችላት ዕገዛ ግን በጣም ጥቂት ነበር፡፡ የሁለቱ አገራት ግንኙነት የታደሰው ከስድስቱ ቀን ጦርነት በኋላ ነው፡፡ በዮም ኪቱር ጦርነት ወቅት የዩናይትድ ስቴትስ በጦር መሳሪያ አቅርቦት በኩል ከፍተኛ እርዳታ አድርጋላታለች፡፡ ዩናይትድ ስቴትስ በመካከለኛው ምስራቅ ላይ ያሏትን ሁለት ተፋታጊ ፖሊሲዎች (ለምዕራቡ ዓለም ዋነኛ የነዳጅ ምንጭ ከሆኑት አረቦች ጋር በሰላም መዝለቅና ከእስራዔል ጋር ያለውን ወዳጅነት ማጠናከር) አስታርቆ ለመዝለቅ ስትጥር ቆይታለች፡፡ ጠንካራ ፅዩናዊነትን

ሰባኪ ቡድን አሜሪካ ውስጥ መኖሩ ቢን ላደን በአይሁዶች ላይ የያዘው አቋም ማጠናከሪያ ሆኖታል።

ቢን ላደን በእስራዔልና በዩናይትድ ስቴትስ መካከል ያለውን ግንኙነት "የአሜሪካም ሆነ የሌሎች አገራት መሪዎች በአይሁድ ፅዮናዊያን ተጠልፈዋል። ህዝባቸውንም በእስልምናና ሙስሊሞች ላይ እንዲነሳ አድርገዋል።" ሲል ለአንድ ጋዜጠኛ ተናግሮ ነበር። ከ9/11 ጥቃት በኋላ ቢንላደን ለጥቃቱ መንስዔነት በከፊል የፍልስጤማውያን ጉዳይ ስለመሆኑ እንደሚከተለው ገልጿል "ፍልስጤም ውስጥ በነፃነት መኖር እስከምንጀምር ድረስ አሜሪካ ሰላም እንዳማይኖራት ምለናል።" በፍልስጤም ምድር እየሆነ ያለው የአሜሪካና ፅዮናውያን ቁርኝት በቀሪው የአካባቢው አገራት ላይም ሊጭኑ ለሚፈልጉት ምሳሌ ነው። ያለው ቢን ላደን "ወንዶች፣ ሴቶችና ህፃናትን የሚጨፈጭፉት፣ እስር ቤቶቻቸው፣ ቤቶችን የሚያፈርሱት፣ የእርሻ ሥራዎችን የሚነጥቁት፣ ፋብሪካዎችን የሚያፈርሱት በአጠቃላይ የሚያሸብሩት፣ በመካከለኛው ምስራቅ ታላቋን እስራኤል የመፍጠር ዓላማቸውን ዕውን ለማድረግ ነው።

በ1979 ተከታትለው የተፈፀሙ ኩነቶች የኦሳማ ቢንላደንን አመለካከት ቀይረው ወደ ዓለማቀፋዊ ጂሃድ እንዲያመራ አድርገውታል። በዚያው ዓመት ጥር ወር ላይ አያቶላህ ሩሆላህ ሙሳቪ ኮመኒ የኢራን ሻህ በአብዮታቸው አውርደው እስላማዊ ሪፐብሊክ መሰረቱ።

የኢራኑ አብዮት በሙስሊሙ ዓለም ለእስልምና መስፋፋት ለሚተጉ ቡድኖች እንደታላቅ ምሳሌ የሚወሰድ ነው። በሕዳር ወር አክራሪ ሙስሊሞች በመካ ታላቁን መስጊድ ተቆጣጥረው እስልምናን የሚያነቃቃው መሪያቸው መሃዲ እንደተተነበየው በእስላማዊ ዓመት 1400 (1979)

እንደሚመጣ አወጁ። ሳዑዲና ፈረንሳይ ከ12 ቀናት ደም አፋሳሽ ትንቅንቅ በኋላ መስጊዱን መልሰው ተቆጣጠሩት።

የ12 ቀናቱ አጋጣሚ በቢን ላደን ሕይወት ላይ ያመጣው ተፅዕኖ በግልፅ ባይታወቅም በኋላ ላይ ቢን ላደን ንጉስ ፋሃድ ሁኔታውን የተቆጣጠሩበትን መንገድ ተችቷል። ቢን ላደን እንደሚለው ንጉሱ መስጊዱን መልሶ ለመያዝ በተደረገው ግብግብ አርክሰውታል። "የሁሉንም ምክር ችላ ብሎ የታጠቁ ኃይሎችን ወደ መስጊዱ እንዲገቡ በመፍቀድ የድንቁርና ተግባር ፈፅሟል።" ብሏል ይህ አባባል ምናልባትም በኋላ ላይ ቢንላደን ከንጉሳዊያኑ ጋር ስለመጣላቱና ስለ መነጠሉ የመነሻ ምክንያት የመስጊዱ ላይ የተፈፀመው ጉዳይ ሊሆን እንደሚችል ፍንጫ ይሰጣል።

በ1979 የተፈፀመው ሶስተኛው ድርጊት ደግሞ ከሁሉም የበለጠ ወሳኝ ይመስላል። በታህሳስ 1979 ሶቭየቶች በመካከለኛው የእስያ እህጉር ወደምትገኘው አፍጋኒስታን ኮምዩኒስት መንግስት ለመመስረት ጦራቸውን ላኩ። ወረራው በሶቭየቶችና በሳዑዲ አረቢያና በዩናይትድ ስቴትስ በሚደገፉ የአፍጋን አማፅያን መካከል ለተካሄደው የአስር ዓመት ጦርነት መነሻ ኾነ። ግጭቱ በርካታ የውጩ አገር ፈቃደኛ ተዋጊዎች (ቅዱስ ተዋጊዎች) ከተለያዩ የሙስሊም አገራት እንዲሰባሰቡ አድርጓል። ከእነዚሁ ተዋጊዎች መካከልኣሳማ ቢን ላደን አንዱ ነበር።

## ባህላዊ እስልምና

አብዛኞቹ ከሚያምኑት በተፃራሪው እስልምና ከሌሎች እምነቶች በተለየ ሁኔታ ብጥብጥን አያበረታታም። እንደሌሎቹ በርካታ እምነቶች ሁሉ ጥቂት ተከታዮቹ ግን የፅንፈኝነት አጀንዳን ያራምዳሉ። እነዚሁ

ጥቂት ፅንፈኞች በምዕራባውያን ሚዲያዎች የተሰጣቸው ከፍተኛ ግምት ግን አብዛኛውን ሙስሊም ይወክላሉ የሚል ግምት እንዲፈጠር አድርጓል።

እስልምና ምንጫቸውን ከወደአብርሃም ከሚቆጥሩ ሶስት ታላላቅ እምነቶች አንዱ ነው። አይሁዶች የዘር ሃረጋቸው ከአብርሃም ልጅ እስማኤል እንደሆነ ይናገራሉ። በእስልምና ትምህርት ላይ እንደተጠቀሰው በ610 C.E ነብዩ መሐመድ መካ በዋሻ ውስጥ እያሉ ነበር መልአኩ ጂብሪል የተገለጠላቸው ። በኋላም ለቀጣይ ዓመታት እየተገለጠ በርካታ እውነቶችን ይነግራቸው ነበር። እነዚሁ እውነቶች ከመሐመድ ሞት በኋላ ተፅፈው ቁርዐን ሆኑ። አምላክ (በአረብኛ አላህ) ከዚያ በፊት ተመሳሳይ መልዕክት መጀመሪያ ለአይሁዶች በሙሴ በኩል በኋላ ደግሞ ለክርስቲያኖች በእየሱስ በኩል አስተላልፎ ነበር። ይሁንና የነዚህ ነብዮች ተከታዮች ራዕዮችን ስለበረዟቸው አምላክ ለሶስተኛ ጊዜ አንድ የመጨረሻ ዕድል ለመስጠት በነብዩ መሐመድ በኩል ለህዝቡ ተናገረ። ራዕዮቹ ከአምላክ ለመሐመድ የተሰጣቸው በአረብኛ በመሆኑም ቁርዐን በሌላ ቋንቋ አይተረጎምም። ሙስሊሞች ለማንበብ ሲፈልጉ አረብኛ መማር አለባቸው።

ዋናዎቹ የቁርዐን አስተምርሆዎች ሙስሊሞች አምስቱ የእስልምና ካስማዎች የሚሏቸው ናቸው። ሻሃዳህ፣ (ለአላህ መስጠት)፣ ሰላት፣ (ፀሎት)፣ ዞካት፣ (መስጠት)፣ ሳውም (ፃም) እና ሃጂ (ጉዞ) ይሰኛሉ። በእንዳቸውም ውስጥ ብጥብጥንና ኹከትን የሚፈቅድ የለም።

# ሱኒ እና ሺዓ

የመሐመድን ሞት ተከትሎ የሙስሊሙን ዓለም ለሁለት የሚከፍል ውዝግብ ተነሳ። አብዛኞቹ ተከታዮቹ ነብዩን የሚተካ ሰው መመረጥ ያለበት

በምክክር ከተከታዮቹ መካከል ነው አሉ፡፡ ቡድኑም ሱኒዎች ተባሉ፡፡ የመሐመድ የአጎት ልጅ አሊ በበኩሉ ነብዩን የሚተካው ሰው (ከሊፋው) የነብዩ ቤተሰብ አባል መሆን አለበት ሲል ተቃወመ፡፡ የእሱ ደጋፊዎችም "የአሊ ተከታዮች" መሆናቸውን ገለፁ፡፡ በአረብኛ ሺአዎች ተባሉ፡፡ እንደአብዛኞቹ አክራሪዎች ቢን ላደንም ሺአዎችን ይመርጣል፡፡ ከ85 እስከ 90 ከመቶ የሚኾኑት የዓለም ሙስሊሞች ሱኒዎች ናቸው፡፡

## ጂሃድ

ከእስልምና ፅንሰ ሃሣቦች ሁሉ የጂሃድን ያህል ቅዱስ ጦርነት በሚል የተሳሳተ ትርጉም የተሰጠው የለም፡፡

- *የአረብኛው ስም ጂሃድ (jhd) ከሚለው ግስ የመጣ ሲሆን ጃሃድ "በከፍተኛ ሁኔታ መጣር" ማለት ነው፡፡ ስለዚህም ከ "ቅዱስ ጦርነት ይልቅ" ቅዱስ ትግል "ወይም " ለእውነት መታገል" የሚሉት ትርጉሞች የተሻለ ይገልፁታል፡፡ ቁርዐን ላይም "አላህ ቀድሶ የፈጠረውን ሕይወት ከፍትህ እና ሕግ ውጪ አታጥፋ" ይላል፡፡*

## ሳላፊዝም እና ዋሃቢዝም

ሳላፊዝም እና ዋሃቢዝም የተሰኙት ንቅናቄዎች በሳዑዲ አረቢያ ማህበረሰብም ኾነ የኦሳማ ቢን ላደንን አመለካከት ላይ ከፍተኛ የቅርፅ ተፅዕኖ ያደረጉ ናቸው፡፡ ሳለፍ "ፅኑ ዝርያ" ማለት ሲሆን ሳላፊዝም በ9ኛው ክፍለ ዘመን ተጀምሮ በ14ኛው ክ.ዘ ታቂ አል ዲን አህመድ ኢብን ታይሚያ ያስፋፋው ሙስሊሞች ወደመጀመሪያዎቹ ኡማዎች (የመሐመድ

ጊዜ አማኞች) ንፁህ ትምህርቶች መመለስ አለባቸው የሚል ነው። በጥሪውም ውስጥ የሱኒዎችን ቀጥተኛ ትምህርት ሲያወግዝ በሙስሊም መሪዎች ላይ ማመፅ እንደማይገባ ይሁንና ለሸሪያ ህግ መሰረት የማይገዙ መሪዎች ላይ ጂሃድ የተፈቀደ መሆኑ ተገልጿል። ጂሃዱም ሙስሊም በሆኑም ኾነ ባልሆኑ መሪዎች ላይ እንደሚካሄድ ይገልፃል።

በ18ኛው መቶ ክ/ዘ ላይ ደግሞ አዲስ የሳላፊስት ንቅናቄ በአረቢያ ምድር ተከስቷል። እንደ ታይሚያ ሁሉ መሐመድ ኢብን አብድ አልዋሃብ (ከ 1703-1792) እስልምና ወደቀደመ ንፅህናው መመለስ አለበት የሚል አቋም አንቀሳቅሷል። በ1745 ዘመናዊ የሳዑዲ ንጉሳዊ አገዛዝ በአልዋሃብ እና በሳዑድ ቤት ትብብር ሲመሰረት አገሪቱ በሸሪያ ህግ እንደምትተዳደር ቃል የተገባላቸው አልዋሃብና ተከታዮቹ አገዛዙን ለመርዳት ቃል ገብተው ነበር። በ19ኛው ክ/ዘመንም ሳላፊዝም በግብፅ፣ ፐርሺያ (ኢራን) እና ሶሪያ ብቅ ብሎ ማለቱ አልቀረም። የ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ሳላፊዝም ኦሳማ ቢን ላደን የሚያራምደው መሆኑ ነው።

## የሙስሊም ወንድማማቾች

በሁለቱ የዓለም ጦርነቶች መካከል በግብፅ እስላሚዝም የተሰኘ የሳላፊዝም ንቅናቄ ተፈጥሮ ነበር። በ1928 ሃሰን አልባና ሙስሊም ወንድማማቾች የተሰኘ ድርጅት ካይሮ ውስጥ መሰረተ። እንደቀዳሚዎቹ ታይሚያና አልዋሃብ አለ ባናም በ7ኛው መቶ ክፍለ ዘመን እንደነበረው ሕይወት ሙሉ በሙሉ በእስላማዊ መንገድ መመራት እንዳለበት ያምናል። የቅኝ አገዛዝ ዘመንን ማብቃት ተከትሎ አልባናም ንቅናቄውን ስር እንዲሰድ የሚያደርግበት ጥድፊያ ውስጥ ገባ። እንግሊዞች ግብፅን ሲለቁ የንጉስ ፋሩክ

አስተዳድርና የኮሎኔል ጋማል አብዱል ናስር ሶሻሊስታዊ የአረብ ብሔርተኝነት እንቅስቃሴ መካከል የስልጣን ሽኩቻ በመካሄድ ላይ ነበር። አል ባና ሁለቱንም በመንቀፍ የምዕራባውያኑን መንገድ በመተውና እስላማዊ ቅርሳቸውን በመቀበል ብቻ ግብፃውያን ወደብልፅግና መምጣት እንደሚችሉ መወትወት ያዘ። "ዛሬ ዛሬ አብዛኞቹ ሙስሊሞች ጠላትን መዋጋት ጂሃድ አሽጋር (ያነሰ ዋጋ ያለው) ይመስላቸዋል። ይሁንና ጠላትን መውጋት ጂሃድ አክባር (ከፍተኛ ዋጋ ያለው) ነው።" ሲልም ተናገረ።

የግብፅ መንግሥት የሙስሊም ወንድማማቾችን ቢሮ በ1948 ከዘጋ በኋላ በ1949 የግብፁን ጠቅላይ ሚኒስትር ሞት ለመበቀል አል ባናን ገደለው። ሙስሊም ወንድማማቾች ግን ውስጥ ውስጡን ያውም ተጠናክሮ ስራውን ቀጠለ። ሰይድ ቁጥብ ሙስሊም ወንድማማቾችን በ50ኛዎቹ ከተቀላቀለ በኋላ የድርጅቱ ዝነኛ ቃል አቀባይ ሆነ። "እስልምና ብቸኛው የሕይወት መንገድ ነው። በዚህም ከሌሎቹ ሁሉ ይለያል። ስለዚህ ከዚህ ስርዐት የተለየ መንገድ የሚፈልግ ማንኛውም ሰው በብሔር፣ ቀለምና ዘር ሳይለዩ የሰው ልጅ ጠላቶች ናቸው።" የሚለው ቁጥብ "ሙስሊሞች በተገኙበት ቦታ ሁሉ ፖለቲካዊ ሥልጣኑን የመውሰድና የተቀደሰውን ኑሮ በምድር የማስፈን መብት አላቸው።" ይላል። ምንም እንኳን በ1952 የንጉስ ፋሩክን መንግሥት ለመገልበጥ ቁጥብና ሙስሊም ወንድማማቾች ከኮሎኔል ጋማል አብዱል ናስር ጋር ቢያብሩም በኋላ ላይ ያሰቡት እስላማዊ ሪፐብሊክ እውን ሳይሆን ሲቀር በናስር ላይም ተነሱበት። ናስር ግብፅ መከተል ያለባት ብሔርተኝነትና ሶሻሊዝምን ነው ብሎ ማመኑ ለቁጥብ በፍፁም የሚዋጥለት አልሆነም።

እንደ ቀዳሚው አልባና ሁሉ ቁጥብም በ1976 በናስር መንግሥት ላይ በማመፅ ተከሶ በሞት ተቀጣ፡፡ የእሱን ሞት ተከትሎ የቡድኑ እንቅስቃሴ እየጐላ መጣ፡፡ ቁጥብ በእስራት ዘመኑ እስላማዊ አመለካከቱንና ፖለቲካዊ ፍልስፍናውን የሚያበራራ Omilestones የተሰኘ መጽሐፍ ደርሷል፡፡ ኦሳማ ቢን ላደንም ተማሪ ኾኖ ይህንኑ መጽሐፍ በማንበቡ የቁጥብ ተፅዕኖ አርፎበታል፡፡ ከቁጥብ ሞት በኋላ ሙስሊም ወንድማማቾች ተከፋፈሉ፡፡ የኾነ ሆኖ በኋላ ላይ መሪ ኾኖ ብቅ ያለው ዶ/ር አይማን አል ዛዋሂሪ ቢን ላደን ዓለማቀፋዊ ጂሃድ እንዲያውጅ በእጅጉ ረድቶታል፡፡

በዩኒቨርስቲ ቆይታ ጓደኛው የነበረው ጀማል ከሊፋ የቁጥብ ጽሑፎች በቢን ላደን ላይ ተፅዕኖ ማሳረፋቸውን ይናገራል፡፡ ከሊፋ እንደሚለው ቁጥብ ቢን ላደን ላይ ብቻ ሳይሆን በዚያ ዘመን በነበሩ ሙስሊሞች ላይ ሁሉ ተፅዕኖው ታይቷል፡፡

ዘመናዊ እስልምና እንደ ናስር ዐይነተኛ የአረብ ብሔርተኛ መንግሥታትን ለመመስረት አማራጭ ስለሚሰጥ አክራሪዎቹ ፖለቲካዊ እስልምና ብለው ይጠሩታል፡፡

## ቤተሰብ

በወቅቱ ከነበሩት የዕውቀት ማዕበሎች በተጨማሪ ሰፋ ያለው የቢንላደን ቤተሰብ አደረጃጀት በኦሳማ አመለካከት ላይ አሻራውን አኑሯል፡፡ ምንም እንኳን አባቱ የሞተው ገና የዘጠነኛ ዓመት ልጅ እያለ ቢሆንም ከመሐመድ ሞት በኋላ የቤተሰቡ አለቃ የኾነው ታላቅ ወንድማቸው ሳሌም ቢን ላደንን ወደአውሮፓና አሜሪካ በመውሰድ ዘናያለ ኑሮ እንዲላመድ ያደረገውን ጥረት ችላ ብሎ አባቱን ለመምሰል ይጣጣር እንደነበር የራሱ

በሆኑ ውስብስብ ምክንያቶች የተነሳ ወግ የሚያጠብቀውን የዋሃቢ እስላማዊ ስርዐት እንደመረጠ ጓደኞቹ ይናገራሉ።

ካሀሊድ በታራፊ ስለቢላደን ሲናገር "የቢን ላደን ቤተሰቦች በሙሉ የሚታወቁት በትምህርትና በታታሪ ሰራተኛነታቸው ነው። የማውቃቸው ሁሉም እንደዚያ ናቸው። ቢን ላደን ግን ይለያል። በእጆቹ መስራት ያዘወትር ነበር። ትራክተሮችን ይነዳል። እንዳአባቱ ሁሉ ከሰራተኞች ጋር ይመገባል። ከንጋት እስከ ምሽት ሳይታክት ሜዳ ላይ ይሰራል። እንደ ሃብታም ልጅ አልነበረም።" ይላል።

# የኦሳማ ቢን ላደን አመለካከት አመጣጥ

የኦሳማ ቢን ላደን አመለካከት በእንደዚህ ዐይነት መንገድ የተቀረፀ ነው ብሎ ግልፅ ትንታኔ ማቅረብ በጣም አስቸጋሪ ነው። ኃይለኩልን ሲያገባድድ ጠንካራ ሐይማኖታዊ አቋሙ ላይ ደረሶ የነበረ ቢሆንም ፖለቲካዊ አቋሙ ግን ገና ቅርፅ መያዝ መጀመሩ ነበር። ከዚያ በኋላ የመጡት የቁጥብ ዕሁፎች፣ የአስተማሪው አብዱላህ አዛም አስተምሮ እና የእስላማዊ ጂሃድ ሃሣብ በሰፊው መንሸራሸር ጉዳዮች መጨረሻ ላይ ወዳዳበረው አቋም ያመጡት ይመስላሉ።

ቢን ላደን ጂዳ በሚኖርበት ወቅት የሚያውቀው የአንድ የሳዑዲ ጋዜጠኛ ያስቀመጠው ነገር ሚዛን የሚደፋ ይመስላል። "ኦሳማ የሙስሊም ወንድማማቾችን እንደተቀላቀልነው ማንኛችንም የሳዑዲ ዜጎች ነው። እሱን የተለየ የሚያደርገው ሐይማኖቱን በእጅጉ ማጠንከሩ ነው።" ይላል ጀማል ካሾጊ።

ለሐይማኖቱ በጣም ጥብቅ ትርጉም ነው ያለው። አያጨስም፤ ከሴቶች ጋር አይጨባበጥም፣ ከቴሌቭዥን የሚከታተለው ዜና ብቻ ነው። ስዕል እስላማዊ አይደለም ብሎ ስለማያምን በግድግዳዎቹ ላይ ምንም ዐይነት ምስሎች አይሰቅልም። የሃብታም ልጅ ቢሆንም ቀላል ኑሮ መኖር ይፈልጋል። አጥፊነት ያልተወደደ ነው ብሎ ያምናል" ሲል ይገልፀዋል ጋዜጠኛው።

ኦሳማ ቢን ላደን ያስፋፋው አመለካከት "ጂሃዲስት ሳላፊዝም" እንደኾነ በበርካቶች ዘንድ ይወሰዳል። ቢን ላደን ጂሃድን እንደግዴታ የሚወስድ ነው። በሸሪያ ሕግ በሚያስተዳድሩ የእስላም መሪዎች ላይ ጂሃድ መታወጅ አለበት ይላል። እነዚህን ጠንካራ አመለካከቶቹን በሙሉ ኃይል ማውጣት የጀመረው ግን ከሳዑዲ አረቢያ ከወጣ በኋላ ነው። ወደ ሽብርተኝነት በሚያመራው ሕይወቱ ውስጥ አረቢያ ከወጣ በኋላ ነው። ወደ ሽብርተኝነት በሚያመራው ሕይወቱ ውስጥ ቀጣዩ ወሳኝ ምዕራፍ በአፍጋኒስታን ከሶቭየቶች ጋር የተካሄደው ጦርነት ነው።

# ምዕራፍ ሶስት

# ኦሳማ በአፍጋኒስታን

አጋጣሚዎች ኦሳማ ቢን ላደንን 'ክተራ ሰውነት' ወደ ዓለማቀፍ የፖለቲካ ማዕከልነት ያስፈነጠሩት በአስር ዓመታት ውስጥ ነው። ቁልፉ ዓመት ደግሞ 1979 ነው። አስቀድመን እንደጠቀስነው የኢራኑ አብዮትና የታላቁ መስጊድ ግጭቶች በሙስሊሙ ዓለም ዘንድ ንቅናቄን ፈጥረዋል። በወቅቱ ቢን ላደን በሁለቱ ክስተቶች ላይ ያለው ነገር ባይኖርም ቆየት ብሎ የሳዑዲ ባለስልጣናት ታላቁን መስጊድ ለመቆጣጠር ያልተገባ ኃይል ተጠቅመዋል ሲል ኮንኗል። እነዚሁ ኹነቶች በኋላ ላይ ላካሄዳቸው ጂሃዶች መነሳሳትን ሳይፈጥሩለት እንዳልቀረ ይገመታል።

## የአፍጋኑ ጦርነት

ኦሳማ ቢን ላደን በአፍጋኒስታን ከሶቭየቶች ጋር ያካሄደው ጦርነት በአመለካከቱ ላይ ያመጣውን ተፅዕኖ ማጋነን የሚከብድ ይመስላል። በሕይወቱ ለመጀመሪያ ጊዜ ከትውልድ ስፍራው ርቆ ለበርካታ ዓመታት የቆየውም ያኔ ነው። ሚያዝያ 14 ቀን 1979 የሶቭየት ጦር የአፍጋኒስታንን ኮሙኒስታዊ ስርዐት እያደገ ከመጣው እስላማዊ አማጽያን ለመታደግ አፍጋኒስታን ገባ። ሶቭየቶች ጦሯቸውን ሲያደራጁ ቆይተው በታህሳስ 27 ፕሬዚዳንቱን ከስልጣን አውርደው ጦራቸው በአማፅያኑ ላይ ከባድ ጥቃት እንዲከፍት አደረጉ። 100,000 ያህል ጦራቸው ተመሳሳይ ቁጥር ካለው የአፍጋን ጦር ተጣምሮ በመንቀሳቀስ ላይ ነበር። አመፅን

የመቆጣጠር ልምዳቸው አነስተኛ የኾኑት የሶቭየት ወታደሮች አማፅያኑን ይደግፋሉ ያሉትን ነዋሪ ሁሉ ጅምላ ጥቃት አደረሱበት። አንድ ሚሊዮን የሚገመቱ አፍጋናውያን በውጊያው አለቁ። ከሞቱት መካከል 80 ከመቶ የሚኾኑት ሰላማዊ ሰዎች ናቸው። በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ ደግሞ ወደጐረቤት ፓኪስታን ተሰደዋል።

ሶቭየቶች በጦር መሳሪያ በኩል ከፍተኛ ብልጫ ቢኖራቸውም አማፅያኑም ጠንካራ አጋሮች ነበሯቸው። ጠንቅቀው በሚያውቁት ህዝብና አካባቢ ተከልለው ነው የሚዋጉት። የኢራንን ተፅዕኖ ከአካባቢው ለማራቅ በመንገት የሳዑዲ አረቢያ ገንዘብ ወደ አማፅያኑ እያፈሰሰ ነበር። ዩናይትድ ስቴትስ በበኩሏ ሶቭየቶች በቬትናም ያደረሱባትን ጉዳት በአፍጋኒስታን መበቀል ትፈልግ ነበር። በቀዝቃዛው ጦርነት ወቅት የጠላትን ጠላት መርዳት የተወደደ ተግባር ነበር። እናም ጦርነቱ ሶቭየቶች እና አፍጋኖች በዩናይትድ ስቴትስ ውክልና የሚዋጉበት ኾነ። ሶቭየቶች የአፍጋኖችን ድንበር አቋርጠው በገቡበት ዕለት የብሔራዊ ደህንነት አማካሪው ዝቢግኒው ብርዜዚንስኪ ለፕሬዝዳንት ጂሚ ካርተር የሚከተለውን ማስታወሻ ልኮ ነበር። *"አሁን ለሶቭየቶች የቬትናም ጦርነትን የምንፈጥርለት ጊዜ መጥቷል። ምስኮ ለአስር ዓመታት የምራል ውድቀቷንና በመጨረሻም መፈራረሷን የሚያመጣውን ጦርነት መዋጋት ሊኖርባት ነው።"* የሚል። አማፅያኑ የገንዘብና አደገኞቹን ኤም-24 ሄሊኮፕተሮችን ሳይቀር የሚያወርዱ በትክሻ የሚያዙ ከመሬት ወደ አየር የሚወነጨፉ ሚሳኤሎችን በእርዳታ መልክ ያገኙ ነበር።

ሶቭየቶችን ፊት ለፊት ላለመጋፈጥ ሲአይኤ ለአማፅያኑ እርዳታውን ይሰጥ የነበረው በሌላ ሶስተኛ ወገን በኩል ነበር። እንደ አጋጣሚ የፓኪስታን መንግሥት ይህንኑ ኃላፊነት ለመወጣት ፈቃደኛነቱ ከፍተኛ ነበር። በካሽሚር ጉዳይ ከህንድ ጋር በከፍተኛ ውዝግብ ተወጥራ የምትገኘው ፓኪስታን በምስራቃዊው ድንበሯ ላይ ማተኮር እንድትችል የምዕራባዊውን ድንበሯን ፀጥታ አስተማማኝ ማድረግ ትፈልግ ነበር። እንደዚህ ዐይነቱ ስትራቴጂ ለማራመድ እንድትችል ደግሞ በአፍጋኒስታን ወዳጅ መንግሥት መመሥረት ስላለበት ፓኪስታን አማጽያኑን በጉጉት ነበር የምትረዳቸው። በፖኪስታኖች ቀመር መሰረት በካቡል የሚገኝ እስላማዊ መንግሥት ከኒው ዴልሂ ሂንዱ ሃጢያተኞች ጋር አብሮ ሊሰራ አይችልም። የፓኪስታን ኢንተር ሰርቪስስ ኢንተሊጀንስ ዳይሬክቶሬት የዩናይትድ ስቴትስና የሳዑዲን እርዳታዎች ለአማፅያኑ ያከፋፍል ነበር።

## የሙጂሃዲንነት ጉዞ

የአፍጋን አማፅያን ከዩናይትድ ስቴትስና ከሳዑዲ አረቢያ ከሚያገኙት የገንዘብና ጦር መሳሪያ እርዳታ ሳይወሰኑ በርካታ የውጪ አገራት ፈቃደኛ ተዋጊዎችንም ለመሳብ ችለዋል። በእስልምናዊ አስተምህሮዎች የተነሳሱት እነዚሁ "ቅዱስ ተዋጊዎች" እስላማዊውን መንግሥት ከአምላክ የለሹ ኮሚኒስታዊ ጦር ለመታደግ ለጂሃድ ወደ አፍጋን ይጉርፍ ነበር። የተዋጊዎቹ ተነሳሽነትና አቅም በእጅጉ ይለያያል። የተወሰኑት የመዋጋት ፍላጉት ኖሯቸው የወታደርነት ስልጠናን ግን ያላገኙ ናቸው። ሌሎች በተለይ የሳዑዲ ቱጃሮች ልጆች ግን የሽምቅ ውጊያን እንደጥቂት ሳምንታት የእረፍት ጊዜ ማሳለፊያ የሚቆጥሩ ነበሩ።

የአማፅያኑ አዛዦች እነዚህን ወጣቶች ከአባቶቻቸው ስለሚያገኙት የገንዘብ እርዳታ ሲሉ ተማፅነዋቸዋል። ዞሮ ዞሮ የውጭ ተዋጊዎች ቁጥር ከጥቂት ሺዎች ያልዘለለና በጦርነቱ ውጤት ላይም ጉልህ ተፅዕኖ ነበረው ለማለት የማያስችል ነው። አንድ የሳዑዲ ጋዜጠኛ ሁኔታውን ሲገልፀው "ስድስት ቀን ከቆዩት አንስቶ ስድስት ዓመት እስካሳለፉት ቁጥራቸው አስር ሺ ሊደርስ ይችላል። ምክንያቱም የጂሃድ ጉብኝት እና የጂሃድ ሽርሽር የሚያካሂዱም ነበሩ።" ብሏል። የውጪ ተዋጊዎች ቀጥተኛ ተፅዕኖ አነስተኛ ነበር ቢባልም በአልቃኢዳ ሚትሎጂ መሰረት የተዋጊዎቹ መሳተፍ ምንም ነገር ማሳካት እንደሚቻል ማረጋገጫ በመሆን ለእንቅስቃሴው የሞራል ስንቅ ሆኗል።

# የአፍጋን አገልግሎት ቢሮ

የ21 ዓመቱ ኦሳማ ቢን ላደን አፍጋኒስታን ሄዶ ውጊያውን ለመቀላቀል አልተጣደፈም። በወቅቱ ምንም ዐይነት ፖለቲካዊ እስልምና አቋም አላዳበረም። ይሁንና ፅንፈኛ እስልምናን በማያራምደው ፍልስጤማዊ አብዱላህ አዛም ተፅዕኖ ስር ወደቀ። አዛም እና ቢን ላደን አንድ የሚያደርጓቸው በርካታ እምነቶች ነበሯቸው። አዛም የሙስሊም ወንድማማቾች አባል ሲሆን ቢን ላደን ደግሞ የሰይድ ቁጥብን ፅሑፎች በጥልቀት አንብቧል። አዛም ከ1960ዎቹ ጀምሮ ለፍልስጤም ነፃነት ሲታገል የቆየ ነው። ምንም እንኳን ጆርዳን በ1971 የፍልስጤም ነፃ አውጪ ድርጅትን ማባረሯ ትግሉን ለጊዜው ቢያቀዘቅዘውም። ቢን ላደንም ለፍልስጤማውያኑ ጥያቄ ድጋፍ ለእስራኤል ደግሞ መሪር ጥላቻ ሲያዳብር የቆየ ነው።

ሶቭየቶች በአፍጋን ሲወረሩ አዛም የፍልስጤማውያን ጥያቄ ከሁሉም ቀድሞ መፈታት ያለበት እስልምናዊ ችግር የሚያምን ቢሆንም የአፍጋን አማፅያንን ጥያቄ ፍትሃዊነት ማጉላት ጀመረ። "ከአረቦች መካከል በፍልስጤም ጂሃድ መሳተፍ የሚፈልግ ሁሉ አሁኑኑ መጀመር አለበት" የሚል ትዕዛዝ ያስተላልፍ ነበር። "ያን ማድረግ የማይችል ግን ወደ አፍጋኒስታን መሄድ አለበት። ቀሪዎቹ ሙስሊሞች ደግሞ ጂሃድን በአፍጋኒስታን መጀመር አላባቸው።" ከሶቭየቶች ጋር የተካሄደው ጦርነት አጣዳፊነትና ውጤታማነት ከሙጅሃዲኖች (ፈቃደኛ ተዋጊዎች) ዓላማ ጋር ተጣምሮ ከእስራኤል ጋር ለሚካሄደው ውጊያ እንደምሳሌ እንዲቆጠር አደረገው።

በ1981 በንጉስ አብዱል አዚዝ ዩንቨርሲቲ ተጋባዥ ሌክቸረር የነበረው አዛም በሳዑዲ መንግሥት አይዞህ ባይነት መሆኑ በማያጠራጥር መልኩ የአፍጋን አማፅያኑን ትግል በይፋ ያበረታታ ነበር። አዛም በአፍጋኒስታኑ ትግል ላይ የነበረውን ሚና ፓኪስታናዊው የምህንድስና ተማሪ ጀማል ኢስማኤል "ከአረብ ሐይማኖታዊ አስተማሪዎች በተለይ ደግሞ በሙስሊም ወንድማማቾች ዘንድ ታዋቂነቱ የጉላ ስለነበር የአፍጋኑን ትግል ጉዳይ ለሙስሊሞች ያስተዋወቀው እርሱ ነው።" ሲል ይገልፀዋል።

አዛም በ1980ዎቹ አጋማሽ በጂዳ ወደሚገኘው የቢን ላዲን መኖሪያ ይመላለስ ነበር። የቢን ላዲን የዩኒቨርስቲ ጓደኛ የነበረው ጀማል ከሊፋ ስለንብኙቱ ሲያስታውስ "ኦሳማ በአል አዚዝያህ ወደሚገኘው ቤቱ ጋብዞኝ ነበር። በዚያ ህንፃ አለው። በጊዜው 25 ወይም 26 ዓመት ቢሆነው ነው። ሁለት ጊዜ ያህል አግብቷል። አብዱላህ አዛምም እንደሚመጣ ነገረኝ። አብዱላህ አዛም ጉበዝ ፀሃፊና የተማረ መሆኑን በመጽሐፎቹ ስለማውቅ

ስለ አፍጋኒስታን ማውራት ሲጀምር በከፍተኛ ጉጉት ነበር የማዳምጠው::" ይላል:: የተጠቀሰው የቢን ላዲን ዕድሜ እንደሚጠቁመው ጊዜው 1982 ወይም 1983 መሆኑ ነው::

አዛምና ቢን ላዲን ስለተነጋገሩበት ጉዳይ ምንም ማስረጃ ባይኖርም ከአዛም ጽሑፎችና ቢን ላዲን ወደ ፓኪስታን ተዛውሮ ጂሃዱን ለማገዝ ከመወሰኑ አንፃር የውይይታቸውን ዐብይ ነጥብ መገመት ከባድ አይሆንም:: አዛም ለአፍጋን ውጊያ ተጨማሪ ገንዘብና ተዋጊዎችን ለማሰባሰብ ፈልጓል:: ለትግሉ የሃብትን አስፈላጊ መሆን ቢያምንም ገንዘብ መላክ ብቻውን የአፍጋን አመፅያንን ለማገዝ በቂ እንዳልሆነ አምኗል:: "ጂሃድን በሃብት ከመዋጋት በአካል መዋጋት እንደሚበልጥ ጥርጥር የለውም::" ሲል የተከራከረው አዛም "በነብዩ ዘመን የነበሩ ሃብታሞች ለምሳሌም ኡትማንና አብዱር ራህማን ኢብን ኡፍ እንዳይዋጉ ይቅርታ አልተደረገላቸውም:: ምክንያቱም ትግሉ የነፍስ ንፅህናና የመንፈስ ለውጥ ከፍ የሚልበት ነው " ብሏል::

አዛም ጂሃድ በእያንዳንዱ ሙስሊም ማህበረሰብ ኾነ ግለሰብ ላይ የተጣለ ግዴታ መሆኑንም አውጇል:: "የሙስሊም መሬት ሲያዝ ጂሃድ በመሬቱ ነዋሪዎች ላይ ሁሉ ግዴታ ይሆናል:: ሚስት ያለባሏ ፈቃድ ከዘመዷ ጋር፣ ልጅም ያለ አባቱ ፈቃድ መንቀሳቀስ አለባቸው:: ከተያዘው መሬት ውጪ ያሉ ሙስሊሞችም የተያዙትን ማገዝ ግዴታቸው ነው:: መላዋን መሬት እስኪያካልል ድረስ ይኸው መቀጠል አለበት::" ይላል::

አዛም በወቅቱ የተናገረው በአፍጋኒስታን ላይ ትኩረት አድርጐ ቢሆንም የጅሃድ ጽንሰ ሃሣቡ ግን ሰፍቷል:: የሙስሊም ነበሩ ተብለው

የሚታሰቡ መሬቶችን ሁሉ ሙስሊም ካልሆኑት የማስለቀቁ ግዴታ ወደእያንዳንዱ ግለሰብ ትከሻ የሚወርድ እንደሆነ ይናገር ነበር።

የአዛም ተፅዕኖ በቢን ላዲን አመለካከት ላይ የጐላ ለውጥ አምጥቷል። ከአፍጋን ጦርነት በፊት ቢን ላዲን ከታላቁ ጂሃድ ሌላ የሚያስብ አይመስልም ነበር። ለእርሱ መልካም ሙስሊምነት ፀሎት፣ ሩህሩህነትና የስጋን ፈተና ከመቋቋም ሌላ አልነበረም። ይሁንና ነገሮች ባሉበት አልቀጠሉም። አዛምን ካዳመጠ በኋላ የአፍጋኑን ትግል ለመቀላቀል ቢወስንም ለአጭር ጊዜም ቢሆን የቤተሰቦቹን ክልከላ ተቀብሎ ነበር። በመጨረሻም የቤተሰቡን ውትወታ ችላ ብሎ በ1984 ወደ አፍጋኒስታን ዘመተ። ለሶሪያዊ ጋዜጠኛ ሲናገር "የጓደኞቼንና የምወዳቸውን ምክር ሰምቼ ወደዚህ ሳልመጣ በመቆየቴ ፀፀት ይሰማኛል። እናም የዘገየሁባቸው አራቱ ዓመታት በእምላክ ስም መስዋትን እንደሚጠይቁኝ እረዳለሁ።" ብሎ ነበር። ይሁንና በክብር ስለመሞት የተናገረው ቢን ላዲን ሶቭየቶችን ወደ መዋጋት አልሄደም። በምትኩ ሃብቱን በመጠቀም ሙጅሃዲኖችን ወደ አፍጋኒስታን ለማስገባት መስራቱን ቀጠለ።

በ1985 መግቢያ ላይ እርሱ፣ አዛምና በዴጃማ ቦኖዋ *ማክታብ አል ኪድማት ሊል ሙጃሃዲን አል አረብ* የተሰኘውንና የውጭ ተዋጊዎች የአፍጋን አማፅያንን እንዲቀላቀሉ የሚያስተባብረውን የአፍጋን አገልግሎቶች ቢሮ ፔሻዋር ፓኪስታን ውስጥ ከፈቱ። "ቢሮውን የከፈትነው አረቦችን ለማሰባሰብና ወደ አፍጋኒስታን ለመላክ ነው።" ያለው አዛም "በዚህ ያለነው ለማገልገሉ ነው። በአፍጋኒስታን የሚገኙ ሙጂሃዲኖችን የእግር መረገጫ እንኳን ለማገልገል ብንችል እንከራለን።" ሲል አሳወቀ።

የአገልግሎቶች ቢሮው ሰነዶቶችን ለመዋጋት የሚሄዱ ፈቃደኛ አረቦችን የመቅጠር፣ የማጓጓዝ፣ የማኖርና የመክፈልን ስራ ያካሄድ ነበር። ባለው የግል ሃብት፣ ከቤተሰቡ ጋር በነበረው ግንኙነትና ከንጉሳዊያንና ከቱጃር ሳዑዲዎች ጋር በነበረው ትስስር የተነሳ በአፍጋን ጦርነት ቢን ላዲንን ማጣት በእጅጉ አክሳሪ ይሆናል። ለዚህም ነው አዛም ቀጣሪና አስተባባሪ እንዲሆን የወሰነው። ከሳዑዲ ወደ አፍጋን ከተላከው የገንዘብ ስጦታ መካከል ከአንድ አስረኛ የሚበልጠው በቢን ላዲን ድርጅት በኩል ያለፈ ነው። በተጨማሪም የአገልግሎቶች ክፍሉ ጂሃድ የተሰኘ የፕሮፖጋንዳ መጽሔት በማሳተም ፈቃደኛ ተዋጊዎችንና ገንዘብ ለጋሾችን ለማነሳሳት ይሰራ ነበር።

ምንም እንኳን ቢን ላዲን በአዛም ጥላ ቢሸፈንም ለትጋቱና ለጋስነቱ ተገቢውን ክብር ይሰጠው ነበር ማለት ይቻላል። በአገልግሎቱ ቢሮ አብሮት የሰራ አብዱላህ አናስ የተባለ አልጄሪያዊ ቢን ላዲንን የማይደክም ታላቅ ራዕይ ያለው መሪ ሲል ይገልፀዋል። "የሚመገበው በጣም ጥቂት ነው። የሚተኛውም ትንሽ። በጣም ለጋስ ነው። ገንዘቡንና ልብሶቹን ሁሉ ሊሰጥ የሚችል ዐይነት ሰው ነው።" ይለዋል።

ቢን ላዲን ፓኪስታን የደረሰው የዩናይትድ ስቴትስና የሳዑዲ እርዳታ የጦርነቱ ሚዛን ወደ አፍጋን አማፅያን እንዲያጋድል ባደረገበት ወቅት ነበር። ይህም አንድ አወዛጋቢ እምነት ፈጥሯል። አብዛኞቹ አሜሪካውያንም ሆነ ሌላው ዓለም ሲ.አይ.ኤም የቢን ላዲንን ተግባሮች ያግዝ እንዲያውም ለቢን ላደን ወርሃዊ ደሞዝ ይቆርጥለት እንደነበር ያምናሉ። ከሲ.አይ.ኤ. ገንዘብ እየተቀበለ ለአማፅያኑ የጦር መሪዎች የሚያከፋፍለው የፓኪስታኑ የስለላ ድርጅት ነበር። ሳዑዲ አረቢያ በበኩሏ

በየዓመቱ በስዊዝ ባንክ አካውንቱ በኩል ከ350-500 ሚሊዮን ዶላር በማስቀመጥ በሲ.አይ.ኤ. በኩል እንዲንቀሳቀስ ታደርግ ነበር።

## ቅዱስ ተዋጊዎቹ የአፍጋን አረቦች

ቢን ላዲን በማገዝ ስራው ውጤታማ እየሆነ ሲመጣ ጂሃዱ ላይ የነበረው ተሳትፎ እንዲጨምር ለማድረግ ዳር ዳር ማለት ጀመረ። ከሶቭየቶችና ከይስሙላው የአፍጋን መንግስታቸው ጋር በቀጥታ ለመዋጋት ፈለገ። ቢን ላዲን ይህ ነው የሚባል የውትድርና ስልጠና ያልወሰደ በመሆኑ ጦር ይዞ ቢዘምት የጦር ቀጠናን እንደሚጉብኙ ታዋቂ ሰዎች ሁሉ የእማዕያኑ አዛዦቾች ስጋት እንደሚሆንባቸው አያጠራጥርም።

ቢን ላዲን መዋጋት ከፈለገ የሚመራውን ጦር ማዘጋጀት ይኖርበታል። ሃብቱና የሙጃሂዲኖች ፈቃደኝነት ይህንን እንዲያደርግ ያስችሉታል። ይሁንና ጦሩም ሆነ ቢንላደን ከአረብኛ ውጭ የትልቁን የአፍጋን ጎሳ ቋንቋ ፓሽቱንንም ሆነ የፓኪስታንን ኡርዱ ቋንቋ መናገር የማይችሉ መሆናቸው ከተነሳሽነታቸውና አጋርነትን ከመገለፅ በተሻለ ለአፍጋናውያን የሚያግዙት በውስጥ መልኩ ነው። የሆነ ሆኖ ቢን ላዲን የራሱን ጦር አዘጋጀ። ቢን ላዲን ያሰባሰባቸው የአፍጋን አረብ ቅዱስ ተዋጊዎች ራሳቸውን ችለው አመርቂ ውጤት ማስመዝገብ እንደሚችሉ እርግጠኛ ነበር። ባይሆን እንኳን እርሱና ወታደሮቹ የሚመኙትን የሰማዕትነት ሞት አያጡትም።

ከአፍጋኖች የተለየ የአረብ ተዋጊዎችን ቡድን የማቋቋሙ የቢን ላደን ዕቅድ ከአዛም ጋር በመጀመሪያ ወደ አለመግባባት ቀየት ብሎም ወደግጭት እንዲያመሩ አደረጋቸው። ሞገደኛው ፍልስጤማዊ የውጭ

ተዋጊዎች ሚና በገንዘብና በጉልበት ማገዝ አለፍ ሲልም የአፍጋን ተዋጊዎችን መደገፍ መሆን እንዳለበት ያምናል። መዋጋት የፈለገ ሁሉ የአፍጋኖችን ቡድን መቀላቀል አለበት የሚል አቋም ያዘ። ይሁንና ቢን ላደን ያሰበውን ከመፈፀም ወደ ኋላ የሚል አልሆነም። አዛም ዕቅድን ከተቃወመባቸው ምክያቶች አንዱ ቢን ላደን ለራሱ ፕሮጀክት የሚያጠፋው ገንዘብ ለቢሮው እንዲውል በማሰብም ይመስላል።

እራሳቸውን ወደ አመፅ ሲያስገቡ ቢን ላዲንና ተከታዮቹ የነደፉት ኋላቀሩን የሽምቅ ውጊያ ስትራቴጂ ነበር። አንድን ቦታ አስለቅቆ በሂደት ተጨማሪ ቦታዎችን እያስለቀቁ መሄድ። ለመጀመር የመረጡት ቦታ ጃጂ ማይዳን ፓኪስታን ድንበር አጠገብ የሚገኝ ተራራማ ቦታ ሲሆን አቅርቦት ለማግኘት የተመቻቸና ጠንካራ የሶቭየት ጦር በአቅራቢያው የማይገኝበት ነው። በ1996 ቢን ላዲን ከቢን ላደን ግሩፕ የማንባታ መሳሪያዎችን አስመጥቶ በአካባቢው የሚገኙ ዋሻዎችን በመጠቀም ጠንካራ ምሽግ መገንባት ጀመረ። ምሽጉንም አል ማሳዳ (የአንበሶች ምሽግ) የሚል ስያሜ ሰጠው። ቢን ላደን እንደገለፀው ምሽጉ የተሰራበት ዓላማ ሶቭየቶች ወደአካባቢው ሲመጡ ቀድመው የሚያዩት ነገር እንዲሆንና ጥቃት እንዲከፍቱበት ነው። ይሁንና ምንም እንኳን የቢንላደን ምሽግ ትኩረት የሚስብ ቢሆንም ሶቭየቶች የበለጠ ትኩረት የሚሰጡት ግን ለተደራጁት ልምድ ያላቸው ተዋጊዎች ለሚያደርሷቸው ጥቃቶች ነበር።

የቢን ላደንን ወኔ ያህል በጦርነቱ ላይ ስኬታማ አልነበሩም። በሚያዝያ 17 ቀን 1987 ሶስት ከተማ አካባቢ 120 ወታደሮችን በመንግሥት ጦር ላይ ጥቃት እንዲከፍቱ ሲያደርግ ከአማፅያኑ አዛዥ ጉልቡዲን ሄክማትያር የከባድ መሳሪያ ሽፋን አግኝቶ የነበረ ቢሆንም

ዘመቻው ውጤታማ አልሆነም። ተዋጊ አረቦቹ ደካማ ዝግጅት በማድረጋቸው ለወታደሮቹ የሚሆን በቂ ምግብ አልተያዘም ነበር። በመጨረሻው ደቂቃ ደግሞ ሮኬቶችን ከማስወንጨፊያቸው የሚያገናኙ ኤሌክትሪካል ገመዶችን የያዘ አንድም ወታደር አለመኖሩን ተገነዘቡ። በመጨረሻ የወታደሮችን ጉታታ እንቅስቃሴ የተመለከተ የአፍጋን ወታደር በአንድ ማሽን ገን አስደነበራቸው። ዘመቻው ቢን ላደንና ተከታዮቹ በአፍጋን አማጽያን ዘንድ የነበራቸውን አመኔታ አሳጣቸው። ከወር በኋላ ቢን ላደን ሌላ የተሻለ ስኬት ያስመዘገበ ዘመቻ ቢያካሂድም በአፀፋው ሶቭየቶች የአንበሶች ምሽግን ለበርካታ ሳምንታት በመደብደባቸው የብዙ የአረብ ተዋጊዎች ሲገደሉ ቢን ላደንም ለጊዜውም ቢሆን ምሽጉን ለቆ እንዲሸሽ ተገዶ ነበር።

በአንድ የግብፅ መጽሔት ላይ ሰፍሮ የነበረ ጽሑፍ እንደሚያስረዳው የአማፅያኑ የጦር አዛዥ አህመድ ሻህ ማሱድ ቢን ላደንና ተከታዮቹን በቁጥጥር ስር አውሎ ጦራቸው የተደራጀ ስለሆነ በውጊያው መሳተፍ እንዳይችሉ ከልክሏቸው ነበር። ለዚህ ልምድ ላነበተ የጦር አዛዥ የቢን ላደን ወታደሮች ሶቭየቶችን ከሚያጠቃ ኃይል ይልቅ ራሳቸውን በመስዋዕትነት ለማቅረብ የቋመጡ ግለሰቦች ሆነውበታል። ለዚህም ይመስላል ከ9/11 ጥቃት ጥቂት ቀናት አስቀድሞ ቢን ላደን የማሱድን ግድያ ያፀደቀው።

ከቬትናም ጦርነት፣ አፍጋኖች ጋር ያደረጉት ጦርነት እንዲሁም ዩናይትድ ስቴትስ በሶማሊያ ስኬት ማጣት በቢን ላደን አስተሳሰብ ላይ ያመጡት ለውጥ በዩናይትድ ስቴትስ ላይ ላወጀው ጦርነት መነሻ የኾኑት ይመስላል። ከሶስቱ ጦርነቶች ውጤት ተነስቶ ልዕለ ኃያላኑ የቱንም የህል

የማይበገር ጉልበት ቢኖራቸው የተበታተኑ ጦርነቶችን መቋቋም እንደማይችሉ ያምድሟል። ሶቭየቶች በአፍጋኒስታን ያፈሰሱት ነጭ ደም ለሙጃሂዲኖች ትልቅ ትምህርት ሰጥቷቸዋል። "የአፍጋኒስታኑን ጦርነት ካሸነፍንና በሚሊየን የሚቆጠሩ ሙስሊሞችን የገደሉት አምባገነኖች ከተሸነፉ በኋላ ልዕለ ኃያላት አይሸነፋም የሚለው አፈ-ታሪክ መክኗል" ብሏል ቢን ላደን በ1998 በሰጠው መግለጫ። ቼቺንያም ዩናይትድ ስቴትስ በአመፅ ውጊያ መሸነፍ እንደምትችል ያሳየች ሲሆን ሶማሊያ ደግሞ ከሶቭየቶችም የቀለለች ተቀናቃኝ መሆኗን አሳብቃለች።

እስኪ አሁንም ቢን ላደንን እንስማ፣

> *«እነሱ [ሙጃሂዲኖቹን ነው] አሜሪካውያኑ ልክ እንደ ሩሲያውያኑ መስለዋቸው ትልቅና ከባድ ዝግጅት አደረጉ። ነገር ግን የአሜሪካ ወታደር እንኳን ሊፋለም የተሰነዘረበትን ጥቃት ለመመከት የሚሆን ሞራል እንኳን ያጣ ማፈሪያ መሆኑን ሲመለከቱ በሕልማቸው እንጂ እውን አልመሰላቸው አለ።»*

እንደተለመደው ሕዝብን ለማነሳሳትና ለማስደመም ሲል ከበድ ባሉ ቃላት እና በተንዛዛ ሁኔታ በሚያደርገው ንግግር ቢን ላደን የሙጃሂዲኖቹን ሚና በሶማልያም ሆነ በአፍጋኒስታን ከሚገባው በላይ በማግዘፍ፣ የአሜሪካ ወታደሮች ደግሞ ሞራል የሚባል እንኳን እንደሌላቸው አድርጎ ለማቅረብ ሞክሯል። በመሠረቱ ቀደም ሲል እንደጠቆምነው ሙጃሂዲኖቹ ዓረብ-አፍጋኖች በቁጥርም ሆነ በብቃት እጅግ አናሳ ከመሆናቸው የተነሳ በአፍጋኒስታን የተደረገውን ጦርነት ሂደት በምንም መልኩ ሊለውጡ የማይችሉ ነበሩ። በሶማልያ የነበራቸው ቁጥርም በጠቅላላም ሆነ በመቶኛ

ሲሰላ ከሌላው ተዋጊ አንፃር እጅግ የወረደ እና ግምት የማይሰጠው ሆኖ እናገኘዋለን:: እርግጥ የአሜሪካ ወታደሮች ጄኔራል ፋራ አይዲድን አድኖ ለመያዝ ከከፈቱት ጦርነት በሞቃዲሾ የነበራቸውን ሁሉ ትተው ወጥተዋል፡ ነገር ግን አሜሪካውያኑ ከዚያ ውጊያ የሸሹት ቢን ላደን እንደሚለው ለመዋጋት የሚሆን ሞራል አጥተው ሳይሆን ራሱ የፕ/ት ክሊንተን አስተዳደር ቁርጠኝነት በማጣቱ ነው:: የክሊንተን አስተዳደር ተሳስቷል እንድንል የሚያደርገን ሌላም ነገር ደግሞ አለን:: ያም የአሜሪካ ሕዝብ በወቅቱ ይኼ ነው የሚባል አንድም የአሜሪካ ጥቅም በሌለበት አገር ውስጥ እንዲያ በተንቦራቀቀ ሁኔታ ጦርነት ውስጥ ሠራዊቱ መዘፈቁን ቢቃወምም እንኳን በሶማሊያውያኑ ላይ የክሊንተን አስተዳደር ጠንከር ፈርጠም ያለ እርምጃ ቢወስድ ኖሮ ግን በትዕግስት ይመለከተው ነበረ:: ቢን ላደን አሜሪካን ውስጧ ገብቶ በገዛ መሬቷ ላይ ሲያጠቃት ግን የቀጣዩ አስተዳደር ምላሽ ከእሳት የፈጠነ፣ የማይደራደርና አረመኔያዊ መሆኑን ያያል::

## የአፍጋን የእርስ በርስ ጦርነት

በአፍጋኒስታን ከጦርነቱ በኋላ የሩሲያው ጦር ጠቅልሎ መውጣቱ ለአገሪቱ መረጋጋትና ሰላምን አላመጣም:: የሞስኮው መንግሥት ከአፍጋኒስታን ሲለቅ ትቶት የወጣው የኢሻንጉሊት መንግሥት ሲሆን የዚህ መንግሥት የጦር አማካሪዎች ደግሞ ዓማፂያኑን የሚዋጉት እጅግ ረጋ ባለ ስልት ብቻ ነበረ:: አማፂያኑ ምንም እንኳን ጠላት የሩሲያን ጦር ለመፋለም በሚገርም ብቃት ቢተባበሩም ሩሲያ ከወጣች በኋላ ግን እርስ በርሳቸው ልክ በሩሲያ ላይ እንደሚያካሂዱት ዐይነት መራራ ትግል ነበረ የሚያካሂዱት:: በአንድ በኩል በመዲናዋ ካቡል ውስጥ የተቀመጠውን አሻንጉሊታዊ የማርክሲስት መንግሥት ለመጣል በሌላ በኩል ደግሞ እርስ በርስ ይፋለማሉ:: እናም

በ1991 ተሳክቶላቸው ያንን የማርክሲስት መንግሥት በመገርሰስ ካቡል በድል አድራጊነት ገቡ። ነገር ግን ወዲያውኑ ካቡልን የነሱ የጦርነት አውድማ አደረጓት። ይህ የእርስ በርስ ጦርነትም ከፓሽቱን ጎሣ ከመጣው የታሊባን ቡድን በ1995 ስልጣን እስከሚፈናጠጥበት ጊዜ ድረስ ቀጠለ። ግን ይህም ሆኖ ታሊባኖች በስልጣን ላይ እያሉ በግላቸው እና ገለልተኛ ሆነው ሲንቀሳቀሱ የቆዩት የሰሜን ታጂቅ ኃይሎች ቅንጅት እና ሌሎች አሜሪካ በ2001 አፍጋኒስታንን ስትወር ታሊባንን ለመጣል ተባብረዋል።

ኦሳማ ቢን ላደን የአፍጋኒስታን መዲና የሆነችዋን ካቡልን ለመቆጣጠርም ሆነ ማርክሲስታዊውን መንግሥት ለመጣል በተደረገው ፍልሚያ ውስጥ የረባ ሚና አልነበረውም። በ1989 እሱ እና ዓረብ አፍጋን ተዋጊዎቹ ጥፋትን ባስከተለው የጃላላባድ ውጊያ ላይ ተሳተፉ። የመንግሥት ኃይሎች ጥቃቱን የመከቱ ሲሆን በሙጃሂዲኖቹ ላይ እጅግ የከፋ ጉዳት አድርሰዋል። ቢን ላደን እና የቀሩት ተዋጊዎቹም ለበርካታ ቀናት ምሽጋቸው በአየር ድብደባ እየተቀጠቀጠ ታግሰው ከዚያ እግሬ አውጪኝ ብለው ለጊዜው ሸሽተዋል። ቢን ላደን ብዙም ሳይቆይ ወዲያው ወደ ሳውዲ ሄደ። ከዚያ ደግሞ ቶሎ ተመልሶ መጥቶ ብዙም ሳይቆይ ወጥቶ በ1995 ነው ተረጋግቶ በደምብ ለመቆየት የሚመጣው። ነገር ግን እሱ ተመልሶ ሲመጣ አገሪቱ ሙላ መሐመድ ኦማር በተባሉት እና በዓለም አለ የተባለውን አሸባሪ ድርጅት በሚመሩት እጅግ አክራሪ እና አምባገነን መሪ ቁጥጥር ሥር ወድቃ ነው የሚያገኛት።

## የታሊባኖቹ ድል

በፓሽቱኖቹ ቋንቋ ታሊባን ማለት «የሃይማኖት ተማሪ» የሚል ትርጓሜ ያለው ነው። በ1995 በአፍጋኒስታን ስልጣን የተፈናጠጠው ቡድን በ5 1970ዎቹ አጋማሽ እና 1980ዎቹ ውስጥ ትምህርት (*madrasa*) የሚባለውን

ሥርዓት እከናውኖ የሚያውቅ ነው:: ነገር ግን በዚህ ቡድን ትምህርት ውስጥ ያለፉ በርካታ ምስክርነታቸውን የሰጡ ተማሪዎች ደግሞ ቁርዓንን ከማጥናት እና ከረር ያለ እስልምናን ከመማር ያለፈ ምንም እንዳልነበረው ይናገራሉ:: አብዛኞቹ በዚህ ማድረስ ውስጥ ያስተማሩ ኢማሞች Neo-Deobandi የተባለው ንቅናቄ አባላት ነበሩ:: Deobandism የተባለው ንቅናቄ ልክ እንደ ዋሐቢዎቹ ከረር ያለ እስልምናን ያራምዳል:: የዚህ ንቅናቄ አቀንቃኞች እስልምና ባሁን ዘመን ከምዕራቡ ወደኋላ እየቀረ የመጣው ሙስሊሙ የነቢዩ መሐመድን ዋና ዋና መልዕክቶችና አስተምህሮቶች በደምብ ስለማያውቃቸው ነው:: እናም ሕዝቡ ወደፊት መራመድ ካለበት ዋንኛው መደረግ የሚገባው የእስልምናን የቀደመ የድል ታሪክ መድገም ነው:: ይህ ንቅናቄ ስሙን በሕንድ ከምትገኘው ዲዮባንድ ያገኘ ሲሆን ሕንድ ውስጥ ደግሞ ላለፉት 200 ዓመታት ያህል የደቡብ ኤሺያ ኢማሞች ሰልጥነዋል:: የኃይል እርምጃ ተፈጥሮአዊ ባሕሪው ባይሆንም Deobandism የተባለው ንቅናቄ በአፍጋን እና ፓኪስታን አዋሳኝ ድንበር መሀከል ባለው ቦታ ሲደርስ አክራሪነትን እየተላበሰ መጣ:: እናም በአስተምህሮቱ፤

> *«እውነተኛው የእስልምና ማኅበረሰብ በፀሎትና ጽድቅን በማድረግ የማይመጣ ከሆነ በኃይልም ቢሆን እናመጣዋለን::»*

የሚል መፈክር ተደጋግሞ ተደመጠ:: ይህ የ Deobandism ማድረስ ይበልጥ ጉልበት እያገኘ የመጣውና የተጠናከረው ከሳውዲ በሚያገኘው የጥሬ ገንዘብ ድጋፍ ነበረ:: በ 1980 በኢራን አብዮት መከሄዱን ተከትሎ አክራሪው የሺዓ እምነት እንዳይስፋፋ ተጨንቃ የነበረችው ሳውዲ ማድረሳዎችን በሙስሊሙ ዓለም በመብራትም ቢሆን እየፈለገች በገንዘብ ማጠናከርን ተያያዘች:: በዚህ ሳውዲ በገፍ በምትረጨው ገንዘብ እና ከረር ባለው

አስተምህሮቱ፡ ይህ ንቅናቄ የአፍጋን እና የፓኪስታን አዋሳኝ ቦታዎች አለመረጋጋት ተጨምሮበት እጅግ እየተካረረ መጣ።

ለአሥር ዓመታት ያህል በጦርነት በረገፈው በዚህ ቦታ ላይ ንቅናቄው ከተለያዩ ምንጮች ባሰባሰበው ገንዘብ ለተማሪዎቹ የማያልቅ የሚመስል አቅርቦቶች ነበሩት። በጦርነቱ በርካታ ቤተሰቦች የተጎዱ በመሆኑ በተለይም የሙት ልጆች እና ማደጎ ውስጥ የሚገኙትም በሰውነት እና በዕድሜ ጎልምሰው ፈጽሞ የማይቻሉ፡ ጥላቻን ያነገቡ፡ ለማንም የማይመለሱ አዲስ ትውልድ ሆኑ። እነዚህ ልጆች በተለያዩ ሁናቴዎች ተገፋፍተው ወይ ወደ ጎዳና ወይ ወደ ወንጀል አልያም ወደ አክራሪ የሐይማኖት ኃይሎች ገብተው ይሆናል። ለጂሀዲስቶቹ ግን የሚመቹ ሆኑ። የእነዚህ ሰዎች መሪ የነበሩት ሙላ መሐመድ አማር ደግሞ አንዱ የማድራሰ መምህር የነበሩት ኢማም ናቸው። ልክ እንደ ኦሳማ ቢን ላደን ሙላ አማር ለልዩ ተልዕኮ አምላክ እሳቸውን እንደመረጠ ነበረ የሚያምኑት። ከዚህ ዓላማቸውና ተልዕኮ ደግሞ አንዳችም የሚያሰናክላቸው እንደሌለ ይናገራሉ። ከዚህ በተጨማሪም አሜሪካን አስመልክቶ ያላቸው አስተያየት ከቢን ላደን ጋር ተመሳሳይ ነበረ።

> *«አሜሪካ እኮ የሙስሊሙን አገራት መንግሥታት የምታሽከረክር ኃይል ናት። ሕዝቡ እስልምናን እንከተል ይላል መንግሥታቱ ግን በአሜሪካ ሳምባ የሚተነፍሱ በመሆናቸው ጥያቄውን ጆሮ ዳባ ልበስ በማለት ይታወቃሉ። አንድ ሰው እንኳን ፂድቁን የእስልምና መንገድ ቢከተል መንግሥት ያስረዋል፤ ከዚያ አሰቃይቶ ይገድለዋል። ይኼ ሁሉ ደግሞ የአሜሪካ ሥራ መሆኑን እናውቃለን። አሜሪካ እነዚህን መንግሥታት መርዳቷን*

*ብታቆም ኖሮ ይኼንን ሁሉ መከራ ሕዝባችን ባላየ ነበረ፡፡»*

በማለት ነበረ ከመስከረም አስራ አንዱ ጥቃት በኋላ ለአሜሪካ ድምጽ ራዲዮ ጣቢያ (VOA) ዘጋቢ የተናገሩት፡፡ ታሊባኖች የያዙት የሐይማኖት አክራሪነት በሳውዲ ዋህቢዎች ከተያዘው ብዙ እጥፍ የሚልቅ ነው፡፡ ይህ አክራሪነትም ሺዓን ለመፋለም ይቻል ዘንድ በአፍጋኒስታን የሽብር ጥቃቶችን በስፋት መፈፀምን በግልጽ የሚሰብክ ነው፡፡ ታሊባኖች ሴቶች ወደ ትምህርት ቤት እንዳይሄዱ ከለከሉ፡፡ እጅግ ጥርት ያለ (puritanical) ሕግን ከመከተላቸው አንፃር ሴቶች *ሂጃብ* ተከናንበው ይሄዱ ብለውም አልረኩም፡፡ ከዚያም አልፈው ሴቶች እጅግ አስፈላጊ ወይ ድንገተኛ ለሆነ ጉዳይ ካልሆነ በቀር ከቤት እንዳይወጡ አሉ፡፡ ሴቶች *burqa* የተባለውን ልብስ ከራስ ፀጉራቸው እስከ እግር ጥፍራቸው ሸፍነው የሚሄዱ ሲሆን ይህ ልብስም እንደ ነጠላ በሚመስል ነገር ብቻ እይታን ይፈቅድላቸዋል፡፡ እንዲያውም ከተቻለ ለአስቸኳይ ወይ አጣዳፊ ጉዳይ የምትወጣ ማንኛዋም ሴት በማንኛውም ጊዜ ወንድ ቢያጅባት ይመረጣል፡፡ ለወንዶች ፂምን ማጎፈር ግድ ይላል፡፡ ከዚያ በተጨማሪም ታሊባኖች ፊልም፣ ሙዚቃ እና አብዛኞቹን የ ቴሌቪዥን ፕሮግራሞች አገዱ፡፡ አመንዝራነት ፈጽሞ የማይታሰብ ይሆን ዘንድም ባላቸው ቁርጠኝነት አመንዝራነትን ፈጽሞ የተገኘ ሁሉ በሕዝብ ፊትና ባደባባይ በድንጋይ ተወግሮ እንዲገደል አዘዙ፡፡ ፂምን እና ፀጉርን የሚያስተካክል ሁሉ አንገቱ በሰይፍ እንዲቀላም ጭምር ተናገሩ፡፡

## የቢን ላደን መንፈስ ውልደት

በአፍጋኒስታን ሶቭየት ኅብረቶችን ለማስወጣት የተደረገው ትግል እና ከእነሱ መውጣት ተከታትሎ ደግሞ የተካሄደው የእርስ በርስ ጦርነት ቢን

ላደን የተባለውን ምናባዊነት ፈጠረ:: የአፍጋን ዓረብ መሪዎች በውጊያው ያላቸው ሚና እዚህ ግባ ባይባልም አግዝፈው ሕዝብ ፊት ተናገሩት:: በዚህ የእርስ በርስ ጦርነት ወቅት እነሱን ሊቃወም የሚችልም ሆነ ሃይ የሚላቸው ባለመኖሩም ታሪክን አጣመውና አዛብተው በድጋሚ ፃፉ:: በጃላላባዱ ውጊያ እንኳን የደረሰባቸውን አገር የማይረሳው ውርደት ከሽነው «ጠላትን ያርበደበደ ስኬት» ሲሉ ዘገቡት:: አቡ ሳላማን የተባለው መሪያቸው በዚህ ቅጥፈት የተዋጣለት ነበረ::

> *«የአፍጋን የጦር መሪዎች በእነሱ ላይ ነበረ የተመኩት:: የዓረብ-አፍጋን ተዋጊዎች ትውልድ! ታሪክም ሆነ ሕዝብ ፈጽሞ የማይዘነጉት ብቃትም በጃላላባዱ ወሳኝ ፍልሚያ ስኬት ተረጋግጧል:: ከዚያም በተጨማሪ አፍጋኖች በተለይዩ የነፃ ማውጣት ዘመቻዎች ተሳትፈዋል::»*

ሌላው ቢቀር የአረብ አፍጋን ተፋላሚዎች ቁጥር እጅግ አናሳ ከመሆኑ አንፃር ይህ ሰው የተናገረው ነገር ሁሉ ንጭ ውሸት መሆኑ ግልጽ ነው:: በወቅቱ የነበረ የጋዜጠኛ ዘገባ ግን በአቡ ሳላማን ተከሽኖ የቀረበው ነገር የፈጠራ ታሪክ መሆኑን ያረጋግጥልናል:: ከዚህ አንፃር በ የካቲት ወር 1989 የቢን ላደንን እና የተከታዮቹን ካምፕ የመጎብኘት ዕድል የገጠመው ጋዜጠኛ ኤድዋርድ ጊራርዴት ቢን ላደን ከአፍጋኖቹ ጋር አታካሮ መግጠሙን ነው የሚያስታውሰው:: ቢን ላደን አፍጋኖቹን ሲያገኛቸው ማንነታቸውን እና ከየት እንደመጡ ለማወቅ አጥብቆ ይሻል::

> *«ስማ! ይኼ የእኛ የራሳችን እንጂ የናንተ ጂሀድ አይደለም:: እኛ እኮ ይኼንን ተራራና ገደል ጥርት አድርገን ለዓመታት እናውቀዋለን:: አንተን እና ጥቂት ተከታዮችህን ግን አይተናችሁ አናውቅም::»*

ብለዋል፡፡ ጋዜጠኛው እንደሚያስታውሰው በዚያች ቀን በዓረቢኛ ከተካሄደው የጋለ ክርክርና እሰጥ አገባ የተረዳው ሁለቱ ተፋላሚዎች እንጥፍጣፊ አንድነት እንኳን እንደሌላቸው ነው፡፡

««ቢን ላደን እንኳን ጂሀድን ሊያካሂድ የመንደር ተጨቃጫቂ ነው የሚመስለው»

ቢን ላደን ለክብሩ እና ሰው ፊት ላለው ስም በጣም እንደሚጨነቅም ጭምር ነው ጋዜጠኛ ጊራርዴት ያስታወሰው፡፡ ሶቪየቶች ከአፍጋኒስታን ነቅለው ከወጡ በኋላ የማርክስ መንግስቱም በካቡል ሲገረሰስ አፍጋን አረቦች የሆኑት ሙጃሂዲኖችን ሌሎቹ አፍጋኖች በትህትና ነገር ግን ፈርጠ ም ብለው፤

«በሉ፤ አገራችንን ለቃችሁ ውጡልን»

አሏቸው፡፡ እንደ አህመድ ሻህ አህማድዛይ (ከ1995-69 የአፍጋኒስታን ተጠ ባባቂ ጠ/ሚ/ር) ከሆነ አፍጋኖቹ ሙጃሂዲኖቹን ላደረጉት ሁሉ አመስግነው ከዚያ በኋላ ግን እዚያ ካለው ሰራዊት ጋር በምንም ሁኔታ ተቀላቅለው የእርስ በርስ ጦርነት ውስጥ እንዲገቡ እንደማይፈልጉ ነገሯቸው፡፡ እሳቸው እንደሚሉት ከሆነ አፍጋን-ዓረቦቹ ከዚያ በላይ እንዲቆዩ ያልተፈለገው በወቅቱ እጅግ አክራሪ የሚባለውን የጉልቡዲን ሔክማይታርን ቡድን በመደገፋቸው ነው፡፡

እንግዲህ ቢን ላደን ዕድለኛ በመሆኑ እነዚህ ጉዶቹ እና በጓዳ ጎድጓዳው የሚታወቁ ምስጢሮቹ ብዙም ወደ ሚዲያ ባለመውጣታቸው ዝናው ሳይበላሽ ቀረ፡፡ በምእራቡ ባብዛኛው ሳይታወቅ ቢቀርም ከአፍጋኑ ጦርነት በኋላ ግን በሳውዲ እና በአንዳንድ የዓረቡ ዓለም ስፍራዎች ስሙ እየገነነ መጣ፡፡ ወደ አገሩ ሳውዲ ሲመለስም ሕዝብ እንደ ጀግና ቆጥሮት

በአፍጋን ስላደረገው ጀብዱ ለመስማት አጣደፈው። ነገር ግን ከሁሉም በላይ በምናባዊነት የገነነው ስሙ በእርግጥም እሷህ ለየት ላለ ክንውን እና ተልዕኮ እንደመረጠው ተደርጎ በብዙዎች ዘንድ እንዲወሰድ ምክንያት ሆነ። በዚህ የተደፋፈረው ቢን ላደንም «አወቅሽ አወቅሽ ሲሏት» እንዲሉ የቀዝቃዛውን ጦርነት ያሸነፈው የሰሜን አትላንቲክ አገሮች ቃል ኪዳናዊ ድርጅት (NATO) ሳይሆን እሱ እና ሙጃሂዲኖቹ እንደሆኑ አድርጎ ተናገረ። በ1996 መጨረሻ ግድም ከ CNN ዘጋቢው ፒተር አርኔት ጋር ባካሄደው ቃለ-ምልልስ፤

> *«ሶቪየት ኅብረት ልትፈራርስና ልትወድቅ የቻለችበት እልህ አስጨራሽ ትግል ውስጥ አሜሪካ አንድም ሊጠቀስ የሚችል የረባ ሚና አልነበራትም። ይልቅ የእሷህ የቁርጥ ቀን ልጆች፣ ሕዝባችን እንዲሁም ፈጥኖ ደራሽ የሆኑት ሙጃሂዲኖች ታሪክና ትውልድ የማይዘነጋው ተጋድሎ ማድረጋቸው ፈጽሞ አሌ የማይባል ሃቅ ነው።»*

በዓረቡ ዓለም ባብዛኛው ይኼ የ «ቀጭ በሉ» አነጋገር እንደ እውነት የተቆጠረ ሲሆን ብዙዎችም ቢን ላደንን የዓለም ጀግና አደረጉት። ቢን ላደን በምዕራቡ ዓለም ሲጠላና በክፉ ሲነሳ በዓረብ ግን ባብዛኛው ተመለከ። ይገርማል! በ2003 ላይ 65% በሚሆኑት ፓኪስታናውያን፣ 55% በሚሆኑት ዮርዳኖሳውያን እና 45% በሚሆኑት የሞሮኮ ዜጎች ዘንድ ቢን ላደን ከፍተኛ ድጋፍ፣ የዝነኛ ስም እንዲሁም የእኩሪ ተጋድሎ መሪነት ዝና ነበረው።

# ምዕራፍ አራት

# አል ቃኢዳ

በ1980 ዎቹ ወደ አፍጋኒስታን ተጉዘው የነበሩት የውጭ አገር ተዋጊዎች ብቸኛ ተልዕኮ የሶቭየቶችን ወረራ መቀልበስና የካቡሉን ኮምዩኒስታዊ አገዛዝ ማስወገድ ነበር። ጦርነቱ ሲያበቃ ወደ የአገራቸው ተመልሰዋል። የአፍጋን አማፅያን በበኩላቸው አገራቸውን ነፃ ለማውጣት የተዋጉትን ያህል በስተመጨረሻ ለስልጣን ከመፋተግ በዘለለ ጦርነት ለደቀሳት አገራቸው ሊያስቡላት አልቻሉም። ለኦሳማ ቢን ላደን ደግሞ የአፍጋኑ ጦርነት እንደመነሻ ነው የኾነው። ውጊያው አቅም ፈጥሮለት ስለሌሎች ሙስሊም አገራት ነፃነት ጉዳይ እንዲያስብ መንገድ ከፈተለት። ከመሰሎቹ ጋር በመተባበርም የአፍጋን አረብ ተዋጊ ወታደሮቹን ከሽምቅ ተዋጊነት ወደ ድርጅትነት (ንቅናቄ) ለወጣቸው።

## አዛምና ቢን ላደን

ወደ ጦርነቱ መገባደጃ አካባቢ አዛምና ቢን ላደን መላውን የሙስሊም ዓለም በፍጥነት ነፃ የማውጣት ፍላጎት አደረባቸው። በተለይ ቢን ላደን የእስልምና ጠላቶች ናቸው የሚላቸውን ሁሉ በተገኙበት ጂሃድ ሊያውጅባቸው ቆረጠ። ከሌሎች ተመሳሳይ አመለካከት ከነበራቸው ሰዎች ጋር ኾነው ቢን ላደንና አዛም በ1988 አልቃኢዳን መሰረቱ። ምንም እንኳን በሰፊው የአልቃኢዳ ግብ ቢስማሙም መስራቾቹ በአንድ ወሳኝ ነጥብ ላይ ግን ልዩነት ነበራቸው። አዛም በጂሃድ የመሳተፍ የሁሉም ሙስሊሞች ግዴታ የሚሰራው በተወረሩ የሙስሊም መሬቶች ነው ሲል የተወሰኑት

የአፍጋን አረቦች በተለይ ከግብፅ የመጡት ደግሞ የይስሙላ ናቸው የሚሏቸውን ሙስሊም መንግስታት ጭምር መገልበጥን ይፈልጋሉ:: እነሱም ግን ሌሎች ሙስሊሞችን መዋጋት አይገባም የሚል አቋም ያዙ:: እነሱም ጂሃድ መካሄድ ያለበት ሙስሊሞች በመሬታቸው ሙስሊም ባልሆኑት ሲጨቆኑ መሆን አለበት ይላል::

"ጂሃድና ጠመንጃ ብቻ... ድርድር፣ ኮንፍረንስ፣ ውይይት ... ብሎ ነገር አያስፈልግም:: ተልዕኳችን በአፍጋኑ ድላችን ብቻ አይወሰንም:: የሙስሊም ግዛት የነበሩ መሬቶች ሁሉ ተመልሰው እስልምና እስከሚያንሰራራ ድረስ ጂሃድ የእያንዳንዱ ሙስሊም ግለሰብ ግዴታ ኾኖ ይቀጥላል:: ከፊታችን ፍልስጤም፣ ቦክሃራ፣ቻድ፣ ኤርትራ፣ሶማሊያ፣ፊሊፒንስ፣በርማ፣ደቡብ የመን፣ ታሽሸንት፣ እና አንዳሉሺያ (ደቡብ ስፔን) ይጠብቁናል::"

ጦርነት ሲካሄድባቸው ይገባል ብሎ ከዘረዘራቸው በርካታ አገራት ውስጥ ግብፅ፣ ሳዑዲ አረቢያና ዩናይትድ ስቴትስ የሉበትም:: በሂደት ግን እነዚሁ አገራትም ከአልቃኢዳ ኢላማነት አላመለጡም:: የተያዙ የሙስሊም መሬቶችን በማስለቀቁ ቢስማማም ቢን ላደን ሙስሊም መንግስታትን የመገልበጡ ሕጋዊነት እና ፍትሐዊነት ጉዳይ ግን ያሳሰቡት አይመስልም:

የኾነ ሆኖ የሳዑዲ ታማኝነቱን ጠብቋል:: ይህንንም ያደረገው ንጉሳውያኑና በርካታ የሳዑዲ ቱጃሮች የአፍጋኑን ጂሃድ በገንዘብ ስለመደገፋቸው ዋጋ በመስጠት ነው:: በቀጣዩቹ ዓመታት ግን የይስሙላ ሙስሊም መንግስታት በሙሉ መገልበጥ አለባቸው የሚለውን ሃሣብ የተቀበለው ይመስላል::

አዛምና ቢን ላደን በደፋ ተለያይተው ባያውቁም በመካከላቸው የነበረው ግንኙነት ግን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀዘቀዘ ሄዷል። ልዩነታቸው ከውስበስብ ጉዳዮች የመነጨ ነው። ዋናው ግን ቢን ላደን የራሱን የአፍጋን ተዋጊ ቡድን በማቋቋም ውሳኔው ገፍቶ ወደ ተግባራዊነት መሰጠጡ ነው። አዛም ፕሮጀክቱን ንብረት እንደማባከን ቢወስደውም ገንዘቡን የሚያወጣው ቢን ላደን በመሆኑ ምንም ማድረግ አልቻለም። በዚህ ምክንያት የተነሳ በውስጣቸው ውጥረት እንዲነግስ አድርጓል። ከአፍጋን አረብ ተዋጊዎቹ መካከል አብዛኛውን ቁጥር በተለይ ደግሞ የአመራሩን ቦታ የያዙት ዕንፊኛ ግብጻውያን ነበሩ። ብዙዎቹ የግብፅ ሙጀሃዲኖች የሙስሊም ወንድማማቾች ከተጠላው የግብፅ መንግስት ጋር አብሮ ለመስራት ፈቃደኛ ሆኗል በሚል ከድርጅቱ ራሳቸውን የነጠሉ ናቸው። አዛም እነዚህን ሰዎች አያምናቸውም። ቢን ላደን ለራሱ ዓላማ የሚያጠፋው ገንዘብም ያሳስበዋል። በነዚህ ምክንያቶች አልቃኢዳ ውስጥ የሚኖራቸውን ሚና ለመገደብ ፈለገ። አዛም አባልነት በምርጫ መሆን አለበት ሲል ቢን ላደን ግን በሃሣቡ አልተስማማም።

የአዛም ስጋት መነሻ ነበረው። ቢን ላደን ከሙስሊም ወንድማማቾቹ ለተገነጠለው ግብፃዊያኑ ቡድን አልጂሃድ የካምፕ መስሪያ አንድ መቶ ሺ ዶላር ሰጠ። ደራሲ ሪቻርድ ራይት ይህ የቢን ላደን ችሮታ ወደ ግብጻውያኑ ማዘንበሉን ያሳያል ቢልም ቢን ላደን ግን የራሱን ወጥመድ እየዘረጋ ነበር የሚለው የበለጠ ያስማማል። የአልጂሃድ ካምፕ ቢን ላደን ከሰራቸው በርካታ ካምፖች መካከል አንደኛው ነው። ከአዛም ጋር አንድ የአረብ ካምፕም አቋቁመው ነበር።

ቢን ላደን ከቀድሞ መምህሩ ጋር የነበረው ግንኙነት ለመቀዝቀዙ ግለሰባዊ ጉዳይም ያለበት ይመስላል። አዛም በዓለም አቀፍ ደረጃ ዝናው የገነነ የሙስሊም ምሁር ሲሆን ቢን ላደን ግን ከሁለተኛ ደረጃ ዲፕሎማ የዘለለ የለውም። በኮሌጅም ያጠናው ኢኮኖሚክስ እንጅ ሐይማኖት አልነበረም። ስለዚህም የአዛም መኖር በቢን ላደን ላይ የዝቅተኛነት መንፈስ ያሳደረበት ይመስላል። አዛም በበኩሉ ቢን ላደንን እንደተከታይ እንጅ እንደ አቻ ለማየት አለመውደዱን ጠቋሚ ነገሮች አሉ። የአዛም የድሮ ባለቤት ይህንን ነጥብ እንደውጥረት መነሻ ታነሳዋለች። ቢን ላደንንም "ጥሩ ትምህርት የሌለው፣ በሁለተኛ ደረጃ ዲፕሎማ የተወሰነ፣ ለኡለማዎችና ሼኮች ትምህርት መስጠቱ እርግጥ ቢሆንም በክርክር ለማሳመን የሚቀል ሰው ነው።" ትለዋለች።

## የአል ቃኢዳ ውልደት

አልቃኢዳ በአረብኛ መሰረት ማለት ሲሆን በ1984 ቢን ላደንና አዛም ከመሰረቱት ማክታብ አል ኪድማት ሊል ሙጃዲን አል አረብ (የአፍጋን አገልግሎቶች) ቢሮ ያደገ ድርጅት ነው። ስለአልቃኢዳ አመሰራረት የሚገልፁ በርካታ መረጃዎች ቢኖሩም በዝርዝር ጉዳዮች ላይ ልዩነት ይታይባቸዋል። ቢን ላደን ራሱ በሰጠው አንድ መረጃ ላይ "አቡ ኡባይዳህ አል ባንጅሽሪ በ1980ዎቹ የሩስያ ሽብርተኝነት ዘመን የስልጠና ማዕከሎችን አቋቋመ። የስልጠና ማዕከሉን አልቃኢዳ እያልን እንጠራው ነበር።ስሙ ከዚያ የመጣ ነው።" ብሏል። በ1988 ሚያዝያ ወር በታተመ *ጂሃድ መጽሔት* ላይ ደግሞ አዛም የተሟላ ገለፃ እንደሚከተለው አስፍሯል።

- *እያንዳንዱ ንድፈ ሃሣብ ወደፊት የሚያስቀጥለው ግንባር ቀደም ያስፈልገዋል። ወደማህበረሰቡ በሚሰርፅበት ጊዜም ዘብድ ስራና የበዛ መስዋዕትነትን ይጠይቃል። ያለውን ሁሉ ለመስዋዕትነት የሚያቀርብ ሰው በሌለበት ማሸነፍ የሚችል ምድራዊም ኾነ ሰማያዊ ንድፈ ሃሣብ የለም። እስከመድረሻው ድረስ ሰንደቁን ተሸክሞ የሚቀጥል አስቸጋሪውን መንገድ የሚወጣ ያስፈልጋል። ቀንዲሉ እንዲመጣ የሚፈልገው ማህበረሰብ ጠንካራ መሰረት (አል-ቃኢዳ ሱልባህ) ይሆናል።*

በምርኮ የተገኙ መረጃዎች እንደሚያሳዩት የአልቃኢዳን ንድፈ ሃሳብ የማስፋፋቱ ሃሣብ ከአይማን አልዛዋሂሪ እስላማዊ ጂሃድ ድርጅት የመጣ ይመስላል። አቡ አል ሪዳ በነሐሴ 1998 ከቢን ላዲን ጋር ሲገናኝ "ይህ ቀጣይ ፕሮጀክት የግብፃውያን ወንድሞቻችን ጥቅም የሚያስጠብቅ ነው።" ብሎት ነበር። ዛዋሂሪ በአልቃኢዳ ውስጥ ወሳኝ ሚና መጫወቱን እስከዛሬም ድረስ በመቀጠሉ የድርጅቱ ማዕከልና መንፈሳዊ መሪ ቢን ላደን መሆኑ እንደተጠበቀ ኾኖ በርካቶች እንደ ድርጅቱ አእምሮ የሚወስዱት እርሱ ነው። አንድ ሳዑዲ አረቢያዊ ተቀጣሪ የሰጠው ማስረጃም የአልቃኢዳ ምስረታ ሃሣብ የመነጨው ከፅንፈኛ ግብፃውያን መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው። "የሩስያውያንን ከአፍጋኒስታን መውጣትና የጂሃዱን ማብቃት ተከትሎ የአልቃኢዳ ምስረታ ጉዳይ ውይይት የተካሄደው ፔሻዋር ውስጥ በኡሳማ ቢን ላደን ቤት ነው።" የሚለው ሃሰን አብድ ራቡህ "አል ቃኢዱ ሲወለድ በቦታው ከነበሩ ምስክሮች አንዱ ነኝ። የአልቃኢዳ ሃሣብ በአቡ

ኡቤይዳህ አል ባንጅሪ እና አቡ ሃፍዝ የሚመሩ ግብግውያን ቡድኖች ሃሣብ ነው።" ብሏል።

አል ባንጅሺሪ ለወጣቱ ሳዑዲያዊ ምልምል የአዲሱን ድርጅት ዓላማና በምስረታው ወቅት ቢን ላደን ስለነበረው ሚና "መቼም የወንድም ኦሳማ ቢን ላደንን ልግስና የምታውቀው ነው" ካለ በኋላ እንደሚከተለው አብራርቶለት ነበር።

*"ለወጣቶቹ ሙጅሃዲኖች የጦር መሳሪያ ለመግዛትና ለማሰልጠን እንዲሁም የጉዞ ወጫቸውን ለመሸፈን በርካታ ገንዘብ አፍስሷል። ይህንን ዕድል ማበላሸት የለብንም። እነዚህን ወጣቶች በእሱ ጥላ ስር ማሰልጠንና ማነሳሳት ይኖርብናል። ለጂሃድ የሚሆን አል ቃኢዳ የሚባል እስላማዊ ጦር መፍጠር አለብን። ይህ ጦር ቢን ላደን በአፍጋኑ ጂሃድ ላይ ላወጣው የድካሙ ፍሬ ይሆናል። እነዚህ ወጣቶችን አሰልጥነን በየትኛውም የዓለም ክፍል እስልምናና ሙስሊሞችን የሚጠብቁ ልናደርጋቸው ይገባል። የጦሩ አባላት የተደራጁና ከፍተኛ ስልጠና የወሰዱ መሆን አለባቸው።"*

መጀመሪያ አካባቢ አልቃኢዳ በኋላ ላይ የመጣው ዐይነት ዓለማቀፋዊ አጀንዳ አልነበረውም። ምንም እንኳን ግብፃዊ አባላቱ አምርረው የሚጠሉትን የፕሬዚዳንት ሁስኒ ሙባረክ መንግስት ማውረድ መፈለጋቸው ግልፅ ቢሆንም ድርጅቱ በሸሪያ ሕግ መሰረት ማስተዳደርን ችላ ላሉ ሙስሊም መንግስታት የሰጠው ትኩረት እምብዛም ነበር። የቢን ላደን ረዳት የነበረው አቡ ማህሙድ ሳዑዲያዊው ሚሊየነር ቋሚ የጂሃድ ቡድን የመኖሩን ሃሣብ ያነሳበትን ጊዜ ሲያስታውስ "ኦሳማ ለጂሃድ ጥሪ ምላሽ

የሚሰጥ ጦር ማዘጋጀት እንዳለበት ያምናል። ሃማቡን ለእኛ ሲያማክረን በአረብ መንግስታት ላይ ስለሚካሄድ ጂሃድ አላነሳም። በፍልስጤም፣ ፊሊፒንስ እና ካሽሚር የሚኖሩ ሙስሊሞችን በሚጨቁን እምነት የለሽ መንግስታት ላይ ስለሚሆነው ነገር ያወራልን።" ይላል።

# አደረጃጀት

አልቃኢዳ በፍጥነት በኮሚቴ የተዋቀረና ሰንሰለት ያለው አመራር ወዳለው ድርጅትነት አደገ። መጀመሪያ ላይ ስራውን ለመቀበል ቢያቅማማም ቢን ላደን የድርጅቱ መሪ ሆነ። ወንድሙ እንደተናገረው ትሁቱና ኃላፊነትን የማይወደው ቢን ላደን ቦታውን እንዲቀበል ለማሳመን ከባድ ነበር። መስራቾቹ ድርጅቱን የሚያንቀሳቅሱ አምስት ቋሚ ኮሚቴዎችን አቋቁመዋል። የስልጠና ካምፖችን የሚቆጣጠርና መሳሪያ የሚገዛ ወታደራዊ ኮሚቴ፣ ፋትዋን ወይም ሐይማኖታዊ ትምህርቶችንና ደንቦችን የሚሰጥ እስላማዊ የጥናት ኮሚቴ፣ ጋዜጦችን የሚያትም የሚዲያ ኮሚቴ፣ የፓስፖርት፣ ቪዛና ቲኬቶችን ጉዳይ የሚከታተል የጉዞ ኮሚቴ፣ እና ገንዘብ የሚያሰባስብ የፋይናንስ ኮሚቴ ናቸው። መሪ ሹራው (ካውንስል) የኮሚቴዎችን ስራ ይከታተላል። ቀስ በቀስ አልቃኢዳ ክልላዊ ቢሮዎች ከ2-15 አባላት ባሏቸው ክንፎች የተከፋፈለ ኾነ። የተወሰኑ ክንፎች ልዩ ተልዕኮዎች ሲኖራቸው ቀሪዎቹ ደግሞ ለአንድ የአሸባሪነት ተግባር ሲባል የሚቋቋሙ ነበሩ።

አልቃኢዳ በአፍጋን አረቦች ዘንድ በሰረፀው ተረት ተጠቃሚ ሆኗል። የሶቭየትን ከአፍጋኒስታን መውጣት ተከትሎ ከውጪ የሚመጡ ሙጃሂዶኖች ቁጥር እየጨመረ ነበር የሄደው። ለዚህም ምክንያቱ

ውጤታማነቱ ተጋኖ ዝናው የናኘው የሙጃሂዲኖች ድል ነው። ሙጅሃዲኖቹ ሶቭየቶች ጥለውት የወጡትን የይስሙላ መንግስት ለመጣል ጓግተው ነበር።ሁሉም ወጣቶች ግን በአልቃኢዳ ተቀባይነት የሚያገኙ አልነበረም። አዲሱ ድርጅት የአባልነት መስፈርትና የስልጠና መመሪያዎች ነበሩት። ሹራው ለአባልነት የሚያበቁ የተወሰኑ መስፈርቶችን አውጥቷል። አመልካቾች ራሳቸውን እስከመጨረሻው ለድርጅቱ የሚሰጡ መሆን ይጠበቅባቸዋል። እንዲሁም አልቃኢዳ የሚሰጣቸውን መመሪያዎች ሁሉ ማክበርና መተግበር አለባቸው። ከዚያም በላይ አልቃኢዳ ውስጥ ባለና በመሪዎቹ ዘንድ አመኔታ ባለው ሰው መጠቆም የግድ ይላል። የመጀመሪያ ቅበላም አባልነትን አያረጋግጥም። ምልምሎች ወደፈተና ካምፖ ከገቡ በኋላ ምርጦቹ ወንድሞች ናቸው ወደ አልቃኢዳ አል አስካሪያ ወታደራዊ ጣቢያ የሚዛወሩት። እንደ አንድ ምልምል ገለፃ የመጀመሪያው ስልጠና ሁለት ሳምንት ይወስዳል። በዚያ ወቅት አሰልጣኞቹ አመልካቾችን በጥንቃቄ ይሰያቸዋል። "በሰልጣኞቹ ዘንድ የተወሰኑ ብቃቶችን ይፈልጋሉ። ዋናው መመዘኛ ወጣት፣ ዕነ፣ ታዛዥ እና ትዕዛዞችን ያለጥያቄ የመቀበል ደካማ ባህሪ ያለው መሆን ነው።" ይላል። መመዘኛዎቹ በማንኛውም የሽብርተኝነት ተቋም የሚታቀፉ ሰዎችን ተመሳሳይነት የሚያሳዩ ናቸው።

አል ቃኢዳ ከአቅሙ በላይ ምልምሎች ቢመጡለትም ሳይቀበላቸው የቀሩት በጉፈቃደኞች በጣም ጥቂት ናቸው። በማሰልጠኛ ጣቢያው ካለፉት በሺዎች የሚቆጠሩ ወጣቶች መካከል ከዋናው ድርጅት ጋር በአፍጋኒስታን የቀሩት ውስን ናቸው። ተቀባይነትን ካላገኙት የተወሰኑት ወደ ቦስኒያ፣ ቼቼኒያና ካሽሚር ለውጊያ ሲላኩ አብዛኞቹ ግን ቀጣይ ትዕዛዞች ከቢን ላደንና ከሹራው እስኪደርሳቸው ድረስ ወደአገራቸው ተመልሰው

እንዲጠባበቁ ተደረጉ:: የአልቃኢዳ ዓለማቀፋዊ ኔትወርክ አስኳሎች እንዲሆኑ የታሰቡ ይመስላል:: በአልቃኢዳ ካምፕ ውስጥ ከ1989 እስከ 2001 ድረስ የሰለጠኑት ወጣቶች ቁጥር ግምት ከ10,000 - 110,000 እንደሚገመት ይለያያል:: አልቃኢዳን የተቀላቀሉት ከእነዚሁ ውስጥ ከ3,000 ያልበለጡ ናቸው:: አብዛኞቹ ሰለጣኞች የመጡት ከአረብ አገራት ነው:: ሙሉ ምዝገባ የያዘ ሰነድ እስካሁን ባይገኝም የፓኪስታን መንግሥት በ1990ዎቹ አገሪቱ ውስጥ የሚገኙትን የውጭ ሙጀሂዲኖች እንዲመዘገቡ ጠይቆ ነበር:: ምዝገባው እንደሚያሳየው ተዋጊዎቹ 1142 ግብፃውያን፣ 981 ሳዑዲያውያን፣ 946 ሱዳናዊያን፣ 792 አልጀሪያውያን፣ 771 ጆርዳናውያን፣ 326 ኢራቃውያን፣ 392 ሶሪያዊያን፣ 199 ሊቢያውያን፣ 117 ቱኒዝያውያን እንዲሁም 102 ሞሮኮያውያን ይገኙበታል::

በ1990ዎቹ መቀመጫውን በአፍጋኒስታን ያደረገው አልቃኢዳ ከባለብዙ ዜግነት ኮርፖሬሽን ጋር የሚነፃፀር ነው:: በ2001 አልቃኢዳ በዓለማቀፍ ደረጃ በአጠቃላይ በ76 አገራት ውስጥ የሚገኙ ክንፎችን ይመራ ነበር:: ከቋሚ ክንፎቹ በተጨማሪ በተለያዩ አገራት ጥቃት መፈፀም ሲፈልግ የዚያው አገር ዜጎችን ይቀጥራል:: በ1998 የዩናይትድ ስቴትስ ኤምባሲ በታንዛኒያ ዳርኤስላም የጋየበት መንገድ አልቃኢዳ የየአገሪቱን ቅጥረኞችና መደበኛ አባላቱን አደራጅቶ ጥቃት ስለሚፈፅምበት መንገድ ጥሩ ማሳያ ነው:: ድርጅቱ በአካባቢው መስጊድ የሚገኙን ካልዳን ካሚስ መሐመድን ቀጥሮ የጥቃቱ ተሳታፊ ለማድረግ ችሏል:: የመሐመድን ታማኝነት ካረጋገጡ በኋላ በወሳኝ ዘመቻ ላይ እንደሚሳተፍ ብቻ ነግረውት ዝርዝር ጉዳዮችን ደብቀው የሚመች ቤት እና ፈንጂዎቹን የሚሸከም የጭነት መኪና እንዲከራይ ነገሩት:: እንደታንዛኒያዊ ነዋሪ እነዚህን ነገሮች

በቀላሉ ማድረግ ችሏል። የአልቃኢዳ አባላት ፈንጂውን የሚሰራ ኤክስፐርት አምጥተው ቢያስሩም መሐመድ መኪናውን ከማንቀሳቀሱ በፊት ነበር ታንዛንያን ለቀው የወጡት። ከጥቃቱ ቀን በፊትም ኢላማውን ያወቀው አይመስልም። ምናልባትም በዕቅዱ እርሱም በቦምቡ እንዲገደል የታሰበ ይመስላል። *"እኛ የምስራቅ አፍሪካ ክንፍ አባላት ፈፃሚዎች በመሆናችን የተልዕኮዎችን ዕቅድ ማወቅ አንፈልግም።"* የሚል ጽሑፍ ከጥቃቱ በኋላ ታንዛኒያ ውስጥ በተያዘ ኮምፒውተር ውስጥ ተገኝቷል። አሸባሪ ድርጅቶች ብዙ ጊዜ ደህንነታቸውን የሚያስጠብቁት የበታቾቻቸው ስለላይኛው ክፍል መረጃ እንዳይኖራቸው በማድረግ ስለሚፈልጉ ተልዕኮ ግን በቂ መረጃ በመስጠት ነው።

ከ9/11 ጥቃት በኋላ የዩናይትድ ስቴትስ ፀረ ሽብር ዘመቻ የአልቃኢዳ መሪዎች ላይ ትኩረት አደርጎ መግቢያ መውጫ አሳጥቷቸዋል። በአልቃኢዳ ውስጥ ከፍተኛ ስልጣን ያለው ሮሃን ጉናራትና በ2002 ባወጣው መጽሐፉ ላይ "አዋጪው መንገዳቸው የአልቃኢዳን አመራሮች መከታተል፣ አመራሩን ማኮላሸት እና የድጋፍ ገመዶቹን መበጠስ ይሆናል" ሲል ፅፏል።

ይህ መንገድ በእርግጥ ከ9/11 ጥቃት በፊት ውጤታማ ይሆን ነበር። አልቃኢዳ የተበታተነ አመራር በሚሰጥበት ሁኔታ ግን ስኬቱ የጐላ አይሆንም። አልቃኢዳ ከዋና መስሪያ ቤቱም በላይ ነው። በአንድ በኩል በኔትዎርክ የተሳሰሩ ንድፈ ሃሣባዊ ንቅናቄዎች ትስስር ሲሆን በሌላ በኩል በኢንተርኔት ሳይቀር በጐ ፈቃደኞች የሚመለመሉበት ድርጅት ነው።

# የአልቃኢዳ መረብ

አልቃኢዳ ከዓለማቀፍ ኮርፖሬሽንነቱ በተጨማሪ በርካታ አሸባሪ ድርጅቶችን በጥላው ስር የሚያገናኝ ድርጅት ሆኖም ያገለግላል። እንዲያውም ተቀናቃኞች "የኔትዎርኮች ኔትዎርክ" ሲሉ ይገልፁታል። በዓለማቀፍ ደረጃ በዕንፈኝነት የተሳሰሩና ደካማ የሚሏቸውን ሙስሊም መንግስታት እንዲሁም ዩናይትድ ስቴትስንና አውሮፓዊ አጋሮቿን የሚያጠቁበት መረብ ነው።

የአልቃኢዳ መረብ ቢን ላደን ሱዳን በቆየባቸው ዘመናት የበለጠ ሰፍቷል። በ1995 የእስላማዊ ህዝቦች ኮንፈረንስ በሱዳን ካርቱም ተካሂዶ ነበር። በኮንፍረንሱ ለመሳተፍ ተዋጊዎች ከአልጀሪያ፣ ፓኪስታን፣ ጆርዳን፣ ኤርትራ፣ ግብፅ፣ የመን፣ ቱኒዝያ እና ፊሊፒንስ ድረስ መጥተዋል። አልቃኢዳም ከሃማስ፣ የፍልስጤማውያን እስላማዊ ጂሃድ ብሎም ከሊባኖሱ ሂዝቦላህ የሺአ ቡድን ጋር ሳይቀር ትስስሩን አጠበቀ። በ1998 የካቲት ኦሳማ ቢን ላደን አዲስ የተፈጠረ ቅንጅት ይፋ አድርጐ ነበር። "ዘ ወርልድ እስላሚክ ፍሮንት ፎረም ጂሃድ አጌንስት ጀውስ ኤንድ ክሩሴደርስ" የተባለ ቅንጅት። በግብፅ፣ ፓኪስታን እና ባንግላዲሽ የሚገኙ ድርጅቶች ትብብሩን በፊርማቸው ቢያጸድቁም የተጠቃለሉትን ድርጅቶች ለመጠበቅ በሚል ስማቸውን ይፋ አላደረገም።

9/11ን ተከትሎ ዩናይትድ ስቴትስ አፍጋኒስታንን ስትወር የዚህ ስብስብ ጠቀሜታ የጐላ ሆኗል። ክንፎቹና ቅርንጫፍ መስሪያ ቤቶች በራሳቸው ሲንቀሳቀሱ ዋና መስሪያ ቤቱ ራሱን ፓኪስታን ውስጥ እንደገና አዋቀረ። ቢን ላደን ወደ ደቡባዊ ምስራቅ የአፍጋኒስታንና ፓኪስታን

ድንበር ለመሻሻ ሲገደድ ለጊዜውም ቢሆን የሽብር ጥቃቶችን የመቆጣጠርና የመምራት አቅሙን አጥቷል። ይህ መቋረጥ አልቃኢዳ የጦር መሳሪያዎችንና ቁሳቁሶችን እንደልቡ እንዳያንቀሣቅስና የዳርኤሰላምና የናይሮቢ ዐይነት ጥቃቶችን መፈፀም እንዳይችል ገድቦታል። ይሁንና በክንፎቹ አማካኝነት በ2004 በማድሪድና በ2005 በለንደን የቦምብ ጥቃቶችን መፈፀም ችሏል።

## የአልቃኢዳ ርዕዮተ ዓለማዊ ንቅናቄ

አልቃኢዳ ከተዘረጋው መረብም በላይ ስለመስፋቱ በርከት ያሉ ማስረጃዎች አሉ። የሽብርተኝነት ተንታኝ የኾነው ማይክል ቻንድለር "የሶስተኛው ትውልድ አሸባሪነት" ይለዋል። ቢን ላደንና ሹራው እንደ "የመጀመሪያ ትውልድ" በአሚሪካ ወረራ እስከሚገቱ ድረስ ተልዕኮዎችን ይመሩ ነበር። የአፍጋኒስታኑ ወረራ መገባደድ የመጀመሪያው ትውልድ አባላት ወደየትውልድ አገራቸው እንዲሄዱ አድርጓል። በዚያም ነባር ክንፎችን በመቀላቀል እንዲሁም አዳዲስ ክንፍ በማቋቋም "በሁለተኛው ትውልድ" አሸባሪዎችን መለመሉ።

ከነዚሁ ክንፎች በተጨማሪ ባለፉት ጥቂት ዓመታት "የሶስተኛው ትውልድ" አሸባሪዎች ብቅ ብለዋል። እነዚህ ቡድኖች በአፍጋኒስታን ያልነበሩና በአፍጋኒስታን ከነበሩት ጋርም ቀጥተኛ ግንኙነት የሌላቸው ናቸው። አዳዲሶቹ ቡድኖች አልቃኢዳ የተወሰነ ማበረታታትና ማነሳሳት ሊሰጥ ቢችልም ሙሉ በሙሉ የመቆጣጠር ስልጣን ያለው አይመስልም። የሶስተኛ ትውልድ አሸባሪዎች በራሳቸው ተደራጅተው፣ የራሳቸውን ገንዘብ ሰብስበው፣ በራሳቸው አቅደው ጥቃት ከፈፀሙ በኋላ ምናልባት የቀደሙ

ትውልዶችን ማረጋገጫ የሚሹ ናቸው፡፡ ፕሬዝዳንት ጆርጅ ቡሽ "ከእኛ ጋር ያልሆነ አገር ከአሻባሪዎች ጋር ነው" ለማለታቸው ምላሽ አልቃኢዳም "ዩናይትድ ስቴትስን የሚቃወም ሁሉ ከእኛ ጋር ነው" ያለ ይመስላል፡፡

አልቃኢዳ አዳዲስ ምልምሎችን ከማሰልጠኑ በላይ የሚያስፈራ መልክ የያዘው ግን የፅንፈኛ ርዕዮተ ዓለም በኢንተርኔት መስፋፋቱ ነው፡፡ ቢን ላደንና ተከታዮቹ ዴሞክራሲና ሃይቶችን ከመጥላታቸው በተፃራሪ የሚጠሉት ስልጣኔ ውጤት የሆኑትን የቴክኖሎጂ መሳሪያዎች ግን ለመጠቀም ተዘጋጅተው ነው የጠበቁት፡፡ የግንኙነት አብዮት ሩቅ በሚባሉት የዓለም ጥጎች እንኳን ተዳርሷል፡፡ በሚያስገርም መልኩ ከዓለም 6.7 ቢሊየን ህዘብ ውስጥ 1.6 ቢሊየኑ የኢንተርኔት ተጠቃሚ ነው፡፡ ከአስር ሰዎች ውስጥ ስድስቱ ወይም 4.1 ቢሊየን ህዝብ የሞባይል ስልክ ተጠቃሚ ነው፡፡ የኤሌክትሪክ ኃይል በሌለባቸው አካባቢዎች እንኳን የፀሃይ ጉልበት ቴሌቭዥኖችን ያንቀሳቅሳል፡፡ እነዚህ እውነታዎች የሚያመላክቱት ነገር አለ፡፡ ከዚህ መለስ የማይባል መረጃ  ከኢንተርኔት መገኘት መቻሉ የሚፈጥረው ያለመረጋጋት ተፅዕኖ አለ፡፡ ኢንተርኔት የድሃና ሀብታምን ልዩነት ቁልጭ አድርጎ ያሳያል፡፡

ያለመረጋጋቱን ተከትሎ ከሚመጣው ፅንፈኝነት ከማስፋፋት በተጨማሪ አልቃኢዳ የግንኙነት አብዮቱ በሚፈጥረው ብስጭት ላይ ትኩረት አድርጎ መስራቱን ቀጥሏል፡፡ በፊት የተናደደ ሰው ጽንፈኛ ለመሆን ሌሎች አሸባሪዎችን ማግኘት ይጠበቅበት ነበር፡፡ አሁን ግን የኢንተርኔት ገጾችን ከፍቶ በመግባት ብቻ እንደእሱ የተበሳጩ በርካታ ሰዎች መኖራቸውን ይረዳል፡፡

በቁጥር ጥቂት የማይባሉ ዌብሳይቶች የአልቃኢዳን ዕንፈኛ የእስልምና ቅጅ አምስተርዳም፣ በርሊን፣ ፓሪስ፣ ለንደን ወይም ሚኒያፖሊስ ላለው ወጣት ያለማቋረጥ ይሰብካሉ። እምነት የለሹን ባህሉን ትቶ ጂሃድን በመቀላቀል ብቻ ሕይወቱን የተሻለ ማድረግ እንደሚቻል ደጋግመው ይናገሩታል። በዚያው በኢንተርኔት ወጣቱ በአካባቢው የሚገኘን የአልቃኢዳ ክንፍ እንዲቀላቀልም ይበረታታል። ስለ ቦምብና ፈንጂ አሰራር በቀላሉ መረጃ ማግኘት ይችላል። ለተልዕኮው የገንዘብ ስንቅም በበጐ አድራጐት ስም እርዳታ ከሚሰበስቡ የአልቃኢዳ ተላላኪዎች በቀላሉ ይገኛል።

## የገንዘብ ምንጮች

እንደማንኛውም ድርጅት አልቃኢዳም ገንዘብ ይፈልጋል። የሽብር ፈንድ ማለት ለአንድ የተወሰነ የሽብረ ጥቃት የሚሰባሰብ ገንዘብ ሲሆን የሽብር ፋይናንስ ደግሞ የዕለት ተዕለት የሽብርተኝነት ወጪዎችን የሚሸፍን ገንዘብ ማለት ነው።

የተወሰነ ተልዕኮን መፈፀም የሚጠይቀው የገንዘብ መጠን በተነፃፃሪ መልኩ ዝቅተኛ የሚባል ሲሆን በሌላ በኩል ዓለማቀፋዊ የሽብርተኝነት መረብን ማስቀጠል የሚያስፈልገው ፋይናንስ ግዙፍ ነው። ተንታኞች እንደገመቱት ከ9/11 በፊት የአልቃኢዳ ዓመታዊ ወጪ 30 ሚሊዮን ዶላር ይደርሳል። የለንደኑ ጥቃት ጥቂት መቶ ፓውንዶችን፣ የ2004ቱ የማድሪዱ የባቡር ፍንዳታ 10,000 ዶላር፣ የ9/11 ጥቃት ደግሞ 500,000 ዶላር ነው የጠየቁት። የማድሪዱን ጥቃት ወጪ የተልዕኮው መሪ ከሃሺሽ ንግዱ ካገኘው ገንዘብ ሲሸፍነው የለንደን ቦምብ አፈንጂዎች ግን ወጪያቸውን

የሸፈኑት ከኪሳቸው ነው፡፡ እንደሚታወቀው የመስከረም አስራ አንዱን ሽብር ወጪ የሸፈነው የአልቃኢዳ ዋና መስሪያ ቤት ነው፡፡

አልቃኢዳ በ20 ዓመታት ታሪኩ የተለያዩ የገንዘብ ምንጮች ነበሩት፡፡ በመጀሪያዎቹ ዓመታት ቢን ላደን ሙሉ ወጪውን ከራሱ ንብረት ሲሸፍን ቆይቷል፡፡ ከሳዑዲ ቱጃሮችና በሙስሊሙ ዓለም ከሚገኙ የተለያዩ ደጋፊዎቹ ዕርዳታም ይቀበል ነበር፡፡ እስላማዊ በጐ አድራጐቶች ቀሪውን ክፍተት ይሞላሉ፡፡ አብዛኞቹ ለጋሾችም የሚሰጡት ገንዘብ ሽብርተኝነትን ለማበረታታት እንደሚውል አያውቁም፡፡ ሁለት በሕጋዊነት ማር የሚነግዱ ድርጅቶችም ትርፋቸውን ወደ አልቃኢዳ ሲያፈሱ ቆይተዋል፡፡ በየአካባቢው የሚገኙ ክንፎች ደግሞ የራሳቸውን ወጪ ከክሬዲት ካርድ ስርቆትና በተራ ወንጀሎች ከሚገኙ ገቢዎች ይሸፍናሉ፡፡

ለታሊባኖችም ሆነ አልቃኢዳ ከፍተኛውን ገቢ የሚያስገኘው የናርኮቲክ ዝውውር ነው፡፡ ከታሊባኖች መውደቅ በኋላ በአፍጋኒስታን የኦፒየም እርሻ በ2001 ከነበረው 50,000 ሄክታር በ2008 ወደ 150,000 ሄክታር አድጓል፡፡ አሁን አፍጋኒስታን ከዓለም የኦፒየም ምርት ውስጥ 75 ከመቶውን ትሸፍናለች፡፡ አልቃኢዳም ሆነ ታሊባኖች ኦፒየምን አያመርቱም፣አይሸጡምም፡፡ ከዚያ ይልቅ ገንዘቡን የሚያገኙት ከምርት ሽያጭ ቀረጥ እንዲሁም ከሽያጭ ድርድር ነው፡፡ በኔቶ ግምት መሰረት ታሊባኖች ከ40-60% ገቢያቸውን የሚያገኙት ከናርኮቲክ ዕፅ ነው፡፡

ከአልቃኢዳ የገንዘብ ምንጮች ብዛትና ገንዘቡን በቀላሉ ለማዘዋወር ከመቻላቸው አንፃር የሽብርተኝነትን ፋይናንሶች ማድረቅ በእጅጉ ከባድ ነው፡፡ በዚያ ላይ የሽብርተኝነት ተንታኞች የአሸባሪዎችን ገንዘብ ከማገድና የገንዘቡን ፍሰት እየተከተሉ አሸባሪዎችን ከማደን የትኛው እንደሚሻል

ከመከራከር ቦዝነው አያውቁም፡፡ ሁሉቱም መንገዶች የየራሳቸው ጥቅሞች ስላሏቸው በጥንቃቄ ጥቅም ላይ መዋል ያለባቸው ናቸው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የሽብር ጥቃቶች የሚጠይቁት የገንዘብ መጠን ከመሆኑ አንጻር የአሸባሪዎችን ገንዘብ መቆጣጠር ያን ያህል አመርቂ ውጤት የሚያመጣ አይመስልም፡፡ የሆነ ሆኖ አልቃኢዳ ከ2005 ወዲዚህ በዩናይትድ ስቴትስና ምዕራብ አውሮፓ ከባድ ጥቃቶችን መፈፀም አለማስቻሉ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ምዕራባውያን ሽብርተኝነትን ለማንገታገት መቻላቸውን የሚጠቁም ነው፡፡

## የቢን ላደን ሚና

ከአልቃኢዳ ምስረታ በኋላ በመጀመሪያዎቹ አስርት ዓመታት የቢን ላደን ሚና ጥርት ብሎ የሚታወቅ አልነበረም፡፡ በግልፅ የሚታወቀው የድርጅቱ ተወካይ መሆኑ ነው፡፡ በተጨማሪም ከራሱ ውርስና ከሳውዲ ቱጃሮች ከሚያገኘው ገንዘብ ለተልዕኮዎች ማስፈፀሚያ ከሚያስፈልገው ገንዘብ አብዛኛውን የሚሰጠው እርሱ ነበር፡፡ አፍጋኖቹም ሆኑ አረቦቹ የቢን ላደንን ገንዘብ በጣም የሚፈልጉት ቢሆንም በችሎታው ላይ ግን ጥርጣሬ ነበራቸው፡፡ እርዳታውን ለማግኘት ይሻኮቱ እንደነበር ቢታወቅም ውሳኔ አሰጣጥ ላይ ምን ያህል ነፃነትና ድጋፍ ይሰጡት ነበር የሚለው ግን በግልፅ አይታወቅም፡፡ ሃጂ ዲ መሐመድ የተባለ ሙጅሃዲን ኮማንደር ስለቢን ላደን ሲያወራ "እውነቱን ለመናገር ስለ ቢን ላደን ብዙ አንጨነቅም ነበር፡፡ ብዙም ትኩረት አንሰጠውም፡፡ የነበረው ብቸኛ ነገር ገንዘብ ነው፡፡ ሃብቱን መጠቀም እስከቻሉ ድረስ ቡድኖቹ ስለቢን ላደን የሚያስቡት በጥቂቱ ነው፡፡" ብሏል፡፡

አንድ የአፍጋን አገልግሎቶች ቢሮ አባል ስለ ቢን ላደን የአመራር ችሎታ የሚከተለውን ይናገራል፡፡

*"ኦሳማ ድርጅት ፈጥሮ ነገሮችን በቁጥጥሩ ስር ማዋል ነበረበት፡፡ እኔ እንደማስበው ግን እንደ መሪ በርካታ ግድፈቶች ነበሩበት፡፡ በ1991 ወደ ካቡል ለመግባት ከ1.5 ሚሊየን ዶላር በላይ መድቦ ከሳምንታት በኋላ ሰዎቹ ገንዘቡን በሙሉ ይዘው በመጥፋታቸው ተልዕኮው መና ቀርቷል፡፡ ኦሳማን እንደመሪ ፍፁም ያልተሳካለት አድርጌ ነው የምወስደው፡፡"*

የአፍጋን መሪዎች በቢን ላደን ላይ ያላቸው ዝቅተኛ አመለካከት በ1992 ወደ አፍጋኒስታን ሲመለስ የበለጠ ተንፀባርቋል፡፡ ወዲያውኑ የተረዳው ነገር በእሱ ስር የነበሩት የአፍጋን አረብ ተዋጊዎች ወደ አፍጋን ክፍሎች ተበታትነው ሊቆጣጠራቸው ወደ ማይችልበት ሁኔታ ውስጥ መግባታቸውን ነበር፡፡ "ከሄክማትያር ጋር የነበሩ ሰዎች ኦሳማን ሲያስጠነቅቁት ትዝ ይለኛል፡፡ ከአሁን በኋላ መሪ አይደለህም፡፡ ብለውታል፡፡ ከዚያ በኋላ ነው ወደሱዳን ለመሄድ የወሰነው፡፡" ይላል የአዛም ወንድም፡፡ በአልቃኢዳና ታሊባን ጉዳዮች ኤክስፐርት የሆነው አህመድ ራሺድ በእነዚህ ዓመታት ውስጥ ቢን ላደን የነበረበትን ሁኔታ እንደሚከተለው ይስለዋል፡፡

*"በጂሃዱ ጊዜ የሚያውቁት አረብ አፍጋኖች ቢን ላደን ጉበዝ አለመሆኑንና በሙስሊሙ ዓለም መደረግ ስለሚገባው ግልፅ ምስል የሌለው ነው ሲሉ ይገልፁታል፡፡ በዚያ መልኩ የእስላማዊ አብዮቱ ሌኒን ወይም ቼ ጉቬራ የሶስተኛው ዓለም አብዮቶች ተምሣሌት ነው ብሎ ለማሰብ ያስቸግራል፡፡*

*የቢን ላደን የቀድሞ ረዳቶች የሚገልፁት ሁል ጊዜም ከእርሱ የተሻሉ ስለሙስሊሙ ዓለም የሚያውቁ አስተማሪዎችን የሚፈልግ ዐይነት አድርገው ነው።"*

## የመሪነት ጉዞ

እነዚህ ጠንከር ያሉ ጉዳዮች በአልቃኢዳ ምስረታ የመጀመሪያዎቹ ዓመታት የገጠሙት ቢን ላደን በቀጣይ ጊዜያት በድርጅቱ ዘንድ የነበረው ሚና የቀዘቀዘ አልነበረም። ያለእርሱ ሃብትና እገዛ ድርጅቱ መፈጠር ቢችል እንኳን ረዥም ርቀት መጓዝ የማይታሰብ ነው። በ1992 ገና 35 ዓመቱ ነበር። ከታላላቆቹ በተቃራኒው ከሳዑዲ አረቢያ ውጭ የመጓዝና የመኖር ልምዱ ዝቅተኛ ነው። በቤተሰቦች የንግድ ተቋም ቢን ላደን ግሩፕ ውስጥም ይህ ነው የሚባል ኃላፊነት ተሰጥቶት አለማወቁ የመምራት አቅሙን እንዳያዳብር አድርጐታል። የአፍጋኑን ጂሃድ ከመቀላቀሉ በፊት የኖረው በታጠረ ሕይወት ውስጥ ነበር ማለት ይቻላል።

አፍጋኒስታን ግን ቢን ላደንን በተጨባጭ ለውጣዋለች። በኋላ ላይ ሲገልፀው "እዚያ የኖርኳቸው ሁለት ዓመታት ሌላ ቦታ ከሚኖሩ መቶ ዓመታት የሚነፃፀሩ አይደሉም።" ማለቱ የሚገልፀውም ይህንኑ ነው። በቀጣይ አስር ዓመታትም ጂሃድን አጥብቆ የፈለገው ያንን ዐይነት ሕይወት ስለሚናፍቅ ይመስላል። ምንም እንኳን የአልቃኢዳ ጭንቅላት ሆኖ ባያውቅም የፅንፈኛ መረቦች የዓለማችንን ጉልበተኛ አገር እንዲያጠቁ በማነሳሳት ግን የአልቃኢዳ ልብና ነፍስ ሆኖ ግን አገልግሏል።

በ1992 ግን ነገሮች ባልተጠበቀ ሁኔታ ተለወጡ። ቢን ላደን አፍጋኒስታንን ለቀቀ። በወቅቱ በተያዙ የሙስሊም መሬቶች ላይ ጂሃድ ማወጅ እንደሚገባ አቋም ቢይዝም በሙስሊም መንግስታት ላይ ስለማመፅ ግን የያዘው አቋም አለነበረም። ስለፍልስጤማውያን ነፃነት ቢያወራም በቀጥታ በትግሉ ለመሳተፍ ግን ፈቃደኛ አልነበረም። ጠንክር አድርጐ የያዘው በመካከለኛው የእስያ አገራት በሰሸየቶች ላይ ጂሃድን መቀጠልንና ህንዶችን በካሽሚር ሙስሊሞች ስም እንዲሁም የፊሊፒንስን መንግስት በአናሳ ሙስሊሞች ስም መዋጋትን ነው።

ከዚያ በኋላ በዋናነት ወደ ትውልድ ቦታው ለመመለስ ወስኗል። ወደአገሩ ሲመለስ የጠበቀውም የጀግና አቀባበል ነበር። በሳዑዲ አረቢያ ሰፊ ንግግር ካደረገ በኋላ ወደቤተሰቡ የንግድ መስመር መመለስ ይችል ነበር። ነገር ግን ፅንፈኛ አቋሙ አገረሸና እምነት የጎደላቸውን ሙስሊሞች ብቻ ሳይሆን በአትላንቲክ የተዘረጋችውን ታላቋን ሰይጣን ለመዋጋት ቆረጠ።

# ምዕራፍ አምስት

## ታላቋን ሰይጣን መፋለም

ኦሳማ ኢብን መሐመድ ቢን ላደን በአፍጋኒስታን ከሶቪየት ኅብረት ላይ በተደረገው ጦርነት ወቅት የተነሣ ሲሆን በወቅቱም አንድ ክበድ ያለ ግዳጅ እና ኃላፊነት እንዳለበት አድርጎ ራሱን ቢያሳምንም ጥርት ያለ ትኩረት ያደረገበት ነገር ግን አልነበረውም:: ያም ሆኖ ግን በመላው ዓለም ላይ በርካታ አባላት ያሉትን እና በዓለም ደረጃም እንደፈለገ ሊለጠጥ የሚችል ድርጅት መስርቷል:: ያ የመሠረተው ድርጅት ግን እጅግ ላላ ያለ መዋቅር ብቻ ያለው እና ግልጽ አቅጣጫም ያጣ ነበረ:: ቢን ላደን በመላው ዓለም እጅግ ውጉዝና የሚጠላ ቢሆንም ግርማ ሞገስ እና ተዝቆ የማያልቅ ሐብትም ያለው ነበረ:: ከምንም በላይ ቢን ላደንን ታዋቂ እንዲሆን ያደረገው ራሱ የፈጠረው እና ያስነገረው ነገር ግን ምናልባትም ራሱም እውነት እንደሆነ አድርጎ ራሱም ጭምር ተቀብሎት ሊሆን በሚችል መልኩ *በአኗህ ፈቃድ፣ በእሱ አደፋፋሪነት እና ወኔ ሰጪነት ብሎም የገንዘብ እርዳታ ሙጃሂዲኖች ታላቋን ሶቪየት ኅብረት ከአፍጋን በማባረር ታሪክ ሰሩ የሚል የፈጠራ ታሪክ* ነው:: ቢን ላድን ከዚህ በተጨማሪም *በመላው ዓለም ዙሪያ ተጨቁነው ያሉ ሙስሊሞችን ነፃ ለማውጣት ሲባል ጂሀድ መቀጠል አለበት* የሚለውን አጠቃላይ መርሆችንም ተቀብሏል:: እንዲህ የመሳሰሉ አቋሞች ቢኖሩትም ቢን ላደን ለረጅም ጊዜ ይህ ነው የሚባል የተነደፈ እና ግልጽ አቅጣጫ ግን አጥቶ ቆይቷል::

## ጂሀድን ፍለጋ

በ1980ዎቹ መጀመሪያ ግድም ኮምዩኒዝም ሲፈራርስ ለቢን ላደን እምቅ ችሎታውን፣ የካበተ ልምዱን እና ሀብቱን ለመጠቀም የሚችልባቸው የተለያዩ ሰፋ ያሉ አማራጮች ተከፈቱለት:: በተለይ የሱ ትኩረት ያረፈባቸው ሙስሊም አገራት በአብዛኛው ከተዘቃዛው ጦርነት ማብቃት እና ከሶቭየት ኅብረት መፈራረስ በኋላ የስልጣን እና የአመራር ክፍተት ተፈጠረባቸው:: በተለይም በዚህ ወቅት በምሥራቅ አፍሪካ እስከዛሬም ባልተቀየረ መልኩ ሙስሊሟ ሶማልያ በድኅረ-ቀዝቃዛው ጦርነት ወቅት ያንን ግዙፍ ሕዝብ እንደያዘች መንግሥት አልባ ሆነች:: በሌላ በኩል ዩጎዝላቪያም ቀደም ሲል ካዋቀሯት ስቴቶች ሶስት ያህሉ ከፌዴሬሽኑ ተገንጠሉና የመበታተን ዕጣ ፈንታ ደረሳት:: ከእነዚህ ውስጥ በመገንጠል ማዕበል ተንቦግቡጋ ቀዳሚውን እርምጃ የወሰደችው በሮማን ካቶሊክ እምነት ተከታይ ሕዝብ ብቻ የተዋቀረችው ስሎቬንያ ናት:: «ያለ ምንም ደም» እንደሚባለው ነው ስሎቬን[illegible]ይት፣ ጩኸትም ሆነ ጦርነት የሚባል ሳይታይ በሰላም የተገነጠለችው:: የሷን ፈለግ እኩተላለሁ ብላ ወደ መገንጠሉ ያመራችው ቀጣዩዋ ደግሞ ክሮኤሽያ ስትሆን የሷ ግን ሳንካ የማይጠፋው ሆኖባት ሰርቢያ የራሷ ተወላጆች የሚበዙባቸውን ቦታዎች «አላስወስድም» በማለት በፈፀመችባት ጣልቃ ገብነት እነዚያ ቦታዎች ለአራት ዓመታት ያህል ሰርቢያ እንድትጨፍርባቸው ምክንያት ሆነ:: ከዚያም መገንጠልን መርጣ በሶስተኛ ደረጃ የወጣችው ቦዝኒያ ስትሆን የሷ ደግሞ እጅግ የከፋው ሆንና የለየለት የእርስ በርስ ጦርነት ተከተለ:: በዚህ ወቅት የተፈፀመው ነገር እጅግ አሳዛኝ ነበረ:: የቦዝኒያ ሰርቦች በቦዝኒያ ሙስሊሞች ላይ ሆነ ብለው የአስገድዶ መድፈር፣ ግድያ እና ስቃይ በመፈፀም ይገባናል ይሉት ከነበረው ግዛት በግድ

አባረው በማስወጣታቸው የተነሳ በዘር እየተመራረጡ መጠቃቃትና የለየለት የብሔር ጦርነት ተከተለ።

ከዚያ በኋላ የቦዝኒያ ሙስሊሞች እና የቦዝኒያ ክሮአቶች ከፉኛ ተጫረሱ። በሌላ በኩል ደግሞ ከሶቪየት ኅብረት ስቴቶች መሀከል ሙስሊም ያለባት ቼቺኒያ ሶቭየት ኅብረት ቀደም ብሎ ለባልቲክ ግዛቶች ማለትም ለዩክሬይን እና ጆርጂያ የሰጠችውን ነፃነት ለሷም እንድትሰጥ መገፋፋት ያዘች። ሞስኮ ግን በጣም በሚያሳዝን መልኩ የቀራትን ጦር ወደ ቦታው በመላክ እጅግ የከፋ እና ጭፍጨፋ ላይ ያመዘነ፣ ነገር ግን ብዙም ውጤታማ ያልሆነላትን ጥቃት በቼቺኒያዎች ላይ ፈፀመች። በፊሊፒንስ መገንጠልን ያነገበ የሙስሊም ቡድን በማሊላው ሥርዓት ላይ ጦርነት አውጆ ድፍን አስር ዓመታት ተፋልሞታል። ፓኪስታን ደግሞ ሆነ ብላ በካሽሚር በሚገኘው ሙስሊሙ ማኅበረሰብ ላይ አለመረጋጋትና ብጥብጥ ለመፍጠር ስትል መደበኛ ያልሆነ ተንኳሽ ጦሯን ወደ ስፍራው ልካ መንካካቱን ተያያዘችው። አንደንድ አረብ የሆኑ አፍጋኖች በዚህ ከፉኛ ተቆጥተው በግጭቱ ቢገቡም ቢን ላደን በኋላ በሰጠው አንዱ መግለጫ ግን «እኔ አዝገርቸው አይደለም» ሲል ተደምሟል። ነገር ግን ይህ ሁሉ ቢከሰትም እንደ አፍጋኑ ሁኔታ ግን ቢን ላደንን የሳበው አልነበረም።

ግን እንደ ዕድሉ ሆነና ወደ አፍጋን ተመልሶ በገባ በሶስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ብቻ ነበረ አንድ ጥሩ አጋጣሚን የፈጠረለት ብጥብጥ የተነሳው። ሳዳም ሁሴን ኩዌትን ወርረው በነበረ ጊዜ ቢን ላደን ከዌትን ነፃ ለማውጣት የራሱን ሙስሊም ጦር ለመላክ የሳውዲን ንጉሣዊ ሥርዓት ቢጠይቅም ምላሹ እምቢታ ሲሆንበት ከፉኛ አቂመና አመረረ። በዚህ

የተነሳ ቀስ በቀስ ከረር ያለው እስተሳሰብ እያጋደለበትም መጣ:: ነገሮችን መልሶ መላልሶ ሲያይም ታሪክ ታወሰው:: በታሪክ እንደሚታወቀው ዑማዎችን (የእማኝ ማኅበረሰቦች ማለት ነው) መልሶ ለመፍጠር እና ለማቋቋም በተደረገው ጥረት ትልቁን ጋሬጣ የፈጠሩት እንደ ግብጽ እና ሳውዲ ዓረቢያ ያሉ እምነትን የካዱ አገራት ነበሩ:: እነዚህም «ጠላት ከሩቅ አይመጣምና የውስጥ ቦርቧሪዎች ናቸው» ተባሉ:: ነገር ግን እነዚህ የውስጥ ቦርቧሪዎች የሚደገፉት እና የሚመሩት በ «ሩቁ ጠላት» አሜሪካ ነው:: እናም የውስጥ ቦርቧሪዎቹ ይሸነፉ ዘንድ በቅድሚያ አሜሪካ በሙስሊሙ ዓለም ላይ የምትፈጥረው ተጽዕኖ ተበታትኖ መጥፋት ይኖርበታል ተብሎ ተወሰነ::

ይሁን እንጂ ቢን ላደን በ1988 ከአፍጋኒስታን «ጀግና» የሚል ስም አግኝቶ ሲመለስ እነዚህ ነገሮች ገና አልተከሰቱም:: የአፍጋኑ ልምዱ ቀየረው:: ምንም እንኳን ወደ ኃይል እና ጥቃት ደረጃ አይድረስ እንጂ ፀረ-አሜሪካ የሆነ አቋም ግን በውስጡ ሰርጿል:: ዋንኛው ቅሬታውም ልክ እንደ ብዙዎቹ፣ «አሜሪካ ለእስራኤል እርዳታ መስጠቷ ነው» የሚለው ነው:: ቢን ላደን በታላቅ ምሬት፣«

> *«አሜሪካ በፍልስጤም በመጨፈር ላይ ለሚገኙት አይሁዳውያኖች እርዳታ መስጠቷን አታቆምም:: ይህን እንድታቆም ካስፈለገ ግን እኛ ተባብረን ብዙ ቡጢዎችን ልናቀምሳት ይገባል:: አሜሪካ ይህንን ድርጊቷን የምታቆመው በበርካታ ጂሀዶች ልካችንን እና ማንነታችንን ስናሳያት ብቻ ነው!»«*

ሲል ተናግሯል። ቢን ላደን በዚህ ወቅት ግን ንግግሩ ምሳሌያዊ ይመስላል።

> *«ባሁን ሰዓት የሚፈለገው ዋንኛ ተግባር በአሜሪካ ላይ የኢኮኖሚ ጦርነት ማወጅ ነው። በመሆኑም ከዚህ በኋላ ማንኛውንም የአሜሪካ ምርት መግዛትን ማቆም ይኖርብናል. . . ልብ አድርጉ! እኛ የአሜሪካን ማንኛውንም ምርት ገዛን ማለት የገዛ ገንዘባችን በእጇ ይገባና ነገ ዐይናችን እያየ ሙስሊም እህትና ወንድሞቻችንን በአረመኔያዊነት ለሚጨርሱት አይሁዶች ወስዳ በእርዳታ መልክ ትሰጣቸዋለች። ከዚያም በገዛ ገንዘባችን ወገናችን ያልቃል።»*

ቢን ላደን ከዚህም በተጨማሪ ወደ አፍጋን ጉዞ ከማድረጉ ቀደም ፊጽሞ ብሎትና ተናግሮት በማያውቅ መልኩ በሳውዲው ንጉሣዊ ሥርዓት ላይ የሰላ ትችትና ተቃውሞ አቀረበ። ሳውዲ ዓረቢያ ምንም እንኳን ሙስሊም አገር ብትሆንም ሙስሊሙን በማስተዳደር ረገድ በጂሀድ የሚቀርበውን አማራጭ ግን ፊፅሞ አትቀበልም። ቢን ላደን እና ደጋፊዎቹ ግን በጂሀድ እንደሚባለው አንድ የሙስሊም አገር መመሪት ያለባት በእስልምና ሪፐብሊክ ሥርዓት እንደሆነ እና ማንኛውም ትዕዛዝና ውሳኔ የሚተላለፈው ደግሞ ከ «ሹራ» ጋር በሚደረግ ምክክር ብቻ ነው ብለው ያምናሉ። እናም ንጉሣዊ ሥርዓትን አጥብቀው ይቃወማሉ። ከዚያ በተጨማሪም ንጉሣዊ ሥርዓቱን ሲመለከተው እጅግ የተትረፈረፈ፣ ተዝቆ የማያልቅ ሀብት ውስጥ የተዘፈቀና ተነግሮ በማይዘለቅም መልኩ ዓለም ባላየው ምቾትና ድሎት ውስጥ የተቀናጣ

ኑሮን የሚኖሩ በርካታ የቤተሰብ አባላትን ያቀፈ በመሆኑ ቢን ላደን ይህንን አጥብቆ ጠላው:: በጣም አብዛኛው የሳውዲ ሕዝብ ምቾት የሌለው ተራ ኑሮ እየኖረ፣ በቁጥር ጥቂት የሚባል የሌላ አገር ዜጋ ደግሞ ጭራሽ ዝቅተኛ ኑሮን ለመግፋት እየተገደደ እነዚያ ንጉሣውያን መንቀባረራቸው ለቢን ላደን የሚነቀፍ ሆነ::

## ደቡብ የመን

ወደ አገሩ ከተመለሰ በኋላ ቢን ላደን በሌላ ጂሀድ ተወጠረ:: በዓረብ ንፍቀ ክበብ ሰሜን ጫፍ ላይ የምትገኘው ደቡብ የመን በ1967 የእንግሊዝ ጦር ለቋት ከወጣ በኋላ ኮምዩኒስት ሆና ቆይታለች:: በቁጥር እጅግ አናሳ የሚባሉ ተቃዋሚ አማፅያን ይህንን የኮምዩኒስት መንግሥት መገርሰስ የፈለጉ ሲሆን ቢን ላደንም ከአጠገባቸው ቆሞ አጋርነቱን መግለጽን አጥብቆ ፈለገ:: የቤተሰቡ ታሪክም የሞራል ጥንካሬን ሰጠው:: የኋላ አመጣጡን ሲያስታውስ አባቱ ከደቡብ የመኗ ሐድራማውት እንደመጣ ተከስተለት:: እናም ከአፍጋን ሳይወጣ ነው አንድ እግሩን እዚህ ፀረ-ኮምዩኒስት ትግል ውስጥ የከተተው:: ከግብረ አበሮቹ አንዱ እንደሚመሰክረው ከሆነ ቢን ላደን በዚህ ጊዜ በሶቪየት ኅብረት ላይ ድልን ከተቀዳጁ በኋላ የሚያስማራቸው የአፍጋን ዓረቦች (ወይንም ሙጃሂዲኖቹ) ወደ ደቡብ የመኑ የጦርነት አውድማ በማቅናት ነፃነት የተጠማውን ሕዝብ ጥሙን ሊያረኩለት ይገባል ብሎ አምኗል:: ቢን ላደን ወደ ሳውዲው የደህንነት ጉዳዮች ከፍተኛ ኃላፊ ልዑል ቱርኪ ዘንድ በመቅረብ በደቡብ የመን የሚፋለሙትን አማፂያን መርዳት ይቻል ዘንድ የዓል-ቃይዳ ተዋጊዎችን ለምን አትልኩም ብሎ ይጠይቃል:: እንዲያውም ሳውዲ የምትልከውን ይህንን ልዩ ሠራዊት እሱ ፈንድ ሊያደርገው እንደሚችል ጭምር ይነግረዋል:: ልዑሉ በኋላ

በተደረገላቸው ቃለ-ምልልስ ቢን ላደንን እዚያው ፊት አፍንጫህን ላስ እንጹሉት ተናግረዋል::

*«ይኼ ፈጽሞ ተቀባይነት የሌለው ሀሳብ ነው ስል ምክሬን ነግሬው ነበረ፤»*

ይሁን እንጂ ሪቻርድ ክላርክ የተባለው በክሊንተን አስተዳደር ውስጥ የሽብርተኝነት ጉዳዮች ኢክስፐርት የነበረ ሰው ግን በዚህ ጉዳይ ላይ ሲጠየቅ፣

> *«ቱርኪ በወቅቱ ቢን ላደን የኮምዩኒስት አስተዳደር ዘይቤን ይከተል የነበረውን የደቡብ የመንን መንግሥት ለመጣል ይቻል ዘንድ በሐይማኖት አክራሪ የሆነ አንድ ቡድን እንዲያደራጅ ራሱ ጠይቆት ነበረ::»* ሲል ምላሹን ሰጥቷል::

በሌላ በኩል ደግሞ በ CIA ውስጥ በመካከለኛው ምሥራቅ ጉዳዮች ላይ ስፔሻሊስት የሆነው ስቲቭ ሬቨል ሲናገር ደግሞ፣

> «የሳውዲው ንጉሣዊ አገዛዝ በእርግጥም በየመን የነበረውን የኮምዩኒስት መንግሥት ለመጣል ፈልጎ ነበረ:: ቢሆንም የግል ጦር ይህንን ግዳጅ እንዲያከናውንለት ግን መፍቀድ አልፈለገም::»

ብሏል::

ለማንኛውም በዓል-ቃይዳው መሪ እና በሳውዲው ደህንነት ሊቀመንበር መሀከል የነበረው ስምምነት ምንም ሆነ ምን ቀዝቃዛው ጦርነት ሲያበቃ ግን ተጻፍኖ የቀረና መልስ ያልተገኘለት ሆነ:: ይህም የሆነበት ምክንያት በ 1982 ላይ ደቡብና ሰሜን የመን ፍፁም ሰላማዊ በሆነ

መልኩ ዳግም ውህደት በመፈፀማቸው ነው። ይህ ለሳውዲው ንጉሣዊ አገዛዝ የሚዋጥና ተቀባይነት ያለው ቢሆንም ቢን ላደን ግን ኮምዩኒስቶቹ ከሰሜኑ ጋር እንዲቀላቀሉ የሚፈቅደው ይህ ዐይነቱ ውህደት አላስደሰተውም። በመሆኑም የሳውዲ መንግሥት ፈቃድና ይሁኝታን ሳያገኝ በግሉ አማጺያኑን ፈንድ ማድረግ ጀመረ። ነገር ግን ንጉሣዊውን አገዛዝ በዚህ መልኩ በእምቢተኝነት መጋፈጡ እጅግ ኃይለኛ የሚባል አፀፋን አስከተለ። የሳውዲው የአገር ውስጥ ጉዳይ ሚ/ር ልዑል ናይፍ ኢብን አብደል አዚዝ የተባሉትና የንጉሱ ወንድም የሆኑት ባለስልጣን ቢን ላደንን ወደ ቢሮቸው አስጠርተው ማንኛውንም እንቅስቃሴውን እንዲያቆም በቃላት ቁጣ አዝዘውት ፓስፖርቱንም ነጠቁት።

# የባሕረ ሰላጤው ጦርነት

የኾነው ሆኖ ግን ቢን ላደን በዚህ ከሳውዲው መንግሥት ይፋዊ በሆነ መልኩ የተሰጠውን ቁጣ-አዘል ማስጠንቀቂያ ብዙ ሊያስብበት ከመቻሉ በፊት አንድ ሌላ መጥፎ ገድ ያለው ቀውስ ደግሞ ተፈጠረ። ሐምሌ 26 ቀን 1989 ላይ ሳዳም ሁሴን በሳዑዲ ዓረቢያ ሰሜናዊ ድንበር ላይ እና በፋርስ ባሕረ ሰላጤው አናት ላይ የምትገኘዋን ትንሿን ኩዌትን ወረሩ። ሳዳም ይህንን ያደረጉት በሀብት እጅግ ተጥለቅልቆ የነበረው የኩዌት ኤሚሬት መንግሥትና የሥርዓቱ ባለሟሎች ኢራቅ ከኢራን ጋር ባደረገችው ጦርነት የተነሳ ከፍተኛ ዕዳ ገጥሟት እያለ ከእነሱ የተበደረችውን ዕዳ አንሰርዝም በማለታቸው ከዚያም በተጨማሪ ደግሞ በኢራቅ የነዳጅ ማምረቻ ቦታዎች ከሚገባው በላይ ዘልቀው ገብተው በመቆፈር የነዳጅን ዋጋ ሆን ብለው በማውረድ ሊያከስሩን ነው በማለት ነው። በዚህ ወቅት ከሳዳም ወደ ግማሽ ሚሊዮን ያህል የሚጠጋ

ጦር ውስጥ 100,000 የሚሆነው ለሳውዲ እጅግ ከፍተኛ ስጋትን ፈጠረ። ሳውዲ ለሕዝቧ መኖሪያ ቦታዎችም ሆነ ለነዳጅ ቁፋሮ ይዞታዎቿ ከዚህ ጦር ከለላ መስጠት አትችልም፣ ለምን ቢባል እጅግ በጣም አነስ ያለ ጦር ብቻ ነው ያላት።

ኦሳማ መሐመድ ኢብን ቢን ላደን በአፍጋኒስታን የሶቪየት ኅብረትን ግዙፍ ጦር ተጠራርጎ በመውጣቱ ኩራትና የድል ስሜቱ ገና በውስጡ ይንቦገቦግ ነበረና ወደ ሳውዲዎቹ በድጋሚ ቀርቦ እጅግ የተወገዘውን የሳዳም ሁሴንን አምባገነናዊ ሥርዓት ጦር ላስወጣላችሁ ብሎ ይጠይቃል።

«አንድ ነገር አስተውሉ እንጂ! እኔ እኮ በሳውዲ ዓረቢያ ምድር ብቻ 40,000 የሚሆኑ ሙጃሂዲኖች አሉኝ። ከዚያም በላይ ደግሞ በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ ቁጥራቸውን ወደ 100,000 ላሳድገው እችላለሁ!»

በማለት ጉራ የመንዛት ያህል ተናገረ። ልዑሉ ቱርኪ በወቅቱ በቢን ላደን ላይ ያስተዋሉትን የባሕሪ ለውጥ በሚከተለው መልኩ ገልፀውታል።

> *«እኔ እውነት ለመናገር በዚያ ሰው ላይ አንዳች ለውጥ ነው የተመለከትኩት። ቀደም ሲል እኮ ሐይማኖታዊ መቆርቆር በሚመስል መልኩ ብቻ ሙስሊሞችን እንርዳ የሚል ሰው ነበረ። አሁን ግን ግዙፍ ጦር አደራጅቼ ኩዌትን ከሳዳም ላስጥል የሚል አደገኛ ጠረኛ ሆኖ ነው የመጣው። ያን ጊዜ ትዕቢትን ነው የተመለከትኩት።»*

ቢን ላደን ሶቭየት ኅብረትን ከአፍጋን ጠራርጎ በራሱ ጦር እንዳስወጣ አድርጎ ይቁጠረው እንጂ ሃቁ ግን የሱ አፍጋን አረቦች በዚያ ፍልሚያ

ወቅት የነበራቸው ክህሎት፣ ብቃትና የተሳትፎ መጠን በከፍተኛ ደረጃ የሚያጠራጥር መሆኑ በተለያዩ አማኞችና መረጃዎች ተረጋግጧል። የሱ ሙጃሂዲኖች ወኔው እና ድፍረቱ እንጂ ሌላ ታክቲካዊ፣ ስትራቴጂካዊም ሆነ ሞያዊ ክህሎትና ዲሲፕሊንን በሚገባ ያልተላበሱ፣ በሌላው ጦር ተውጠውም የማታ ማታ በተገኘው ድል የተኩራሩ ናቸው። ይህ በሚገባ የሚታወቅ በመሆኑም የሳውዲው መንግሥት በነዚህ በአጉል እምነት ብቻ የተኩራሩ በሚመስሉ የቢን ላደን ወታደሮች ላይ መመካት የቱን ያህል ሞኝነት እንደሚሆን አላጣውም። በመሆኑም የሁል ጊዜ አጋሩን አሜሪካን እርዳታ ጠየቀ። አሜሪካም ለሳዑዲው ንጉሣዊ አገዛዝ ፈጥና በመድረስ ከ100 ሰዓታት ባነሰ ጊዜ ውስጥ ብቻ ከበድ ያለ የአየር እና የምድር ውጊያ በመፈፀም የሳዳምን ጦር ጠራርጋ ከኩዌት አስወጣች።

## ስደት

ቀደም ሲል በደቡብ የመን ኮምዩኒስቶቹን ለመገርሰስ ከፍተኛ ፍላጎት ኖሮት ለአገሩ መንግሥት ባቀረበው የእርዳታ ጥያቄ ባገኘው የእምቢታ መልስ አዝኖ የነበረው ኦሳማ ቢን ላደን አሁን ደግሞ ይኸው መንግሥት ጭራሽ እሱን ጥሎ ወደ አሜሪካ በመሮጥ ድል አግኝቶ ሲያሳፍረው ቂሙና ጥላቻው እየጨመረበት መጣ። በተለይም «እምነቷን የካደች» (apostate) የምትባለው አሜሪካ የላከቻቸው ወታደሮች ለዚያውም ነቢዩ መሐመድ ባንድ ወቅት እንደረገሚት በምትታወቀዋ በቅዱስ አገሩ ሳውዲ ዓረቢያ ምድር ለዚያውም በወታደር ጫማ መርገጣቸው ከፋኛ አንገበገበው። ቢን ላደን በዚህ ወቅት በኋላ እንዳወጀው፣

*«የሳውዲው መንግሥት ከሀዲዎችን ሊከላከልና ሰፊውን ሙስሊሙን ማኅበረሰባችንን በሃይማኖታችን ሕግ ሊታደግ ይቅርና ራሱም ቢሆን ከከሀዲዎቹ የማይተናነስ ነው!»*

የሚል አቋም ገና ባያዳብርም አሁን ያየው ነገር ግን ቀስ በቀስ ወደዚያ እየመራው መጣ:: ይህ በእንዲህ እንዳለም በገዛ ፈቃዱ ስደት ለመሄድ ወሰነ:: ነገር ግን በደቡብ-ሰሜን የመን ውህደት ጦስ የተነሳ የተነጠቀውን ፓስፖርቱን በእጁ ማስገባት ካልቻለ ከአገር እንዴት ይወጣል? በዚህ ወቅት ስለ ቢን ላደን ከተነገሩት ነገሮች አንዱን ብናይ በአፍጋኒስታን ጦርነት የተነሳ ተፈናቃይ የሆኑ ወገኖችን ለመርዳት ወደ ፓኪስታን መሄድ ይችል ዘንድ ፓስፖርት እና የመውጫ ቪዛ እንዲሰጠው ጠየቀ ይላል:: ሌላኛውን እንዲሁ የቀረበ ነገር ብንመለከት ደግሞ በአፍጋኒስታኑ የእርስ በርስ ጦርነት የማስማማትና የመሸምገል ሚና ለመጫወት ይችል ዘንድ እንዲሄድ ፈቃድ ጠየቀ ይላል:: አሁንም ሌላ ስለ ቢን ላደን የተወራ የወቅቱ ነገር ደግሞ ወደ ፓኪስታን ሄዶ በዚያ የነበሩትን ሀብቶች በሙሉ ሰረዘ ይላል:: እንግዲህ ከእነዚህ ሁሉ እርስ በርሳቸው ከሚቃረኑት ታሪኮች መረዳት የሚቻለው የቅርብ ጊዜው የቢን ላደን ታሪክ እንኳን የቱን ያህል አወዛጋቢና እንቆቅልሽ የበዛበት መሆኑን ነው:: የሆነው ሆኖ ግን የማያከራክረው ነገር የሳውዲ መንግሥት ቢን ላደን ምንም ሰበብ ፈጥሮ ሆነ ምንም «ፓስፖርቴን እና የመውጫ ቪዛ ስጡኝ!» ብሎ ሲጠይቀው በደቡብ የመን የነበረው ስጋት ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ በመወገዱ፣ ትምክህተኛው የሳዳም ጦርም ዕድሚ ለአሜሪካ ከኩዌት በመልቀቁ አሳማ ምንም ሊያመጣ የሚችለው ጉዳት ስላልታየው ጥያቄውን መቀበሉን ነው:: ቢን ላደን ፈቃዱን አግኝቶ ከአገሩ ወጥቶ ወደ ፓኪስታን ተጉዞ ፔሽዋር ሲደርስ ግን በዚያ

የነበረው የአረብ ጦር እንደተድሞው ለሱ የሚታዘዝና በቀላሉ ሊቆጣጠ ረው የሚችል ዐይነት እንዳልሆነ ተረዳ። ሶቪየት ኅብረት ለቃ ከወጣች በኋላ በአፍጋኒስታን የተፈጠረውን የስልጣን ክፍተት ለመሙላት ሔክማታር ከተባለው ጦር ጋር ተቀላቅሉ እየተፋለመ መሆኑን ነው ያወቀው።«

ይህ በእንዲህ እንዳለ በ1989 ዓ.ም ኮሎኔል አህመድ ኦማር ሐሰን አል በሽር በመፈንቅለ መንግሥት ስልጣን ለመያዝ እያናወጧት ወደሚገኙባት ሱዳን ከቤተሰቡ ጋር ለማቅናት ነው ቢን ላደን የወሰነው። በዶ/ር አል-ቱራቢ እርዳታ ኮ/ል ኦማር አል-በሽር በትረ ስልጣኑን ተረከቡና አገሪቱን ወደለየላት አምባገነናዊ እስላማዊ አስተዳደር ቀየሯት። ቢን ላደን ከፓኪስታን ከመውጣቱ በፊት ግን አስቀድሞ እዚያ ያለውን አጥሬሽኑን ቀየረ። ስለዚህ ጉዳይ ምስክርነት ሲሰጥ አሳማ ፋሽዲ የተባለው ግብረ አበሩ፣«

> *«ወደ ሱዳን ከመጓዙ ቀደም ብሎ ግን አሳማ በፓኪስታን ሁሉም ነገር መጠናቀቁን አረጋገጠ። ወቅቱ 1992 ነበረ። በፔሻዋር ሁሉንም ነገር ሸጡና ዓል-ቃይዳ ተጠናቋል አሉ። ይኼንን ባይኔ አይቻለሁ። የፓኪስታኑ መንግሥት በአረቦቹ ላይ ጠንከር ያለ ዱና ፈጠረ። በመሆኑም አብዛኞቹ ሳውዲዎች ወደ አገራቸው ተመለሱ። አንዳንዶቹ ወደ ቦዝኒያ ሄዱ። በመሠረቱ አሳማ ቢን ላደን ወደ ቦዝኒያ፣ ቼቺኒያም ሆነ ሌላ ቦታ እንዲሄዱ አላዘዛቸውም። በሰላም ወደ አገራቸው መመለስ የሚችሉትን ግን ተመለሱ አላቸው። ችግሩ*

*የመጣው አንዳንዶቹ በቀላሉ ወደ አገራቸው መመለስ የማይችሉት ላይ ነው። ቢን ላደን ደግሞ ሊተዋቸው አልፈለገም። ኃላፊነት እንዳለበት ተሰማው።»*

ብሏል። እንግዲህ ቢያንስ አንዳንድ በዚህ መልኩ ኃላፊነት ወስዶ ልርዳችሁ ያላቸው አፍጋን አረቦች ተከትለውት ወደ ሱዳን ሄዱ። ቢን ላደን በዚህ ወቅት እነዚህን ሰዎች የሚኖሩበት፣ የሚጠለሉበትን ሁኔታ ከማመቻቸት የዘለለ ነገር እንዲኖር ባይፈልግም ቀስ በቀስ ግን ዓል-ቃይዳን አጠናክረውና ለየት ባለ መንገድ አብረውት ይመሰርታሉ።«ቢን ላደን ለምን ወደ ሱዳን እንደተጓዘም ሆነ እዚያ ሄዶ ምን እንደሰራ ግን እርግጠኛ ሆኖ መናገር ያስቸግራል። ሎውረንስ ራይት እንደሚሉን ከሆነ የሱዳን መንግሥት በ1997 በደብዳቤ ጠርቶ እዚያ እንዲኖር ጋበዘው። ሱዳኖች ቢን ላደን በዚያች በእውነተኛው ሸሪያ በምትመራው አገር ውስጥ ደህንነቱ ተጠብቆ መኖር እንደሚችል ብቻ ሳይሆን ለሱ ግሩፖች የተለያዩ የኮንስትራክሽን ጨረታዎችን ሊሰጡት እንደፈቀዱም ጭምር ነግረውታል። ደብዳቤ ጽፈው ጠሩት የሚባለውን የሎውረንስን ግምት ሌሎች ምንጮች ላይ ባናገኘውም የሱዳን መንግሥት ግን ለቢን ላደን ግሩፕ የሳይድ ወደብን ግንባታ ጨረታ መስጠቱ ተረጋግጧል። የቢን ላደን ቤተሰብ እጅግ አስቸጋሪና ደፋር የነበረ ልጁን ወደ ሱዳን የላከው ባንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ እንዲመታለት በማሰብ ነው። ባንድ በኩል ቤተሰቡ በሱዳን ላሉት ስፋፊ ፕሮጀክቶች ታማኝ የቅርብ ሰው ይፈልጋል፤ በሌላ በኩል ደግሞ ልጁ እጅግ ሞገደኛ እና አለሁ አለሁ ባይ በመሆኑ በሚፈልገው የለየለት በሸሪያ በሚመራ አገር ውስጥ ደስተኛ ሆኖ እንዲኖር በማሰብ ነው። ነገር ግን የቤተሰቡ ፍላጎት

በእርግጥ ይህ ቢሆን ኖሮ ግን ቢን ላደን በኋላ ከፈፀመው ነገር አንፃር ባንድ ድንጋይ አንድ ወፍ እንኳን ሳይመታ መቅረቱ ነው የሚረጋገጠው።

እንግዲህ ቢን ላደን በምንም ተነሳሳ በምን ካርቱም ውስጥ ለጊዜው መቆየትን መረጠ። ምናልባት አንዳንድ የአፍጋን ዝርያ ያላቸው ዓረብ ደጋፊዎቹን እሱ እዚያ ከመድረሱ በፊት ቤት እና የእርሻ ቦታ ተከራይተው እንዲጠብቁት አድርጎ ሊሆን ይችላል። በመቀጠል ቢን ላደን ከአራት ሚስቶቹ እና ከብዙ ልጆቹ ጋር በመሆን ወደ መዲናዋ ካርቱም በመግባት ቢሮ ከፍቶ ከከተማዋ ወጣ ባለ ቦታ ላይ ደግሞ እርሻ ቦታ አገኘ። በዚህ ወቅት የፈለገው አንዳንዶች እንደሚሉን በእስልምና ሕግ በምትመራ አገር ውስጥ ደስተኛ ሆኖ መኖርን ወይንስ ሌሎች እንደሚሉን የበሳለጡ የጂሀድ እንቅስቃሴዎችን ለማድረግ እንዲረዳው ጥሩ መሰረትን በአዲስ ቦታ ላይ ማግኘት ነው?«

ብቻ የሳዑዲው ሚሊየነር ቢን ላደን ምንም አስቦ ይሁን ምን ብዙም ሳይቆይ የጂሀድ ጥሪ ለማቅረብ ተገደደ። የአካባቢው ሁኔታ ደግሞ ዕንፈኛ ተግባሩን የሚያበረታታ ኾነ። በ1980ዎቹ መጀመሪያ ላይ ሱዳን ከተለያዩ የዓረቡ ዓለም አገራት ሸሽተው ለሚመጡ አክራሪዎች መጠለያ ትስጥ ነበረ። በዚህ ወቅት ቢን ላደን የተቀላቀላቸው ቡድኖች ከረር ያለና «የእስልምና መነቃቃት» ወይንም «አዲስ የእስልምና መንገድ» የሚልን ዓላማ ያነገቡ ሆኑ። ይህ ንቅናቄም በዘመናዊነት ለተደቀኑ የዓለም ችግሮች መፍትሄን በእስልምና ውስጥ የሚፈልግ ሲሆን የምዕራባውያንን አስተሳሰብም ሆነ ቀመር ግን ማካተት ፈጽሞ የማይሻ ነው። እነዚህ አክራሪ ወገኖች በምዕራባውያን የተሠሩ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ይጠቀማሉ ነገር ግን የምዕራቡን እሴቶች፣ ወጎችና አስተሳሰቦች ይጠላሉ። እንግዲ ከዚህ በመነሳት በተለይም እንደ ግብጽ ባሉት ጭቆና

በሙስሊሞች ላይ ይካሄድባቸው የነበሩትን ቦታዎች አስመልክቶ በግልጽ፡ «ሐይማኖታዊ ያልሆነው (secular) መንግሥት ተመራጭ አይደለም» በማለት ቀሰቀሱ፡፡ ይህንን ቅስቀሳ ተከትሎ በግብጽና በሌሎችም የነበረው ጭቆናና አፈና በጣም በማየሉ አክራሪነት ተፈጠረ፡፡ መንግሥታቱም ዐይናቸውን ጨፍነው ማጥፋት፡ መግደልና በሐይል መግዛትን በመያያዛቸው ሙስሊሙ ማኅበረሰብ ሲያንገሸግሸው ወደ ኃይል ዓመፅ ገባ፡፡ ነገር ግን በጣም የሚያሳዝነው በ 1970ና 80ዎቹ ከሕዝቡ ይልቅ አክራሪ የእስልምና ተፋላሚዎች በተለይ በመካከለኛው ምሥራቅ እየፈሉ መምጣታቸው ነው፡፡ አክራሪ ቢባሉም ብዙዎቹ ኃይልን አላራመዱም፡ አንዳንዶች ግን በሚከተሉት ከረር ያለና አደገኛ አቋም የሚፈልጉትን ለማግኘት ሲሉ በሴቶች፡ በሕፃናትና በሕዝቡ ላይ ኃይል ከመጠቀም ወደኋላ የማይሉ ሆኑ፡፡ ጅምላ ጥቃትም መለያቸው ሆነ፡፡ እነዚህ ቡድኖች በተናጠልም ሆነ ቢጋራ በገዛ መንግስቶቻቸው ላይ ብሎም መንግስታቱን በሚደግፏቸው አሜሪካ እና ሌሎች ምዕራባውያን ላይ አደጋ የደቀኑ ሆኑ፡፡

## በሽብር የተሞሉ አስር ዓመታት

ቀጣዩ የሽብር ጥቃት ዐይነ ስውሩ ሼህ ተብሎ የሚጠሩት ሼ አማር አብዱል ራህማን አሞኒየም ናይትሬት የተሞላ የጭነት መኪና ኒውዮርክ ከሚገኘው የዓለም ንግድ ማዕከል የመኪና ማቆሚያ ጋራዥ በታች ሲያፈነዱት ኾነ፡፡ ፍንዳታው ስድስት ሰዎችን ሲገድል በብዙ ሚሊዮኖች የሚገመት ንብረትም አውድሟል፡፡ ወንጀለኞቹ ደግሞ ወዲያው ሊያዙ ችለዋል፡፡ ይሁንና ቢን ላደን የሼሁን ቡድን በገንዘብ ሲደግፍ ቢችልም በጥቃቱ ላይ ግን ሲሳተፍ አልታየም፡፡ ወይ ደግሞ ከመጀመሪያውኑ

ስለሁኔታው የሚያውቀው ነገር የለም። በዚያው ዓመት ጥቅምት ላይ ደግሞ የሶማሊያ ዓመፀኞች ብላክ ሃውስ ሄሊኮፕተር መትተው ከጣሉ በኋላ፣ የወታደር ልብስ የለበሱ አድፋጮች የሄሊኮፕተሩን አባላት ከአደጋ ለመታደግ በሚል ሽፋን ተጠግተው የአሜሪካኖቹን ሙት ገላ በሞቃዲሾ መንገዶች ላይ ጐተቷቸው። ኋላም ቢን ላደን የአረብ እስላሞች በሶማሊያ ውስጥ ያደረጉትን ፍልሚያ እና የሄሊኮፕተሩን ተልዕኮ አስመልክቶ አድናቆቱን አቅርቧል። "ከአላህ ሞገስ ጋር" አለ ቢን ላደን በ1997ቱ ቃለ ምልልሱ "በሶማሊያ ውስጥ ያሉ ሙስሊሞች አፍጋኒስታን ውስጥ ከነበሩ በርካታ አረብ ተዋጊዎች ጋር ተባብረዋል። በጋራ ሆነውም ብዙ ቁጥር ያለው የአሜሪካን ቅጥረኛ ወታደሮች ገድለዋል።" እንደተለመደው፣ ቢን ላደን የአረብ ወታደሮችን ተሳትፎና ውጤቱን አጋኖታል። ይሁን እንጂ አረቦቹ ከአልቃይዳ ጋር ያላቸውን ግንኙነትና የእሱንም ክጥቃቱ ጋር የተያያዘ ልባዊ ተሳትፎ አስመልክቶ ያለው ነገር የለም። የሶማሊያ ተዋጊዎች ግን ሄሊኮፕተሯን በመጣሉ ተልዕኮ ውስጥ ያለውን የእሱን ተሳትፎ አይጠቅሱትም።

የዕንፈኛ አክራሪዎቹ ጥቃት በ1990ዎቹ አጋማሽ ውስጥም የቀጠለ ቢሆንም ቢን ላደን ግን በርግጠኝነት ከየትኛውም ጥቃት ጋር ተያይዞት የለውም። በ1995 የሳሁዲ አሸባሪዎች፣ ሪያድ ውስጥ የሚገኘውን የሳዑዲ ብሔራዊ የመከላከያ ማሰልጠኛ ላይ ቦምብ ጥለው እዚያ የታሰሩት አምስት አሜሪካዊያን ገደሉ። ኋላም በሳዑዲያውያን የተያዙት አራት አሸባሪዎች ለፍርድ በቀረቡበት ወቅት የቢን ላደን መግለጫ ተፅዕኖ ፈጥሮባቸው እንደነበር አምነዋል። ይሁንና ለማዕከላዊው የአሜሪካ ስላለ ድርጅት ተንታኝ ለብሩስ ሬዲዮስ በሳዑዲ የመረጃ ሰራተኞች የተሰጠው ምስጢራዊ

መረጃ እንዳመለከተው በዚህ ጥቃት ውስጥ ቢን ላደን በግሉ አልተሳተፈበትም:: ሆኖም የአሸባሪዎች የፈቃድ ወረቀቶች እንደሚያሳዩት አልቃኢዳ ሙሉ በሙሉ የራሱን ተልዕኮ በሚያስተባብርበት ሰዓት ሴሎችን ለተግባር ለማነሳሳት እንደ ርዕዮተ ዓለማዊ ንቅናቄ የሚጠቀምበት ነው:: በቀጣዩ ዓመት ደግሞ አሸባሪዎቹ፣ በሳዑዲ አረቢያ የዳህራን አየር ኃይል ቀጠና ውስጥ የሚገኘውንና የዩናይትድ ስቴትስ የወታደሮች መኖሪያ የሆነውን ዳሃራን ማፈንዳት መኪና ላይ በተጠመደ ቦምብ ተጠቅመው 19 አሜሪካውያንን ገደሉ:: አሁንም ቢን ላደን ግንባር ቀደምትነት ተጠርጣሪ የነበረ ሲሆን ኋላ ላይ ሱማሊያውያን እንዳሉት እሱ አሁንም ይህንን ተልዕኮ ያደነቀ ቢሆንም (በምርመራው ስራ ውስጥ ተባባሪ እንደነበረው ራይድል ከሆነ) በድርጊቱ ውስጥ ግን ተሳታፊ አልነበረም:: በ1995 ደግሞ የዛዋሪ አልጅሃድ ቡድኖች፣ አዲስ አበባ ኢትዮጵያ ውስጥ በግብፅ ፕሬዚዳንት ሆስኒ ሙባረክ ላይ የግድያ ሙከራ አደረጉ:: ቢን ላደን በሁኔታው የተስማማ ቢሆንም በድርጊቱ ውስጥ ግን የተሳተፈ አይመስልም::

ቢን ላደን ወደ ሱዳን የሄደበት ዓላማ ምንም ይሁን እገር አልባው ሰው እዚያ መኖሩ ግን የአሳማን የጅሃድ ዓላማ አጠናክሮለታል:: በ1994 መጀመሪያ ላይ ቢን ላደን ሶማሊያን፣ ኬንያን፣ የመንን፣ ግብፅን ሊቢያን እና ፓኪስታንን ጨምሮ በርካታ አገራት ውስጥ አዳዲስ የአልቃይዳ ሴሎችን ገነባ:: በሳዑዲ መንግስታዊ አገዛዝ ላይ ያለውን ትችትም አባሰው:: ለረጅም ጊዜያት በንጉሣዊ ቤተሰብ ሲደገፍ የቆየው የቢን ላደን ቤተሰብ በመጀመሪያ ከአስቸጋሪው ወንድማቸው ራሱን ያራቀ ሲሆን በየካቲት 1994 ደግሞ ልጅነቱንም ካደ:: "እኔ አራሴና ከሃምሳ የሚበልጡ ሁሉም

የቤተሰቡ አባላት፣ እኛ የማንቀበለውንና የማንስማማበትን የኦሳማ ጠቅላላ ባህርይ አስመልክቶ ያለንን ተቃውሞና ውግዘት ለመግለፅ እንወዳለን።" ሲል የቤተሰቡ መሪና ታላቅ ወንድሙ የሆነው በክር ቢን ላደን አስታውቋል።

*"ምንም እንኳን ኦሳማ ከሳውዲ አረቢያ ግዛት ውጭ የሆነ ቦታ ላይ ተወስኖ እየኖረው ነው እንደተባለ፣ ከሁለት ዓመታት በላይ ወደ ትክክለኛው መንገድ ይመለስ ዘንድ ልንለምነው ሙከራ ያደረግን ቢሆንም ከዚያ በኋላ ግን ለመግለጫዎቹ፣ ደድርጊቶቹ እና ለባህሪው ብቸኛ ተጠያቂ እንደሆነ አድርገን ወስደነዋል እውነት እነዚህ ነገሮች ሁሉ ከእሱ የመጡ ከሆኑ።"* ብሏል።

በተጨማሪም ቢን ላደኖች አስቸጋሪው ዘመዳቸው ከቢን ላደን ቤተሰብ አባላት ጋር ትርፍ የመካፈሉ ነገር እንዲቋረጥ ማድረጋቸውን ገልፀዋል። ለቤተሰቡ ቢዝነስ መጥፎ መሆኑ የማይካድ ነው። ለገንዘብ ከእነሱ የማግኘቱን ነገር ስለማቋረጣቸው ማረጋገጫ ግን የለም። ቢን ላደን ለገንዘብ ጣጣ እንዳልነበረው ደግሞ ምንም ጥርጥር የለውም። ጥቂት ሀብቱን በአፍጋኑ ጅሃድ ላይ፣ እንደ በርካቶች ግምት የበዛውን ደግሞ ሱዳን ውስጥ አጥፍቷል። ይሁን እንጂ በሱዳን ያለ ስራ ቤሰተቡን ለመርዳት፣ ብሎም ወደ አፍጋኒስታን ለማሸጋገርና እዚያ ሆነው ለመደገፍ ሁሌም በቂ ገቢ ያለው ይመስላል። በተጨማሪም ወደ ድህነት ቢያሽቆለቁል ኖሮ ሊሞክር የማይችለውን አልቃይዳን የመምራት ስራውን ቀጥሏል። በ1996 ወደ አፍጋኒስታን ሲሰደድ የአገሬውን ሼሆች በስጦታ ለማንበሽበሽ በቂ

ገንዘብ ነበረው ይህ መረጃ የሚያመለክተው፣ እነሱ በተቃራኒው የፈለጉትን ይበሉ እንጂ ቢን ላደኖች ሙሉ በሙሉ የእሱን ገቢ እንዳላቋረጡበት ነው፡፡

የገዛ ቤተሰቡና የሳዑዲ ባለስልጣናትም ቢሆኑ የሱን የተጠላ ባህሪና የሚያስቆጣ ንግግር ችላ በማለት ሊዘልቁ አልቻሉም፡፡ ወንድሙ በከር መግለጫውን በሰጠበት በዚያው ወር የታጠቁ ሊቢያውያን ካርቱም ውስጥ የሚገኘውን የቢን ላደን ቤት አቀጣጠሉት፡፡ ለደረሰው ጥፋት ሲ.አይ.ኤን ተጠያቂ ቢያደርግም ከድርጊቱ በስተጀርባ ያለው እውነተኛው አጥፊ ግን የሳዑዲው የመረጃ አካል ሳይሆን አይቀርም፡፡ ይሁንና የመረጃ አካሉ ደግሞ ተሳትፎውን አስተባብሏል፡፡ አልፎ ተርፎም መጋቢት 1994 የሳዑዲው ሙፍቲ (ሃይማኖታዊ መሪ) ለሼህ አብዱል አዚዝ ቢን ባዝ መራና ትችታዊ ደብዳቤ ፃፈላቸው፡፡

ደብዳቤው ሼሁን የሚቃረኑ ያንድ የልብስ ጥበት አገልገሎት ስጪ ድርጅት ስምታዎችን በውስጠ ወይራ ደግሞ አጠቃላይ ንጉሣዊ አስተዳደሩን የሚቃወም ጉዳይ አካቶ ይዟል፡፡ ቢን ላደን ንጉሣዊ አስተዳደሩ ማድረግ የሚፈልጋቸውን ነገሮች ለማድረግ ይረዳው ዘንድ የሚያሳምንበትን ፋትዋዎች (ሀይማኖታዊ አዋጆች) መውጣት አንስቶ ቢን ባዝን ይከሳቸዋል፡፡

በተለይ ደግሞ ከአይሁዳውያን ጋር የተደረገውን የሰላም ጥሪ አስመልክቶ ያለውን ፋትዋ (አዋጅ) ይነቅፋል፡፡ ለዓይነተኛ ውግዘት ነጥሎ ያወጣቸው ጉዳዮች ደግሞ፣ የሳዑዲው ሃይማኖታዊ መንግስት እሱ እንደ

ኮሚዮስት ለሚያየው የየመን መንግስት ተመልሶ ትብብር ለማድረግ ፈቃደኛ መሆኑና በተለይ ደግሞ "ለአይሁዳውያንና ለመስቀል ጦረኞች ወራሪ ኃይሎች (አሜሪካውያንና ተባባሪዎቻቸው) አገሪቷን ክፍት የማድረግ ውሳኔን የሚመለከቱት ናቸው::" "በእግዚአብሔርና በመልዕክተኞቹ ላይ ጦርነቱ የከፈቱ ከሃዲ መሪዎች በሙስሊሞች ላይ ሕጋዊነትና ሉዓላዊነት የላቸውም::" ብሎ ቢን ላደን በግልፅ ሲናገር ምናልባትም ይህ የመጀመሪያው ጊዜው ሳይሆን አይቀርም::

ሳዑዲዎቹን ከመናደዱ በተጨማሪ ቢን ላደን የዩናይትድ ስቴትስን ትኩረትም ስቧል:: አሜሪካንና በመቃረን ምንም ዐይነት የሽብር ጥቃት አይፈፀም እንጂ እጅግ በርካታ ከሆኑ አሸባሪ ቡድኖች ጋር ባለው ግንኙነትና ለሚፈፅሙት ጥቃትም በሚያሳያቸው ሐይማኖታዊ ማፅናኛ ዋሽንግተን ውስጥ ጭንቀት ፈጥሯል:: በዚያውም የሱዳን መንግስት ለፅንፈኞች ባለው የክፍት በር ፖሊሲው ላይ ተራራ የሚያህል ትችት ተጋፍጧል::

በ1996 ፀደይ ወቅት የተባበሩት መንግሥታት የፀጥታው ምክር ቤት በካርቱም በሚገኘው መንግሥት ላይ ውሳኔ አሳልፏል::

*አሸባሪዎችን ከመርዳት፣ ከማገዝና እንቅስቃሴአቸውን ከማመቻቸት እንዲሁም ለመሪዎቻቸው መጠለያና መሸሸጊያ ከመስጠት ተግባር በመታቀብ ከአሁን በኋላ ከጎረቤትና ከሌሎችም ሀገራት ጋር*

*ያለውን ግንኙነት ሙሉ በሙሉ ከተባበሩት መንግሥታት ከአፍሪካ አንድነት ድርጅት ቻርተር ጋር በተስማማ መልኩ እንዲያካሄድ።*

በተጨማሪም ከካርቱም ጋር ያላቸውን ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት እንዲቀንሱ ውሳኔው ለሁሉም አባል አገራት ተላልፏል። አለማቀፋ ግፊት የራሱ ተፅዕኖ ነበረው። በዚህ የተነሳም ሱዳኖች ቢን ላደን ወደ ሃገሩ ይመለስ በሚል ሳዑዲያውያኑን ጠየቁ። ለአመፀኛ ንግግሩ ይቅርታ ከጠየቀና የዕንፈኝነት ተግባሩን ካቆመ እኛ ምን ገዶን ሲሉም ሳዑዲያን ተስማሙ። እርሱ ግን ሳይቀበለው ቀረ።

## የታሊባን እንግዳ

ኦሳማ ቢን ላደን በአስር ዓመታት ውስጥ ቤት አልባ ሲሆን ይህ ለሁለተኛ ጊዜው መሆኑ ነው። የትኛውም አገር "አለሁ" ብሎ እሱን ለመቀበል ፈቃደኛ አይደለም፣ ካንዲት አፍጋኒስታን በስተቀር። ከዓመታት የርስ በርስ ጦርነት በኋላ አክራሪው ታሊባን የአገሪቷን ዘጠና በመቶ ተቆጣጥሮ ይዟል። የቡድኑ መሪ የሆነው ሙላህ መሐመድ ኦማር ፍፁምነት የቀረበ ስልጣን በእጁ አስገብቷል። ሐይማኖታዊ ቁጥጥሩ ደግሞ በመላው አገሪቱ ውስጥ የአስጨናቂ አገዛዝን ስሜት አስፍኗል። ወንዶች ረጃጅም እንዲያገለድሙ ይወተወታሉ ሴቶች ደግሞ ባደባባይ ሲሆኑ ከራስ እስከ እግራቸው ድረስ በቡርቃስ እንዲሸፈኑ። ይህ እርምጃ ከቢን ላደን የሙስሊም ጥራቅ (ንፅህና) አስተሳሰብና እምነት እንኳን ልቆ የሚሄድ ነው። ቢሆንም እሱና ሙላህ ኦማር ስለጅሃድ የጋራ አመለካከት

ያላቸው ሲሆን ለምዕራባዊያን ያላቸውን ከፍተኛ ጥላቻም የሚጋሩ ናቸው። እሁንም የቢን ላደን የማይናቅ ሀብት፣ ሶቭየትን ለመቃወም እንደተደረገው የአፍጋኑ ጦርነት ወቅት ሁሉ ዛሬም የተከበረ እንግዳ እንዲሆን አደረገው። ወደ አገሪቱ የመሻገሩን ነገር አመቻችናም ደግሞ የታሊባኖችን ነቃሽ ወቃሾች አዳዲስ አውቶሞቢሎችን በመሳለሉ ተወዳጅ ስጦታዎች አባበላቸው። ይህ ስጦታ ቢን ላደን ከበቂ በላይ የሆነ ገንዘብ እንደነበረው በግልፅ የሚያሳይ ነው። ከቤተሰቡ ሃብትም ይሁን ወይ ከእያንዳንዱ አባላት፣ አልያም ደግሞ ከአልቃይዳ ምንጮች፣ ምናልባትም ደግሞ ከሶስቱም። እናም ግንቦት 1996 አሳማ ቢን ላደን ከቤተሰቡ ጋር ከሱዳን ለቀቀና ከንደሃር አጠገብ ወደሚገኘው ህንፃ ተንቀሳቀሰ።

የታሊባን መሪዎችም ከሱዳን ተገዶ እንዲወጣ አድርጎት ከነበረ ባህሪው ይታቀብ ዘንድ ጠየቁት ከእሱ ጋር በመርህ ደረጃ የቱንም ያህል የሚስማሙ ይሁን እንጂ በሱዳን ላይ ከሆነው በላይ የምዕራባውያኑ ብስጭት የሚያስከትለውን ሳንካ ግን አይፈልጉም። እንዲያም ሆኖ ሙላህ አማርና ተከታዮቹ አፍጋኒስታን ውስጥ ስልጣን ከማጠናከር ይልቅ ዓለም አቀፍ ጅሃድ የመክፈት ፍላጐት ነበራቸው። ሆኖም ለምናልባቱ ታሊባንን የሚረዳው የሳዑዲ መንግስት ቢን ላደንን ፀጥ አድርገው እንዲይዙት ጠይቀዋቸው ሊሆን ይችላል። ቢን ላደንም ለጊዜው የአስተናጋጆቹን ፍላጐት ያከበረ ቢሆንም ዝምታው ግን ዘልቆ ሊጓዝ አልቻለም።

# አይሁዳውያንና የመስቀል ጦረኞችን የሚቃወመው ፋትዋ

እስልምናን ለመከለከል የሚደረግን ፍልሚያ የነቢዩ አስተምህሮ ይፈቅዳል። ቢን ላደን ደግሞ ይህን አስተምህሮ የሚረዳው ሁሉም የሐይማኖቱ ጠላቶች ድል እስኪሆኑ ድረስ መታገልን የሚያመለክት የፍልሚያ ጥሪ አድርጎ ነው። ሳዑዲ አረቢያ እና ግብፅ እንዲሁም ጥብቅን የሼሪያ ሕግ የማይተገበሩ ሌሎች ሐይማኖት ከሃዲያን የሆኑ ሙስሊም መንግሥታት መመታትና መነቀል ይኖርባቸዋል። እንደገናም እነዚህን መንግሥታት የምትረዳው፣ የሙስሊም አገራትን ጥሬ ሃብት የምትበዘብዘውና በተለያዩ ዘርፍ ብዙ መንገዶች በሙስሊም ጉዳዮች ውስጥ ጣልቃ የምትገባው ዩናይትድ ስቴትስም ጭምር መመታት አለባት። ቢን ላደን ዩናይትድ ስቴትስን ለመጥቀስና እግረ መንገዱንም ለማስጠንቀቅ "የመስቀል ጦረኛ" እና "ፅዮናዊ የመስቀል ጦረኛ" የሚሉ ቃላትን ይጠቀማል። በእሱ አመለካከት (ከብዙዎቹ እስላማዊ ፅንፈኞች አመለካከት ጥምር) እስራኤልና አሜሪካ በዘላቂነት ተቆራኝተዋል።

ፅዮናዊያን የዩናይትድ ስቴትስን ፖሊሲ በሙስሊሙ ዓለም ላይ በኃይል ለመተግበር የሚንቀሳቀሱ ሲሆን እስራኤል ደግሞ በመካከለኛው ምስራቅ ውስጥ የእሷ መከታ በመሆን የምትሰራ ናት ሲል ቢን ላደን ይሟገታል። የቢን ላደን የጅሃድ ፅንስ ሀሳብ አንድምታ በሁለት ፋትዋዎች ውስጥ ምሉዕ እስከ መሆን ደርሶ ነበረ አንደኛው የ1996ቱ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በ1998 የወጣው ነው።

"የሁለቱ ቅዱሳን ስፍራዎች አገር ውስጥ የሰፈሩ አሜሪካውያንን የሚቃወም የጦር አዋጅ" የተሰኘው የ1996ቱ ፋትዋ ምዕራባውያንንና ቢን ላደን እንደ ዩናይትድስቴትስ ደንበኛ አድርጐ የሚመለከታት ሳዑዲ አረቢያን የሚቃወም የጥልቅ ቅሬታዎች ዝርዝር ነው። "በፅዮናውያን መስቀለኞች የጋራዊነትና ተባባሪዎቻቸው አማካይነት በሙስሊሞች ላይ የተጫነው ስቃይ፣ በደልና ኢ-ፍትሃዊ ድርጊት ከእናንተ የተሰወረ አይሆንም።" ሲል ይናገራል። በማከልም "ደብልጡን ደግሞ የሙስሊሞች ደም ደመከልብ ሆኗል። ሀብትና ንብረታቸው በምርኮነት ስም በጠላቶቻቸው እጅ ገብቷል። ደማቸውም በፍልስጥኤምና በኢራቅ ውስጥ ፈሷል።" ይላል። ቢን ላደን የጠቀሳቸውን ኢራቃውያን ጉዳተኞች በባህረ ሰላጤው ጦርነት ወቅት የሞቱት ሳይሆኑ በአሜሪካን መሽ የኢኮኖሚ ማዕቀብ የተነሳ መድሃኒትና ሌሎች አስፈላጊ ነገሮች ወደ አገር ውስጥ እንዳይገቡ መደረጉን ተከትሎ አብላጫው ዕድ ዓና የሆኑበትን ሲቪል ኢራቃውያን ዕልቂት ነው። ከሁሉም በላይ አንገብጋቢ የሆነው ጉዳይ ደግሞ ከሳዳም ሁሴን መስመርና ሳዳምን የመግደል ዛቻ ከተነገረ በኋላ የአሜሪካን ወታደሮች በሳዑዲ መሬት ላይ ለረጅም ጊዜ ለመቆየት መሻት ነው። በመሆኑም ቢን ላደን ወታደሮች ሳዑዲ አረቢያን ለቀው ይወጡ ዘንድ በአሜሪካ አቅርቦትና ፍጆታ ላይ አድማ የማድረግ ጥሪውን አቀረበ። ለመጀመሪያ ጊዜም ዩናይተድ ስቴትስ የእስልምና ቀንደኛ ጠላት መሆንዋን አወጀ።

*በአገሬቷና በሕዝቧ ላይ ለደረሰው ፍዳ አገዛዙ ሙሉ ለሙሉ ተጠያቂ ነው፤የሆነ ሆኖ ለሁኔታው መከሰት ዓይነተኛና ዋነኛ ምክንያት አሜሪካውያን ጠላቶቻችን ናቸው። ስለዚህ ትግሉ ማተኮር*

*ያለበት በአሳህ ድጋፍ፣ ጠላቶቻችን ሙሉ በሙሉ ድል እስኪሆኑ ድረስ ማውደም፣ መፋለምና መግደል ላይ ነው።*

የ1996ቱ ፋትዋ ርዕስና ይዘቱ እንደሚያመለክተው ቢን ላደን አሁንም በተዋጊዎችና ተዋጊ ባልሆኑት መካከል ልዩነት አድርጓል። በሳዑዲ አረቢያ በሚገኙ የአሜሪካ ወታደራዊ ሰራተኞች ላይ ጥቃት እንዲከፈትም ጥሪ አቀረበ። ሆኖም ጥሪው ሁሉንም የአሜሪካ ሕጋዊ ተቋማትና ከአረብ አገራት ውጭ የሚገኙ ወታደራዊ ሰራተኞችን አያካትትም። ይሁንና ጥቅምት 1998 በወጣውና "አይሁዳውያንና መስቀለኞችን የሚቃረነው ጅሃድ" በተሰኘው ፋትዋ ላይ እነዚህ ገደቦች ተነስተዋል። "በመስቀለኞችና ፅዮናዊያን ህብረት አማካይነት በተከሰተው ውድመት የተነሳ በኢራቅ ህዝብ ላይ መከራ ወድቋል፣ ይባስ ብሎም ቁጥራቸው ከአንድ ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ሰዎችም ተገድለዋል።" ሲል አዲሱ ፋትዋ ያስፋትን ምሬቶች ደግሞ በማውሳትና የኢኮኖሚ ማዕቀቡ ያደረሰውን የተጨማሪ የጉዳት ውጤት በማሳየት የአሜሪካንን ወንጀል ደማምሯል። ከዚያም ቢን ላደን ቀጣዩን ይናገራል።

*የአል-አቅሳንና የቅዱሱን የመካን መስጊዶች ከእነሱ ጥቃት ነፃ ለማውጣት ሲባል፣ ጦራቸውን ከሁሉም የሙስሊም ምድር ለማስለቀቅ ሲባል፣ ማንኛውንም ሙስሊም እነሱ ከሚያደርሱበት ስቃይ ለመከላከል ሲባል ሲቪሎችም ይሁን ወታደሮች ብቻ የትኞቹንም አሜሪካዊያንና ተባባሪዎቻቸውን የመግደሉ መመሪያ፣በማንኛውም አገር ውስጥ በማንኛውም መንገድ ይፈፀም ዘንድ ለማንኛውም ሙስሊም የተሰጠ የተናጠል ግዴታ ነው።*

በማንኛውም ጊዜና ቦታ ማንኛውንም አሜሪካዊ መግደል በሚለው ጥሪው የቢን ላደን አዲሱ ፋትዋ ከ1,000 ዓመታት በላይ ከሆነው የእስላማዊ የተገቢ ጦርነት ዕንሰ ሀሳብ፣ እንዲሁም ጦረኞች ያልሆኑትን እንዲለዩና ሴቶችንና ህፃናትን እንዲያድኑ ለሙስሊም ተዋጊዎች በነቢዩ መሃመድ አስተምህሮ ውስጥ ከወጣው መመሪያ ያፈነገጠ ነው።

አሜሪካውያንን በጅምላ ከመግደሉ ጥሪ በስተጀርባ ያለውን ሎጂክ ቢን ላደን በስተኒላ አብራርቶታል። ወታደራዊ ሰራተኞች ባነጣጠረው ጥቃት ላይ ከእነሱ ጋር የሚኖሩና የሚሰሩ ሴቶችና ህፃናት ጭምር ሰለባ ይሆናሉ ብሎ ቢን ላደን ባረጋገጠው ሲቪላውያንም የማተኮር ጉዳይ ላይ ዛዋሪም ቢሆን ይሰማማበታል። "ወታደራዊ ዩኒፎርም ባጠለቁና ባላጠለቁት መካከል ልዩነት አናደርግም። በዚህ ፋትዋ ሁላቸውም ተተኩረዋል።" ሲል ገልጿል።

*የአሜሪካን ታሪክ ሲቪሎችንና ወታደሮችን አይለይም ሴቶችንና ህፃናትን አንኳን። እነሱ ናጋሳኪ ላይ ቦምቦችን የተጠቀሙ ሰዎች ናቸው። እነዚህ ቦምቦች ህፃናትና ወታደሮችን መለየት ይችላሉ? አሜሪካ ሁሉንም ሰው ከማውደም የሚያቅባት ሐይማኖት የላትም።*

ይህ ያልተለመደ ዙሪያ ገብ ምክንያት የሂትለርን የጅምላ ጭፍጨፋ ሰበብ ያስታውሳል። ጀርመን በአይሁድ ዝርያ ላይ ባላት ጥላቻ የተነሳ ሞገደኛ ወደ ሆነ ጦርነት ገባች። ይህ ሁኔታም ፀረ ጀርመን ለሆነ ጠንካራ

ፖለቲካዊ ህብረት መፈጠር ሰበብ ሆነ። በዚህ ህብረት መፈጠር የተነሳም አይሁዳውያን ይብልጥ ተጠያቂና ተወቃሽ ሆነው ነበር። ቢን ላደን የ1998ቱን ፋትዋ ያወጣው "የዓለም እስላማዊ ግንባር" የሚል ደግሞ አዲሱ የአልቃኢዳ ስም ሊሆን ይችላል። ነገሩ ምንም ይሁን ብቻ "አልቃይዳ" ለቢን ላደንና ተከታዮቹ ድርጅት ዋነኛ ስያሜ ሆኖ ዘልቋል።

የቢን ላደን ፋትዋዎች በጦረኞችና ጦረኛ ባልሆኑ ሰዎች መካከል ልዩነት የማያደርገውን ዕድሜ ጠገብ የእስላም መመሪያ የሚቃረን ነው። ከዘጠኝ አስራ አንዱ ጥቃት በኋላ ቢን ላደን በዚህ ጉዳይ ላይ በተወሰነ ደረጃ ተናግሮ ነበር። በጥቅምት 2011 ቃለ ምልልሱ ላይ እንደገለፀው አሜሪካን ያለ ምንም ምክንያት የገደለቻቸውን ሰዎች ለመበቀል ሲል ነበር አልቃይዳ ሲቪሎችን የገደለው። "የንፁሃን ሲቪሎች ግድያ የሚለው የአሜሪካና የአንዳንድ ምሁራን አነጋገር በጣም እንግዳ የሆነ አነጋገር ነው" ሲል ይደመድማል።

የእነሱን ንፁሃን ዜጎች ስንገድል ከምስራቅ እስከ ምዕራብ ያለው መላው ዓለም እኛ ላይ ይጮሃል። የእነሱ ብቻ ነው? የእኛስ ደም፣ ደም አይደለም ያላቸው ማነው? ይህን ድንጋጌ ያወጣውስ ማነው? ለበርካታ አስርታት በገዛ አገራችን ውስጥ ሲሞት የነበረው ማን ሆነና? ከአንድ ሚሊዮን በላይ ህፃናት ኢራቅ ውስጥ ሞተዋል፣ አሁንም የተቀሩት እየሞቱ ነው። ታዲያ አንድም ሰው ሲጮህና ሲያወግዝ ያላየነው ለምንድነው? ወይም አንድም ሰው እንዳች የሀዘን መግለጫና የማፅናኛ ቃላት ያልሰማነው ለምን ይሆን? እነሱ በገደሏቸው ልጆቻችን ፊንታ እኛም እምነት የለሽ

ሲቪሎችን ገድለናል፡፡ ይህ በሕግም በአእምሮአዊ አስተሳሰብም የሚፈቀድ ነው፡፡

ነገር ግን የትኛው እስላማዊ ሕግ ንፁሃን ዜጎችን በመግደል ብድር መመለስን እንደሚፈቅድ በግልፅ ለመናገር ተስኖታል፡፡ ስለ ዘጠኝ አስራአንዱ ሲገልፅ ደግሞ ጠላፊዎች "ህፃናትን ለመግደል ፍላጐቱ አልነበራቸውም፡፡" ሲል ጥቅምት 26 ቀን 2002 ለአሜሪካ ህዝብ መልዕክት ያስተላለፈው ቢን ላደን

*እንግዲህ ይህ ሙግት አሜሪካ፣ ሁሉም አሜሪካውያን ለመምረጥ የጾታ፣ የቀለም፣ የዕድሜ ወይም የማሰብ ችሎታ የሚከበርባት የነፃነትና የዴሞክራሲ አገር ናት የሚለውን ሀሳባችሁን ይቃረናል፡፡ የህዝቡ*

*መሪዎቹን መምረጥ ብሎም የፓርቲዎች ለተመረጡ መሪዎቹ ደንቦችን ማፅደቅ የማንኛውም ዴመክራሲ መሠረታዊ መረህ ነው፡፡ በመሆኑም "በነፃነትዎ ምድር" አሜሪካውያን መሪዎቻቸውን ለመምረጥ "ነፃ" ናቸው፣ ምክንያቱም ያንን ለማድረግ መብቱ አላቸውና፡፡ እንደዚያ ከሆነ ደግሞ የመረጡት መንግስት ለሚያረቃቸው ፖሊሲዎች ዕውቅና ይሰጣሉ፡፡ ይህም በቢሊዮን ዶላሮች የሚገመት ወታደራዊ ድጋፍን ጨምሮ በብዙ የተለያዩ መንገዶች ሊገለጽ የሚችለውን ለእስራኤል የሚደረግ ትብብር ይጨምራል፡፡ እነዚህን መሪዎቻቸውን በመምረጥ፣ ለፍልስጥኤማውያን መታሰር፣ ለፍልስጥኤማውያን መኖሪያ ቤቶች መውደምና ለኢራቅ ህፃናት መጨፍጨፍ ፈቃድ ሰጥተዋል፡፡*

*አሜሪካን፣ የህዝባዊ ዴሞክራሲ አገር እስከሆነች ድረስ፣ መንግስታቸው ለሚፈፅማቸው ተግባራት ሁሉም ዜጎቿ ሀላፊነቱን ይጋራሉ:: እንደዚህ ጠማማ ወይም ምክንያት ቢስ አመክንዮ ከሆነ ጦረኛ ያልሆነ አሜሪካዊ ብሎ ነገር የለም::*

ከዚህ አኳያ ደግሞ በ9/11ዱ ጥቃት ወቅት ያለቁት ህፃናት እንዴት እንደወላጆቻቸው ሁሉ በዚህ የሞት ድንጋጌ ስር ሊካተቱ እንደቻሉ፣ ለማብራራት ተቸግረዋል - ቢን ላደን::

# የአልቃይዳ ጥቃት

የ1998ቱ ፋትዋው በወጣበት ጊዜ ግን ቃሎችን በተግባር ለመተርጎም የጥፋት ዝግጅት ዕቅዶች ተሰናድተው ነበር:: እናም ነሐሴ 7፣1998፣ አሸባሪዎች በናይሮቢ ኬንያ እና በዳሬሰላም ታንዛኒያ ውስጥ በሚገኙ የአሜሪካ ኤምባሲዎች ላይ ተከታታይ ጥቃቶችን ከፈቱ:: የናይሮቢው ፍንዳታ 291 ሰዎችን የገደለ ሲሆን አምስት ሰዎች ደግሞ ቆስለዋል አብዛኞቹም ኬኒያውያን ነበሩ:: በዳሬሰላሙ ጥቃት ደግሞ 291 ሰዎች ሲሞቱ አስር ሰዎች ደግሞ ተሳዳጅ ሆነዋል:: ምንም እንኳን በዚህ ጥቃት ውስጥ እንደሌለበት የመካድ ጥረቶች ቢያደርግም፣ ቢን ላደን ግን ከአውዳሚው ጥቃት ተጠያቂ ከመሆን ሊያመልጥ አልቻለም:: በጊዜው አንድ ታንዛኒያዊ አሸባሪ ተይዞ ነበርና በተደረገለት የምርመራ ጥያቄ አልቃኢዳ ጥቃቱን እንዳቀነባበረና ተልዕኮውን እንደመራም ይፋ ወጥቷል::

በዚህና በሌሎችም መረጃዎች ላይ በመመስረት፣ የክሊንተን አስተዳደር በአሸባሪ ድርጅቱ ላይ ቁርጥ እርምጃ የመውሰድ ውሳኔ አስተላልፏል። በመሆኑም አፍጋኒስታን ውስጥ በሚገኘው የአልቃይዳ ማስልጠኛ ካምፕና በሱዳኑ የመድሃኒት ፋብሪካ ላይ፣ የአሜሪካ መንግስት የክሩዝ ሚሳኤል ጥቃት ከፈተ። የካምፑ ጥቃት ግን ፋብሪካው ለጦር መሣሪያና ለመድሃኒትነት የሚውሉ ኬሚካሎችን በማምረት የሁለትዮሽ ጥቅም የሚሰጥ ነው በሚል የተሳሳተ መረጃ ላይ ተመስርቶ የተከናወነ ነበር። በኤምባሲዎች ላይ ተደረጉ የነበረው ጥቃት ደግሞ ቢያንስ ለጊዜውም ቢሆን አሜሪካ ከአሸባሪዎች ዛቻ የአውሮፕላን ጣቢያ ማፈንዳትን ጨምሮ በአሜሪካን የሚሊኒየሙ ክብረ በዓል የአዲስ ዓመት ዋዜማ (1999/2000) ላይ ሊፈፀም የታቀደውን የሽበር ጥቃት ሴራ የጉምሩክና የሕግ አስከባሪ ባለስልጣናት የማክሸፉን ስራ ሊቆጣጠሩት ችለዋል። ይህ ለኬታማ የማጨናገፍ ስራ ከአሜሪካን የጠረፍ ደህንነት አኳያ ከልክ በላይ ወደሆነ መተማመን ሳይመራ አልቀረም።

ጥቅምት 12፣2000 አልቃይዳ ዳግመኛ ተነሳ- አሁን ደግሞ ለወታደራዊ ኢላማ። በኤደን ወደብ የመን ውስጥ Uss Cole የተሰኘችዋ ፈጣን የጦር መርከብ ነዳጅ ለመሙላት መልህቋን ጥላ እንደቆመች አጥፍቶ ጠፊ ደምሳሾች ፈንጅ የተጫነች አነስተኛ ጀልባ እያበረሩ ተጠግተው መርከቧን አፈነዷት። ጥቃቱም 19 መርከበኞችን ሲገድል በርካቶችን ደግሞ አቁስሏል። በዚህም የተካበተ ችሎታ ባለው ካፒቴን አማካይነት ተንሳፍፊው የውሃ መያዣ ብቻ ተረፈ። እነዚህ ከአገር ውጪ ጥቃቶች በራሳቸው ሊኖራቸው የሚችለውን የማስጠንቀቅያ ደወል አሳዘጋጁም ነበር።

አሜሪካኖች በቤይሩት ሊባኖስ ውስጥ በ1983 ከደረሰው የባህር ላይ ወታደራዊ ሰፈሮች ፍንዳታ ጀምሮ በአገር ውጭ የወታደራዊ ኃይሎች ላይ በሚደረገው ጥቃት የበሰለ ችሎታ ነበራቸው፡፡ ውጪ ጉዳይ መስሪያ ቤቱ ኤምባሲዎችን በይበልጥ ያጠነከረ ቢሆንም በአገር ውስጥ ጥቃት ለጋስ አኳያ ግን በቁም ነገር የወሰደው ጥንቃቄ እጅግ በጣም ጥቂት ነበር፡፡ ይህ በጥቂቱ የመርካት ሁኔታ እንደሚያመለክተው ከሆነ አየር መንገዶች በውጪ በረራዎች ላይ ተሳፋሪዎችንና ጓዞችን በጥብቅ የሚያጠሩ ቢሆንም በአገር ውስጥ ላይ ግን ግድየለሽነት ነበር፡፡

## ምትሃታዊ ጀግና

የአልቃይዳ ተልዕኮ ስኬታማና የአሜሪካ ውጤታማ አፀፋ ለእነሱ መመለስ አለመቻል ቢን ላደንን ሲያደፋፍረው በሙስሊሙ ዓለም ደግሞ ማዕረጉን ከፍ አድረጉታል፡፡ የቅርብ ተባባሪ የሆኑ በርካታ ሸሪኮቹም የቢን ላደንን ምትሃታዊነት ለአሜሪካ ያረጋግጣሉ፡፡ "እሱን ዝነኛ ያደረገው ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ?" ሲል አንድ የጓንታናሞ እስረኛ በማጋነን ይጠይቃል፡፡ "እነግራችኋለሁ፣ አሜሪካኖች፡፡ በሚዲያ፣ በቴሌቭዥንና በመፅሔቶች፡፡ ሁሉም ሰው ስለ ኦሳማ ቢን ላደን ነው የሚያወራው፡፡" የታሊባን አባላት የሚመረቁበት የፔሻዋር ማድራሳ ሀላፊ ይህንኑ ማጠቃለያ ይደግፋል፡፡

እንደማስበው አሜሪካ ኦሳማ ቢን ላደንን መለኮታዊ ወይም ከሰብአዊ ባህር ውጭ የሆነ ኃይል አድርጋዋለች፡፡ የትም ስፍራ ላይ ሽብርተኝነተ ይከሰት ስለ እሱ ነው የሚያስቡት፡፡ እሱ ይሄን ያህል ተዕዕኖ፣

ይሄን ያህል የበላይነትና አቅም ያለው አድርጌ አላስብም። ኦሳማ ቢን ላደን ለሙስሊሙ ዓለም ተምሳሌት ሆኗል። እነሱ ጋር ያለውን ጣልቃ ገብነት ለመስበር የሚሞክሩት የውጭ አገር ኃይላትም እዎን እሱ ለእኛ ጀግናችን ነው። ነገር ግን በመጀመሪያ ጀግና ያደረገችው አሜሪካ ራስዋ ናት። ይህ አነጋገር ቢን ላደን ከዋነኞቹ ግቦቹ አንዱን በማሳካት ላይ እንደነበር የሚገልፅ ነው። አሜሪካ እሱንና አልቃይዳን በመቃረን የምታደርገውን ጦርነት፣ እስልምናን በመቃወም የምታደረገው ጦርነተ አድርጐ ለማሳየት ይመኛል።

የመስከረም 11፣2001ዱ ክስተት በጊዜው በሁሉም ህያዋን አሜሪካውያን ትውስታ ውስጥ ተቀርጿል። የጥቃቱ ዕቅድና አፈፃፀም በ9/11 ኮሚሽንና በአካዳሚና በህዝባዊ ስፍራዎች ተጋባዥ በብርቱ ተጠንቷል። አብዛኞቹ ቀሪ መረጃዎች ምስጢር ቢሆኑም የበለጡት ደግሞ ተደርሶባቸዋል። ክስተቱ ደግሞ በራሱ በጣም በትክክል የሚረዳ ነው። ቢን ላደንና ተባባሪዎቹ ተልዓኮውን በርካታ ዓመታት ሲያቅዱት የነበር ሲሆን ከጥቃቱ አንድ ዓመት አስቀድሞም አሽባሪዎችን በምስጥር ወደ አገሪቱ ሲያስገቡ ቆይተዋል። የጥቃቱ ዕለት ጠዋት አንድ ሰዓት ላይ ጠላፊዎች አራት አውሮፕላን ላይ ተሳፈሩ። ሁለቱን ወደ ኒውዮርክ የዓለም አቀፍ ንግድ ማዕከል መንትያ ህንፃዎች ሲያበሩ አንዱን ደግሞ ወደ ፔንታጉን ወሰዱት።አራተኛውን ተምዘግዛጊ ሚሳኤል ወኒያም ተሳፋሪዎች ጠላፊዎቹን በጉልበት አስገድደው አውሮፕላኑን በፔነሲልቫኒያ ሜዳ ላይ እንዲወድቅና ወደ ዒላማው እንዳያመራ አስቀርተውታል።

እንደ ቀደምት የአልቃይዳ ተልዕኮዎች ሁሉ የዘጠኝ አስራአንዱ የጥቃት ሀሳብም በኦሳማ ቢን ላደን የመነጨ አይመስልም። የዘጠኝ አስራ

አንዱ ኮሚሽን ሪፖርት ዕቅድን በመንደፍና በማጉልበቱ ረገድ ግብፃዊውን ካሉድ ሺህ መሐመድን ባለሟና ያደርጋል፡፡

በመጀመሪያ እሱ በርካታ አውሮፕላኖችን ለማፈንዳት በ1994 በፓስፊክ ላይ ወደሚገኘው የማኒላ አውሮፕላን ጣቢያ ሄዶ ነበር፡፡ ሆኖም ታማኞች ሴራውን አክሽፈውታል፡፡ ከዚያም በ1996 አፍጋኒስታን ውስጥ ከቢን ላደን ጋር ተገናኘ፡፡

በመጀመሪያውና የዓለም ገበያ ማዕከል ፍንዳታ የማኒላ የአየር ማረፊያ ሴራ፣ ዕቃ ጫኝ መኪናውን ዕቅድ እና ፊሊፒንስ ውስጥ በእሱና በስራ ባልደረባው ክትትል የተፈፀሙ ሌሎች ተግባራችን አስመልክቶ ካሼማ ለ9/11ዱ ጠላፊ ለመሐመድ ኢተፋና ለቢን ላደን ገልፆላቸዋል፡፡

በተጨማሪም ካሼመ በድናይትድ ስቴትስ ውስጥ አውሮፕላኖችን

ከህንፃዎች ጋር የሚያጋጩ የሰለጠኑ አብራሪዎች ስለማይሳተፉ ያለውን ዕቅድ (ፕሮፖዛል) አቅርቧል፡፡ በመጨረሻም ፕሮፖዛሉ የ9/11ዱ ሴራ ሆኗል፡፡

የዘጠኝ አስራ አንዱን ሴራ ካሼማ ከኋላ ሆኖ መምራቱን የሚደግፈው በርካታ የመረጃ አካል እንደሚገልፀው ቢን ላደን የአልቃይዳ ጭንቅላት አልነበረም፡፡ የአልጀዚራ ቴሌቭዥን ኔት ወርክ ዋና የምርምራ (የክትትል) ዘጋቢ የሆነው ዮስሪ ፋርዳ የቢን ላደን ችሎታዎችና አልቃይዳ ውስጥ ባለው ሚና ዙሪያ አሳዛኝ ግምቱን አቅርቧል፡፡ "(የዘጠኝ አስራ አንዱን ጉዳይ ካሊድ ሼህ መሐመድ ማደራጀቱ) እኔን የሚያስደንቀኝ አይደለም" ሲል ያመለክታል ፋርዳ፡፡

በትክክል የቢን ላደን ግዛት አይደለም እሱ ዝርዝሮችን ተመልካች አይደለም፡፡ እሱ አንቆቆልሽ ሰው ነው፡፡ እሱ የኩባንያው ሊቀመንበር ነው የድርጅቱ ተምሳሌት፡፡ አሁንም ድረስ በተወሰኑ ተልዕኮዎች ላይ ያማክሩት ዘንድ እንደ ካሉድ ሼህ መሐመድ ዐይነት ሰዎችን ይፈልጋል፡፡ ካሊድ ሺህ መሐመድ በበኩሉ ነገሮችን ለማስፈፀም ሰዎችን ይፈልጋል፡፡

እንደ ተልዕኮው የዘጠኝ አስራ አንዱን ጥቃት በብቃት የተቀናጀና ባብዛኛው እንከንም የተፈፀም ነው፡፡ አጥቂዎች ታላቅ ስትራቴጂካዊና ተምሳሌታዊ ጠቀሜታ ያላቸውን ኢኮኖሚያዊና ወታደራዊ ዒላማዎችን መትተዋል፡፡ ሁሉም አሻባሪዎች የሚፈልጉትን ድራማዊ ውጤት ተቀናጅተዋል የጥቃቱን የቪድዮ ምስል ያዩ ተመልካቾች ቁጥር አንድ ቢሊዮን እንደሚደርስ ግምቶች ያስቀምጣሉ በተጨማሪም የዘጠኝ አስራ አንዱ ጥቃት የኦሳማ ቢን ላደንን ጅሃዳዊ ጉዞ መደምደም ያሳያል፡፡ በትምህርት ቤት ውስጥ በአስተማሪው እንደተማረከ ወጣት ሐይማኖተኛ ሆኖ ነበር የጀመረው፡፡ ሶቭየትን በመቃወም በተደረገው የአፍጋን ጦርነት ወቅት አዛም ለጅሃድ ሲል መረጠው፡፡ እሱ ወደ ጀግናነት ተቀየረ ኢራቅ ኩዌትን በወረረችበት ወቅት ብቻ ነው የገዛ አገሩ ያሳፈረችው ሳዑዲ፣ ንጉሱን ለመከላከል የቢን ላደንን ስምምነት ተቀብላ የሙጃሃይንን ተዋጊ ኃይሎች ከመደገፍ ይልቅ የሳዳም ሁሴንን ወረራ ለመመከት ስትል ፊቷን ወደ አሜሪካ አዞረች፡፡ ከባህረ ሰላጤው ጦርነት በኋላ በፈቃደኛ ግዞተኛነት ተሰደደ መጀመሪያ አፍጋኒስታን፣ ቀጥሎም ሱዳን፡፡ በዚያ የስደት ወቅት ከሃዲ የሙስሊም አገዛዞችና እንዲሁም ከእነሱ ጀርባ ባለችው አሜሪካ ላይ ጅሃድ መከፈት እንዳለበት እያመነ መጣ፡፡

# ምዕራፍ ስድስት

# ቢን ላደን እና አል ቃኢዳ ከ9/11 በኋላ

ቢን ላደን ብዙም ሳይቆይ የሽብር ጥቃቱ ምን ዐይነት የታለመለትን ውጤ ት እንዳስገኘ በይፋ ተናግሯል።

> *«እኔ በወቅቱ አውሮፕላኑ ከሕንፃው ጋር ከተጋጨ በኋላ የተፈጠረው እሳት የሕንፃውን የብረት ምሰሶ በማቅለጥ አውሮፕላኑ የተጋጨበት የሕንፃው ክፍል እና ከዚያ በላይ ያሉ ፎቆችን ብቻ ሊያጥሉ ይተዋል ብዬ ነው የጠበቅኩት። በወቀቱ ሁላችንም ተስፋ ያደረግነውና የጠበቅነው ከዚህ ያለፈ ነገር አልነበረም።»*
>
> (በ1993 መጨረሻ ግድም ለአንድ የሳውዲ ዜግነት ያለው ደጋፊው ከተናገረው ላይ የተወሰደ)

ቢን ላደን ጥቃቱ በሚደርስበት ሰዓት በደስታ ሰክረው የነበሩ ደጋፊዎቹን ልክ አውሮፕላኑ የሰሜን ጫፉን ሕንፃ ሲገጨው፣ «ግድ የለም ታገሱ፣» ብሏቸዋል። እሱ ይህን ባለ በአንድ ሰዓት ከግማሽ ጊዜ ውስጥ የበለጠ ጥቃት ደረሰ። አንድ ሌላ ደጋፊ ደግሞ በቴሌቪዥን ጥቃቱን አስመልክቶ የተላለፈውን ከተመለከተ በኋላ ለቢን ላደን ለመናገር ተጣደፈ። ቢን ላደን ግን እጁን በማንሳት፣ «አውቃለሁ፣ አውቃለሁ» በሚል ዐይነት መለሰለት።

እንግዲህ ቢን ላደን በመስከረም 11 የሽብር ጥቃት እጁ ያለበት መሆኑ ቅንጣት ታህል የማያጠራጥር መሆኑ በነዚህና በሌሎች ማስረጃዎች ሊረጋገጥ ቢችልም እሱ ግን ልክ ከዚያ በፊት በምሥራቅ አፍሪካ ኤምባሲዎች ላይ በደረሰው ጥቃት ጊዜ እንዳደረገው፣ «ዐይኔን ግንባር ያድርገው፤» በማለት ሽምጥጥ አድርጎ ነው በጥቃቱ እጁ እንዳለበት የካደው:: አል-ቃይዳ ከሌሎች ሽብርተኛ ደርጅቶች ለየት የሚያደርገው አንዱ ነገር ጥቃት ከደረሰ በኋላ እንደነሱ በብርሃን ፍጥነት ተንደርድሮ ሃላፊነትን ከመውሰድ ይልቅ፣ «እጄ የለበትም!» በማለት ጠላቶቹ በግምትና በመላምት እንዲቆዩ ማድረጉ ነው::

> *«በተደጋጋሚ እንደገለጽኩት በአሜሪካው የመስከረም 11፣ 1994 ጥቃት ፈጽሞ እጄ አልነበረበትም::»*
>
> (መስከረም 18 1994 በፓኪስታን ውስጥ ለሚገኝ አንድ ወኪል ከተናገረው የተወሰደ)
>
> *«ሙስሊም እንደመሆኔ መጠን ውሸትን ለመሸሽ ነው ጥረቴ:: እኔ በዚህ የሽብር ጥቃት አለመሳተፌ ብቻ ሳይሆን እንዲህ ሴቶች፣ ሕፃናት እና ሌሎች ንፁህን ዜጎች በገፍ ያለቁበትን ጥቃትም የማልደግፈው መሆኑም ጭምር ነው መታወቅ ያለበት:: እስልምና በሴቶች፣ በሕጻናት እና በንፁህን ላይ የሚደርስን ጥቃት ያወግዛል:: እንዲህ ዐይነቱ ጥቃት አይደለም በሰላሙ በጦርነት ጊዜ እንኳን ክልክል ነው::»*

ቢን ላደን እንዲህ ያለውን ቅጥፈት ምንም እንዳላደረገና ንፁህ ሀሊና እንዳለው ሆኖ ያለ ሀፍረት ሊናገር የሚችለው አክራሪ የሆኑ የእስልምና አስተምህሮት ሰዎች የእስልምናን ጠላቶች መሸወድን እና መዋሸትን በግልጽ በመፍቀዳቸው ነው::

የአል-ቃየዳ መሪዎች ግን በዚህ መልኩ የመስከረም 11ዱን የሽብር ጥቃት አልተሳተፍንበትም ብለው ቢክዱም አሜሪካ በአፍጋኒስታን የፀረ-ሽብር ዘመቻዋን ማጧጧፍ ከጀመረች በኋላ ግን ይህን አቋማቸውን አልገፉበትም:: ለምሳሌም በሚያዚያ ወር 1994 ላይ አል-ጄዚራ የተሰኘው የቴሌቪዥን ጣቢያ ኔትዎርክ አንድ ቪዲዮ ቴፕ የለቀቀ ሲሆን በዚህ ቴፕ ላይም ቢን-ላደን እና ሁለተኛው የአል-ቃይዳ አዛዥ የሆነው አይማን አል-ዛዋሒሪ ስለሽብር ጥቃቱ የተሰማቸውን እውነተኛ ስሜት ለመጀመሪያ ጊዜ ሲገልፁ ተሰምተዋል::

> *«ይኼ እጅግ አስደሳች የሆነ ትልቅ ድል የተገኘው በአሏህ ፈቃድ ብቻ ነው::»*
>
> (ዛዋሒሪ ከተናገረው ላይ የተወሰደ)
>
> *«ይኼ ድል የተገኘው በእኛ ብልጫም ሆነ ጉብዝና ሳይሆን በአሏህ ባርኮት ብቻ ነው:: ታላቁ አሏህ ለፈለገው ምህረቱን ያወርዳል:: አሏህ የባሪያዎቹን ልብ በደምብ ከፈተሸና ከመረመረ በኋላ የሱን ፀጋ፣ ምህረትና ምርቃት ለማግኘት ብቁ የሆኑትን ከመሀከላቸው ይመርጣል:: እነዚያ [ከቤታቸው] የወጡ -ቱ 19 ወንድሞች ለታላቁ አሏህ ሲሉ ጥረት በማድረጋቸውና ሕይወታቸውን መስዕዋት*

*በማድረጋቸው ይኸው አሏህ ደገፋቸውና አሁን ለምናጣጥመው የወረራ ድል በቃን።»*

ቢን ላደን በበኩሉ ከዚህ በኋላ ይበልጥ ጥቃት እንደሚደርስ ቃል ከመግባቱም ባሻገር ለጥቃቶቹም ደግሞ አዘውትሮ እንደሚያደርገው በፍልስጤሞች ላይ የሚደርሰውን መከራ እና የአሜሪካ ወታደሮች በሳውዲ ዓረቢያ መኖርን እንደምክንያት ጠቀሰ። እንዲህ ሲልም በይፋ ለደጋፊዎቹ ተናገረ፤

*«አሜሪካ በሁለቱ ቅዱስ ታላላቅ መስጂዶች መዲና እና የሁሉም ሙስሊሞች ዋንኛ የቅድስና ስፍራ በሆነችው ፍልስጤም እኛ ሰላም ሳናገኝ ሰላምንም እንኳን ልታገኘው ልታስበውም አይቻላትም።»*

# ለነፃነት ተብሎ የታቀደ ኦፕሬሽን

ቢን ላደን ምንም እንኳን የሰው ሕይወት በገፍ ተቀጥፎ፤ ከፍተኛ እና መጠነ ሰፊ ውድመት በንብረት ላይ ደርሶ እንዲሁም በኒው ዮርክ ደግሞ ታላቅ የኢኮኖሚ ኪሳራ ደርሶ የነበረ መሆኑ ቢያስደስተውም አውሮፕላኖቹን ይህንን መሰሉን ' ጥቃት እንዲያደርሱ ሲልካቸው ግን ከእነዚህ የበላለጡ እና ጥልቅ ነገሮችን በማሰብ ነው። ዋንኛው ደግሞ የአሜሪካ ወታደሮች ፍፁም ቅጥ ባጣ እና ማለቂያ የሌለው በሚመስል ውስብስብ ውጊያ ውስጥ እንዲገቡ ማድረግ ነው። ይኼ ሰው አሜሪካ በቬትናም የቱን ያህል እንደተንደፋደፈችና እንዳልተሳካላት ብላም ደግሞ ሩሲያውያኑ በአፍጋኒስታን እንዲሸነፉ ጥረት ማድረጉን አሳምሮ ያውቃል። ምን ይህ ብቻ? ብዙዎቻችን በደምብ የምናስታውሰውን የ 1985ቱን

የሞቃዲሾ ውርደትና ፕ/ት ቢል ክሊንተን ወዲያውኑ ሬንጀር ለባሾች በመሸነፋቸው ከሶማልያ ጦራቸው ጠቅልሎ እንዲወጣ ማድረጋቸውን ያውቃል:: ቢን ላደን በ 1974 ዓ.ም አሜሪካ የባሕር ኃይሏ በሊባኖስ ከፋኛ በቦምብ ከተደበደበ በኋላ እንዴት ፈርጥጣ እንደወጣችም ሳያውቅ አልቀረም:: እናም ቢን ላደን የመስከረም 11ዱን ጥቃት ሆነ ብለው የመራውና ያቀነባበረው አሜሪካ አፍጋኒስታን ላይ ወረራ እንድትፈጽም ለመተንኮስና ለመገፋፋት ነው:: ከታሪክ መማር የሚቻላቸው ቢሆን የቡሽ አስተዳደር ባለስልጣናት ወረራውን ባልፈፀሙ ነበረ:: ዝርዝር መማሪያን በብቃትና አትረፍርፎ የያዘው ታሪክ ለዋሽንግተን ባለስልጣናት ባንድ ወቅት በደቡብ ምሥራቅ ኢስያ የቬዬት ኮንግ ላይ እንደደረሰው አልያም ደግሞ ሙጃሂዲኖች በአፍጋኒስታን ሩሲያውያን ላይ እንዳደረጉት አሁን አሜሪካ ወደ አፍጋኒስታን ጦሯን ብትልክ ከፋኛ አቅሟ እንደሚሟጠጥ፣ ተፋላሚዎቹ መሻገዎችም የጦሩን ስስ ብልት በመፈለግ እንደሚያደባዩት ማስጠንቀቂያ ሰጣቸው::

በሚያዚያ ወር 1994 ላይ ቢን-ላደን ወደፊት የገዛ የሕይወት ታሪክ ፀሐፊው ለሚሆነው ፓኪስታናዊ ሰው ከመስከረም አስራ አንዱ የሽብር ጥቃት በስተጀርባ የታለሙ ነገሮችን አብራርቶለታል:: ይኼ ሐሚድ ሚር የተባለ ሰው እንደሚለው ከሆነ አል-ቃይዳ የአሜሪካን ዋንኛ የንግድ ማዕከል ቢያጠቃ አሜሪካ አፍጋኒስታንን ትወራለች:: ከዚያ ደግሞ ታሊባኖች ይወርዷሉ ከዚያም አል-ቃይዳ ልክ ሩሲያውያን ላይ አፍጋኒስታን ውስጥ እንዳደረገው በዋሽንግተን ላይ የጂሀድ ጦርነት ያውጃል:: የአል-ቃይዳ አዛዥ በመሆን የሚታወቀው ሳይፍ አዴል ደግሞ ስለ ኦፕሬሽኑ በዚህ መልኩ ገለፀ::

«ከእነዚህ እጅግ አደገኛ ጥቃቶች በስተጀርባ አቅደነው የነበረው ያ እባብ ከተደበቀበት ቀዳዳ እንዲወጣ መገፋፋትን ነው:: እንዴ በዚህ መልኩ

ከተደበቀበት ከወጣልን ጉልበቱን እና ኃይሉን ከፉኛ ተፈታትነን እንዳልነበረ እናደርግና እንጨርሰዋለን:: ይኼ ደግሞ በጠላት ተከብቦ በሚገኘው የዓለም ሕዝብ ፊትም ሆነ በኛ በራሳችን ሕዝብና ደጋፊ ፊት ይበልጥ ተዓማኒነትን ያላብሰናል:: አንድ ሰው ለዚያውም ማንነቱ ካልተገለፀ ምንጭ ጭንቅላቱ ላይ ሲመታ ከፉኛ ነው የሚደነብረው:: ይህ ሰው በዚህ መልኩ ከተጠቃ ፍፁም ተቀባይነት የሌለውን እና ለከፍተኛ ስህተት የሚዳርገውን ጉዳት እንዲያደርስ ነው የሚገፋፋው:: በኋላ የሆነውም ይኸው ነው:: በመጀመሪያ ልክ በወጥመዳችን ገቡና እንዳሰብነው አፍጋኒስታንን ያዙ:: በኋላ ቀጠሉና ኢራቅ ላይ ወረራ ፈጸሙ::»

እርግጥ የታሰበው ስትራቴጂ ተፈላጊ የሆነውን እና የተጠበቀውን የአሜሪካ መንግሥት አፀፋ ቢያስከትልም በአፍጋኒስታን የተደረገው ወረራ ግን ቢን ላደን ባሰበው መልኩ አልሄደም:: በቪዬትናም ከደረሰበት ውርደት በጥቂቱም ቢሆን የተማረ የሚመስለው የአሜሪካ ጦር በአፍጋኒስታን ሲገባ በከፍተኛ መጠን እግረኛ ሠራዊት ማሰማራት እንደማያስፈልገው ወሰነ:: ያ ብቻም ሳይሆን የፔንታጎን ወታደራዊ ባለስልጣናት ሙሉ በሙሉ ኮንቬንሽናል የሆነ የወታደራዊ ውጊያ ውስጥ መግባት እንደሌለባቸውም ተረድተዋል:: በመሆኑም ባሏቸው አማራጮችና ተጨባጭ ሁኔታዎች ላይ ቁጭ ብለው መከሩ:: የአሜሪካ ኃይሎች በስተሰሜን አቅጣጫ በምድር ጥቃት መሰንዘር ይችላሉ ነገር ግን ይኼ ደግሞ ዋይት ኃውስ ሊታገሰው ከሚችለው በላይ ጊዜን ይወስዳል:: በመሆኑም ሶቪየቶች ተዋርደው ከወጡ በኋላ በአፍጋኒስታን የቀጠለውን የእርስ በርስ ጦርነት ሊጠቀሙበት ወሰኑ:: የአሜሪካ ልዩ ኦፕሬሽን ኮማንድ እና የማዕከላዊው ስለላ ድርጅት (CIA) በጋራ በመተባበር የፓሽቱን ጎሣ ተወላጅ የሆኑ የታሊባን ኃይሎችን እና የአል-ቃይዳ ደጋፊዎቻቸውን ለማጥቃት ይንቀሳቀሱ የነበሩትን የሰሜን የታጂክ ትብብር ኃይሎችና

የቱርከማን ጎሳዎችን ረዳቸው። የሰሜኑ ትብብር የሚቆጣጠረው የአፍጋኒስታንን 10% ብቻ የሚሆን ስፍራ ቢሆንም ድንበሩ ግን ለቀድሞው የሶቪየት ማዕከላዊ እሲያ ሪፐብሊክ በእጅጉ የቀረበ ነበረ። በሌላ በኩል ደግሞ በሚያስቸግሯቸው የቼቼን አማፂያን ላይ ድልን ለመቀዳጀት እጅግ የጓጉ የነበሩት ፐ/ት ቭላድሚር ፑቲን አሜሪካ የቀድሞዎቹን እና ዕድሜ ጠገብ የሆኑትን ዑዝቤኪስታን እና ካዛኪስታን የአየር ማቢያዎች እንድትጠቀም ፈቀዱ። አሜሪካም እነዚህን ቦታዎች በመያዝ አፍጋኒስታን ላይ ለከፈተችው ወረራ በደምብ አቀነባበረችበት።

እንግዲህ በዚህ መልኩ የወታደራዊ እቃና ቁሳቁስ አቅርቦት እና ፈንድ በእጅጉ የነበረው ጦርነት ተሟሟፈ። ትልቁ ድጋፍ የተደረገለት የሰሜን ትብብሩ ኃይልም ታሊባኖቹን በሳምንታት ጊዜ ውስጥ ብቻ ጠራርጎ አባረረ። ይኼ ጦርነት እንዲሁና ትልቁ አስገራሚው ገጽታው በ 13ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ወቅት ይታወቅ የነበረውን የጦርነትና የውጊያ ስልት ከ 21ኛው ክፍለ ዘመን ታክቲክ ጋር በማቆራኘቱ ነው። ይህም ሲባል ባንድ በኩል አሜሪካውያኑ የሳተላይት ግንኙነት መሣሪያዎችን እና ላፕቶፖችን በመጠቀም የአየር ድብደባ ሲያካሂዱ የሰሜን ትብብሩ ኃይሎች ደግሞ ልክ እንደ 13ኛው መቶ ክፍለ ዘመኑ ጊዜ በቦምብ መጋየት አደጋ ክፉኛ ተደናግጠው የነበሩ ታሊባኖችን በእግርና በፈረስ ውጊያ ጨረሷቸው። እናም በጦርነቱ ዋንኛውን የእግር እና የምድር ላይ ውጊያ ከታሊባኖች ጋር ገጥመው ያለቁትና መስዕዋትነት የከፈሉት አፍጋኒስታናውያኑ ሆኑ። በሌላ በኩል ደግሞ ታሊባኖች በሕዝብ እጅግ የተጠሉና የተወገዙ በመሆኑ መቃብራቸው ባንድ ጀምበር እንዲቆፈር አስተዋፆ አደረገ። የታሊባኑን የአፈና አገዛዝና ሥርዓት ለዚያውም በውጭ ጉዳይ ሚ/ር መስሪያ ቤት ውስጥ ሆነው በባለስልጣንነት ሲያገለግሉ የቆዩ አንድ ሰው ከዚያ በኋላ ባሳተሙት መጽሐፍ ላይ ቡድኑ ሕዝብን በማሸበርና

በማሰቃየት ይገዛ የነበረ እና ከፍተኛ ተቃውሞም ስለነበረበት በዚያ በወረራው አስቸጋሪ ወቀት ሕዝቡ ቂም በቀል ያደርስብኛል ብሎ ስጋት ውስጥ ገብቶ እንደነበረ አትተዋል:: ከዚህ ሌላ የቴሌቪዥን ካሜራማን እና የእንግሊዝ የጦር ባለስልጣን የነበረው ፒተር ጆንቫን ካቡል በሰሜን ትብብሩ ኃይሎች እጅ ከወደቀች በኋላ የነበረውን ሁኔታ በሚከተለው መልኩ ገልፆታል::

> *«እጅግ አብሪተኛ እና አፋኝ የሆነው የታሊባን መንግሥት በመወገዱ ሕዝቡ ከመጠን በላይ ተደስቶ ነው የተመለከትኩት::»*

የሆነው ሆኖ ግን ታሊባኖች እንዲህ በከፍተኛ ፍጥነት መውደቃቸው ደጋፊዎቻቸውንም ሆነ ተቃዋሚዎቻቸውን በእጅጉ ያስደመመ ሆነ::

«አገሪቱ በቶሎ እንዲህ ትያዛለች ብሎ ያሰበ ማንም አልነበረም::» ሲል ነው ተይዞ በምርመራ ላይ ይገኝ የነበረ አንድ የኩዌት ተወላጅ የሆነ ምርኮኛ ለአሜሪካውያን መርማሪዎች የገለፀው:: ኦሳማ ቢን ላደን እንደ እውነቱ ከሆነ ለጥቀት; ነው ከመማረክ ያመለጠው:: ለዚያ ለነዋነት ተብሎ የታቀደ የተባለውን ወረራ ወደፊት በአሜሪካ ላይ የበለጠ ጥቃት እንደሚደርስ በማስፈራራት ነው አፀፋ የመለሰው:: በታሊባኖች ላይ የአሜሪካ ቦምብ ጥቃት በጀመረበት ቀን ምናልባትም ጥቂት ቀደም ብሎ ብቻ የተቀዳ እንደሆነ በሚገመት አንድ ቴፕ ላይ፣

> *«ለአሜሪካ እና ለሕዝቧ ጥቂት ቃላት ብቻ ማለት እፈልጋለሁ፣ እኔ ሰማይን ያለምንም መደገፊያ ቀጥ አድርጎ ባቆመው አምላክ ስም ነው የምምልላችሁ:: እኛ*

*በፍልስጤም በሰላም መኖር ከመቻላችን በፊት አሜሪካም ሆነች ሕዝቧ ሰላምን ሊያስብ ከቶም አይችልም፡፡ ሌላው አሜሪካና ሕዝቧ ሰላም ማግኘት ከመቻላቸው በፊት መቅደም የሚገባው አረመኔው ጦር የነቢዩ መሐመድን መሬቶች በሙሉ ለቆ መውጣቱ ነው፡፡ ሰላም ለነቢያችን፡፡»*

ቢን-ላደን እንዲህ እንዲህ ያለውን ነገር በቴፕ እየለቀቀ ተፈላጊውን እና የጠበቀውን ያህል ትኩረት ባይሰብም አሳዳጆቹን ግን ማበሳጨቱ አልቀረም፡፡ ከ 1970ዎቹ አጋማሽ ጀምሮ በደምብ የሚያውቀውን የመሬት አቀማመጥና የቦታ አቅጣጫ በመጠቀም የፓኪስታንን ድንበር አቋርጦ ከካንደሐር በማምለጥ እጅግ አስቸጋሪ ወደ ሆነው ቶራ ቦራ ገባ፡፡ የአሜሪካ ኃይሎች እንዲህ ያለውን አስቸጋሪና በጣም ሩቅ የሆነ ቦታ ሊቆጣጠሩት የማይችሉት ሲሆን ይኼ አልበቃ ብሎ ደግሞ በአፍጋኒስታን የሚገኙ በርካታ ዋሻዎች ከአሜሪካ ኃይሎች የአየር ድብደባ በቀላሉ ለመደበቅና ለማምለጥ የሚያስችሉ ነበሩ፡፡ ቢን ላደን እና ደጋፊዎቹ ለጊዜው ማድረግ አላስፈለጋቸውም እንጂ ሁኔታዎች ቢባባሱ ኖሮ በፓኪስታን እንደገና አቋርጠው እጅግ ለአገዛዝ አስቸጋሪ እንደሆነ ወደሚታመንለት በፌዴራል ደረጃ ወደሚተዳደር ብዙ ጎሣ ያለበት ስፍራ መግባትም ይችላሉ፡፡ በወረሀ ታሕሳስ የተካሄደ የምንጠራ ዘመቻ አል-ቃይዳንም፤ ቢን ላደንንም ሆነ ታሊባንን ለመያዝም ሆነ ለመጨረስ ሳይችል ቀረ፡፡ ከዚያ በኋላ በመጋቢት ወር የተካሄደው እና አናኮንዳ ተብሎ የሚታወቀው ኦፕሬሽን በአማ ተራራዎችና በሳሂ-ኮት ግድም መሽገው የነበሩ ሽማቂ ኃይሎችን እና አማፂያንን ማጥፋት ቢችልም ቢን ላደን እና ሙላ ኦማር ግን እንደተለመደው አመለጡ፡፡

አሜሪካ በቶራ ቦራ ያካሄደችው ኦፕሬሽን ሳይሳካ መቅረቱ የቡሽን አስተዳደር ለከፍተኛ ትችት ያጋለጠው ሲሆን ገና ከዚህ በኋላም ቢሆን ረዘም ላለ ጊዜ በወታደራዊ ዓለም-ነክ ጉዳዮች ዙሪያ በሚደረጉ ውይይቶች ትልቅ ቦታን ይዞ ይቀጥላል:: ለምሳሌም ሲይን ኔይለር የተባለውና *Army Times* ለተባለው መጽሔት የሚሠራው ጋዜጠኛ በትንታኔው፣

> *«ከባድ መሣሪያን በሸለቆው ዝቅተኛ ስፍራዎች ላይ እና ወለል ግድም ላለመጠቀም መወሰኑ ለድሉ መታጣት ከፍተኛ አስተዋፆ አድርጓል::»*

ብሎ ነው የፃፈው:: ግን ከዚህም ሌላ አሜሪካ ሽምቅ ተዋጊዎቹን እንደሚፈለገውና እስከመጨረሻው አድኖ ለመያዝ ብዙም ፈቃደኝነቱና ተነሳሽነቱ በሌላቸው የአፍጋን ወታደሮች ላይ መተማመኗ ሊላው ለውድቀቱ መንስዔ እንደሆነም ይታመናል:: በመሠረቱ የአፍጋኒስታን ባሕል እጅግ ከባድ ነው፤ ቂም በቀል ለምዕት ዓመት ያህል በትውልድ እየሰረፀና እየተላለፈ የቅድመ ትውልድን ገዳይ ለመበቀል ከፍተኛ ጥረት ማድረግ፤ ደም መቃባትና የጥላቻ ግድያ ፍጹም ስር በሰደዱበት በዚህ ማኅበረሰብ ውስጥ ከአል-ቃይዳ ጋር አሜሪካን እረዳ ብለው ደም በመቃባት ኋላ ጠላት የማፍራት አደጋን ለመጋፈጥ ዝግጁ የነበሩት አፍጋኖች በጣት የሚቆጠሩት ብቻ ናቸው:: ከዚህ በላይ ደግሞ ፈቃደኛ ቢሆኑ እንኳን የአሜሪካ ጦር እስከመቼ እዚህ ሰፍሮ እነሱን ሊጠብቃቸውና ሊከላከላቸው እንደሚችል በማያውቁበት ሁኔታ ያንን ማድረግ ያስቸግራል:: ቀደም ሲል የተመለከትነው ፊልም እንሺ እና የእንግሊዝ የጦር ባለስልጣን ፒተር ጄቨናል የሚከተለውን ማጠቃለያ ሰጥቷል፤

> *«የአሜሪካ ጦር [በቶራ ቦራ] ውጊያ ወቅት ከፍተኛ ብቃት ቢኖረውም ትልቁ የሰራው ስህተት ግን መረጃ ለማግኘት በአፍጋናውያን ላይ እምነት መጣሉ*

> *ነው:: እናም በዚህ የተነሳ እነ ኦሳማ ሁሌ ሾልከው ያመልጣሉ:: በዚህ ረገድ ልዩ ጦሩን ብዙም ልንተቸው አንችልም:: ለምን ቢባል እኔ እንደሚመስለኝ ጥቂት አግረኛ ጦር ብቻ ነው የነበረው::»*

አንድ ከአሜሪካ ጎን ተሰልፎ ሲዋጋ የነበረ የአገሬው ሚሊሻ መሪ ደግሞ ያስተዋለውን አንድ ሌላ የታክቲክ ስህተት በሚከተለው መልኩ ነው የገለፀው::

> *«እኔ እንደተመለከትኩት ከሆነ ወደ ፓኪስታን የሚወጣበትን መንገድ አሜሪካ ዘግታው ቢሆን ኖሮ አል-ቃይዳ የትም አባቱ አያመልጠንም ነበረ::»*

ቢን ላደን በማምለጡ ከፍተኛ ቁጭት ቢፈጠርም አሜሪካውያኑ ግን አፍጋኒስታንን በመያዛቸው የተነሳ ታሊባንን ከዚያ በኋላ በቀላሉ ሊረግፍ ወደሚችል እና ብዙም አደጋ ወደማያመጣ ተራ ልፍስፍስ ጦር ለመለወጥ፣ ብሎም ደግሞ መሀከለኛውን አል-ቃይዳን እንደ ድርጅት ለመበታተን ትልቅ ዕድል ፈጠረላቸው:: ይሁንና የቡሽ አስተዳደር ይህንን ወርቃማ ዕድልና አጋጣሚ አባከነው:: ገና ለገና ጦርነቱ የሚራዘምና ብዙ አቅጣጫዎች ያሉት ነው በማለት የአፕሬሽኑን ኃላፊነት ከራሱ በማውረድ በሰሜን አትላንቲክ ቃልኪዳን ድርጅት (NATO) ውስጥ ለነበረው የዓለም ዓቀፍ የፀጥታ እርዳታ ኃይል (ISAF) ለተባለውና ከ 20 አገራት የተውጣጣ ዩኒት ላለው አካል አሳልፎ ሰጠ:: ግን የሚያሳዝነው ነገር ከእነዚህ 20 የዩኒቱ አገራት መሀከል ይህንን የመሰለ በቀላሉ የማይወጣበት፣ አደገኛ ውጊያ ለማካሄድ አቅሙ፣ ስልጠናውም ሆነ ቁርጠኝነቱ የነበራቸው እጅግ በጣም ጥቂቶቹ ብቻ መሆናቸው ነው:: ከዚያ በላይ ደግሞ አሜሪካ ለዚያ

በጦርነት ክፉኛ ለተጎዳና ኢኮኖሚውም ለተደቋቆሰ አገርና ሕዝብ እጅግ ጥቂት ብቻ የሚባል የልማት እርዳታ ነው ያደረገችው:: ፕ/ት ሳዳም ሁሤንን በ «ዓለም ዓቀፍ የፀረ-ሽብርተኝነት ዘመቻ» በሚል የተጠጸደፈና የችኮላ ዘመቻ ለማውረድ በማቀድ ፕሬዚዳንት ቡሽ እና ሁለቱ የቅርብ ባለሟሎቻቸው ምክትል ፕሬዚዳንት ዲክ ቼኒ እና ራምስፌልድ የተባለው የመከላከያ ሚኒስትር ጦራቸውን ኢራቅን ለመውረር ይችል ዘንድ በፋርስ ባሕረ ሰላጤ ላይ አሰፈሩ:: ደግሞ በጣም የሚቆጨውና የሚያንገበግበው አንዱን የከፈቱትን ጦርነት ሳይጨርሱ በጥድፊያ እንደገና የከፈቱት አዲሱ የኢራቅ ጦርነት አሜሪካን እጅግ ውድ ዋጋ የሚያስከፍላት መሆኑ ነው:: የታከቲኩን ጉዳይ ስናነሳ እንዲህ ያለው ውሳኔ ከምንም በላይ በአል-ቃይዳ እና በታሊባን ላይ ተከፍቶ የነበረውን ትንፋሽና ጊዜ የማይሰጥ ግፊትና ዘመቻ ጋብ ያደረገው በመሆኑ ድርጅቶቹ በድጋሚ ለማንሰራራትና ራሳቸውን ለማጠናከር ጥሩ የትንፋሽ ጊዜ ማግኘታቸው ነው:: እናም በቀጣዮቹ 8 ዓመታት በመጠኑ እጅግ እየጨመረ የሚመጣ የአመጽና የሽምቅ ውጊያ ጀመሩ::

# ዓለም ዓቀፍ ጂሀድ

ዓል-ቃኢዳ «መሀከለኛው» ለቀጣዮቹ በርካታ ዓመታት በፓኪስታን ራሱን ሲያጠናክርና በድጋሚ ሲያደራጅ የቆየ ቢሆንም የተለያዩ የሴል ድርጅቶቹና ኔትዎርኮቹ ግን በምዕራቡ ዓለም ላይ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ የመጣ የሽብር ጥቃትና ጦርነት ለማወጅ ቻሉ:: እንዲያውም ብሩስ ራይዴል እንደተባሉ አንድ የቀድሞው የሲ.አይ.ኤ ተንታኝ ከሆነ ዓል-ቃይዳ ከ መስከረም 11ዱ ጥቃት በኋላ ባለ ሶስት አቅጣጫ ጦርነት ነው የከፈተው:: አንደኛው የአሜሪካን ጦር በማዳከም ጦርነቶች (ኢራቅና አፍጋኒስታን ውስጥ) ተጠምደው እንዲቆዩ ማድረግ ነው:: ሁለተኛው

በደቡብ እሲያ ያለውን መሠረቱን ማጠናከር ሲሆን ሶስተኛው ደግሞ «የመምረጥ ባለሙሉ መብት የሆኑ ደርጅቶች» የተባሉትን በተለያዩ የሙስሊም አካባቢዎች ማቋቋም ናቸው። እነዚህ «የመምረጥ ባለሙሉ መብት የሆኑ ደርጅቶች» (franchises) «ሐይማኖታቸውን የከዱ» በመባል የተፈረጁ እና በምዕራቡ ዓለም የሚገኙ መንግስታትን በተቻለ መጠን በቀላሉ በማይወጡት የጦርነት ጭቃ ውስጥ በመክተት ይፋለሟቸዋል። የዓል-ቃይዳ መሪዎች ስሌት ግን ከዚህም የዘለለ ነበረ። እነዚህ «ሐይማኖታቸውን የከዱ» በመባል የተፈረጁ መንግሥታት የሚቃጣባቸውን የሽብር ጥቃትና አደጋ ለመከላከል በሚመልሱት አፀፋ በአገራቸው በሚኖሩ አንዳንድ ተጠርጣሪ የሙስሊሙ ማኅበረሰብ አባላት ላይ ያልተፈለገ አደጋ ሊፈጠር ይችላል። ይህን ጊዜ ሙስሊሞቹ በሐይማኖታቸው ብቻ በመጠርጠራቸውና ለአደጋ በመዳረጋቸው ሳይወዱ በግዳቸው ዓል-ቃይዳን መደገፍ ይጀምራሉ፤ ከዚያም ሲያልፍ ደግሞ ኦሳማ ቢን ላደን ሁልጊዜ የሚለው ማለትም፤ «የአሜሪካ እና የሸሪኮቿ ዋንኛ ዒላማ ዓል-ቃይዳ ሳይሆን ራሱ እስልምና ነው፤» የሚለውን ክርክሩን ያጠናክርለታል።

አሜሪካ እንደ መስከረም አስራ አንዱ ዐይነት ሌላ ክስተት ቢፈጠር እያለች ገና ለሚቀጥሉት በርካታ ዓመታት እንቅልፍ አጥታ መዋተቷና መጨነቋ አይቀርም። ጥቃቱ የቱንም ያህል የከፋ ቢሆንም በዋናነት ግን አሜሪካና ምዕራቡ በፍርሀትና በሽብር እንደዋተቱ እንዲቀሩ አድርጓል። ካለፉት የሽብርና የአመጽ ድርጅቶች በተለየ መልኩ ዓል-ቃይዳ ዕድሉና አጋጣሚው ቢመቻችለት የጅምላ ጨራሽ መሣሪያ (WMD)ን ከመጠቀም ወደኋላ የማይል ነው። እነዚህ ደግሞ እንደ ኬሚካል፣ ጀርም፣ የኒውክሌር በምብ ወይንም ራዲዮአክቲቭ የሆኑትን ይጨምራሉ። ኬሚካል <u>ለመጀመሪያ ጊዜ በጥቅም ላይ የዋለው በአንደኛው የዓለም ጦርነት ወቅት</u>

ሲሆን በዚህ ጊዜም ታሪክ እንደሚነግረን የተበከለ ጋዝ ከበዛ ስቃይና መከራ በቀር ሌላ አንዳችም ፋይዳ አልነበረውም:: በሌላ በኩል የኬሚካል የጦር መሳሪያዎች ጠላትን እጅግ ውሱን ወደሆነ ቀጠና አታልሎ ማስገባት እስካልተቻለ ድረስ ብዙም ጥቅም የሌለው ነው:: በኬሚካል የጦር መሳሪያ አማካይነት ተፈጠረ ሊባል የሚችለው ብቸኛው ያለማችን የሽብር ጥቃት ቢኖር በ 1988 ዓ.ም. የጃፓናዊው አሸባሪ መሪ አውም ሺንክረዮ በቶኪዮ ሳብዌይ ላይ ሳሪን መልቀቁ ነው:: በዚህ ጥቃት 54 ንፁሀን ሕይወታቸው ሲቀጠፍ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሌሎች ደግሞ ቆስለዋል:: የባዮሎጂካል መሣሪያዎች ደግሞ ይበልጥ ጉዳትን የሚያደርሱ ነገር ግን ለመጠቀም ይበልጥ አደጋ ያላቸው ናቸው:: የባዮሎጂካል የጦር መሳሪያን ደፍሬ እጠቀማለሁ የሚል አንድ አሸባሪ በሽታው ወደራሱም አገር እንደሚዛመት እያወቀ መሆን አለበት:: እንዲህ መዘዝ ሳያመጣ መግደል የሚችለው ብቸኛ መሣሪያ ቢኖር አንትራክስ ነው:: ቢሆንም ከመስከረም 11 በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ እንዲህ ዐይነቱ ጥቃት ሲሰነዘር በቦታ በጣም ውሱን እና ብዙም ውጤት ያላመጣ ሆነ:: ትልቁ አደጋ ያለው የኒውክላር መሣሪያዎች ዘንድ ነው:: በቀዝቃዛው ጦርነት ወቅት ሶቪየቶች በሳምሶናይት መጠን የተሰሩ ኒውክላር ቦምቦችን የፈለሰፉ ሲሆን እነዚህ ደግሞ የአንድ ከተማን ልብ ያደባያሉ:: የጦር መሪም በኮንቴነር ወደተፈለገው አገር ይጋዛል:: ሌላኛው አማራጭ ደግሞ «ቆሻሻ ቦምብ» በመባል የሚታወቀው ነው:: ይህ የሬዲዮአክቲቭ ሲሆን በኮንቬንሽናል ፍንዳታ እጅግ ሰፋ ያለ ቦታ ላይ ይጣላል:: ችግሩ ግን ከዚያ በኋላ እዚያ ቦታ ላይ ሰዎች ለዓመታት ያህል ሊኖሩ አይችሉም:: ቢን ላደን በጅምላ ጨራሽ መሣሪያዎች ላይ ትኩረቱን እና ፍላጎቶቹን ያደረገው ከ 1991 ዓ.ም ጀምሮ መሆኑ ይታወቃል:: «የኒውክሌርና የኬሚካል የጦር መሣሪያዎችን ማግኘት ሐይማኖታዊ ግዴታ ነው» በማለት ነበረ የተናገረው::

# አል ቃኢዳ ካምሪንን በቦምብ ማጋየቱ

ዓል ቃኢዳ ከላይ እንደተመለከትነው የጅምላ ጨራሽ መሳሪያዎችን አግኝቶ ለመጠቀም የቱንም ያህል ቢጓምጥ በተግባር ግን እጅግ አዳጋች ሆኖበታል:: በመሆኑም በኮንቬንሽናል ቦምብ ለመጠቀም ተገደደ:: ይኼኛውም ቢሆን አደገኛና ጨራሽ ነው:: ከመስከረም 11ዱ ጥቃት በኋላ በነበሩት አራት ተከታታይ ዓመታት ወቅት የዓል-ቃይዳ ሴሎችና ረዳት ድርጅቶች ከኤሽያ ወደ አውሮፓ ገቡ:: አንድ የተሳካ የሽብር ጥቃት በተፈፀመ ቁጥር የምዕራባውያኑ የደህንነት ኃይሎችና የጸጥታ አባላት ምንም የማያውቀውን እየሄዱ ይመታሉ:: እነዚህን ጥቃቶች ለማምከን እየተባለ በቢሊዮን ዶላር የጠፉ ሲሆን ዛሬ በሚልዮኖች የሚቆጠሩት ዜጎች ደግሞ ሕይወታቸውና አኗኗራቸው በመጥፎ ሁኔታ እንዲቀየር ምክንያት ሆኗል::

ዓለም ዓል ቃኢዳ እንኳን ሊሞት በሞተ የሚስቅ ገና በደምብ አፍጥጦና አግጥጦ ያለ መሆኑን ለመረዳት ብዙ ጊዜ አልፈጀበትም:: ጥቅምት 12፣ 1995 ላይ ከዓል-ቃይዳ ጋር ንክኪ ካለው ጀማ-ኢስላሚያ የተባለ በኢንዶኔዢያ የሚገኝ የሽብርተኛ ድርጅት ባሊ በተባለው ሪዞርት ባለ የምሽት ክለብ ላይ አደጋ ጣለ:: በዚህ ጥቃት 202 ንፁሀን ሲረግፉ 100 ያህል የሚሆኑት ደግሞ ቆሰሉ:: ከሞቱት መሀከል ከፍተኛውን ቁጥር የያዙት የአውስትራሊያ ቱሪስቶች ናቸው:: ቢን ላደን ታዲያ ይህንን አረመኔያዊ ጥቃት ለማወደስ በብርሃን ፍጥነት የመጣ ሲሆን ምን እንዳነሳሳውም ገለፀ::

> *«ቀደም ሲል አውስትራሊያውያኖቹን እና መንግሥታቸውን በፀረ-ሽብሩ አርምጃ አትሳተፉ*

*ብለናቸው ነበረ። ኢስት ቲሞርን ለመገንጠል የሚያደርጉትንም ተዉ አልናቸው። ማስጠንቀቂያችንን ችላ አሉ፤ ከዚያም ዋጋቸውን በባሊ ሰጠናቸውና ከእንቅልፋቸው ተጨንባብበው ተነስተው እየደነገጡ ተመለከቱ።»*

(ቢን ላደን በቴፕ በተቀዳ መልዕክት
ለአልጀዚራ ቴሌቪዥን ኅዳር 2፤ 1994
ከተናገረው የተወሰደ)

በዓል-ቃኢዳ አማካይነት ስምንበር የተደረጉ ሌሎች ጥቃቶች ቀጠሉ። በዚሁ ወር ደግሞ ሩሲያ በሽብር ጥቃቶች ትናወጥ ገባች። እነዚህ ጥቃቶች ምንም እንኳ በቼቼንያ አማጺያን የተቀነባበሩ ቢሆንም በየቦምብ አደጋዎቹ ግን በዓልቃይዳ ስምንበር የተደረጉ እልያም ቀጥተኛ ድጋፍን ያገኙ እንደነበሩ ግን ይታመናል። በኅዳር ወር 1996 ላይ ዓል-ቃይዳ ጭራሽ በቱርክ ኢስታንቡል ጥቃቶች ፈጸመ። ኅዳር 5፤ 1996 ላይ አሸባሪዎች በሁለት ምኩራቦች ላይ ቦምብ ያጋዩ ሲሆን ኅዳር 10 ቀን ላይ ደግሞ HSBC በተባለው ባንክና በእንግሊዝ ቆንጽላ ጽ/ቤት ላይ ሁለት ተጨማሪ ቦምቦች ፈነዱ። በነዚህ ጥቃቶች 57 ሲቪሎች የተገደሉ ሲሆን ከ 700 በላይ የሚሆኑ ደግሞ ቆሰሉ። ኅዳር 6 ቀን ላይ ደግሞ ቢን ላደን በአልጀዚራ ወጥቶ ምኩራቦቹ ላይ ለደረሰው ጥቃት ኃላፊነቱን የወሰደ ሲሆን ለዚህ አቡ-ሀፍ የተባለው ብሪጌድ ከአል-ቃይዳ ጋር ለፈጸመው ለዚህ ጥቃት ምክንያቱን ሲሰጥም፤ «የእስራኤል የፀጥታ ጥበቃ አባላት እዚያ ይሰሩ ስለነበረ ነው፤» ብሏል።

እርግጥ እስከ አሁን ያየናቸው ሶስቱ ጥቃቶች ከምእራብ ራቅ ያሉ የሚመስሉ (ሞስኮ፤ ባሊ እና ኢስታንቡል) ቀጣዮቹ ግን ወደ አውሮፓ በደምብ የዘለቀ ሆኑ። መጋቢት 2፤ 1996 ላይ አሸባሪዎች በማድሪድ ስፔን

በርካታ ባቡሮችን በቦምብ በማጋየትና የአየር ማረፊያ ጣቢያን በማቃጠል 191 ሰዎችን ለሞት እስከ 600ና ከዚያ በላይ የሚሆኑትን ደግሞ ለቁስለት ዳረጉ:: እርግጥ የስፔን ፖሊሶች ባደረጉት መረባረብ ይህ የአሸባሪዎች ቡድን ባንድ ሕንፃ ውስጥ ለሁለተኛ ዙር ጥቃት ሲያሴርና ሲዘጋጅ ደርሰው ከብበውታል:: ግን ቡድኑ የቆረጠ በመሆኑ ለሌሎች ያዘጋጀውን ቦምብ አፈንድቶ ራሱን በራሱ አጠፋ:: ከአል-ቃይዳ ጋር ግንኙነት እንዳለው የሚታወቅ አንድ ቡድን በስፔን ለደረሰው ጥቃት ኃላፊነት የወሰደ ሲሆን ይህንንም ለማድረግ ያነሳሳው ስፔን አሜሪካ በመራችው የኢራቅ ወረራ ወቅት እገዛ በማድረጓ ነው ብሏል:: እንዲያውም ጥቃቱ በስፔን ከሚደረገው ምርጫ ጋር እንዲገጣጠምለት ነው ያቀደው:: ግን እንዳለመታደል ሆኖ የስፔን መራጭ ሕዝብ በደረሰው የቦምብ አደጋ ምክንያት ባይሆንም አሸባሪዎች የፈለጉትን አደረገ:: ፕ/ት አዝነርን በድምፁ ከስልጣናቸው አባረረና በቦታቸው ተመርጠው የገቡት አዲስ ፕሬዚዳንትም የስፔንን ኮንቲንጀንት ከኢራቁ ጣምራ ጦር ውስጥ አስወጡ:: የስፔን ሕዝብ ቀድሞውንም የፀረ-ሽብር እርምጃ ውስጥ መንግሥት መግባቱን አልደገፈውም::

በማድሪድ ይህን መሰሉ እጅግ የሚቀፍና የሚዘገንን የቦምብ ጥቃት ከደረሰ ከአንድ ወር በኋላ ቢን ላደን በሚዲያ ባሰራጨው መልዕክት አውሮፓውያን መንግሥታትን «ሰላም ብንሆን ይሻላል» የሚል ጥሪ አቀረበላቸው:: በዚሁ ጥሪውም ቢን ላደን ጥቃቶቹን ለመፈጸም ያነሳሱትን ምክንያቶች ገለፀ::

> *«ባሁኑ ሰዓት በግድ ተይዛ በምትገኘው ፍልስጤም በሆነው፤ በመስከረም 11 በተፈፀመው እንዲሁም መጋቢት 2 ላይ በደረሰው ሁሉ የምንቀስመው*

*ትምህርት ሰለ:: እኛ የምናደርጋቸው ጥቃቶች ሁሉ እናንተ የፈፀማችሁትን የተከተሉ ናቸው:: በኢራቅ፣ በፍልስጤም እና በአፍጋኒስታን ሕዝባችንን ለገደላችሁት ለእያንዳንዷ ደም ነው ዋጋ እየከፈላችሁ ያላችሁት::»*

ስፔን ጦሯን ከኢራቅ እንደምታስወጣ ይፋ ባደረገች ጊዜ ዓል-ቃይዳም በሀገሪቱ ላይ አንዳችም ተጨማሪ ጥቃት እንደማይደርስ አስታወቀ:: ይኼ ደግሞ ለሽብርተኞቹ ሌላ የሚፈንጥዙበት ትልቅ ድልን አጎናፀፋቸው::

በማድሪድ ከደረሰው ጥቃት አንድ ዓመት በኋላ እንግሊዝ ደግሞ ተረኛዋ የሽብር ጥቃት መደፍደፊያና ማራገፊያ ወደብ ሆነች:: እጅግ በጣም ምጥቀት ያለው አንድ የዓል-ቃይዳ ሴል በእንግሊዝ የትራንዚት ሲስተም ላይ ጥቃት ፈፀመ:: ሰኔ 30፤ 1997 ላይ በሎንዶን ምድርቤት ሶስት የአጥፍቶ ጠፊ ፍንዳታዎች ደረሱ:: አራተኛው ሰው ደግሞ በኋላ ላይ እገባበታለሁ ብሎ አስቦት የነበረው የሎንዶን ምድርቤት በደረሰው አደጋ ለአድሳት መዘጋቱን ሲያይ በታቪስቶክ አደባባይ ቦምቡን አፈነዳ:: በነዚህ ጥቃቶች 52 ንፁህን ለሞት ሌሎች እስከ 700 የሚደርሱ ደግሞ ለጉዳትና ለቁስለት ተዳረጉ:: ሶስቱ አጥፍቶ ጠፊዎች በእንግሊዝ ደሴቶች የተወለዱ ሲሆኑ አራተኛው ደግሞ ሕጻን ሳለ ከቤተሰቦቹ ጋር እንግሊዝ የገባ ነው:: ሁለቱ አጥፍቶ ጠፊዎች በኅዳር ወር 1996 እና የካቲት 1997 ላይ ወደ ፓኪስታን ተጉዘው የነበሩ ሲሆን እዚያም ሳሉ ምናልባትም ከዓል-ቃይዳ መሪዎች ድጋፍና ስልጠና ሳያገኙ እንዳልቀሩ ይገመታል:: ሰኔ 14 ላይ ደግሞ አንድ ሌላ ሴል በሎንዶን ምድርቤት ተጨማሪ ጥቃት ለማድረስ ተንቀሳቀሰ:: በዚህኛው ዙር ግን የቦምብ አደጋው የከሸፈ ሲሆን አሸባሪዎቹም ሙሉ በሙሉ በፖሊስ ቁጥጥር ሥር ዋሉ:: እነዚህ ምርኮኞች

በሰኔ 30 ጥቃት እጃቸው እንደሌለበት ቢያስተባብሉም ብዙ ተንታኞች ግን ጥቃቱ በዓል-ቃይዳ እንደታቀደ ይስማሙበታል፡፡

የቢን-ላደን ተከታይ አይማን ዓል-ዛዋሒሪ የደረሱትን ጥቃቶች አንድ ባንድ እያስታወሰ ያደነቀ ሲሆን እንግሊዝም አሜሪካን በፀረ-ሽብር እርምጃው እደግፋለሁ ብላ በመቆሟ ክፉኛ ኮንናት፡፡ ዛዋሒሪ፤

*«ከኒው ዮርኩ የመስከረም 11ዱ ድላችን እና የማድሪዱ ስኬት በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ የጣማምናቸው ድሎች ናቸው፡፡ እናም የተባረኩ ከላይ በጌታችን የተሰጡን ድሎች ናቸው፡፡ እንደሚታወቀው ለመቶ ዓመታት ያህል ታግለናቸዋል፡፡ ከቀዬያችን እና ከመሬታችን ላይ ልናስወጣቸው ጥረናል፡፡ በቼቺኒያ፤ አፍጋኒስታን፤ ኢራቅ እና በፍልስጤም መሬታችንን ይዘው ይገኛሉ፡፡ ይኼ እጅግ የተቀደሰ ነፃ የማውጣት የጥቃት ዘመቻ ግን ለቅድስናችን፤ ለእምነታችን፤ ለሃይማኖታዊ ክብራችን እና ለማንነታችን ሲሉ በጽናት ባደረጉት ተጋድሎ ውድ ሕይወታቸውን እስከመሰዋት በደረሱ ጀግኖች ወንድሞቻችን የተገኘ መሆኑና ከላይም ባርኮት ያለው መሆኑ ይታወቅ፡፡»*

እነዚህ ተከታታይ ጥቃቶችም ከመስከረም አስራ አንዱ በኋላ የደረሱ ከፍተኛ እና አሰቃቂ የሚባሉ እልቂቶች ሆነው ተመዝግበዋል፡፡ ጥቃቱ በደረሰ ጊዜ ማን ሊያቀነባብረው ይችል ይሆን የሚለው ብዙ አነጋግሯል፡፡ ለረጅም ጊዜ በብዙዎች «መሪ የሌላቸው ራስን የመከላከል እንቅስቃሴ» ካሉት በኋላ ግን ዓል-ቃይዳ ጥቃቶቹ በትክክል በማን፤ የት እና መቼ መድረስ እንዳለባቸው የወሰነ መሆኑ ታውቋል፡፡ በአፍጋኒስታን በተደረገው ወረራ ማግስት ብዙ እልቂት ከደረሰ በኋላም ዓል-ቃይዳ ግዙፉና ከባዱ የአሸባሪዎች ሴል ሆኖ ነው የቆየው፡፡ ከላይ ሆኖ ጥቃቶችን እና የተለያዩ

ኦፕሬሽኖችን ቢያቅድም የእነዚህን አፈፃፀም ግን ያቀነባበሩትና የተከታተሉት ከታች የሚገኙ ምስጢራዊ ሴሎቹ ናቸው:: ውስጣዊ አዋቂ ምንጮች ይፋ እንዳደረጉት ከሆነ በዓል-ቃይዳ በተግባር የሚታወቀው እና «የውሳኔ ሰጪነት ማዕከላዊነት እንዲሁም ያልተማከለ አፈፃፀም» የሚለው አሠራርና የማኔጅመንት ዘይቤ ዓል-ቃይዳን ውጤታማ አድርጎት ቆየ:: ይህ ግን ለምን ሆነ? በዋናነት የሚጠቀሰው አሜሪካ ቢን-ላደን እና ሌሎች መሪዎች ላይ እጅግ ከፍተኛ እና አስጨናቂ ክትትል ማድረግ በመጀመሯ እነሱም በምስራቅ አፍሪካ የኢምባሲ ጥቃቶች ወቅት እንዳደረጉት በቀላሉ ራሳቸው ኦፕሬሽኖችን መምራት ስለተሳናቸው ነው:: በዚህ የተነሣም የአገሬው የሆኑ ወኪሎቻቸው ላይ መተማመን ጀመሩ:: እንዲህ ዐይነቱ ስልጠና እና ልምድ ከዓል-ቃይዳ በ 1990ዎቹ ውስጥ ወስዶ ወደ አገሩ ተመልሶ ተጨማሪ ትዕዛዝ እስኪመጣ በተጠንቀቅ ይጠባበቅ በነበረው ወጣት ኃይል ነው የተከናወነው::

ከዚያ በኋላ ቡድኑ መስከረም 11 ቀን በኒው ዮርክ እንዲሁም ከዚያ በኋላ በተለያዩ ስፍራዎች የተጎናፀፋቸው ድሎች ተጨማሪ አዳዲስ ምልምሎችን እንዲያገኝ በር ከፈቱለት:: አዳዲስ ምልምሎች የሚገኙበት መንገድም የሚከተሉትን ዐይነት ነው:: ለምሳሌም በማድሪድ የባቡር ጣቢያውን በቦምብ ያጋየው ሰው ቀደም ሲል የአደንዛዥ ዕፅ አዘዋዋሪ የነበረ እና በዚህ የተነሣ ተይዞ ታስሮ ሳለ በሌሎች ሙስሊሞች በከፍተኛ ደረጃ አክራሪነት በውስጡ እንዲሰርጽ ከተደረገ በኋላ የተለቀቀ ነው:: በሌላ በኩል ደግሞ የለንደኑን የምድር ላይ ጥቃት የመራው መሐመድ ሳዲቅ ካን በሊድስ በሚገኘው የሰፈሩ መስጂድ ነው በአንድ ወጣት አማካይነት የተመለመለው::

# ኢራቅና አፍጋኒስታን

ከመስከረም 11 በኋላ ባሉት ስምንት ዓመታት አሜሪካ በዓል-ቃይዳ ምንም ጥቃት ደርሶባት አያውቅም። አሜሪካ ሌሎች ሲታመሱ ለረጅም ጊዜ እንዲህ ፀጥታ፣ ሰላሟ እና ደህንነቷ የተረጋገጠ ሆኖ መቆየቱ ብዙዎችን ሲያነጋግር ከርሟል። የቡሽ ደጋፊዎችና አስተዳደሩ አሜሪካ በቁርጠኝነት የተገበረችው የተጠናከረ የጥበቃ፣ የስለላ እና የሰላም ማረጋገጥ ሥራ በተያዙ ተጠርጣሪዎች ላይ የተወሰዱ ጥብቅ እርምጃዎች (ቶርቸርና ስቃይን ጨምሮ) ተዳምረው ያገኘ ውጤት እንደሆነ ነው የሚናገሩት። ተቃዋሚዎቻቸውና ሌሎች ግን ዓል-ቃይዳ በርካታ ወጣት አሜሪካውያን ወንድና ሴት ተዋጊዎች ለዚያውም በቀዬው በአፍጋኒስታን እና በጎረቤቷ ኢራቅ እንደቅጠል ሲረግፉ በየቀኑ እየተመለከተ ጂሀድን ለማሳካት ብሎ አሜሪካ ገብቶ መልፋት እንዳላስፈለገው ነው የሚሞግቱት። ተቃዋሚዎች በዚህ ብቻም ሳያበቁ ዓል-ቃይዳ ከደነበረ አውሬና ከሌሎች ሽብርተኞች በተለየ መልኩ ቀስ ብሎ በማድባትና ጊዜ በመግዛት የሚያምን ቡድን በመሆኑ መቆየቱን ይናገራሉ። ለዚህም መረጃ ሲጠቅሱ በ 1993 ዓ.ም በዓለም የንግድ ገበያ ማዕከል (ኒው ዮርክ መሆኑን ልብ ይሏል) ጥቃት ለማድረስ ሞክሮ ሲከሽፍበት መንታ ሕንፃዎቹን ማጋየት እስከቻለበት እስከ 2001 ድረስ ለስምንት ዓመታት በትዕግስት እያቀደና እያሴረ መቆየቱን ያሳያሉ።

እርግጥ ነው ጥበቃና ደህንነት ከመስከረም 11ዱ ጥቃት በኋላ በበርካታ ስፍራዎች ተጠናክሯል። ለምሳሌም የአገር ውስጥ ደህንነትና ፀጥታ ዲፓርትመንት (Security Homeland Department) የተባለው ከተቋቋመ በኋላ ከዚህ ቀደም ተበታትነው የቆዩ በደህንነት ላይ የተሰማሩ በርካቶችን ወደ አንድነት እንዲመጣቸውና እንዲጠናከራቸው ይገለፃል።

የመስከረም አስራ አንዱ ጥቃት ከመድረሱ ቀድሞ ብለው ባሉት ጊዜያት የደህንነት ጥበቃውን አስመልክቶ አሜሪካ የነበረባት አንድ ትልቅ ችግር በFBI እና በCIA መሀከል የረባ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት አለመዘርጋቱ ነው:: ከዚህ ጥቃት በኋላ ግን የመረጃ ልውውጥ፣ ፍሰትና ትብብር ተጠናከረ:: በሌላ በኩል አንዳንዶች አሜሪካ በጓንታናሞ-ቤይ እስረኞች ላይ እጅግ የሚቀፍና ኢ-ሰብዓዊ ቶርቸር በማድረስ የአውጣጪኝ ምርመራ በማድረጓ የተገኘው መረጃ የተለያዩ ጥቃቶችን አስቀድሞ አውቆ በማጨናገፍ ሚና ተጫውቷል ብለው ቢሞግቱም እንዲህ ያሉ መረጃዎች ግን በምስጢር የሚቀሩና ወደ ውጭ የማይወጡ በመሆኑ የዚህን ሙግት እውነታነት ማረጋገጥ አይቻልም:: ከዚያ ሌላ ግን እስረኞችን ለከፉ ስቃይና ተነግሮ ለማያልቅ የሰብዓዊ መብት ረገጣ በመዳረግ በዓለም ላይ የገዛ ስምን አጉድፎ፣ በዓለም ሕዝብ ፊትም ተቃውሞን ቀስቅሶ ተገኘ የሚባል ማንኛውም ጥቅም በሚዛን ላይ ወጥቶ ሲታይ እጅግ የቀለለ ነው የሚሆነው::

እንደ አንዳንድ ግልጽ የሆኑ ምንጮች ከሆነ አሜሪካ የዓል-ቃይዳን በዓለም ዙሪያ የሚደረጉ አፕሬሽኖች በማዛባትና መሠረቱን በመቀየሩ ረገድ የተወሰነ ስኬት አግኝታለች:: በ2004 የለንደንን ትራንዚት ሲስተም በቦምብ ያጋዩት አሸባሪዎች እጅግ የተዋጣለት እቅድን ባማተር ደረጃ ብቻ ካለው አፈጻፀም ጋር ነው ያቀናጁት:: በደረቁ ሲያቅዱት የነበረውን እና በወረቀት ላይ ጥሩ ሰርተውት የመጡትን ስትራቴጂ ውደ አፈፃፀም በሚገቡበት ጊዜ አጉል ከሚገባው በላይ በመፍጠን ከዋናውና እውነተኛው ጥቃት ቀድመው በመግባታቸው የለንደኑ ምድርቤት አራተኛውና ተከታያቸው የሚገባበት ከመሆኑ አንፃር በአደጋው ለጥገና የመዘጋቱ ነገር ትዝ ሳይላቸው ቀረ:: እናም በችኮላ ሁለቱን ቦምቦቻቸውን ላዩ አካባቢ ሲያፈነዱ እዚያው ግድም

ያሉ ትራኮች የፍንዳታውን ኃይል ሊያለዝቡት ችለዋል። ከ52 ያህሉ ጉዳቶች 26 ያህሉ ወይንም ግማሹ በተኑል ውስጥ ይጓዝ በነበረ ባቡር ላይ ነው የተከሰተው። ዒላማዎቻቸውን በጥንቃቄ የመምረጥ ስራ ሰርተው ቢሆን ኖሮ ከዚህ የበለጠ ጉዳት ሊያደርሱ በቻሉ ነበረ። ሐምሌ 14 ቀን ሁለተኛው ጥቃት ሊከሽፍ የቻለው ለፍንዳታው የተጠቀሙበት ቅልቅል እጅግ ጊዜ ያለፈበት በመሆኑ ነበረ። እንግዲህ እንዲህ ጊዜ ባለፈበት ፈንጂና ቅልቅል መጠቀም፣ ዕቅድን በሚገባ ለማሳካት አለመቻልና ዝርክርክነት አማተር የሆነ አሠራር ተጨምሮበት የሚያመለክተው ትልቁ ቁምነገር ቢኖር ዓል-ቃይዳ በዓለም ዙሪያ ብቃት ያላቸውና ሊተማመንባቸው የሚችሉ ኔትዎርኮችን መዘርጋት ተስኖት እንደቆየ ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ እነዚህን መሰሎቹ ስኬቶች በዓል-ቃይዳ ላይ ቢገኙም የእንግሊዝ የስለላና ደህንነት ሲስተም ደግሞ በርካታ ችግሮች የተበተቡት ሆኖ ቆይቷል። የሎንዶኑ ፍንዳታ ከመከሰቱ ከአንድ ዓመት በፊት M15 የተባለው የእንግሊዝ የስለላ አገልግሎት በምስጢራዊ ኦፕሬሽን በርካታ አሸባሪዎችን አሰረ። ግን በጣም የሚያሳዝነው ነገር ከእነዚህ "Crevice" በተባለው ዘመቻ ከታሰሩት ውስጥ ሁለቱ ናቸው በኋላ የምድርቤቱን ቦምብ የሚያፈነዱት። M15 የተባለው ድርጅት እነዚህን ሲለቅ «በራሳቸው ቦምብ ለማፈንዳት ብቃትም ሆነ እምነት የሚጣልባቸው ባለመሆናቸው» ብሉ ተሞኝቶ ነው። በ2003 በቁጥጥር ሥር ውለው የነበሩት አሸባሪዎች ምናልባትም የእንግሊዙን የዓል-ቃይዳ ጥቃት ያቀነባበሩት ይሆናሉ። ባይታሰሩ ኖሮ ከአንድ ዓመት በኋላ የተፈፀመው ጥቃት ከዚያም በባሰና ትልቅ ጉዳት ባስከተለ ነበረ። M15 የተባለው ድርጅት እነዚያን ሁለቱን ሰዎች ከራዳር እይታው ውጭ እንዲሆኑ መሳሳቱ ጥፋት ነው። ከዚያ በተጨማሪ ደግሞ በአፍጋኒስታን 2000 ያህል ዜጎቹን አሰማርቶ ቢያስስም ፈጽሞ ሊያገኛቸው አልቻለም።

በሌላ በኩል አሜሪካ እጅግ በጣም አስደናቂ ድሎችን የተጎናፀፈች ሲሆን በርካታ የአሸባሪ አፕሬሽኖችን አጨናግፋለች። በቁጥጥር ሥር ካዋለቻቸው መሀከል በዋናነት የሚጠቀሰው ካሊድ ሼህ መሐመድ ነው። ይህ ሰው የመስከረም 1ዱን ጥቃት ሲያቀነባብር የነበረ ነው። የካቲት 221 1996 የፓኪስታኑ Inter-Services Intelligence Directorate ከሊ.አይ.ኤ. ጋር ባደረገው ትብብር መሐመድን በራዋልፒንዲ ፓኪስታን በቁጥጥር ሥር ሊያውለው ችሏል። መሐመድ ከዚህ በኋላ ወደ አሜሪካው የጓንታናሞ-ቤይ ተላልፎ የተሰጠ ሲሆን በባልዲና ጋን ውሃ ውስጥ በጣም ለበርካታ ጊዜያት መድፈቅና ማስቃየትን ጨምሮ ሌሎች በርካታ ኢ-ሰብዓዊ ድርጊቶችን ያካተተ አስጨናቂ ምርመራ ተካሂዶበታል። ይህ ሰው በደረሰበት ስቃይና እንግልት የተነሳ ለመገላገል ሲል ጠቃሚ መረጃ ሰጥቶ ሊሆን ቢችልም ምን ዓይነት መረጃ ሰጠ? ወይንም የቱን ያህል ጠቃሚ ነበረ? የሚሉት ግን ልናውቃቸውም ሆነ ልናረጋግጣቸው የምንችላቸው አይደሉም። በየካቲት ወር 2001 ዓ.ም አሜሪካ መሐመድን በተለያዩ የግድያ እርከን ወንጀሎች ከሰሰች። ባለፈው 2002 በኒው ዮርክ ለፍርድ ቀርቦ የነበረ መሆኑም ይታወቃል።

እጅግ እየተሻሻለ የመጣ የደህንነት ጥበቃ፣ የተሻለ የስለላ ስራ እና የዓል-ቃይዳ ቀንደኛ አባላትን በተለያዩ ጊዜያት በቁጥጥር ሥር ለማዋል መቻልን የመሳሰሉት ነገሮች ግን በራሳቸው ለምን አሜሪካ ለረጅም ጊዜ ከመስከረም 11ዱ መሰል ጥቃት ነፃ ሆና ልትቆይ እንደቻለች አይገልፁም። ቢን ላደን እና ጓደኞቹ ያንን ጥቃት ሲፈፅሙ ዋንኛው ያነሳሳቸው ነገር አሜሪካን ሆነ ብለው አፍጋኒስታንን እንድትወር ለማድረግ ነው። አሜሪካ ኢራቅንም ጨምራ ልትወር እንደምትችል ፈጽሞ ባይገምቱም ወረራውን ስትፈጽም ግን በደስታ ተቀበሉት። ዓል-ቃይዳ እና ተጠርጣሪዎቹ በነዚህ በተወረሩ አገራት ውስጥ ያሉ አሜሪካውያን ላይ አዲስ ጥቃት ሊከፍቱ

ይችላሉ:: ግን በሌላ በኩል ደግሞ አሜሪካ ለስምንት ዓመታት ያህል ከመስከረም 11ዱ ጥቃት በኋላ ሽብር ባይቀነባበርባትም ያ ወደ ሌሎች የምዕራብ አውሮፓ አገሮች ሄዶ ሲፈፀም ተመልክተናል:: ይህንን መሰሉን ነገር ስንመለከት አንድ ማሰብ ያለብን ነገር ባለፉት ስምንት ዓመታት የዓል-ቃይዳ ስትራቴጂ መቀየሩን ነው:: ኦሳማ ቢን ላደን በአሜሪካ መሰል ጥቃቶችን ቢፈጽም ወይንም ሊያቅድ ቢችል ደስ ባለው ነበረ፣ ነገር ግን ከዚያ ይልቅ ቀለል ያለውና አመቺው በኢራቅና አፍጋኒስታን ላይ እንዲሁም አውሮፓዊ በሆኑ የፀረ-ሽብር የአሜሪካ ሸሪኮች ላይ ማተኮሩ በመሆኑ ነው::

ኦሳማ ቢን ላደን የኢራቁን ጦርነት አስመልክቶ በርካታ መግለጫዎችን ሰጥቶ ያውቃል:: ጥቅምት 7 ቀን 2005 ላይ በአል-ጀዚራ ቴሌቪዥን ለአሜሪካውያን መልዕክት አስተላልፏል:: በዚህ መልዕክቱም የቡሽ አስተዳደር በኢራቅ ላይ ወረራ የፈፀመው የአገሪቱን የነዳጅ ሀብት ለመቀራመትና የፅዮናውያኑን ፍላጎት ለማሳካት ነው ብሏል:: «እምነትን የካዱ» በማለት የጠራቸው የአሜሪካ ቅጥረኛ ወታደሮች የገቡበትን የጦርነት ጭቃ ያብራራው ይኼ መግለጫ አሜሪካና ሸሪኮቿ ከዚህ በኋላ ለሚፈጽሙት ማንኛውም ጥቃት የጀቸውን እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ማመቻቸቱን አመልክቷል:: አሜሪካ በአፍጋኒስታን እና በኢራቅ ላይ ወረራ መፈጸሟ አምላክ ማንነቷን ለዓለም ያጋለጠበት መሆኑን የጠቀሰው ቢን ላደን ንግግሩን በመቀጠል ወረራው ጂሀድን ለማጠናከርም እንደረዳቸው አልሸሸገም::

> *«ቅዱስ አምላካችን አሏህ እሱን [ቡሽን] ወደ ካሊፌቶች መዲና፣ ከማር ይልቅ ሞትን ወደሚመርጡት ጀግና ሕዝቦቻችን ምድር ያመጣው ለዚሀ ነው:: እነሱም [ኢራቃውያን] አገኙት ያለውን ትርፍና ድል ሁሉ*

> *ወደ ሲኦል ቀዮሩብት። እናም አሁን ከሚችለው በላይ ተዋርዶ ወደ አገሩ መመለስን ነው የሚፈልገው።»*

ቢን ላደን በዚህም ሳያበቃ በአውሮፓ የቡሽ አጋሮች ላይ ወቀሳና ዛቻ ሰንዝሯል።

> *«ብማናቸውም ወረራ በመፈፀም እገዛ በሚያደርጉ ሀገራት ለምሳሌም እንደ እንግሊዝ፣ ስፔን፣ አውስትራሊያ፣ ፖላንድ፣ ጃፓን እና ጣልያን ያሉት ላይ ጥቃት ለመፈፀም መብቱ አለን።»*

ቢን-ላደን ፎክሮ አልቀረም። ቀደም ሲል እንዳየነው የባሊውን አሰቃቂ ጥቃት በማስፈጸም አውስትራሊያን ተበቀለ። በማድሪድም ያየነውን ዘግናኝ የባቡር ግድያ አስፈፀመ። ከአንድ ዓመት በኋላ ለንደንን በጥቃት አጥለቀለቃት። ከዚያ በኋላም ቀደም ሲል እንዳየነው ስፔን ከጣምራ ጦሩ «በቃኝ» ብላ ወጥታለች። ቀደም ሲል እንዳየነው የስፔን ሠራዊት ከጣምራ ጦሩ የወጣው በምርጫ መንግሥት ስለተቀየረና ሕዝቡ ራሱም ቀድሞውኑ ጣምራ ጦሩ ውስጥ መግባቱን ስላልደገፈው እንጂ ዓል-ቃይዳ ስላስፈራራቸው አይደለም። እንዲያም ሆኖ ግን ዓል-ቃይዳ የስፔንን እርምጃ እንደ ድል ቆጠረው። ጣልያን ደግሞ በኢራቅ 12 ወታደሮቿ ከተገደሉባት በኋላ ጣምራ ጦሩን ለቃ ወጥታለች።

በ2008ቱ ፕሬዚደንታዊ ምርጫ ዋዜማ ቢን-ላደን በድጋሚ ለአሜሪካ ሕዝብ መልዕክቱን አስተላለፈ። አሜሪካውያኑ የመንግስታቸውን የተጣመመና የተበላሸ ፖሊሲና ስትራቴጂ እንዲፋለሙ ጠየቀ። ዓል-ቃይዳ ለወደፊቱም ያሰበውን የማዳከም እርምጃና ዕቅድም ገለፀ።

*«እኛ ምንም አላደረግንም። አላዩ ላይ አል-ቃይዳ የሚል ጽሁፍ የያዙ ምስራቁ ራቅ ያለ አፗራማ ክፍል ላይ በሁለት ሙጃሂዲኖች አስይዘን ሰቀልን—ቢቃ! ቡሽ ግን በሺዎች የሚቆጠሩ ወጣት ሰራዊቱን አሰማርቶ ለከፍተኛ የሰው፣ የማቴሪያል፣ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ኪሳራ በገዛ እጁ ራሱን ዳረገ። ከዚያ ሌላ መጥቀስ የምፈልገው ደግሞ እኛ የማዳከም ጦርነትን ለመቀጋት ባደረግነው ጥረት የጎረላ የውጊያ ስልትን እየወቅነውና እየተለማመድነው መምጣታችንን ነው። ለእሷህ ምን ይላሉዋል? በ1989 ዓ.ም ያቺን እጅግ ያስቸገረችንን ሩሲያ በአፍጋኒስታን አፈር ድባቁ አብልተን በኪሳራ አስወጣናት። አሁንም ምንም የተለወጠ ፖሊሲ የለንም። ስለዚህ አሜሪካ የሩሲያ ዕጣ ፈንታ ደርሷት ውርደትን ተከናንባ መውጣቷ የጊዜ ጉዳይ ብቻ ነው የሚሆነው።»*

ቢን ላደን ይህንን ንግግሩን ካደረገ በኋላ ግን ለአንድ ዓመት ያህል ጊዜ ከማንኛውም ሚዲያ ርቆ ቆየ። ከዚያም በጥር ወር 1998 በለቀቀው በድምጽ የተላከ መልዕክት አሜሪካውያንን «ሰላም እንፍጠር» ሲል የሚለምን መሰለ። ቡሽ ጦሩን ከኢራቅ እና አፍጋኒስታን ካስወጣ ዓል-ቃይዳ በአሜሪካና በመሰሎቿ ላይ የከፈተውን የሽብር ዘመቻ ያቆመዋል አለ።

*«በኢራቅ የተከፈተው ጦርነት ይኸው ማለቂያና መቋጫ አጥቶ [ለጊዜው ሊታይ በሚችል ሁኔታ]*

*እየቀጠለ ይገኛል:: በአፍጋኒስታን ለአጋሀ ምሲጋና ይግባውና ሚዛኑ ወደ እኛ ነው ያጋደለው::»*

በዚህ ንግግሩ ቢን ላደን ጦርነቱ በአሜሪካ ላይ ያስከተለውን ኪሳራ ገልጿል::

*«የራሳችሁ ፔንታጎን በየጊዜው የሚለቃቸው መረጃዎች ወታደሮቻችሁ ይበልጥ እያለቁ መሆኑን ያሳያሉ:: ትልቁን የኢኮኖሚ ኪሳራ እንኳ መተው ሳይሻል አይቀርም:: በሠራዊታችሁ ሞራል ላይ የደረሰው ነገርም ማሳያ ይመስለኛል:: ስንቶቹ ወታደሮቻችሁ ራሳቸውን በራሳቸው ሲያጠፉ ተመልክታችኋል»*

እዚህ ጋ የተወሰኑ ነገሮችን ማለት ይቻላል:: በንግግሩ ሊጠቅስ እንደሞከረው ጦርነቱ በኢራቅም ሆነ በአፍጋኒስታን በጥሩ ሁኔታ አልሄደም:: ነገር ግን «ሰላም» ያለውን ነገር ዋይት ሐውስም ሆነ የአሜሪካ ሕዝብ ይቀበለኛል ብሎ ቢን ላደን የተጥኘ አይመስለንም:: አሁንም ልክ እንደበፊቱ በሙስሊሙ ዓለም ያሉ አንዳንዶች ናቸው ከምር የወሰዱት:: እሱም ሁሌ የዓል-ቃይዳን ዓላማ ከእስልምና እና ከነፃነት ጋር በማቆራኘት ነው ልባቸውን የተቆጣጠረው::

## ዓል ቃኢዳ የፈጠረው ስጋት

ዓል ቃኢዳ ይበልጥ ምስጢራዊ በመሆን እና የኦፕሬሽን ስልቱን በመቀየር ይበልጥ እየተደረጀና እየጠነከረ ሲመጣ መረጃ ማግኘቱ ለተሩላሚዎቹ አስቸጋሪ ሆነ:: እንዲህ ያሉትና ሊገኙ የሚችሉ መረጃዎችን በመንተራስ ልንደርስባቸው የምንችላቸው ማናቸውም ዓይነት ድምዳሜዎች ብዙ ዘላቂ አይሆኑም:: ይኸው ዛሬ መረው ተገድኋል፤ የሞራል ኪሳራ

ደርሶበታል ካልተባለ በቀር ዓል-ቃይዳ ከተመሰረተ በ 20 ዓመቱ እንዲሁም በአሜሪካ ኒው ዮርክ እጅግ ትልቅ የጥቃት ስኬቱን ከተቀዳጀ ከ 9 ዓመታት በኋላም ቢሆን አስፈሪ የዓለማችን የሽብር ኃይል ነው፡፡ ዓል-ቃይዳ «መሀከለኛው» በማለት የሚታወቀው የድርጅቱ ክንፍ መንግሥታት ፈጽሞ ሰላምና መረጋጋት እንዲሁም አስተዳደር በማስፈን ሊቆጣጠሯቸው በማይችሏቸው የፓኪስታን እና የአፍጋኒስታን አዋሳኝ ቦታዎች መሀከል ዛሬም ተጠናክሮ አለ፡፡ በቢን ላደን ሞት ጥቂት መደነቃቀፎችና ድንጋጤ ለጊዜው ቢፈጠርም ይህ ድርጅት ከታሊባኖች ጋር በመተባበር በፓኪታን እና በአፍጋኒስታን የተጠናከረ ጥበቃ፣ ሰላምም ሆነ መረጋጋት እንዳይኖር ተግቶ እየሰራ ነው፡፡ ድርጅቱ በዚህም ብቻ ሳይወሰን አሁንም ቢሆን ወደ ሌሎች የዓለም ክፍሎች ጥቃት መፈጸም ይችላል፡፡ እርግጥ ይህ ሲባል በምሥራቅ አፍሪካው የኤምባሲ ጥቃት ያሳየውና የመስከረም 11ዱ ብቃት በምዕራባውያኑ መጨናገፋና መዳከሙ እንዳለ ሆኖ ማለት ነው፡፡

ባራክ ሁሤን ኦባማ በ2008 ኅዳር ወር ላይ ፕሬዚዳንት ሆነው የዴሞክራቲክ ፓርቲውን ወክለው ወደ ስልጣን መምጣታቸው በአሜሪካ ፖሊሲ ላይ ለውጥን ማሳየቱ አይካድም፡፡ ኦባማ ወደ ስልጣን ሲመጡ በኢራቅና በአፍጋኒስታን ያሉ የሠራዊቱን አባላት ቁጥር ቀንሰዋል፡፡ አሜሪካ እንደ በፊቱ ጣልቃ እየገባች ለኪሳራ ከምትዳረግና ኃይሏን ከምታባክንም የፓኪስታን መንግሥት በገዛ አገሩ ላይ ዓል-ቃይዳ ከታሊባኖች ጋር እንዳይፈነጭ ጥብቅ ቁጥጥር ማድረግ እንዳለበት ከማስገንዘብ አልቦዘነችም፡፡ በ2009 አጋማሽ ላይ የፓኪስታን ጦር ከአፍጋኒስታን ጋር በሰሜን ምዕራብ አዋሳኙ የስዋት ሸለቆ ቦታ ላይ ታሊባኖችን ለማጥቃት ከፍተኛ ዘመቻ ከፈተ፡፡ በዚያው በ 2009 ሐምሌ ግድም ወደ 4000 የሚጠጉ የአሜሪካ የባሕር ኃይሎች ከአፍጋኖች ጋር በመተባበር ሄልሙድን ለመቆጣጠር ሲፋለሙ ፓኪስታኖች ደግሞ ወደ

ድንበራቸው አምልጦ የሚመጣውን አሸባሪና ሴሎች ለመቆጣጠር ሲሉ ዘግተው ጠበቁ። ይህ ጥቃት የአሜሪካ ወታደሮች ብዛት በ 20,000 እንዲጨምር ከተደረገ በኋላ የመጣ ሲሆን "Clear and hold" የሚል ስያሜም ተሰጥቶታል። በ2009 ማብቂያ ግድም ፓኪስታኖች በታሊባን ለረጅም ጊዜ ተይዛ የቆየችውን ደቡብ ዋሪስታንን መቆጣጠር ችለዋል።

ነገር ግን ይህ ሁሉም ሆኖ የዓል-ቃይዳን በዐለም ዙሪያ የተሰማሩ ኃይሎች፣ ሴሎችና የምስጢር ድርጅቶች ኔትወርክ ሁኔታ ለማወቅ መሞከር የ «ማዕከላዊው»ን ድርጅት ውስጣዊ አሰራርና ጥንካሬ ለመፈተሽ ከሚደረገው እስጨናቂ ጥረት ያልተናነሰ ፈተና ነው የሚሆነው። እርግጥ ነው በቋሚነት፣ በተከታታይነት እና በፍጹም ምስጢራዊነት አሜሪካ በልዩ ኃይሏ የፈፀመችበት የማዳከም እርምጃ ብቃቱን በእጅጉ ጎድቶት በፊሊፒንስ ጨርሶ መንቀሳቀስ የማይችል እንዲሆን አድርጎታል። በኢንዶኔዥያም ቢሆን ከባሊው አሳዛኝ አደጋ በኋላ የእስልምና አክራሪነት ድጋፉን እያጣ ነው የመጣው። በሌሎች አካባቢዎች ግን አልቃይዳ ቢሻሻልና ቢያድግ እንጂ አልተዳከመም። በአውሮፓ ውስጥ የተመለከትን እንደሆን ያላቸውን ዝቅተኛ ደረጃ እና በዜግነታቸው የተነፈጓቸውን ነገሮች በሚቃወሙ የሁለተኛው ትውልድ አባላት የሚያነሷቸው የተለያዩ ቅሬታዎች አሳሳቢ ናቸው። በርካታ የፖለቲካ ተንታኞች በነዚህ አካባቢዎች የሽብር ጥቃቶች በቁጥር፣ በዓይነትና በመጠን በቀጣዮቹ አሥር ዓመታት እየጨመሩ እንደሚሄዱ ይጠብቃሉ። ለምሳሌም *Die Welt* (በእንግሊዝኛ ትርጉሙ The World) የተባለው ጋዜጣ በጀርመን በ2008 የፕሬዚዳንታዊ ምርጫ ከመካሄዱ አስቀድሞ ምናልባትም የሽብር ጥቃት የመቃጣቱና የመሞከሩ ነገር ዕድሉ የሰፋ እንደሆነ ግምት ሰጥቷል። እርግጥ እነዚህ የተባሉት ጥቃቶች ሳይከሰቱ ቀርተዋል። የሆነው ሆኖ ግን ዓል-ቃይዳ በቅርቡ በምዕራብ አውሮፓ ጥቃት ሊፈጽም እንደሚችል ግን ይገመታል።

ከዓመጽና ከኃይል የፀዳ ወይንም ሰላማዊ (Non-violent) እስልምናም በቱርክ እጅግ እያደገ እና እየተጠናከረ መጥቷል:: እርግጥ እንዲህ ዐይነቱ እስልምና በምርጫ ድምጽ መስጫ ሳጥን ወይንም ኮረጆ በለስ በቀናው ቁጥር ከሸብር እየራቀ እንደሚመጣ እሙን ቢሆንም በዚያች አገር ውስጥ ሃይማኖታዊ ያልሆነውን የመንግሥት ሥርዓት (Secularism) በማካሄድና በመምራት በታሪክ የሚታወቁት ማለትም የቱርክ ጦር አባላት ልክ ከዚህ ቀደም እንዳደረጉት ቁጥጥራቸውን ካሰፉ ሁኔታዎች ወዳልተፈለገ አቅጣጫ ሊያመሩ ይችላሉ::

አፍሪካ በቅርብ ዓመታት የእስልምና አክራሪነት እያደገና እየተጠናከረ ሲመጣባት ተስተውሏል:: በማግሬብ የሚገኘው ዓል-ቃይዳ ማለትም ከዓል-ቃይዳ ጋር ግንኙነት ያለው ድርጅት በሰሜን አፍሪካ አብዛኞቹ ቦታዎች በጂሀድ ጦርነት መሪዎች መሀከል ግንኙነት እንዲፈጠር እያደረገ ይገኛል:: በሌላ በኩል ሶማልያ ላለፉት ሁለት አሥርት ዓመታት ያህል መንግሥት-አልባና እጅግ የወደቀች (failed state) ሆና የቆየች ስትሆን የእስልምና አክራሪዎችም አብዛኛውን የደቡብና የመሀከለኛውን የአገሪቱን ክፍል በመቆጣጠር ላይ ይገኛሉ:: የባሕር ላይ ሽፍቶችና ወንበዴዎች እጅግ እየተበራከቱ መምጣታቸውም የጂሀድ መሪዎችና አክራሪዎችን መጠናከር ያሳያል:: በሶማልያ የነበረው የዓሣ ኢንዱስትሪ እየተዳከመ መምጣቱና አሁን ደግሞ ጭራሽ መንኮታኮቱ ለባሕር ላይ ወንበዴነትና ዘረፋ ትልቅ አስተዋፆ አድርጓል:: ወጣቶችም ዓሣ ኢንዱስትሪው ሲቀር ወደ ወንበዴነቱ ጭልጥ ብለው ይገባሉ:: እነሱ በሚያደርጓቸው ነገሮችም በመበረታታት አክራሪዎች መፈንጨት ይጀምራሉ:: በተለይም የእንዲህ ዓይነቱ የሽብርተኝነት እንቅስቃሴ ወደ ጎረቤት ኬንያ የመዛመቱ ዕድል ሰፊ ነው ተብሎ አሁንም ይታመናል::

ነገር ግን ከዓል-ቃኢዳ በኔትወርክ መጠናከር በላይ ይበልጥ አስፈሪ የሆነው የርዕዮተ ዓለም ጥንካሬው ነው። ኦሳማ ቢን ላደን እስከ ዕለተ ሞቱ ድረስ በበርካታ የአረብ አገራትና በእስልምናው ዓለም የነበረውን ታዋቂነትና ተወዳጅነት እናስታውሳለን። ከመስከረም 11ዱ ጥቃት በኋላ ቀደም ሲል ጋዜጠኛ አሁን ደግሞ ወደ ፀሀፊነት የተሸጋገረው ሪክ ሞሬና በናይጄሪያ በነበረ ጊዜ አንዱ ወጣት የቢን-ላደን ምስል ያለበትን ቲ-ሸርት በግልጽ ለብሶ ሲሄድ የተመለከተ ሲሆን ከስሩ የነበረው ጽሁፍም «ጀግናችን» ይል እንደነበረ ያስታውሳል። አሜሪካ ደግሞ በድሆች፣ የተገፉ እና የተጨቆኑ ዜጎች ዘንድ ይህ አመለካከት ተቀባይነት እንዳይኖረው ለማድረግ ሞክራ አልተሳካላትም። ከመስከረም አስራ አንዱ ጥቃት በኋላ በነበሩት ሰባት ዓመታት አሜሪካ ባንድ በኩል ነገሮችን በማክረር፣ በሌላ በኩል ደግሞ ሁሌም በራሷ ብቻና ሰብዓዊ መብት እና ክብርን እየረገጠች በምታካሂዳቸው ነገሮች ሕዝብ ይበልጥ ሲበሳጭና ቁጣውን ሲገልጽባት ነው የተስተዋለው። ሆኖም ምናልባት ነገሮች እየተለወጡ ነው ብለን እናስባለን። ሰኔ 5፣ 2008 ላይ ፕ/ት ባራክ ኦባማ በእስልምናው ዓለም ታሪክ እጅግ ትልቅ ቦታ ባለው የካይሮ ዩኒቨርሲቲ ለሙስሊሙ የዓለም ሕዝብ አንድ ንግግር አደረጉ። በአሜሪካና በሙስሊሙ ማህበረሰብ መሀከል አለመተማመን ሰፍኖ መቆየቱን ያመኑት ፕሬዚዳንቱ አሜሪካ ሽብርተኝነትን ለመዋጋት ያላትን ቁርጠኝነት እና ከእስራኤል ጋር ያላትን ታሪካዊ ትስስር እንደምትገፋበት በመግለጽ ከሙስሊሙ ማህበረሰብ ጋር ግን የተሻለ ግንኙነት እንዲኖራት አጥብቃ እንደምትሻ ገለፁ።

*«ውድ ወገኖቼ ሆይ! በዛሬዋ ታሪካዊ ዕለት እዚሁ ካይሮ የተገኘሁት በግንኙነታችን አዲስ የሚባል*

*ምዕራፍ እንዲከፈት በመሻት ነው:: ይህ አዲስ ግንኙነት ደግሞ በሁለትዮሽ መከባበር እና ጥቅም ላይ የተመሰረተ እንዲሁም አሜሪካ እና እስልምና ጠላት እንዳልሆኑና አንዱ ሌላው የሚያስፈልገው እንደሆነ በማመን ላይም ጭምር የተመሠረተ ነው የሚሆነው::»*

ፕሬዚዳንቱ ይህንን ሲናገሩ እዚያው ሆኖ ያዳምጣቸው የነበረው ተመልካች ታላቅ ድጋፍ ቸሯቸዋል:: ሆኖም ነገሩ ወደ ሚዲያውና ወደ ቀሪው የዓለም ሕዝብ ሲወጣ የተደበላለቁ አፀፋዎች ታዩ:: በሙስሊሙ ዓለም በምሁርነትና በተንታኝነት የሚታወቁ ሰዎች ጥንቃቄ በተሞላበት መንገድ ንግግሩን ገምግመው ነገር ግን ቃላት ወደ ተግባር ሲለወጡ ለማየት እንደሚሹ ገለፁ::

ይህንን ንግግር በአንክሮና በንቃት ከተከታተሉት መሀከል ዋናው ራሱ ኦሳማ ቢን ላደን ሲሆን ባለው መረጃ ላይ በመንተራስ ኦባማ በካይሮ ንግግር ከማድረጋቸው አንድ ቀን ቀደም ብሎ ነው አቋሙን የገለፀው:: እንደተለመደው ለአልጄዚራ በቴፕ ባስተላለፈው መልዕክት ቢን ላደን፤ *«ፕ/ት ኦባማ በአሜሪካ ላይ አዲስ የጥላቻ ዘር ይበቅል ዘንድ እየሰሩ ነው!»* ሲል አወገዘ:: ቢን ላደን በዚሁ መልዕክቱ የፕሬዚዳንቱ ንግግር ሊታመን የማይገባው ስለ ሰላምና መቻቻል ያውሩ እንጂ የሳቸውን መንግሥት ፈቃድ የሚፈጽሙ የፓኪስታን ኃይሎች በሺዎች የሚቆጠሩ ንፁህን ነዋሪዎችን ከስዋት ሸለቆ ቀያቸው በጉልበት እያስወጡና እያባረሩ መሆኑን ጠቀሰ:: ቢን ላደን ከፕሬዚዳንት ኦባማ ንግግር በስተጀርባ ስላለው የአሜሪካ የልብ ትርታ ያወቀ ይመስል ነበረ:: ይህም ከቀደሙት ፕ/ት ቡሽም እጅግ በባሰ መልኩ አሜሪካ ትልቅ ውድቀት ለዓለ-ቃኢዳ እየደገሰች እንደሆነ ነው የገመተው::

# ማጠቃለያ

## የአሸባሪዎች አፈጣጠር

የኦሳማ ቢን ላደን የግል ታሪክ እዚሁ ባሰፈርናቸው ነገሮች እንደሚጠቃለል እሙን ነው። ሰውየው የመጨረሻ እስትንፋሱን በሚፋለማቸው አሜሪካውያን እጅ ለዚያውም ደግሞ ደጋግሞ በጠቀሳት ፓኪስታን አቡታባድ ውስጥ ለመተንፈስ በቅቷል። የሱ መሞት ወደየት እንደሚያመራ ወደፊት የሚታይ ነው የሚሆነው። ከመሞቱ አስቀድሞ በተለይ ይህ ጽሁፍ በተቀናበረበት ጊዜ በፓኪስታን እና አፍጋኒስታን አዋሳኝ የሆኑ በሕግና በአስተዳደር የማይመሩ አስቸጋሪ አካባቢዎች እንዱጋ ተደብቆ እንዳለ ይታመን ነበረ። ሌላው ግምት ደግሞ ቄታ በተባለችዋ የፓኪስተን ከተማ ውስጥ እጅግ እውቅ ከሆነው ሙላ መሐመድ ዑመር ጋር ይኖር እንደነበረ ነው።

የሆነው ሆኖ ሰውየው ሞቷል። እንግዲህ አሁን ግን ወሳኙ ጉዳይ ከመስከረም 11ዱ ጥቃት በኋላ የዚህ ሰው አመለካከትም ሆነ ዓላማ እንዳችም ለውጥ ሳይታይበት የቀጠለ መሆኑ ነው። ሰውየው ላለፉት 9 ዓመታት ከመስከረም 11ዱ ጥቃትና ተያያዥ ከነበሩት እሱንና መሰሎቹን ያነሳሱ ጉዳዮች ጋር በተገናኘ ለበርካታ ጊዜያት መግለጫ በአልጄዚራ ቢልክም እንዳችም አዲስ የሚናገረው ነገር በማጣቱ መልዕክቶቹ ገና ሳይናገሩ ሕዝብ በግምት ምንነታቸውን የሚያውቃቸው ሆነው ቆይተዋል። ቢን ላደን ከ 1984-1986 ባሉት ጊዜያት ነው ዓለምን አስመልክቶ በወቅቱ አዲስ ሊባል የሚችለውን አመለካከቱን የያዘው። በወጣትነቱ እጅግ ኃይማኖቱን አክባሪ ሙስሊም መሆንን መረጠ። ነገር ግን እንዳለመታደል ሆኖ እንበለውና በሁለተኛ ደረጃ ተማሪ ሳለ የጂም መምህሩ ነው እጅግ የከረረውን የሃይማኖቱን ገጽታና ሀሳቦች እንዲጨብጥ ያደረገው። ከዚህ

በኋላ በሐይማኖታዊ ሥርዓቶችና በግል ተነሳሽነቱ ላይ ከፍተኛ ለውጥ ቢታይም አኗኗሩ ግን አልተቀየረም ነበረ:: አራት ሚስቶች ያገባ ሲሆን ለአራቱም እጅግ ጥሩ የሚባል፤ ስርዓት ያለውና ሃይማኖቱን አክባሪ ባል ሆነ:: ለልጆቹም ተወዳጅና እንክብካቤና ፍቅር የማይለየው ጥሩ አባት ሆነ:: እናም ሃይማኖቱን አስመልክቶ የያዛቸው እምነቶች ፖለቲካዊ ገጽታ አልነበራቸውም::

ቢን ላደን ለየት ወዳለ ለውጥና ማክረር ያመራው ግን በታዋቂው የንጉሥ አብዱልአዚዝ ዩኒቨርሲቲ ከገባ በኋላ ነው:: የተማረው ኢኮኖሚክስ ቢሆንም ዲግሪ ግን አላገኘም:: ይልቅ በመሐመድ ቁትብ የሚሰጡ የተለያዩ ሌክቸሮችን ተከታትሏል:: ከዚያም በላይ ደግሞ በሰማዕትነት በእስልምናው የሚታወቀውን የቁትብን ወንድም ማለትም የሳይድን ጽሁፎች በሚገባ አንብቧል::

የቁጥብ ወንድማማቾች ያስተምሩት የነበረው የግብፃውያን እስልምና ወንድማማችነት (Egyptian Muslim Brotherhood) በቢን ላደን ጭንቅላት ውስጥ እስልምናን እና ዋና ዋና ዓላማዎቹን ይበልጥ አሰረጹበት:: ነገር ግን አሁንም ቢሆን ወደ ጂሀድ እንዲያመራ አላደረጉትም:: እርግጥ በአፍጋኒስታን የሩሲያውያን መኖርና ውጊያው ጂሀድን ለማወጅ ለቢን ላደን ጥሩ አጋጣሚ ሊፈጥርለት ይችል ነበረ:: ነገር ግን አብዱላህ አዛም ባይኖር ኖሮ ጂሀድን ባላወጀ ነበረ:: የሆነው ሆኖ ግን በአፍጋኒስታን ጂሀድ ሲታወጅ ቢን ላደን እንደተዋጊ ሳይሆን ሙጃሂዲኖች አፍጋንን ነፃ ለማውጣት ወደዚያ ሲገሰግሱ የፈንድ እርዳታ እንዲያገኙ ከማድረግና አንዳንድ ሁኔታዎችን ከማመቻቸት የዘለለ ሚና አልነበረውም::

ግን አንድ ጊዜ ፈንድ አፈላላጊ፤ አዋጊና መሪ የሆነ ሰው ወደ ተዋጊነት ለመቀየር ብዙ አይፈጅበትም:: ቢን ላደን ደግሞ ሁልጊዜም

የተግባር ሰው ነው:: ሌሎችን ከደጀን ላይ ሆኖ በመምራትና በማዋጋት ብቻ የማይረካ፣ ራሱ ገብቶ ዋናውን ሥራ በመከወን ለውጥ እንደሚመጣ የሚያምን ሰው ነው:: ግን ቢን ላደን በወቅቱ በአፍጋኒስታን ሙጃሂዲኖች ይመሩ በነበሩት የውጊያ አዛዦችና መሪዎች ተፈላጊው ሥልጠናና ችሎታ ስለሌለው ተቀባይነት ማግኘት ባለመቻሉ የራሱን ሙጃሂዲኖች አሰልጥኖ ወደ ጦርነቱ ላካቸው:: እርግጥ እነዚህ ተዋጊዎች ያን ያህል ሊጠቀስ የሚችል አስተዋፆ ካለማድረጋቸውም በላይ በውጊያውም ችሎታ ያነሳቸው ነበሩ:: ቢሆንም ለወደፊቱ የሽብርተኛ ቡድን መመስረት ትልቅ ሚና ተጫውተዋል፤ በሌላ በኩልም በተዋጊዎች ዘንድ ቢን ላደንን ስሙን ከፍ አድርገዋል:: የአፍጋን ዓረቦች ወደ ዓል-ቃይዳነት የተቀየሩ ሲሆን ቢንላደን ደግሞ ወደ አገሩ ተመልሶ ሳውዲዎች የጀግንነት ታሪኩን በእጅጉ መስማትና ለራሳቸው ለመጠቀም ፈልገው ነበረና እነሱ እየረዱት ይበልጥ የጀግንነትን ካባ አለበሱት::

ስለ ዓለም በእስልምናው ያለውን አመለካከት ለመለወጥ እጅግ ከፍተኛ አስተዋፆ ቢያደርግም የአፍጋኒስታኑ ጦርነት ግን ቢን ላደን ወደፊት አሸባሪ ይሆናል ብሎ ለመገመት አንዳችም ፍንጭና ማረጋገጫ አልሰጠም:: ሁኔታዎች ለየት ያሉ ቢሆኑ ኖሮ ይህ ሰው የሳውዲ ነጋዴ ሆኖ በቀረ ነበረ:: ነገር ግን ያ እንዳይሆን ያደረገው የባሕረ ሰላጤው ጦርነት መከሰት ነው:: በዚህ ወቅት ቢን ላደን ለሳውዲ ዓረቢያ መሪዎች ግዛቲቱን ለማስከበርና ሳዳም ሁሴንን ለማባረር ይቻል ዘንድ የሙጃሂዲን ጦር ላዋጣላችሁ ብሎ ይጠይቃቸውና እነሱ ግን ጥያቄውን ውድቅ ያደርጉበታል። ይህን ጊዜ ቢን ላደን በሳውዲ መሪዎች ላይ ከፍተኛ ቂምና ቅሬታ ይይዛል:: እናም በራሱ ፈቃድ ወደ ሱዳን ስደት ሲገባ እጅግ አክራሪና ዋንኛ ዓላማቸውም ጂሀድ ማወጅ ከሆኑ የእስልምና ቡድኖች ዘንድ ይቀሳቀሳል:: እንግዲህ እዚያ ነው የአክራሪነት ስልጠናውን ያጠ

ናቀቀው:: በ1993 ዓ.ም. ከካርቱም ለቅቆ ሲወጣ በመላው ዓለም የሚዛመት ጂሀድን ለማወጅ እጅግ ቆርጦ ነበረ:: የዚህ ጂሀድ ዋንኛ ዓላማም አሜሪካን እና በተለያዩ መንገዶች የሷን የሃያልነት እና የመስፋፋት ግብ የሚያግዙላትን «ሃይማኖትን የከዱ» (Infidels/apostates) በማለት የጠራቸውን ማጥቃትና ማሸበር ሆነ::

# የቢንላደን ተፅዕኖ

ባሁን ሰዓት በዚህ ጉዳይ ላይ ኤክስፐርት የሆኑ ሰዎች በፓኪስታን የሚገኘውን ዓል-ቃይዳ ከሌሎች በዓለም ከሚገኙ የድርጅቱ ሴሎች ለመለየት ሲሉ «ዓል-ቃይዳ ማዕከላዊ» ብለው ይጠሩታል:: ዓል-ቃይዳ ማዕከላዊ ከ 1994ቱ የአፍጋኒስታን መወረር ጋር ተያይዞ ከደረሰበት ድቀት ያገገመ ቢሆንም ከዚህ በኋላ በምስጢር ብቻ ለመንቀሳቀስ ያደረገው ውሳኔ እዚያ ትልቅ ድጋፍ ባገኘበትና ሲንቀሳቀስበት በቆየው አፍጋኒስታንም ቢሆን ያልተማከለ አደረጃጀትን እንዲከተል አስገድዶታል:: ይህ ደግሞ ቀደም ሲል በካንደሀር በግልጽ ሲያካሂደው ከነበረው እንቅስቃሴ በጣም የተለየ ነው:: ዓል-ቃይዳ ረጅም ለሚባል ጊዜ ያህል እጅግ የጠነከረ፣ በብዙ ተፈትኖ በአሸናፊነት መውጣት የቻለ ድንቅ አመራር እና ፈጽሞ የማይቋረጥ የሚመስል የገንዘብ የማቴሪያልና የሰው ኃይል ድጋፍ አለው:: እናም አንድ መሪው ቢገደል ለጊዜው ይፍረከረክ፣ ሞራሉ ላይ ስብራት ይደርስበት ወይ ደግሞ አፕሬሽኖቹ ሊቋረጡ ይችሉ እንደሁ እንጂ ለዘለቄታው ግን በድርጅቱ ላይ የሚያመጣው አንዳችም ጉዳት የለም:: እስዚያ ቢን ላደን ሲያዝ ነገሩ ሁሉ ያልቅለታል ብሎ የሚያስብ ካለ ፖውል ብሬመር ልክ ሳዳም ሁሴን መያዛቸውን ለጋዜጠኞች፤

"Ladies and gentlemen, we got him!"

ካሉ በኋላ ብዙ ቢጨፈርም እማኒነትን እና አክራሪነትን ግን በሳዳም ሞት እንድም ስንዝር ለመቀነስ አለመቻሉን ማስታወስ ይገባዋል።

በሌላ በኩል ደግሞ ቢን ላደንን ማስወገዱ ሽብርተኝነትን በጥቂቱ ብቻ ነው የሚነካው የምንልበት ሌላ ምክንያት አለ። ኦሳማ ቢን ላደን ፈንድ በማፈላለግ እና በቃል አቀባይነት ለዓል-ቃይዳ እጅግ ወሳኝ ሰው እንደነበረ ማንም ይስማማል። ነገር ግን አሜሪካ እንቅልፍ አጥታ ስሙን በመጥራት ልታጎድፈው ሁሌ በመሞከሯ በተለይም ደግሞ ከምስራቅ አፍሪካው የቦምብ አደጋ በኋላ ነገሩ ሁሉ ተባብሶ ይኸው እንደ ጀግና እየተቆጠረ ነው። ዛሬ በዓረቡ ዓለም አብዛኞቹ ቦታዎች እንሂድ፣ ይህን ሰው፣ «ጀግና» የማይል አይገኝም። ወዳጆቹና ደጋፊዎቹ ደግሞ፣ «ድንቅ መሪ» ይሉታል። እናም ዋናው የሚነሳው ጥያቄ ቢን ላደን እስከአሁን በዓል-ቃይዳ የነበረው ሚና ነው። በሕዝብ ግንኙነት በሶቪየቱ የአፍጋን ወረራ ጊዜ ያበረከተው አስተዋፆ ስለ ድርጅታዊ ችሎታና ጥንካሬው ብዙም የሚነግረን ነገር የለም። ከአፍጋኖቹ አገልግሎት ድርጅት በስተጀርባ አልነበረም። ቀደም ሲል እንዳልነው በአፍጋን ራሱን ችሎ የሚዋጋና አመራሩም ከአፍጋኖቹ ጋር ግንኙነት የሌለው የሙጃሂዲን ክንፍ ፈጥሯል፣ ግን ያ ክንፍ በውጊያው ብቃት አንሶትና ተንደፋድፎ፣ ሚናውም ሳይጎላ ነው የወጣው። እንዲያውም ከዚህ አንፃር ማለት የምንችለው ነገር ቢኖር የአፍጋን ሌሎቹ ሙጃሂዲኖች እጅግ ቆራጥ፣ ልፍስፍስ የሚጠሉ ቢሆኑም የዚህ ሰው በራሱ ዘይቤ የተፈጠረ ሙጃሂዲን (self-styled Arab contingent) እንደዚያ ሲውተረተር በትዕግስት ለማየት የደፈሩት ቢን ላደን ገንዘብ ያመጣላቸው ስለነበረ ነው። ቢን ላደን የዓል-ቃይዳ መስራች አባል ቢሆንም በድርጅቱ መዋቅር እና እንቅስቃሴ አመራር ውስጥ ግን ሙሉ በሙሉ የበላይነት ነበረው ለማለት አይቻልም። እንዲያውም እሱ ይሁን ምክትሉ ዛዋሒሪ ጂሀድን ዓለም ዓቀፍ ያደረጉት ያጠራጥራል። ኦሳማ ቢን ላደን

ይህንን ድርጅት በተለይም በ 1980ዎቹ አጋማሽ የነበረውን በሕዝብ ዘንድ የነበረ ከፍተኛ ስም እና ዝና አጎናጽፎታል:: አሁን አሁን ግን ጂሀድ ዓለም ዓቀፋዊ ከሆነ በኋላ ያ የ 1980ዎቹ በተወሰነ ቦታ ላይ ያነጣጠረውና ቢን ላደንን ያሳወቀው ውጊያ ብዙም ዋጋ የለውም:: እናም ስናጠቃልለው ዓል-ቃይዳ አሳማ ቢን ላደንን ማጣት ባይፈልግም ያለ እሱ ግን በሚገባ ራሱን ችሎ መንቀሳቀስ ይችላል:: አሳማ ቢን ላደን ለዚህ ድርጅት በሥራውና በአመራሩ ሳይሆን በተሰጠው የገዘፈ ስም እና በሚፈጥረው ስሜት ሊጠቅመው ቢችልም አሁን አሁን ግን ያ ስም ቀስ በቀስ ቀዝቀዝ እያለ መጥቷል::

# የአሸባሪው መልክ

እስከ አሁን ካነሳነው የምታገኙት ዋንኛ ነገር የድርጅቱ መስራች አባል የነበረው የአሳማ ቢን ላደን ድርጅት፣ ግለሰባዊ ማንነት፣ የኖረው ሕይወት እንዲሁም ይህ ሰው የነበረበት ትልቅ ርዕዮተ-ዓለማዊ እንቅስቃሴ ነው:: የአሳማ ቢን ላደንን ሙሉ የሕይወት ታሪክ ዘርዝሮ ማስቀመጡ አስቸጋሪ ይሆናል:: ይህ ለወደፊት የታሪክ ፀሐፊዎች የሚተው ጉዳይ ነው መሆን ያለበት:: ነገር ግን እነዚህ የታሪክ ፀሐፊዎች እኛ እና ይህ ትውልድ ከተወላቸው መረጃዎችና ዶክመንቶች በተለይ ሰውየው የአስተሳሰብ፣ የርዕዮተ ዓለም እና የአኗኗር ለውጥ ማድረግ ስለጀመረባቸው ጊዜያት የመረጃ ክፍተትና እጥረት እንደሚገጥማቸው በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል:: ምናልባት ጓደኞቹና በቅርብ የሚያውቁት ሰዎች የሚያስታውሱትን ከሚናገሩ ላይ የተወሰዱ ካልሆኑ ሌላ መረጃ ላይኖር ይችላል:: የቤተሰቡ አባላት ምንም በማያጠራጥር መልኩ ሞገደኛ ስለሆነውና ለቢዝነሳቸውም እልመች ስላለው አሳማ ሳለማውራት የዝምታ ሴራ ውስጥ መዘፈቅን መርጠዋል:: ከእነዚህ የቤተሰቡ አባላት መሀከል

ወደፊት ይህንን ሴራ ትቶ ለሕዝብ፣ ለዓለምና ለሚዲያዎች አንዳንድ መረጃዎችን ግልጽ ለማድረግ የሚደፍር ይኑር አይኑር ጊዜ የሚፈታው ይሆናል:: ምናልባትም ደግሞ ምዕራባውያን ፀሐፊዎች የሚገጥማቸውን የመረጃ ክፍተት በሚፈታ መልኩ ከልጆቹ አንዱ ወደፊት መረጃን ያፈነጥቅ ይሆናል::

ነገር ግን በዚህ የመረጃ ክፍተት ባለበት ሁኔታም የቢን ላደንን አስተሳሰብ ስለለወጡ ነገሮች ጥቂት ማለት ይቻላል:: ኦሳማ ገና የዘጠኝ ዓመት ልጅ ሳለ የመሐመድ ቢን ላደን መሞት የዚህን ልጅ ስነ-ልቡና እንደነካው ይታመናል:: አባትየው መሐመድ እጅግ ተወዳጅና ልጁ ኦሳማም የሚቀርበው ሰው ነበረ:: የአባት መሞት ለልጁ የማይሞላ አስቸጋሪ ክፍተትን ፈጠረ:: ቢን ላደን ካደገ በኋላ ተቀባይነትን በእጅጉ የሚፈልግ ሰው መሆኑ ከዚህ የኋላ ታሪኩና በአባት ሞት ከተፈጠረው ትልቅ ክፍተት ጋር ይያያዛል:: በሁለተኛ ደረጃ ሳለ የጂም መምህሩ የነበረው መሐመድ ቁትብ፣ አብዱላ አዛም እና አይማን አል-ዛዋሒሪ እያንጻንጻቸው በሰዎች ለመማረክና የሚወዳቸውን ለማግኘት ባለው ተነሳሽነት በሚገባ ተጠቅመዋል:: በሌላ በኩል ደግሞ መሐመድ ልጁን ብዙም አብሮት ሳይሆን፣ ብዙ ጊዜም አብረው ሳያጠፉ ነው የሞተው:: በእርግጥ ኦሳማ ቢን ላደን በልጅነቱ የነበረበት እጅግ ትልቅ የሚባል ቤተሰብ በመሆኑ የአባቱን ጥሩ ሞዴልነት ሊተካ የሚችል ሌላ ሰው ማግኘት አልቸገረውም:: ቢሆንም የዓል-ቃይዳው መሪ ወደ ሥነ-ልቡና ሕክምና ሄዶ የማያውቅ በመሆኑ ስለ ሥነ-ልቡናው መናገር አይቻልም::

የሆነው ሆኖ ግን ይህ ጥናት በዓለማችን ላይ ቁጥር አንድ ታዳኝ እና ተፈላጊ ስለሆነው ሰው የተወሰኑ ጊዜያዊ ማጠቃለያዎች ላይ ለመድረስ ይረዳናል:: ኦሳማ ቢን ላደን የትም የተፃፉትን፣ እስከ አሁንም ስለ እሱ የተባሉትን ነገሮች ብንወስድ በጣም ዓይን አፋር እና ትሁት ነው:: የቀድሞ

መምህራኑ በክፍል ተሳትፎውና በግንዛቤው ከአማካይ በላይ አድርገው ቢገልፁትም ያመጣቸው ውጤቶች ግን አማካይ ነበሩ። ለንገሩ እዚህ ላይ ክፍል ውስጥ ቃል ትንፍሽ ላለማለት የሚያደርገው እጉል ትግል ባመጣው ውጤት ላይ አስተዋፆ እንዳለው እሙን ነው። ባጠቃላይም መልካም ባሕሪን እና ታማኝነትን በእጅጉ የተላበሰ ሰው ነው። ሲያድግ እንዲም የተደባደቢነትም ሆነ የጸብ ባሕሪን አሳይቶ አያውቅም። ሰከር ተጫውቷል፣ ግን አብሮ አደጎቹ ብዙም ተሳትፎ የሌለው ወይንም ግድ የለሽ አድርገው ነው የሚገልጹት። እነዚህን ረስተን አብሮ አደጎቹ ስለሚሉት አንድ ትልቅ ጉዳይ ብንሄድ ኦሳማ ባልተለመደ ሁኔታ ከፍ ከፍ ማለትን እና መብለጥን መውደዱን እናገኛለን።

ኦሳማ በሃይማኖት ፍቅሩ፣ በመስጂድ ሕይወቱ እና በመሳሰሉት ከጓደኞቹ የሚበልጥ ቢሆንም ማናቸውም በዚህ ምንም ችግር ታይቷቸው አያውቁም። ይህ በእያንዳንዱ ሀብታም የሳውዲ ቤተሰብ ውስጥ እንግዳ አይደለም——በየቤቱ አንድ እንዲህ ያለ ልጅ ይኖራልና። ነገር ግን ቢን ላደን ስለ ዓለም ያለውን አመለካከት የሳውዲዎቹን ዋሀቢ ዕምነት ከግብፁ የሙስሊም ወንድማማችነት (ከማንም በላይ በተለይ በሳይድ ቁትብ ይቀነቀን የነበረው)ን ከረር ካለ የሃይማኖት አቋም ጋር በማቆራኘት ነበረ የሚገልፀው። ቁትብ በቢን ላደን ላይ የፈጠረው ነገር ቀላል አይደለም። ለምሳሌም ለዘመናዊነት ችግር እስላማዊ ምላሾችና መፍትሄዎችን አመላክቷል። በሌላ በኩል ደግሞ ዘመናዊ ቴክኖሎጂን ከባሕላዊ የእስልምና እምነት ጋር ለማስታረቅ ሞክሯል።

ቁጥብ ግን ከዚህ ባለፈ ለጂሀድ የሚሆን ርዕዮተዓለማዊ ነገር አልፈጠረም። ልክ እንደ አብዛኞቹ የእስልምና ወንድማማችነት አባላት የፖለቲካ ስልጣንን ከምርጫ ኮረጆ በሚገኝ ውጤት ብቻ መያዝን የሚያምን፣ እንዲሁም ደግሞ ጠመንጃን እና ኃይልን የሚኮንን ነው። የሱ

ተከታይ የሆነው አይማን-አል-ዛዋሒሪ ደግሞ ከዚህ የተለየ አመለካከት ነበረው:: ይህ ሰው ዐይኑ እያየ የወንድማማችነቱ እንቅስቃሴ በግብጽ መንግሥት ከፍኛ ረገጣ ተካሄደበት፤ ከፐ/ት አንዋር ሳዳት ግድያም እሱም ተይዞ በእረመኔዎቹ የግብጽ ስለላ አባላት ቆም ስቅሉን አይቶ ተሰቃየ:: እነዚህ ነገሮችም ተደማምረው እስልምና በምንም ተዐምር በዴሞክራሲያዊ ሂደት ስኬትን እና ድልን ሊያገኝ እንደማይችል አሳመኑት::

አል-ጂሀድ የተባለው ድርጅቱ በኃይል ትግል ዙሪያ ከእስልምና ወንድማማችነት ቡድን ጋር ባለመስማማቱ ተገንጥሎ ወጣ:: ዛዋሒሪ ከዚህም በተጨማሪ በእስልምና አስተምህሮት ከማይታወቀው ተቃራኒ በሆነ መልኩ ቁር'ዓን «ሃይማኖትን የካዱ» የተባሉትን መንግሥታት በሃይል መገርሰስን ይፈቅዷል ብሎ ሲናገርም ተደመጠ:: በመሆኑም ዛዋሒሪ ቀደም ሲል በፓኪስታን የአፍጋን ጦርነት በመካሄድ ላይ በነበረ ጊዜ የመጀመሪያውን የጂሀድ ትምህርት ለቢን ላደን እያስተማረ ሱዳን ላይ ፍፁም አክራሪና ጽንፈኛ እንዲሆን በማስቻል ጨረሰው::

# ሰውየው እና ጊዜያቱ

እኔ ይህንን ጥናታዊ ጽሁፍ ማዘጋጀት ስጀምር የታሪክ ተመራማሪዎችን ዘውትር እንቅልፍ በሚያሳጣው ጥያቄ ነው:: ይህም፤ *ለመሆኑ ግለሰቦች ናቸው ታሪክ የሚሰሩት ወይንስ ሁናቴዎች ናቸው ግለሰቦችን ወደ ታሪክ መስሪያው አውድማ የሚያመጡት?* የሚል ሲሆን ስለ ኦሳማ ካወራን ግን ምላሹ ሁለተኛው ጥያቄ ላይ የሚገኝ መሆኑ ይታወቃል:: ኦሳማ በድርጊቶችና በሁናቴዎች ራሱን ለመለወጥና ለመቀየር በቃ እንጂ እሱ ሁኔታዎችን አልቀየራቸውም:: ቢን ላደን የዓል-ቃይዳ መሪ ለመሆን አቅዶም አልተነሳም፤ ሌላ ሰው መሪ ሊሆን ይችል ነበረ:: ይልቅ ሁኔታዎች

ናቸው የቀየሩት:: እርግጥ ሰውየው የተለያዩ ቡድኖችን፣ ግለሰቦችን እና ተቋማትን አብረው እንዲሰሩ ማስተባበር ችሏል ቢሆንም ይህንን ድርጅት በማደራጀቱም ሆነ የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴውን በመከታተሉ ረገድ የነበረው ሚና እጅግ አናሳ ነበረ:: ዓል-ቃይዳ በታሪኩ ያካሄዳቸው እጅግ የተሳኩ የሚባሉ ጥቃቶች ምንም እንኳን ቢን ላደን ከመካሄዳቸው በፊት አጽድቋቸው የነበሩ ሊሆኑ ቢችሉም አንዳቸውንም ራሱ እንዳላቀደ ግን ግልጽ ነው::

ከዚያ ሌላ ቢን ላደን በቅርብ የሚያውቁት ሁሉ እንደሚመሰክሩት ከሆነ ሀሳብ አፍላቂ ወይንም የፈጠራ ችሎታ አለው የሚባል ዓይነት ሰው አይደለም:: ብዙውን ጊዜ መግለጫ ሲሰጥ ሕዝብ ምን ሊል እንደሚችል ቀድሞ የሚያውቅበትም በዚህ የተነሳ ነው:: ይህ ሰው ብዙውን ጊዜ በደምብ ሳስተዋለው ሰው በየመግለጫው አሰልቺ፣ ብዙ የተባለላቸው እና አንዳንዴም ጊዜ ያለፈባቸው በሌሎች የተፈጠሩ የእስልምና አክራሪነት ጽንሰ ሀሳቦችን ነው ሲያንፀባርቅ የሚታየው:: እስኪ ኦሳማ ቢን ላደን ከየትኞቹ አክራሪዎች ጋር ነው ትስስርና ግንኙነት የነበረው? ብለን ብንጠይቅ ደግሞ ነገሩን ጭራሽ የባሰ ሆኖ እናገኘዋለን:: ግርማ ሞገስ የተባለው ነገርም እጅግ አጠራጣሪ ነው:: ይህ ሰው ወደ ዓለም መድረክ ከመውጣቱ በፊት አንድም ሰው አንድ ጊዜ «ግርማ ሞገስ አለው እኮ!» ብሎ ሲናገር አላደመጥንም:: ይህ ሰው በመጥፎ ሁኔታ ስሙ ከታወቀ በኋላ ሰውየው ግርማ ሞገስ ይኑረው አይኑረው ለማጣራት ዕድሉ የነበራቸው በጣት የሚቆጠሩ ነበሩ:: እነዚህም በጂሀድ አስተሳሰብ አእምሯቸው የሰከረ ጥቂት ባለሟሎቹ አልያም ደግሞ በጥንቃቄ ተጽፎ የተሰጠውን ቴክስት ሸምድዶ ከጨረሰ በኋላ «ቃለ ምልልስ» እያለ ዓለምን ሊያደናግር የሚሞክርበትን ድራማ ለመቅረጽ የሚገቡት ጥቂት ጋዜጠኞች ብቻ ናቸው::

አንዳንድ የእስልምና ተመራማሪዎች ይህን አባባሌን የሚያጠናክርልኝ ምርምር ሰርተዋል:: ከነዚህ መሀከል አንዷ ትልቅ ግምት የሚሰጠውን *A Hundred Osamas* (መቶ ኦሳማዎች) የሚል ጥናት ያደረገችው ሽረፋ ዙኹር ናት:: በዚህ ሊደነቅ የሚገባ ጥናቷም ተመራማሪ ዙኹር እንደነገረችን ከሆነ የጂሀድ ንቅናቄው የመሪ ችግር እንደሌለበትና አንዱ መሪ ቢሞት ካሉት በመቶዎች የሚቆጠሩ አማራጮች አወዳድሮ ሌላውን ወዲያው መተካት የሚችል ነው ብላለች:: ለዚህ ምሳሌ ስትጠቅስም አቡ ሙሳብ ዓል-ዛርቃዊን ዳስሳለች:: በወረሀ መስከረም 1996 ላይ ዛርቃዊ «ዓል-ቃይዳ በኢራቅ» በመባል በሚታወቁት ሁለቱ የጂሀድ ወንዞች ላይ የጂሀድ ድርጅቶችን መሠረቱ:: አሜሪካ በኋላ መኖሪያ ቤታቸው በሰርጎ ገብ እስከታስገድላቸው ድረስ የኚህ ሰው ድርጅት ለ 3 ድፍን አመታት ኢራቅን ሲያናውጣትና ሲያተረማምሳት ቆየ:: ታዲያ ግን ፓኪስታን ያለው ዋንኛው ዓል-ቃይዳ አልነበረም የዛርቃዊን ድርጅት የፈጠረው:: እሳቸው ናቸው ከነሱ ጋር ግንኙነት ለማድረግ የወሰኑት:: እንዲያውም ለጥቂት ዓመታት ያህል የእኚህ ሰው ስም በሚዲያ የኦሳማ ቢን ላደንን ስም እየዋጠውና እየገዘፈ መጥቶ ነበረ:: ባጠቃላይ ስናየውም ሁናቴዎች፣ የጥቃቶች ጊዜና ተጨባጭ እውነታና የመሳሰሉት ባይሆኑ ኖሮ ከኦሳማ ይልቅ እኚህ ሰው መሪ ሊሆኑ ይችሉ ነበረ::

በሌላ በኩል ደግሞ ኦሳማ ቢን ላደን በሚልዮን እንደሚቆጠሩ የጂሀዲስት ታጋይ ወታደሮች ከደሀ ቤተሰብ የመጣ ቢሆን እና ቅሬታና ቁርሾ ያዘለ ሰው ቢሆን ኖሮ በዓል-ቃይዳ ውስጥ በቃል አቀባይነት እና በፈንድ አፈላላጊነት ሳይሆን በሌላ ደረጃ ባገለገለ ነበረ:: በብዙ መልኩ ሲታይ በሀሳብ የምንስለውን አጥፍቶ ጠፊ (Suicide bomber) ን በእጅጉ

የሚመስል ስብዕና ነው ያለው:: በእምነቱ፣ ለሌሎች ባለው ታማኝነት፣ በስብዕና ጥንካሬውና በመሳሰሉት እጅግ የሚደነቅ ነው::

ነገሩን ስናጠቃልለው ታዲያ ይህ ሰው ዓል-ቃይዳን በፈንድ አፈላላጊነት፣ በማቴሪያላዊ ድጋፍ አቅራቢነትና በመሳሰሉት ካደረገው መርዳት ሌላ ትልቁ ድሉ በፈጠረውና በገነባው ስም ለድርጅቱ የተጫወተው ቁልፍ ሚና ነው:: እስልምና እንደታፈነ፣ የቆመላቸው ዓላማዎችም በዓለም ልዕለ ኃያላን እንደተረገጡ አድርገው ራሳቸውንም በሁኔታዎች ፍፁም ከቁጥጥርና ከአቅም በላይ መሆን የተነሣ ምንም ሊያደርጉ እንደማይችሉ አድርገው ለሚያስቡት ሁሉ አሳማ ቢን ላደን ከቤተ-መንግስት እስከ ተራው አደባባይና መንደር ብንወስድ ትልቅ ተቃዋሚና ጀግና ተደርጎ ነው የሚወሰደው:: በተለይ ደግሞ በነጋዴነቱና ባለው ንክኪ በዓለም ሊታሰብ ከሚችለው በላይ ተንደላቆ መኖር ሲችል ለዚህ የጂሀዲስት ዓላማ ሲል ራሱን መስዕዋት ለማድረግ፣ የስቃይ ኑሮ ለመኖርና አመራር ለመስጠት መፍተዱ ሁሌም የማይረሳ የሞራል ማመላከቻ ያደርገዋል:: በመሆኑም እንዲህ ያለው ሰው የደቀነውን አደጋ እዋጋለሁ የሚል ማንኛውም ኃይል ሰውየውን በቁጥጥር ስር ማዋል ወይ መግደል ሳይሆን ቀድሞውንም ይህ ሰው እንዲያብብ፣ እንዲበለጽግ፣ አክራሪ እንዲሆን እና ይህን የመሪነት ሚና ተጫውቶ ጥቂትም ሆነ ከዚያ በላይ ድጋፍ እንዲያገኝ ያስቻሉትን እና ያደረጉትን ነባራዊ ሁኔታዎች መቀየር ነው የሚኖርበት::

# ተጨማሪ ፡ የተመረጡ አባሪ ዶሴዎች

በዚህ ክፍል የምንዳስሳቸው ዶሴዎች ይህ ጸሐፊ መጽሐፉን ለመፃፍ ከተጠቀመባቸው ውስጥ የተወሰኑትን ብቻ ነው። ነገር ግን እያንዳንዱን ዶሴና ተያያዥነቱን መረዳት ይቻል ዘንድ በቅድሚያ አጠር ያለ መግለጫ ተሰጥቷል። እያንዳንዱ የተጠቀሰ ምንጭ የቀረበው በቀን ቅደም ተከተል ነው። ይህም አሜሪካ ዓል-ቃይዳን አስመልክቶ ያላት መረጃና አረዳድ ከጊዜ ወደ ጊዜ እንዴት እየተለወጠ እንደመጣ ያሳያል።

## አባሪ 1

በ 1990 ዓ.ም. *Patterns of Global Terrorism Reoprt* ኦሳማ ቢን ላደንን እጅግ በጣም ባነሰ መልኩ አንድ ወይ ሁለት ጊዜ ብቻ ጠቀስ አድርጎ ቢያልፈውም የሽብርተኝነት እንቅስቃሴ በዓለም ላይ እንዲስፋፋ ላደረገው አስተዋጽና ለፈጠረው ተጽዕኖ ግን እውቅና ይሰጣል። ሪፖርቱ ግን ኦሳማ ቢን ላደንን ለአሜሪካ አስጊ አድርጎ አልወሰደውም። ሪፖርቱን መመልከት ለሚፈልጉ አንባቢያን በዚህ ያገኙታል፡ http://www.hri.org/docs/USSD-Terror/97/asia.html.

## አፍጋኒስታን

በዓለማችን ከሚገኙ የተለያዩ አገራት—ከግብጽ፣ አልጄሪያ፣ ፍልስጤም እና ሳውዲ ዓረቢያ—የተውጣጡ አክራሪ እስልምናን የሚያራምዱ ወገኖች አፍጋኒስታንን ከ 1997 ጀምሮ ለእንቅስቃሴያቸው እንደ ዋንኛ መሠረታቸውና መነሻቸው አድርገው መጠቀም ጀመሩ። ይህ በእንዲህ እንዳለ ደግሞ በአፍጋኒስታን በወቅቱ ይካሄድ በነበረው የእርስ በርስ ጦርነት ውስጥ ትልቅ ተሳትፎ የነበራቸው ታሊባኖች ለእነዚህ በዜግነት እና ትውልድ አፍጋን ላልሆኑት ተዋጊዎች አፕሬሽን መሳካት ትልቅ አስተዋፆና ድጋፍ ማድረግ ጀመሩ። ሌሎች የአፍጋን ቡድኖችም

ለተለያዩ አፍጋናዊ ላልሆኑ የሽብርተኝነት እንቅስቃሴዎችና ድርጅቶች የሎጂስቲክ ድጋፍ ከማድረግም አልፈው ወደ አፍጋን የሚያልፉና የሚገቡበትን መንገድ ሲያመቻቹ አንዳንድ ጊዜ የይለፍ ወረቀት እንዲያገኙም ረዷቸው:: እነዚህ እርዳታና ድጋፍ ተደርጎላቸው የገቡ አፍጋን ያልሆኑት አክራሪዎች ደግሞ በበኩላቸው በቦዝኒያ እና ሔርዞጎቪና፣ በቼቺኒያ፣ ታጂኪስታን፣ ካሽሚር፣ በፊሊፒንስ እንዲሁም በተለያዩ የመካከለኛው ምሥራቅ ቦታዎች ላይ ገብተው ውጊያ ማድረግ ጀመሩ::

ትውልዱ ሳውዲ የሆነው እና አሸባሪዎችን በገንዘብ በመደገፍ የሚታወቀው ኦሳማ ቢን ላደን ከጀላላባድ በመልቀቅ ወደ አፍጋኒስታን መዲና ካንደሐር ሄደ:: ጊዜው በ 1989 አጋማሽ ሲሆን እዚያም አዲስ አፕሬሽኖችን ለማቀናበርና ለማዘዝ የሚረዳ ጣቢያ አቋቋመ:: በዚህ ወቅት በአሜሪካ ላይ አመጽና የኃይል ተቃውሞ ማነሳሳቱን የቀጠለ ሲሆን በተለይም ዋነኛ ትኩረቱን በሳውዲ ዓረቢያ በሚገኙ የአሜሪካ ተዋጊዎች ላይ አደረገ:: ቢን ላደን ሙስሊሞች በሚር አይማል ካንሲ የፍርድ ሂደት ጊዜ ዋና አቃቤ ሕግ የነበረው አሜሪካዊ ፓኪስታናውያንን አስመልክቶ በሰነዘረው የማንኳሰስ አስተያየት የተነሳ አሜሪካ ላይ የበቀል እርምጃ እንዲወስዱ ጠየቀ:: ቢን ላደን በዚህም ብቻ ሳይወሰን HUA የተባለውን እና በወቅቱ አሜሪካ በአሸባሪነት ፈርጇ የነኘችውን በፓኪስታን የሚገኝ የካሽሚር ድርጅት አወደሰ:: እንደ ፓኪስታን የፕሬስ ዘገባዎች ከሆነ ካንሲ ለአሜሪካ ተላልፎ ከተሰጠ በኋላ ቢን ላደን፣

> «ካንሲን ለመማረክ እንሞክራለን ብትሉ በሶማልያ የቀሰማችሁትን ትምህርት በድጋሚ የምንሰጣችሁ መሆኑን ሳስጠንቅቃችሁ እወዳለሁ!!» ሲል አሜሪካን አስፈራራ::

# አባሪ 2

ቢን ላደን ለመጀመሪያ ጊዜ በአሜሪካ ሕዝብ ዘንድ ስሙ የታወቀው በምሥራቅ አፍሪካ የኤምባሲ ቦምብ አደጋ ካደረሰ በኋላ ነው:: ዓለ-ቃይዳ እንደ ድርጅት ለአሥር ዓመታት ያህል ቢቆይም ቢን ላደን በአሜሪካ የአሸባሪዎች ዝርዝር ላይ የሰፈረው ግን ከ 1990ው የዳሬሰላም እና የናይሮቢ አደጋ በኋላ ነው:: የአሜሪካ ስቴት ዲፓርትመንትን መግለጫ ማንበብ ከፈለጉ በ

http://www.state.gov/www/global/terrorism/1998Report/intro.html#foot1

ላይ ያገኙታል:: የአሜሪካ መንግሥት በዚህ ወቅት በዳሬሠላም እና በናይሮቢ በሚገኙት የቆንጽላ ጽ/ቤቶቹ ላይ አደጋ ከደረሰ በኋላ ኦሳማ ቢን ላደን የዘረጋው የሽብርተኝነት መረብ በዚህ አደጋ እጁ እንዳለበት የሚጠቁም መረጃ ደረሰው:: አሜሪካም ተጨማሪ ጥቃትን በሚጋብዝ መልኩ ነሐሴ 14፣ 1990 ላይ በአፍጋኒስታን እና በሱዳን በሚገኙ አሸባሪዎች ላይ ወታደራዊ ጥቃት ፈጸመች:: በዚያች ዕለትም ፕ/ት ክሊንተን በተለይም Executive Order 12947 በመባል የሚታወቀውን እና ይህም በስቴት ዲፓርትመንቱ ጥቁር መዝገብ ላይ ስማቸው የሰፈሩትን አሸባሪዎች በአሜሪካ የሚገኙ ንብረቶች እና የባንክ ሂሳቦች እንዳይንቀሳቀሱ ማገድን፣ ብሎም ግለሰቦቹ በአሜሪካ ሲያደርጓቸው የነበሩ የገንዘብ ልውውጦች፣ ሽያጮችና የመሳሰሉትም እንዲቋረጡ የሚያዝ ሕግ ነበረ:: ከዚህ በኋላ ወዲያውኑ ክስ ለማዘጋጀት የአሜሪካ መንግሥት ሽርጉድ በሚልበት ጊዜ አብሯ የነበረችው ጃኔት ሬኖ የተባለችዋ አቃቤ ሕግ እንዳለችው አሜሪካ ከዚህ ቀደም አካሂዳ ከምታውቃቸው ውጪ አገር ድረስ የሚዘልቁ ምርመራዎች እጅግ ትልቅ የተባለውን አከናውና ከታንዛንያ እና ኬንያ መንግሥት ጋር በመተባበር ኦሳማን እና ሌሎች 11 ገዳማ የሚሆኑ ግብረ

አበሮቹን ለደረሱት ሁለት ጥፋቶች ተጠያቂ አድርጋለች:: ክስም ወዲያው ተመሰረተባቸው:: በዚህ የተነሣም በርካታ ተጠርጣሪዎች ወደ አሜሪካ ድረስ ተወስደው ችሎት ፊት ቀረቡ:: የአሜሪካ መንግሥትም ከተጠ ርጣሪዎቹ ወደ አንዱ ወይንም ወደ ሌሎቹ የሚያደርስ መረጃና ጥቆማ ለሚሰጥ ለማንኛውም ለተሳካለት ሰው እስከ 5 ሚልዮን ዶላር እንደሚሸልም አስታወቀ::

# አባሪ 3

ኦሳማ ቢን ላደን በ 1989 ዓ.ም. ላይ ያካሄደው ፋትዋ በአሜሪካ እና በአጋሮቿ ላይ የታወጀ ጦርነት መሆኑ ይታወቃል:: የዚህ ሰው ዓለማዊ/ሃይማኖታዊ አመለካከት ቅርጽ ከመያዝና ከመጸበር አልፎ ጭራሽ ወደ ትግበራ የገባበትን ሁኔታም ያመላክታል:: ይህንን ዶሴ ማንበብ ለሚፈልጉ ሁሉ: http://www.fas.org/irp/world/para/docs/980223-fatwa.htm. በሚለው ማግኘት ይችላሉ::

**በአይሁዶችና በመስቀል ጦርነት ተዋጊዎች ላይ የታወጀ ጂሀድ**

**ከዓለም የእስልምና ግንባር የተሰጠ መግለጫ**

**የካቲት 15፤1988**

**ሼህ ዑሣማ ቢን-ሙሐመድ ቢን-ላደን**

**አይማን ዓል-ዛዋሒሪ፤ በግብጽ የሚገኘው የጂሀድ ቡድን አሚር**

**አቡ-ያሢር ሪፋ'ኢ አህመድ ጣሀ፤ ከግብጽ የእስልምና ቡድን**

**ሼህ ሚር ሐምዛህ የጃሚያር-አል-ዑለማ-ኢ-ፓኪስታን ዋና ፀሐፊ**

**ፋልዙር ራሕማን፤ በባንግላዴሽ የጂሀድ ንቅናቄ አሚር**

**ታላቅ ምሥጋና እና ክብር ደመናን ለሚቆጣጠር፤ ቅዱስ መጽሐፋችንን ለገለጠልን፤ ቡድንተኝነትን እና ክፍፍልን ድል ለሚነሳው ለአሏህ ይሁን፤ አምላካችን አሏህ በመጽሐፍ፤ «የተከለከሉ እንደበቶች ልካቸውን ሲያልፉ**

ግን በያዝክበት ቦታ እዚያው ኢ-አማንያንን ቅላቸው:: ያዛቸው፣ ማርካቸው፣ አድብተህም [ለማንኛውም ጦርነት] ጠብቃቸው::» ይለናል:: ከብርም ለመሐመድ-ኢብን-አብድአኋህ ይሁን:: አብድአኋህም በመጽሐፋቸው፣ «አኋህ እንጂ ሌላ ፈጽሞ አይመለክ ዘንድ ጎራዴን ጨብጬ መጣሁ:: በጥላውና በእንክብካቤ የሚያኖረኝን ጌታ ከኢ-አማንያን ከሀዲዎች ለመጠበቅም ስል ባንገብኩት ነፍጥና ጦር ታላቅ ውርደትና ጥላቻን በእነርሱ ላይ አደርሳለሁ፤» ብለዋል::

የዓረብ ንፍቀ ክበብ አኋህ ጠፍጣፋ አድርጎ ከፈጠረው—በረሐውን በውሃ ከቦ ካስቀመጠው——በኋላ በታሪኩ በመስቀል ጦርነት አዋጅ ተዋጊዎች እንደ አንበጣ ተወርሮ፣ አኋህ የሰጠውና ያደለው የተፈጥሮ ሀብቱ ተቦጥቡጦ እንዲሁም እርሻዎቹም እንደ ጎመን ተሸርክተውና ተጨፍጭፈው አያውቅም:: ደግሞ ከሁሉም በላይ የሚያሳዝነን ይህ ሁሉ ውርጅብኝና ጥፋት እየደረሰ ያለው ልክ በምግብ እንደሚጣሉ ሰዎች ሌሎች የዓለም ሕዝቦች ሙስሊሙን ለጉድ እያጠቁ ባሉበት ሰዓት መሆኑ ነው:: በዚህ ማግጣፊያው ፍጹም ባጠረበት፣ ድጋፍ በሌለበት እና ከድቅድቅ ጨለማም ጠቁር በሚታየው አሳዛኝ ነገር ዙሪያ እኛ እና እናንተ ወቅታዊ ሁኔታዎች ላይ መክረን ጉዳዩን ለአኋህና ለሰሚም በሚመች መልኩ ለመቋጨት ስምምነት ላይ ልንደርስ ግድ ይለናል::

ዛሬ ማንኛውም ሰው የማይሞግታቸውና የማይከራከርባቸው ስስት መሠረታዊ ሀቆች አሉ:: እስኪ ዘርዝረን እንያቸው::

የመጀመሪያው ኢምፔሪያሊስትና ተስፋፊ አሜሪካ ላለፉት 7 ዓመታት በዚህች ከምትችለው በላይ መከራን ባሳለፈች ዓለማችን ላይ እጅግ ቅዱስ ከሚባሉት ቦታዎች ዋንኛውና የእስልምና ማዕከልን፣ የዓረብን ንፍቀ ክበብ ወዞተ. መያዧ ሲሆን ሀብቱን በመቦጥቦጥ፣ ሕዝቡን በማሸበር

በንፍቀ ክበቡ ውስጥ የሚገኘውን ቦታ ወደ መሠረቷና አውድማዋ በመቀየር አጎራባች ቦታዎች ላይ የሚገኙ ሙስሊሞች ላይ ጦሯን መሰበቋ ነው::

እርግጥ «ከሰው ስህተት. . .» እንዲሉ ጥቂት በመናፍቅ ወሬ ናላቸው የላሸቀ ሰዎች ይህንን መሠረታዊ ሃቅ ሲጠራጠሩት ታይተዋል፤ በንፍቀ ክበቡ ውስጥ የሚገኝ ሁሉ ግን——ማለትም ሰፊው ሕዝብ——ሀቁን ተቀብሎታል:: ለዚህ ደግሞ ማሳያ ብንፈልግ በጣም በቀላሉ አሜሪካ አሁንም ድረስ ኢራቅን በጉልበት፣ በግዳጅና በነፍጥ ይዛ ያለች መሆኗ እና በንፍቀ ክበቡ ውስጥ ለኢምፔሪያሊስቶች መፈንጫ ሲሆን የበዪ ተመልካች ሆነው መገኘታቸው ነው::

ሁለተኛው ጨርሶ የማይካድና የማይታበል——በምንም መልኩ የማይጠረጠር ሃቅ ደግሞ በመስቀል ጦርነቶችና በጽዮናውያኑ መሀከል በተሸረበው የትብብር ሴራ አማካይነት አሜሪካ በኢራቅ ሕዝብ ላይ ብዙ ግፍና ስቃይ ካደረሰች——ይኸው 1,000,000 ንጹሀን ተገደሉ፣ ብዙዎችም አለቁ——በኋላም ቢሆን ግፍና የደም በከንቱ መፍሰስ በጣም የጠማት በመሆኗ ምድራችን እንደ መንግሥት እርሻ በጥፋት ከታረሰ፣ ብዙዎች ከሞቱ፣ በተራዘመውና መቋጫ ባጣው ጦርነት ሺዎች እዬዬ እያሉ——አሜሪካ ይህንን ታሪክ ወደኋላ ሄዶ ሁሌም አልቅሶ የሚዘክረውን እልቂት ለመድገም አሁንም እየተሯሯጠች መሆኗ ነው::

ይኸው እንግዲህ በዚሁ ጭፍን፣ ጦረኛ እና ሕዝብን ለጦስ በሚዳርገው እብሪታቸው ነው አሁን ደግሞ የሙስሊሙን ማኅበረሰብ ለማዋረድ ቆርጠው የመጡት::

በሶስተኛ ደረጃ ደግሞ ታላቁ፣ ስንቱን ያየውና ግፍ ያንገሸገሸውም ሆነ ሌላው ሕዝብ ከቶም የማይስተው ሃቅ አሜሪካ ከዚህ ከምታካሂደው ወደር-የለሽ የሆነ ስቃይና እልቂት በስተጀርባ ያሰበችው ኢኮኖሚያዊ እና ሃይማኖታዊ ነገር ነው ቢባል እንኳ ዞሮ ዞሮ ዋንኛው ዓላማ ግን

የአይሁዳውያኑን ቁራጭ የምታህል ግዛት ለማገልገል ብሎም የዓለምን ሕዝብ ትኩረት ከኢየሩሳሌም በቅኝ መያዝ እና ከነዋሪዎቿ ሙስሊሞች ትጥ ያጣ ግፍ ለማስቀየስ ሲባል የተደረገ መሆኑ ነው:: አሜሪካ በዋናነት የምትፈልገው በኅረቤት ከሚገኙት የአረብ አገራት በጣም ቅርቧ የሆነችውን ኢራቅን ለመበታተን ነው:: እንደ ኢራቅ፣ ሳውዲ ዓረቢያ፣ ግብጽ፣ እና ሱዳን ያሉትን ደግሞ ኅርፍ እንደመታው ደሳሳ ጎጆ ለማደባየት አቅደዋል:: ይህ ሁሉ ንጹኅ፣ ለአሏህ ተገዢ የሆነ ሕዝብና አገር በኢምፔሪያሊስት እሳት ሲጋይና ለሰቀቀን ሲዳረግ እነሱ ግን በዚህ እልቂት ላይ እስራኤልን ለማኖር ብሎም ደግሞ ኢ-ሰብዓዊው የመስቀል ጦርነት በንፍቀ ክበቡ ላይ እንዲቀጥል ለማድረግ ነው እቅዳቸው::

ታላቁ ሕዝባችን ሆይ! አሜሪካ የፈጸመቻቸው እነዚህ ተንግረው ቀርቶ ታስበው የማያልቁ ወንጀሎች በታላቁ አሏህ፣ በመልዕክተኛው እንዲሁም በሙስሊሙ ላይ የተቃጡ መሆኑን ከቶ እንዴት ልትጠረጥር ትችላለህ? እም፣ አትችልም:: በመሆኑም ዑለማዎች ታሪክ ደግሞ ደጋግሞ እንደሚነግረን እምነትህን ለመናድ በከሀዲዎችና በኢ-አማኝያን ሙከራ በሚቃጣበት ጊዜ ጂሀድ ግዴታህ እንደሆነ ነው:: እጅግ እጅግ የተከበሩት ኢማም-ቢን-ቃዳማህ «አል-ሙጃኒ» በተሰኘው ጊዜ በማይሽረው ጽሁፋቸው ላይ፣«

> *«ጠላትን ለመከላከል የሚደረገው ውጊያ በተመለከተ ቅድስናን እና ሃይማኖትን ለመጠበቅና ለመታደግ መሆኑ ይታወቃል:: ደግሞስ ሃይማኖትን እና ቅድስናን ከጠላት ከመከላከልና ከመጠበቅ በላይ ምንስ የበለጠ የተቀደሰ ተግባር ሊኖር?»*

ብለው እቅጩን ተናግረዋል:: እናም ታላቁና የተከበርከው ሕዝባችን ሆይ እነዚህን ከላይ የተጠቀሱ የማንነታችን አሻራዎች ብሎም ከአሏህ በተሰጠን

ፈቃድና ትዕዛዝ መሠረት የሚከተለውን ፋትዋ ለሁሉም ሙስሊሞች አስተላልፈናል።

እያንዳንዱ ሙስሊም በሚኖርበት አገር ባሉት ምቹ ሁኔታዎች በመጠቀም አቅሙ በፈቀደ መጠን የአል-አቅሳን መስጂድ እና መካን ከኢ-አማንያኑ ጦር ለማስለቀቅ ሲባል በሚኖርበት አገር በሚገኙ የአሜሪካና የሸሪኮቿ ወዳጅ በሆኑ ጦሮችና ሲቪል ሕዝብ ላይ ጥቃት የማድረስ ግዴታ አለበት። በዚህም መሠረት ልካቸውን በማሳየት ወደ ሙስሊሙ ግዛት ፈጽሞ መግባት አይደለም ለመግባትም ማሰብ እስከማይችሉ ድረስ ማዋረድ ዋንኛ የውጊያው ዓላማ ነው። ታላቁ አሏህ ያለንን አትርሳ፤

*«ጭቆና መረቡ ተበጣጥሶ በአሏህ እምነት ላይ*
*የሚደቀን ማንኛውም ማነቆ እስኪጠፋ ተዋጋ።»*

ቅዱስ አሏህ ካለው በተጨማሪም ደግሞ በተለይት በኢምፔሪያሊስትና በጽዮናውያን ትምክህት ቅኝ ተይዘው በሚገኙ መሬቶች ላይ የሚገኙ ራሳቸውን መከላከል የማይችሉ እንደ ሴቶች፣ ሕፃናት እና የመሳሰሉት ወገኖቻችን ሙስሊሞች፤ «ፈጣሪ እባክህን ከዚህ አፋኝ መንግሥትና ጦር፣ ከጨቋኝ ሕዝቡም አድነን» ሲሉ ልንደርስላቸው ይገባል።

በመሆኑም እኛ በአሏህ እርዳታ ማንኛውም በአሏህ የሚያምን እና ታላቅ ሽልማት እንዲጠብቀው የሚፈልግ፤ በረከትን የሚሻ ሁሉ ለዚህ ጥቃት የዳረጉንን የአሜሪካውያንን ሕይወት በመቅጠፍ፣ ንብረታቸውንም የትም ተገኘ እንዴት እንዲዘርፍ ጥሪ እናቀርባለን። ከዚህ በተጨማሪም ደግሞ ለሁሉም የሙስሊም ዑለማዎች፣ መሪዎች፣ ወጣቶችና ወታደሮች በሰይጣናውያኑ የአሜሪካ ወታደሮች ላይ ጥቃት እንዲፈፀም፣ ደጋፊዎቻቸው ላይም እልቂት እንዲደርስ አለሁ አለሁ የሚሏቸውንም በማፈናቀልና ለችግር በመዳረግ አብረውን ይቆሙ ዘንድ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን።

ታላቁ አሏህ፤

*«እናንተ ምዕመናን ሆይ አሏህና ደቀ-መዝሙሩ ሕይወታችሁን መስዕዋት እንድታደርጉ ጥሪ ባስተላለፈ ጊዜ ስሙት:: አሏህ በልብና በሰውየው መሀከል ሁሌም የሚኖር፣ ማንኛችንንም ደግሞ የሚሰበስብ መሆኑንም እወቁት::» ይላል::*

ታላቁ አምላካችን አሏህ ከዚህ በተጨማሪም፤

*«እናንተ አማንያን ሆይ! ለመሆኑ ችግራችሁ ምንድነው? ለአሏህ ክብር ተዋደቁ፣ ነፍሳችሁን ስጡ ስትባሉ ምን ከዚህች ከንቱ ዓለም ጋር ያጣብቃችኋል? ለመሆኑ በዚህች ዓለም ላይ ብዙ መኖርን ታስባላችሁ እንዴ? ግን እውነቱን ልንገራችሁ የዚህች ዓለም ኑሮ ከንቱና የማይመች ነው:: እናም እምቢ የምትሉ ከሆነ አምላክ እስላም ይቀጣችኋል:: እሱን ግን አትጎዱትም፤ አታስቀይሙትም ምክንያቱም እሱ አሏህ ታላቁ ከማንኛውም ነገር የላቀ ነውና::» ይለናል::*

ታላቁ አምላካችን አሏህ፤ «ልብህ አይዳከም፤ ተስፋ መቁረጥ ውስጥም አትግባ:: እውነትን ከፈለግህ በያዝከው ቀና ጎዳና መቀጠልና መታገል ይኖርብሀልና» ይለናል::

# አባሪ 4

ቀደም ሲል እንደተገለፀው በፌዴራል ልዩ ፍ/ቤት የሚገኘው የአቃቢያነ ሕግ በቢን ላደን እና ግብረ አበሮቹን በምሥራቅ አፍሪካዎቹ ሁለት የቆንጽላ ጽ/ቤቶች ላይ በደረሰው አደጋ ከሰሳቸው:: ከዚህ በመቀጠል ለዚህ ጽሁፍ ማጠናከሪያ በአባሪነት የቀረበው የክሱ መግቢያ ነው:: ክሱን በእንግሊዝኛ በኢንተርኔት ላይ አግኝተው ማንበብ ለሚፈልጉ ሁሉ፡ http://fl1.findlaw.com/news.find.law.com/hdocs/docs/binladen/usbinladen1.pdf ላይ ማግኘት ይችላሉ::

የአቃቢያነ ሕጉ ስብስብ ክስ እንደሚከተለው ይቀርባል፡

## የኋላ ታሪክ፤ ዓል ቃኢዳ

1. ከዚህ ክስ ጋር ተያያዥነት አላቸው የሚባሉ ጉዳዮች በተፈጸሙበት ጊዜያት ሁሉ ከ 1981 ይህ ጽሁፍ እስከተጠናከረበት ጊዜ ድረስ አንድ ሙስሊም ያልሆኑ መንግሥታትን በኃይል እና በጉልበት ማጥቃት የሚፈልግ የአሸባሪ ድርጅት ቁርጠና ዓላማዬ ብሉ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል:: ይህ ድርጅት ደግሞ ያደገውና ያቆጠቆጠው በተለያዩ የዓለማችን ክፍሎች ማለትም አፍጋኒስታን፤ ፓኪስታን (በተለይ በፔሽዋር) በአሜሪካ (በተለይ ብሩክሊን፤ ኒውዮርክ ውስጥ በሚገኘው ዓልቂፋህ የስደተኞች ማዕከል) ውስጥ ከሚንቀሳቀሰው እና ራሱን «መኽታብ ዓል-ቃይደማት» ወይንም ወደ እንግሊዝኛ ሲተረጎም «The Services Office» የሚል መጠሪያ ካለው ድርጅት ውስጥ ነው:: ቡድኑ የተቋቋመው በተከሳሾች ኡሳማ ቢል-ላደን፤ መሐመድ አጤፍ (ወይንም በሌላ መጠሪያው «አቡ ሐፍስ አል ማስሪ» እንዲሁም አቡ ኡባያድ አል ባንሺሪ እና በሌሎችም ነው:: ይህ ቡድን ከ 1981 ጀምሮ እስከዛሬ ድረስ ራሱን «ዓል-ቃይዳ» (The Base) በማለት ይጠራል:: ከ 1981 እስከ 1983 ድረስም ይህ ቡድን (ከዚህ በኋላ በክስ

ፋይሉ ዓል-ቃይዳ ተብሎ ይጠራል) በአፍጋኒስታን እና በፓኪስታን፣ ፔሻዋር ውስጥ ነው ዋና መሥሪያ ቤቱን ያደረገው:: ከ 1983 በኋላ ግን የዓልቃይዳ አመራር አባላት፣ ኢማሩን ጨምሮ (ወይንም ልዑሉ ልንለው እንችላለን) ኡሣማ ቢን ላደን መቀመጫውን ወደ ሱዳን ቀየረ:: ዓል-ቃኢዳ ከ 1983 እስከ 1989 ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ዋና መስሪያ ቤቱ በሱዳን ይገኝ እንጂ በተለያዩ የዓለማችን ክፍሎች ውስጥ ቢሮዎች ነበሩት:: በ1989 ዓ.ም. ተከሳሾች ዑሣማ ቢን ላደን እና መሐመድ አጤፍ ከሌሎች የዓል-ቃይዳ አመራር አባላት ጋር በመሆን ዋና መቀመጫቸውን ወደ አፍጋኒስታን ቀየሩ:: ዓል-ቃኢዳ በክስ ፋይሉ በሚጠቀሱት በማናቸውም ጊዜያት የተመራው በተከሳሽ ኦሳማ ቢን ላደን ነው:: የዚህ ቡድን አባላት ለመሪውና ለተከሳሽ ኦሳማ ቢን ላደን እና ለዓል-ቃኢዳ ቃል የገቡ ሲሆን ይህ የመተማመኛ ቃላቸውም «ባያት» ተብሎ ይጠራል:: በዓልቃይዳ ላይ ይተባበራሉ ተብለው የሚጠረጠሩት ሁሉ ታድነው ይገደሉ ዘንድ ትዕዛዝ ተላለፈ::

2. ዓል-ቃይዳ አሜሪካን የሚቃወምባቸው የተለያዩ ምክንያቶች አሉት:: በመጀመሪያ ደረጃ ቡድኑ ከያዘውና ከሚያራምደው እጅግ የከረረ የእስልምና አተረጓጎም ጋር በማይሄድ መንግሥት ስለምትመራ «እምነቷን የካደች/መናፍቅ» ተብላ በመፈረጇ ነው:: በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ አሜሪካ ለሌሎች ልክ እንደሷው «እምነታቸውን የካዱ/መናፍቃን» በመባል ለተፈረጁት እንዲሁም የቡድኑም ጠላት በመባል ለሚታወቁት ለሌሎች መንግሥታት እና ተቋማት በተለይም እንደ ግብጽ፣ እስራኤል፣ ሳውዲ ዓረቢያ እና የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ትልቅ ትርጉም ያለውና መሠረታዊ እርዳታ ታደርጋለች በሚል ነው:: በሶስተኛ ደረጃ ደግሞ ዓልቃይዳ «የእስልምና አራማጅ አገራትን ለመያዝ የተደረጉ የሰበብ አስባብ

ቅድሚያ ጣልቃ ገብነቶች» በማለት በሰየማቸው ማለትም አሜሪካ በ 1983 በኤደን ባሕረ ሰላጤው ጦርነት እና በኋላም «Operation Restore Hope» ብላ በጠራችው የሶማልያው ጦርነት ውስጥ በ 1984 እና 1985 ውስጥ መሳተፏን በመቃወሙ ነው:: ዓል-ቃይዳ በተለይም ከኤደን ባሕረ ሰላጤው ጦርነት በኋላ የአሜሪካ ታጣቂ ኃይሎች በሳውዲ አረቢያ እና በተቀረው የአረብ ንፍቀ ክበብ ክልል ውስጥ መገኘታቸውን አጥብቆ ተቃውሟል:: በአራተኛ ደረጃ ደግሞ ዓል-ቃይዳ አብሯቸው ሲሰራ ከቆያቸው አባላቱ ወይንም ከርሱ ጋር ንክኪ ባላቸው ሌሎች ድርጅቶች ውስጥ የነበሩ ግለሰቦችን መያዝ፣ መክሰስና መታሰር አጥብቆ ስለሚቃወም ሲሆን በተለይም በዚህ ረገድ የሼህ አማር አብደልራሕማን በቁጥጥር ሥር መዋል፣ ለፍርድ መቅረብና በእስር መቀጣት ለዚህ ጥላቻውና ተግባሩ አነሳስቶታል::

3. ዓል-ቃኢዳ ይዟቸው ከተነሳቸው ዓላማዎች መሀከል ዋንኛ የሚባለው በሳውዲ ዓረቢያ እና በተቀረው የዓረብ ንፍቀ ክበብ ብሎም በሶማልያ ይገኝ የነበረውን የአሜሪካን ጦር በኃይል ማስወጣት ነው:: የዓል-ቃኢዳ አባላት ባስተላለፏቸው ፋትዋዎች (ፋትዋ በእስልምና ታላቅ ትዕዛዝና ጥሪ ነው) እንደዚያ ዓይነት የኃይል እርምጃዎች አስፈላጊም ተገቢም እንደሆኑ በተደጋጋሚ ገልፀዋል::

4. ከ1994 ጀምሮ አይማን ዓል-ዛዋሒሪ ወይንም በሌላ መጠሪያው «አብደል ሙዋዝ» ወይንም በሌላ መጠሪያው «ዶ/ር አይማን ዓል ዛዋሒሪ» ወይንም በሌላ መጠሪያው «ዑስታዝ» ወይንም በሌላ መጠሪያው «ሐኪሙ» ወይንም በሌላ መጠሪያው «አቡ መሐመድ» ወይንም በሌላ መጠሪያው «አቡ መሐመድ ኑር ዓል-ዲን» በከፊል በግብጽ ያለውን መንግሥት በመደገፉ የተነሳ የግብጽን መንግሥት በሃይል መገርሰስን እና አሜሪካ ላይ ሃይል እና አመጽ የተቀላቀለበት ተቃውሞ ለማድረግ ቆርጦ የተነሳውን የግብፁን የእስልምና ጂሀድ መምራት ጀመረ:: የግብፁ የእስልምና ጂሀድ

አባላትም ለዓል-ዛዋሒሪ እና ለእስልምና ጂሀዱ ቃል ገቡ:: ከዚህ በመቀጠ ልም ተከሳሾች አይማን ዓል-ዛዋሒሪን እና መሐመድ አጤፍን ጨምሮ በርካታ የግብጽ እስልምና ጂሀዱ አባላት በዓል-ቃይዳ ውስጥ ተጽዕኖን መፍጠር የቻሉ አባላት ለመሆን በቁ:: ቀስ በቀስም በየካቲት 1998 በዓል-ዛዋሒሪ የሚመራ የነበረው የግብጹ እስልምና ጂሀድ ከዓል-ቃይዳ ጋር ውጤታማ ውህደት የፈፀመ ሲሆን ውህዱ ቡድንም አሜሪካውያን ሲቪሎችን የጥቃት ዒላማው አደረገ::

5. ዓል-ቃይዳ ይንቀሳቀስ የነበረው በራሱ እንዲሁም በጥላው ድርጅቱ ስር ይንቀሳቀሱ በነበሩ አንዳንድ የሽብር ድርጅቶች ሲሆን ከእነዚህ መሀከልም የግብፁ የእስልምና ጂሀድ እና አንዳንዴም የእስልምናው ቡድን (ኤል ጋማ ኢስላሚያ ወይንም ጋማዕት ብቻ ተብሎ ይታወቃል) ይህም በሼህ ኦማር አብደልራሕማን እና በኋላም ላይ በአሕመድ ራፋይ ጣሀ ወይም በሌላ መጠ ሪያው ያሲር አል ማስሪ የሚመራው ነው:: እነዚህ ደግሞ በዚህ የክስ ፋይል የሴራው ጥንስሳ አጋሮች (co-conspirators) እንጂ ተከሳሽ ተብለው አይጠሩም:: ዓል-ቃኢዳ ከእነዚህም በተጨማሪ ሱዳን፣ ኤርትራ፣ ሶማልያ፣ የመን፣ ግብጽ፣ ሳውዲ ዓረቢያ፣ ጅቡቲ፣ አፍጋኒስታን፣ ፓኪስታን፣ ቦስኒያ፣ ክሮኤሽያ፣ አልባንያ፣ አልጄሪያ፣ ቱኒዢያ፣ ሊባኖስ፣ ፊሊፒንስ፣ ታጂኪስታን፣ አዘርባዣን፣ በሕንዷ የካሽሚር ግዛት እና በቼቼንያዋ ሩሲያ ባሉ የጂሀድና የሽብርተኝነት ቡድኖች ድጋፍም ጭምር ይንቀሳቀሳል:: ዓልቃይዳ እንደ ኬንያ፣ አሜሪካ፣ እንግሊዝ፣ ታንዛኒያ እና ካናዳ ባሉ አገራት ውስጥ ሴሎችና አባላትን አሰማርቷል::

6. ዓል-ቃይዳ የሽብር አፕሬሽኖችን ጨምሮ ዋና ዋና የሚባሉ ተግባራትን ተወያይቶ የሚያፀድቅ ማጅሊስ አል-ሹራ (የውይይት ምክር ቤት) የሚባለውን ጨምሮ ሌሎች የትዕዛዝ እና ቁጥጥር መዋቅሮች አሉት::

በመተባበር በሉንዶን የሚገኝ የሚዲያ መረጃ ቢሮ (ከዚህ በኋላ «የሉንዶኑ ቢሮ» በመባል ይታወቃል) የከፈቱ ሲሆን ቢሮውም የዑሣማ ቢን ላደንን መግለጫዎች ለሕዝብ ይፋ ማድረግ፣ የአል-ቃይዳን «ወታደራዊ» እንቅስቃሴዎች ይህ ሲባልም የወታደር ምልመላን፣ የፈንድ መስጠት እና አስፈላጊ ቁሳቁሶች (እንደ ሳተላይት ቴሌፎን ያሉትን ይጨምራል) መግዛታቸውን እና አስፈላጊ አገልግሎቶች መኖራቸውን የመሳሰሉትን ጨምሮ ሽፋን መስጠትና መዘገብን የመሳሰሉ ኃላፊነቶች ተሰጥተውታል። የሉንዶኑ ቢሮ ከዚህም በተጨማሪ የኬንያውን ሴል ጨምሮ በተለያዩ የዓል-ቃይዳ ሴሎች የሚካሄዱ የደህንነት እና የወታደራዊ እንቅስቃሴዎች ለዓል-ቃይዳው ዋና መስሪያ ቤት ሪፖርት የማድረግ ኃላፊነትም ተሰጥቶታል።

# የቀረቡ ክሶች ከአንደኛ እስከ ስድስተኛ

የግድያ፣ የቦምብ፣ የአካል ጉዳት ማድረስ ሴራዎች

## አንደኛው ክስ፡

የአሜሪካን ዜጎች ለመግደል ማሴር

10. ከ 1990 ጀምሮ ይህ ክስ እስከተዘጋጀበት ጊዜ ድረስ በደቡባዊዋ የአሜሪካ ከተማ ኒው ዮርክ፣ በአፍጋኒስታን፣ በእንግሊዝ፣ በፓኪስታን፣ በሱዳን፣ በሳውዲ ዓረቢያ፣ የመን፣ ሶማልያ፣ ኬንያ፣ ታንዛንያ፣ አዘርባዣን፣ ፊሊፒንስ እና በሌሎችም ቦታዎች ከማንኛውም የዲስትሪክትም ሆነ ከመንግሥት ቁጥጥር ነፃ በሆኑ ቦታዎች ላይ ዑሳማ ቢን ላደን. . . [የሌሎች ተከሳሾች ስምም ሰፍሯል] የተባሉት ተከሳሾች መሀከል ቢያንስ አንዱ በኒው ዮርክ ደቡባዊ ግዛት ውስጥ ከሌሎች የዓልቃይዳ አባላትና ደጋፊዎች፣ ከግብጽ የእስልምና ጂሀድ እና ሌሎች አሁን ለጊዜው ለዚህ ፍርድ ቤት የማይታወቁ ሰዎች ጋር ታስሮ በሕገወጥ መንገድ ነገር ግን

ራሱ ፈቅዶ በማሴር፣ በመምከር በንፁሀን አሜሪካውያን ላይ ጥቃት ለመሰንዘር ተስማማ::

# አባሪ 5

መስከረም 23፣ 2001 በአሜሪካ የተወካዮች ም/ቤት የዓለም ዓቀፍ ጉዳዮች ኮሚቴ በዓል-ቃይዳ አማካይነት የተሰነዘረውን አደጋ አስመልክቶ ተወያየ:: ከዚህ በመቀጠል አባሪ ተደርጎ ለዚህ ጽሁፌ ማጠናከሪያ የቀረበው ጽሁፍም ይህ ኮሚቴ ስብሰባውን ሲጀምር ከውይይቱ አስቀድሞ በንባብ የቀረበለት ሰነድ ነው:: በዚህ ጽሁፍ ላይም በዋናነት የተንፀባረቀው አሰቃቂው የ መስከረም 11፣ 2001 ጥቃት በሚደርስበት ወቅት የአሜሪካ ስለላ የነበረውን መረጃ ነው:: በዚህ ወቅት ታዲያ ስለ ቢን ላድን ድርጅቱ የነበረው ምስል እና አጠቃላይ ግንዛቤም የተንሸዋረረና ስህተት ያጋደለበት እንደሆነ ተረጋግጧል:: ይህንን ዶሴም ሆነ የዚያን ስብሰባ ጭብጥ በጽሁፍ ኢንተርኔት ላይ ማግኘት ለሚፈልጉ ሁሉ፣ http://www.internationalrelations.house.gov/archives/107/75562.pdf ላይ ማግኘት እንደሚችሉ እገልፃለሁ::

## በአሜሪካ የስለላ ድርጅት የቀድሞው የፀረ-ሽብርተኝነት አጥፊሽኖች ኃላፊ ቪንሰንት ካኒስትራሮ ተዘጋጅቶ የቀረበ መግለጫ

በቅድሚያ በዚህ በተከበረው ኮሚቴ ፊት ቀርቤ ስለ ዓል-ቃይዳ፣ መዋቅሮቹ እናም አጠቃላይ ዓላማዎቹ እንድገልጽ ዕድሉ ስለተሰጠኝ የተሰማኝን ደስታ ልገልጽ እወዳለሁ:: በዚህ ባለንበት ዘመን ሰፊው የአሜሪካ ሕዝብ እንደ ዓልቃይዳ ያሉትን ሃይማኖትን እጅግ አደገኛ ከሚባል አክራሪነት ጋር በግድ በማጣመር የሚንቀሳቀሱ ድርጅቶችን ምንነት የመረዳት ችግር እንደገጠመው ይታወቃል:: በመሆኑም አገራችን አሜሪካ ውስጥ በሕዝብ

ይሁኝታ መንግሥታችን ስልጣኑን ከጨበጠ በኋላ ሕግና ሥርዓትን ለማስከበር በተለያዩ ደረጃዎች ያቋቋማቸው ኤጀንሲዎችና ድርጅቶች በአገር ውስጥም ሆነ በውጪ ሃይማኖታዊ ማክረርን ያነገቡ ወገኖችን ባሕሪ ተንትኖ ማቅረብ ይኖርባቸዋል:: በመሠረቱ እንደ ሕዝብና እንደ አገር የመጣብንን እና የተደቀነብንን ወረራ በስኬት ከመመከታችን በፊት የአደጋውን ተፈጥሮአዊ ባሕሪ መረዳት ግድ ይለናል:: ለነገሩ የአክራሪነት ነገር ከተነሳ በዚህ በአሜሪካችን ውስጥ እንኳ በእግዚአብሔር ስም እየማሉና እየተገዘቱ፤ ስሙንም እየጠሩ የግድያ እና የአካል ማጉደል ጥቃት በሌሎች ላይ የሚያደርሱ እንደ Christian Identity ያሉ ድርጅቶችም መኖራቸው ይታወቃል:: ዑሣማ ቢን ላደን የተባለው አሸባሪና በሱ ኔትወርክ ውስጥ የታቀፉ ጀሌዎቹ ሁሉ ያላቸውን የዓለም አመለካከት በቅጡ ለመረዳት ብሎም የደቀኑብንን አደጋ ለመመከት ካስፈለገ በቅድሚያ የእንደዚህ ዓይነቱን አክራሪነት ባሕሪ መረዳት ቅድሚያ የሚሰጠው ነው:: እንደዚህ ያሉ በሚፈጽሙት ጥቃት ወቅት በራሳቸው ሕይወት ላይም ጭምር አደጋ በማድረስና መስዕዋት እስከመሆን ለመድረስ ፈቃደኛ የሆኑትን ግለሰቦች አስተሳሰብና ስነ-ልቦና ካልተረዳን በቀር በመላው ዓለም መጋረጃ ያስቀደደውን የመስከረም አስራ አንዱን ሐዘን እንዲያውም በባሰ ሁኔታ ተደግሞ ብናየው ላያስገርም ይችላል:: እናም በዚህ የተነሣ እንደ ዓል-ቃይዳ ያሉ ቡድኖች እንዴት ሊፋፉና ሊያንሰራሩ እንደቻሉ መረዳት ያስፈልጋል:: አገራችን አሜሪካ ለዓለም ሰላም መከበርና ደህንነት ባላት ቁርጠኛና ከቶም የማይጠረጠር አቋም በመታገዝ በመካከለኛው ምሥራቅ እየፈጠረችው ያለውን ታላቅ ተጽዕኖ አጥብቆ የሚቃወመው ዑሣማ ቢን መሐመድ ቢን ላደን በ1990 በተካሄደው የኤደን ባሕረ ሰላጤው ጦርነት ወቅት በርካታ የአሜሪካ እና የሌሎች ምዕራባውያን አገራት ወታደሮች በሳውዲ አረቢያ ገብተው የነበረ በመሆኑ ነው ቅያሜና ጥላቻ አድሮበት

እንዲህ ለመሆን የበቃው። ቢን ላደን በአሁኑ ወቅት በተከበሩት የዓል-ሳዑዲ ንጉሣውያን ቤተሰቦች የምትመራውን ሳውዲ ዓረቢያን እንደ እስልምና ቅዱስ ቦታ መገኛ አድርጎ ነው የሚቆጥራት። ለነገሩ ባሁን ሰዓት በዚያች አገር ስልጣን ይዘው የሚገኙት እና የዘውዳዊው ሥርዓት መስራች የሆኑት ንጉሥ አብዱልአዚዝ ዓል-ሳዑድም ቢሆኑ አክራሪ በነበረው በዋሐቢ ቡድን ድጋፍ ይደረግላቸው እንደነበረ ይታወቃል። እናም የዘውዳዊው ሥርዓትና የዓል-ሳዑድ ቤተሰብ በዋህቢ ድጋፍ ነው ለዚህ በቅቶ የዛሬዋን ሳውዲ ዓረቢያ የሚመራው። ይህ ውለታ ግን በነፃ አይደለም የተደረገለት። ይህንን ውለታ ዛሬ በእስልምና ሃይማኖት እጅግ ከፍተኛ ክብር የሚሰጣቸውን መካ እና መዲናን ደህንነታቸውን በማረጋገጥ ነው የሚመልሰው። ዑማማ ቢን ላደን እንደሚያምነው ከሆነ የእስልምና ሃይማኖትን ኦፊሴላዊ በሆነ መንገድ በማራመድ የተቀደሱትን ሥፍራዎች ደህንነት ለማረጋገጥ እጅግ የከበደ ኃላፊነት እና የክብር ጠባቂነት አደራ ተሰጥቷት የነበረችው ሳውዲ ዓረቢያ ውስጥ የክርስትያን ምዕራባዊ ወታደሮች በባሕረ ሰላጤው ጦርነት ጊዜ መርመስመሳቸው ነው እንደ ውጉዝ የተቆጠረው። ቢን ላደን በዚህ የተነሣ ዘውዳዊውን ሥርዓት አጥብቆ በመኮነኑ በተፈጠረው አለመግባባት ከአገር እንዲወጣ ታዘዘ። ቢን ላደን ግን ውስጡ አምርሯልና ከተባረረም በኋላ በሱዳን እያለ የራሱን የተለያዩ የሀብት ምንጮች እንዲሁም በሳውዲ እና በባሕረ ሰላጤው የሚያውቃቸውን ነጋዴዎች ከፍተኛ ድጋፍ በማስተባበር ወደተለያዩ እስላማዊ አገሮች የሚዘረጋ መዋቅር መፍጠርን ተያያዘ። ይህን መሰሎቹ ድጋፎች፣ በቢን ላደን ዋርካ የሚመራው የዓለም ዓቀፍ የእስልምና የእርዳታ ድርጅት፣ እንዲሁም ከሌሎች የተለያዩ የእርዳታ ድርጅቶችና ግንባሮች እና ሌሎችም ጭምር ናቸው ዛሬ ቡድኑን የሚያንቀሳቅሱት።

ምንም እንኳ አብዛኞቹ «ሙጃሂዲን» በመባል የሚታወቁት የውጊያ ልምድ ያላቸው «የዓረብ አፍጋኖች» ሩሲያውያኑ እስከወጡበት እስከ 1988 ድረስ በአፍጋኒስታን ባይገኙም ቢን ላደን ዛሬ በመላው ዓለም ያስማራቸው ካድሬዎቹ እና ኔትዎርኮቹ ግን በእነዚህ ሰዎች ነው ስልጠና ያገኙት:: የቢን ላደን ዋንኛ ዓላማም እነዚህን የሰለጠኑ ተዋጊዎች ዓለማዊና ሕጋዊ (secular) መንግሥት መስርተው የሚገኙትን የአረብ መንግስታት ገብተው እንዲያስወግዷቸው እና በቦታቸውም በሰሪያ ብቻ የሚተዳደሩ የሃይማኖት መንግሥታትን ማስፌን ነው:: በዚህ ጥቃትም ዒላማ የተደረጉት እንደ ግብጽ እና አልጄሪያ እንዲሁም በሩሲያ ውስጥ የሚገኙት ሙስሊም ቁጥር የሚያመዝንባቸው አገራት ለምሳሌም ቼቼኒያ እና ዳጌስታን፣ ቦዝኒያ እና ኮሶቮ ናቸው:: ከዚህም በተጨማሪ በሊቢያ እና በቱኒዥያ ፀረ-መንግስት እንቅስቃሴዎች እንዲደረጉ ግፊት ሲካሄድ ቆይቷል:: በእርግጥ የቢን ላደን ዋንኛ ፍላጎት እና ዓላማ የተደመሰውን እና በታሪክ የሚታወቀውን የኦቶማን ቱርክን «እስላማዊ ካሊፌት» ዓይነት መንግሥት በእያንዳንዱ ሙስሊም አገር ውስጥ በታሊባኑ በሙላ አማር መሪነት መልሶ ለመጫን ነው:: አሜሪካ እና ምዕራባዊ ሸሪኮቿ ደግሞ በአሣማ ዓይን ለዚህ ዋንኛ ዓላማው እንቅፋቶች ናቸው::

እንግዲህ ከዚህ በኋላም አሜሪካ እና ሳውዲ ዓረቢያ በሱዳን መንግሥት ላይ በጋራ በፈጠሩት ጫና የተነሳ ቢን ላደን የግድ ወደ አፍጋኒስታን መቀመጫውን ለመቀየር ተገደደ:: በፓኪስታን ይገኙ በነበሩ የእስልምና ሃይማኖት ትምህርት ቤቶች ውስጥ ከፍተኛ ስኬትን ባገኙት ተማሪዎች የተመሠረተው ታሊባን በፓኪስታን የወታደራዊ ስለላ አገልግሎት እንዲሁም በ Inter Services Directorate (ISI) አማካይነት ባገኙት ድጋፍ በአብዛኛው አፍጋኒስታን ላይ ቁጥጥር ማድረግ ቻሉ:: በዚህ ወቅት ፓኪስታን እውቅና ሆነ ብላ ታሊባኖችን በአፍጋኒስታን ላይ

ያነገበችው በፓኪስታን ውስጥ እጅግ የተከበረ የሚባለው የፓሽቱን ጎሣ በአፍጋኒስታን ውስጥ አገር እያስተዳደረ የነበረውን ነገር ግን ለፓሽቱን ጠላት ተደርጎ የሚታየውን ጎሣ ለማስወገድና ቁጥጥሯንም ለማስፋት ስትል ነው። ፓሽቱኖች ወይንም በምዕራብ ብዙውን ጊዜ ፓታን በመባል የሚታወቁት ጎሣዎች በተለይ በአፍጋን እና በፓኪስታን አጎራባች ድንበር ቦታዎች ላይ በብዙ መልኩ ተስፋፍተው ይገኛሉ። እንግዲህ ችግሩ ያለው ምንም ዓይነት ዓለማዊ ወይንም ሲቪል (secular) ትምህርትን ያልቀሰሙት ታሊባኖች በመንግሥት አስተዳደር ላይ ያላቸው አቋም ከመካከለኛው ዘመን ፈጽሞ የማይሻል መሆኑ ላይ ነው። የታሊባን መሪዎች አገሪቱን እጅግ በተበላሸና በተጣመመ ሁኔታ አስተዳድረዋል፤ ቢሆንም ግን ሙሉ በሙሉ በፓኪስታን ተጽዕኖ ስር ወድቀዋል ለማለት ባይቻልም ፓኪስታን የፈለገችውን ግን ብዙ ጊዜ ፈጽመውላታል። በዚህ መልኩ የታሊባኖችን በጎ ፈቃድና ድጋፍ ያገኘችው ፓኪስታንም የምትሰጣቸውን የተለያዩ ድጋፎች መከታ በማድረግ በአፍጋኒስታን ውስጥ የካሽሚር ሽብርተኞች እንዲፈጠሩ እና ለእነሱ ማሰልጠኛ የሚሆን ካምፕ በታሊባኖች እንዲቋቋም አድርጋለች። በእነዚህ ሙፍቲ በሚሰኙ የማሰልጠኛ ተቋማት ውስጥ የ ISI አባላት በአካል ለመሪነትና ለአስተባባሪነት ተመርጠው ይገኛሉ። እንግዲህ በዚህ ዓይነት የተወሳሰበ አደረጃጀት ገብተው ነው ፓኪስታን ግን በካሽሚር ሽብርተኝነትን ስለማስፋፋቷ ስትጠየቅ «ግልጽ ክህደት» የምትፈጽመው። ፓኪስታን ከዚህም በተጨማሪ የታሊባንን ቁጥጥር ለማደናቀፍ በሚሞክረው እና እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስም በአብዛኛው ሰሜን ካቡል እና ፓንሺር ግዛቶች ውስጥ እስከ 7% የሚሆን ቁጥጥር ለነበረው «የሰሜን ትብብር» ("Northern Alliance") መፋለም ይቻላቸው ዘንድ ለታሊባኖች የመሣሪያ ድጋፍ ስትሰጥ ቆይታለች። «የሰሜን ትብብር» ("Northern Alliance") የተባለው ቡድን ምንም እንኳ አንዳንድ የፓሽቱን ጎሣ ተወላጆችን በውስጡ

ቢያቅፍም የሚመራው ግን በብሔር የታጂክ ተወላጅ በሆነው አህመድ ሻህ ማሱድ ነው:: ከሶስት ሳምንታት በፊትም ማሱድ ከቢን ላደን ቡድን ጋር ቁርኝት እንዳለው በተደረሰበት አንድ ቡድን ነው ሆን ተብሎ በተጠመደ ቦምብ እንዲገደል የተደረገው::

በመሠረቱ በሙላ አማር እና በዑሣማ መሐመድ ኢብን ቢን ላደን መሀከል ያለው ግንኙነት የሥጋ ዝምድና ነው:: በዚህ እጅግ የጠነከረ ዝምድናም ቢን ላደን የሙላ አማርን አመራር፣ ፍላጎት እና ዓላማዎች ልክ እንደ ራሱ አድርጎ ሊተገብር እና ሊያስፈጽም ቃል ገብቷል:: ቢን ላደን በቅርቡ በታሊባኖች የምትተዳደረውን አፍጋኒስታን «አዲሷ መካ» ብሎ ሲሰይም ሙላ አማርን ደግሞ «አዲሱ ካሊፍ» በማለት አወድሷል:: እናም በዚህ የተነሣ የአሜሪካ መንግሥት ብዙ ጊዜ ሲለው እንደቆየው ሙላ አማር ቢን ላደንን አሳልፎ ለአሜሪካ እንዲሰጥ ማሰብ ማለት ፈጽሞ የማይሆን ነገር ነው እላለሁ:: እንዴ. . . ሌላው ቢቀር እኮ ቢን ላደን ያሰማራቸው እና በቁጥር ከ 4,000 እስከ 5,000 እንደሚደርሱ የሚገመቱት ተዋጊዎቹ ከታሊባን ጦር ጋር ፍፁም የጠበቀ ቁርኝት አላቸው፣ ሙላ አማርም ቢን ላደንን እንደ ቀኝ እጁ አድርጎ ይቆጥረዋል!

እሺ፣ ክቡራትና ክቡራን የም/ቤቱ የዓለም ዓቀፍ ግንኙነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት! ለመሆኑ ዓል-ቃይዳ ምንድነው? የዓረቢኛ ቃሉ ትርጉም «መሠረት» የሚል ነው:: ቢን ላደን በዓለም አቀፍ ደረጃ የዘረጋውን ኔትዎርክ አንድም ጊዜ ዓል ቃይዳ ብሎ ጠርቶት አያውቅም:: ዓል ቃይዳ አሁን በደቡብ አፍጋኒስታን በሚገኘው ዋናው የቢን ላደን ቢሮ ጦርን በተመለከተ ከፍተኛ እገዛ የሚያደርግለት ክፍሉ ነው:: በዚህ ስልጠና ካምፕ ውስጥ እስከ 10,000 የሚደርሱ የባንግላዴሺ፣ የፓኪስታን፣ የቱኒዝያ፣ የሞሮኮ፣ የአልጄሪያ፣ የግብጽ፣ የቺቺንያ፣ዳጌስታን፣ ኮሶቮ እና የሌሎች አገራት ተወላጆችም እንደሰለጠኑበት ይታመናል:: አንዳንዶቹ

እጅግ ለየት ያለ የስለላ ስልጠና የተሰጣቸው ሲሆን ሌሎቹ ደግሞ ፈንጂዎችን በመስራት፣ ቀሪዎቹ ደግሞ የኬሚካል መሣሪያዎችን በማምረት የሰለጠኑ ናቸው:: በዚህ መልኩ ለየት ያለ ስልጠና ያላገኙቱ ደግሞ የውትድርና ስልጠና አግኝተው አንድም የአገራቸውን ሃይማኖታዊ ያልሆነ (secular) መንግሥት ጥላቻ በመቀስቀስ እንዲፋለሙ ወደአገራቸው የተላኩ ወይንም ደግሞ ታሊባኖች በ «ሰሜን» ተቃዋሚዎቻቸው ላይ በሚያደርጉት ፍልሚያ እንዲቀላቀሏቸው የተደረጉ ናቸው:: ላለፉት አራት ያህል ዓመታትም የቢን ላደን ሰዎች ከታሊባኖች ጋር በመሆን ማሱድን የተፋለሙ ሲሆን የዛሬ ሰባት ወራት ገደማ የተገደለውን አንድን የቢን ላደንን የገዛ ልጅ ጨምሮ በቁጥር ከ 7,000 እስከ 1,0000 እንደሚደርሱ የሚገመቱ ሰራዊቶቻቸውን አጥተዋል::›

በመሠረቱ መዋቅርን አስመልክተን ስንነጋገር ግን ለዓል-ቃይዳ ድጋፍ የሚሰጡትን የአጋር ድርጅቶች «ላላ ያሉ» (loose networks) እና ዋንኛውን ስትራቴጂካዊ ኦፕሬሽን በእነ ቢን ላደን መሪነትና ጥብቅ ቁጥጥር የሚያከናውነውን ዓል-ቃይዳን መለየት ግድ ይለናል:: ለምሳሌም የ USS Cole በቦምብ መጋየት በዓል-ቃይዳ ጥብቅ ቁጥጥር ሥር የተካሄደ ኦፕሬሽን ሲሆን በየመን ውስጥ በዑሣማ ፈንድ እየተደረገ በቢን ላደን ቀርሣ የተቋቋመው ከረር ያለ እስልምናን የሚያራምደው ኤደን የተባለው ቡድን ሠራዊት በማቀጣት ያገዘው ነው:: ይህ ኦፕሬሽን የተመራውም ለቢን ላደን የኦፕሬሽኖች ኃላፊና አዛዥ (Chief of Operations) በመሆን እያገለገለ በሚገኘው በግብፃዊው መሐመድ አጤፍ ነው:: ለነገሩ በሁለቱ መሀከል ያለው ትስስር ቀደምት ንጉሶች እንደሚያደርጉት ዓይነት የጋብቻ ትስስርም የተፈፀመበት ነው:: ባለፈው የግንቦት ወር ላይ የቢን ላደን አንደኛው ልጅ የአጤፍን ሴት ልጅ ያገባ ሲሆን ይህ ጋብቻም በግብጹ የእስልምና ጂሀድ እና አል-ቃይዳ መሀከል የተፈፀመውን ውህደት

ያመላከተ ክስተት ሆኗል። በዚህ ውህድ እንቅስቃሴ ውስጥም አንደኛው ውስጣዊ ኑዲስ ክንፍ «ጂሀድ-ዓልቃይዳ» ተብሎ ተሰይሟል።

በሌላ በኩል ደግሞ የአህመድ ራሳምን ጉዳይ ስናነሳ ዓል-ቃይዳ አጋሮቹን በመጠቀም በአሜሪካ ላይ የፈፀመው ጥቃት መሆኑን እንመለከታለን። ይህንን «ሚሌኒየም» ብለው የሰየሙት ኦፕሬሽን የተበላሸው ራሳም በአሜሪካ እና በካናዳ ድንበር ላይ ሆኖ ለአምስት ቦምቦች የሚሆኑ የማቴሪያል ግብዐቶችን እያጓጓዘ በሚገኝበት ሰዓት በመደንገጡ ነው። በራሱ በዑሣማ ቢን ላደን ፈንድ ከሚደረገው አንድ የአልጄሪያ የሽብርተኝነት አንጃ የመጣው ራሳም በአፍጋኒስታን በሚገኘው የዓል-ቃይዳ ተቋም ስልጠና ተሰጥቶት በኋላም ለሥራ ማስኬጃ ተብሎ እስከ 12,000$ ዶላር የሚሆን ገንዘብ የተሰጠው ነው። ዓል-ቃይዳ ለራሳም ይህንን ገንዘብ ከሰጠው በኋላ ቀሪውን አስፈላጊውን ገንዘብ ደግሞ በካናዳ ውስጥ የተለያዩ ወንጀሎችን በመስራት እንዲያሰባስብ፣ ከዚያ ሴሎቹን በሀቡዕ እንዲያደራጅና በአሜሪካ የሚመቱ ንፁሀን ዒላማዎችን እንዲመርጥ ጥብቅ ትዕዛዝ ሰጠው። ራሳምም የቻላቸውን ያህል ንፁሀን ተሳፋሪዎችን ለመግደል በማሰብ በሎስ አንጀለስ ዓለም ዓቀፍ አውሮፕላን ማቢያ ቦምብ ለማፈንዳት አቀደ። ልክ ይህ በሚሆንበት ጊዜ ደግሞ ዓል-ቃይዳ እጅግ ጥብቅ ቁጥጥር የሚያደርግበት አንድ ኃይለኛ ኦፕሬሽን በኤደን ወደብ የከል መርከብ የሆነውን USS The Sullivansን ለመምታት ታቅዶ ይካሄድ ነበረ። በዚህ ወቅትም በአጥፍቶ ጠፊዎቹ ትነዳ የነበረችዋ ፈንጂ ጫኟ ጀልባ ወደቡ ውስጥ ሰጠመች። ሁለቱ አጥፍቶ ጠፊዎች ኦፕሬሽናችን በጠላት ይታወቃል ብለው እርግጠኛ ሆኑና ከሰጠሙበት ወጥተው ጻርቻው ላይ ጀልባውን አቁመው ተሰወሩ። ነገር ግን የኦፕሬሽኑ ሙከራ ሳይታወቅ ቀረ። ከ 8 ወራት በኋላ እጅግ የበለጠ ዘመናዊ የሆኑ መሣሪያዎችን እና ቴክኒኮችን ከአስደናቂ ብቃት ጋር በመጠቀም በ Cole ላይ ታቅዶ

የነበረው የቦምብ አደጋ አጥሬሽን ተፈፀመ:: የደረሰውን ጉዳት ለናንተ መንገር «ለቀባሪው. . .» እንደሚሉት እንዳይሆንብኝ እያዘንኩ አልፈዋለሁ:: ክቡራትና ክቡራን የም/ቤቱ የዓለም ዓቀፍ ግንኙነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት! ለመሆኑ ዓል-ቃይዳ በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ያሉትን ኔትወርኮችና አጋሮቹን እንዴት ነው ፈንድ የሚያደርገው? በመሠረቱ በርካታ በሳውዲ ዓረቢያ የሚገኙ የቢዝነስ ሰዎችና ቱጃሮች፣ ከዚህም በተጨማሪ ደግሞ በኤደን ባሕረ ሰላጤ የሚገኙ ሀብታሞች ገንዘብ ያዋጡለታል:: በእርግጥ ከእነዚህ መዋጮ አድራጊዎች ውስጥ አብዛኞቹ ገንዘባቸውን የሚሰጡት የእስልምናን አንድነት ለማጠናከር ባላቸው ፍላጎት በመነሳሳት ብቻ ነው:: ነገር ግን ገንዘብ የሚያዋጡት ሰዎች የሚመሯቸው ድርጅቶች ጥቃት እንዳይደርስባቸው ሲሉ «ራሳቸውን ለመከላከል» እንደሚያዋጡም ነው መረጃዎች የሚጠቁሙት:: ባንድ ወቅት የሳዑዲ ዓረቢያው መንግሥት ባንኖ በርካታ ሰዎችን በቁጥጥር ሥር በማዋል ቻናሉ እስኪዘጋ ድረስ የብሔራዊ ባንኩ ለቢን ላደን የሚላከውን ገንዘብ ዝውውር ይፈጽም የነበረ መሆኑን ብዙም መጠራጠር አልፈልግም::

በርካታ የሳውዲ ቱጃሮችና ባለፀጎች በዚሁ በመንግሥት ባንክ ተጠቅመው ነው ዛሬ ለዚህ የበቃውን ቢን ላደንን ሲደግፉ የቆዩት:: ዛሬስ? ዛሬ ዛሬ ደግሞ የሳውዲ መንግሥት ያንን አስደንጋጭ እርምጃ ከወሰደ በኋላ እነዚህ ባለጠጎችና ቱጃሮች ሌሎች ድንቃ ድንቅ የፈጠራ መንገዶችን በመጠቀም ነው ገንዘብ ለቢን ላደን እና ለቡድኑ የሚያግዙት:: ለምሳሌም በኒው ዮርኩ ፖርትፎሊዮ ገበያ ውስጥ ያለ አንድ ስቶክ እንዲዘጋ ትዕዛዝ ይተላለፋል:: ከዚያም ያ በስቶኩ ያለው ፈንድ ወደ ኤደን ባሕረ ሰላጤ ይላካል:: ይህንንም የሚያደርጉት በአፍሪካ በሆንግኮንግ ወይ በባሕረ ሰላጠ ,ው ያለ የቢን ላደን ሸሪክ የሆነ አንድ ባንክን በመጠቀም ነው:: ሌሎች ደግሞ በተባበሩት ዓረብ ኤሚሬት እና በኳታር ያሉ የገንዘብ ተቋማት

ከቢን ላደን ጋር ባላቸው ቁርኝት ይህንን ፈንድ የማስተላለፉን ተግባር ይፈጽማሉ:: ሌላው ፈንድ የሚገኝበት ምንጭ ደግሞ በተለያዩ አገናኞች (intermediaries) አማካይነት የሚደረግ የጥሬ ገንዘብ ዝውውር ነው:: ከዚህ በተጨማሪም ከሳውዲ ዓረቢያ በኢደን ባሕረ ሰላጤ ወደሚገኘው የቢን ላደን የ «ግንባር» የቁጠባ ሒሳብ አካውንት ገንዘብ የሚያስተላልፉ ሴት የገዛ ቤተሰቡ አባላት ለመኖራቸውም ማስረጃዎች ያሉን መሆኑን ለመግለጽ እወዳለሁ::

ከቡራትና ከቡራን፣ ቀሪ ፍሬ ነገሮችን እና ጭብጦችን በጥያቄና መልስ ውይይት ጊዜ ይበልጥ ልናጸብራቸው እንደምንችል እምነቴን በመግለጽ ጽሁፌን በዚሁ እቋጫለሁ:: የምታነሷቸውን ማናቸውንም ጥያቄዎችና አስተያየቶች ለመቀበል ዝግጁ ነኝ:: በጣም እግዚር ይስጥልኝ!!

# አባሪ 6

«የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት የዓለም ዓቀፍ ግንኙነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ መስከረም 23፣ 2001 ባካሄደው ስብሰባ በዓል-ቃይዳ የተደቀነውን አደጋ አስመልክቶ ውይይት አድርጓል:: የቀረቡለትን ገለፃዎችም አዳምጧል:: ግን በጣም አስገራሚው ጉዳይ አሊቨር ሬቬል የተባለው የ FBI ባለሥልጣን ቢን ላደን ፈጽሞ እንዳልተሳተፈባቸው የምናውቃቸውን ጥቃቶች «ቢን ላደን ነው ያደረሰው» እያለ ገለፃ የሚያደርግ መሆኑ ነው:: ይህ አሊቨር ሬቬል ያቀረበው እና ለም/ቤቱ ቋሚ ጉዳዮች ኮሚቴ አባላት በንባብ የተሰማው ጽሁፍም ሆነ የስብሰባው ፍሬ ጭብጦች መግለጫ በ http://www.internationalrelations.house.gov/archives/107/75562.pdf ላይ ማግኘት የሚቻል መሆኑን እገልፃለሁ::

በቀድሞው የፌዴራል የምርመራ ቢሮ የፀረ-ሽብርተኝነት ኦፕሬሽን ዩኒት የምርመራና ስለላ ጉዳዮች ኃላፊ አሊ.ቨር «ቡክ» ሬቬል የቀረበ መግለጫ

ክቡር የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት የዓለም ዓቀፍ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሊቀመንበር ሃይድ፣ ክቡራትና ክቡራን የኮሚቴው አባላት በሙሉ! በዛሬው ዕለት በርካታ ጉዳዮችን ይፋ እንደሚያወጣና ለፀረ-ሽብርተኝነታችን ዘመቻም ፊር-ቀዳጅ እንደሚሆን በሚታመንለት ስብሰባ ላይ ምስክርነቴን እንድሰጥ ዕድሉን ስላገኘሁ እጅግ አድርጌ ላመሰግናችሁ እወዳለሁ:: ባሁን ሰዓት አገራችን አሜሪካ በአሸባሪዎች ከተደቀነባት አደጋ ራሷን እና መላውን ዓለማችንን ለመከላከል እጅግ የተከበሩት ፕሬዚዳንታችን፣ መንግሥታቸው፣ ቆራጡና ጀግናው ጦራችን፣ የዲፕሎማሲና የሕግ ማስከበር ዩኒቶቻችን በሚያደርጓቸው ርብርቦሽ ውስጥ እናንተ የተከበረው ም/ቤት የዓለም ዓቀፍ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት የምታበረክቱት አስተዋፅኦና አገርና ሕዝብ የጣለባችሁ ኃላፊነት እጅግ የከበደ እንደሆነ ይገባኛል:: እኔም አገሬን እና ሕዝቤን ላለፉት 40 ዓመታት በዚህ ዩኒት ውስጥ ሆኜ ሳገለግል እንደመቆየቴ መጠን ያየሁትን፣ የሰማሁትን እና የታዘብኩትን አንድም ሳልጨምርና ሳልቀንስ በፊታችሁ በሚከተለው መልክ አቀርባለሁ::

መቼም መስከረም 11፣ 2001 በሁለቱ የኒው ዮርክ መንትያ ሕንፃዎች ላይ የደረሰው ዓለማችን ገና ከዚህ በኋላ ብዙ የሚቆጭበትና የሚያዝንበት የሽብር ጥቃት ከሕሊናችን እንደማይጠፋ እሙን ነው:: እኔ በፊታችሁ ቆሜ ምስክርነቴን የማሰማችሁ አሊ.ቨር «ቡክ» ሬቬልም ይህንን ጥቃት እኛ በስለላና በፀረ-ሽብር ዩኒቱ ውስጥ ያለን ወንድሞቻችሁ እና እህቶቻችሁ፣ ፖሊስ፣ ደህንነት፣ መከላከያ፣ እጅግ የተከበሩት ፕሬዚዳንታችንም ሆኑ ሌሎች የሕግ ማስከበር አካላት ፈጽሞ ይመጣል ብለው ያላሰቡት መሆኑን

አገልዕላችኋለሁ:: ነገር ግን ብቻ እንዲህ ያለውን ተርከንም የማንጨርሰው እልቂት ፈጽሞ ዳግመኛ እንደማናይ እምነቴን አገልዕላችኋለሁ ብዬ በእርግጠኝነት ብነግራችሁ ደስ ባለኝ:: እኔም እንደ በርካታ አሜሪካውያን የማውቃቸውን ሰዎች እና ጓደኞቼን በአረመኔያዊው ጥፋት ተነጥቄያለሁ:: ነገር ግን ያ ምኞት እንጂ እውነት አይደለም፣ እኛ አሜሪካውያን ከ 1980 ጀምሮ የተለያዩ የሽብር ጥቃቶች ዒላማ ሆነን ቆይተናል:: ለምሳሌም በኢራን የሻህ መንግሥት ወድቆ በአያቶላ ኮሚኒ የሚመራው እጅግ አክራሪ መንግሥት በስልጣን ላይ መውጣቱ እና በ1980 ሩሲያ አፍጋኒስታንን መውረሯ ይህ እጅግ አሳዛኙ የመስከረም 11 እልቂት ሊመጣ እንደሚችል ያመላከቱ ክስተቶች ነበሩ:: እና ማን ነው ተጠያቂው እህት ወንድሞቼ የተከበረው ም/ቤት አባላት? እኮ ማንን እንጠይቅ? ኢራኖችን በደፈናው ጥፋተኛ ማድረግ እንደማይቻል እየተናነቀንም ቢሆን ልናምን ይገባናል:: አዎ፣ እንደፈለጉ ንፁህ አሜሪካውያንን እያገቱ የፈለጉት እየተደረገላቸው ያለ ምንም የአፀፋ እርምጃም ሆነ ጉዳት ማምለጥ እንደሚችሉ አሳዩናቸው እኮ:: በመሆኑም በእነዚህ የልብ ልብን በገዛ ዝምታችን እና ቸልተኝነታችን የሰጠናቸው ኢራናውያን ያደፋፈሩት ሂዝቦላ በቤሩት የሚገኘውን ቆንጽላ ጽ/ቤታችንን ካንዴም ሁለቴ፣ በኩዌት ደግሞ አንድ ጊዜ ሲያቃጥልብን በአንድ ትልቅ ተሽከርካሪ ላይ ባደረሰው የቦምብ ጥቃትም 200 ያህል የባሕር ኃይል አባላቶቻችንን ገድሎብናል:: ሂዝቦላ በግልጽ አውሮፕላናችንን ጠልፎ፣ ንጹህን ዜጎቻችንን ሲያግት አፀፋ ለመመለስ ከሚገባው በላይ ተውተረተርን፣ ወኔም አጣን:: የቢን ላደንን መኖር ገና ሳንሰማ ነው የሒዝቦላው ኢማድ ሙግኒያ ወደ አገራችን አሸባሪዎችን የላኩብን:: እኚህ ሰው እና ድርጅታቸው በሊባኖስ በሚገኙ የወታደራዊ ቀጠናዎቻችን እና ተቋሞቻችን ላይ ለደረሱት ጥቃቶች ተጠያቂ ቢሆኑም በዚህ በሕዝብና

በአገር ላይ ለፈፀሙት ታላቅ ጥፋት ግን ቅጣት ሳይደርስባቸው እስከዛሬ እየፈነጩ ይገኛሉ።

ታዲያ ዓል-ቃይዳን የመሰረቱትም ሆኑ ከአረብ አገራት እንደመጡ የሚታወቁት የአፍጋን ሙጃሂዲኖች እነዚህን የእኛን ቸልተኝነት የሚያሳዩ ክስተቶችን በሚገባ ነው የሚያውቋቸው። ዑሳማ ኢብን መሐመድ ቢን ላደን እና ጀሌዎቹ «ልዕለ ኃያል» የሆነችን አገር በጎሪላ ውጊያ እና በሽብር ጥቃት ማሸነፍ ይቻላል ብለው አመኑ። በሙማኒያ ላይ ካሳየነው ቸልተኝነትና ልፍስፍስነት በመነሳትም ቢን ላደን አሜሪካ ቢወጓት መልሳ ለመውጋት ቁርጠኝነት የሌላት እንደሆነች አመኑ። ከዚህ በተጨማሪም በ1991 በሶማልያ ሰብዓዊ እርዳታ ለማድረግ እና ልዩ ጥበቃ ለማካሄድ አገራዊና ዓለማዊ ተልዕኮን አንግቦ ይንቀሳቀስ የነበረው ሠራዊታችን ከፍተኛና መጠነ-ሰፊ ጥቃት ከደረሰበት በኋላም ቢን ላደን እና ጓደኞቹ ትልቅ ብርታት አግኝተው በአሜሪካና በሕዝቧ ላይ በርካታ ጥቃቶችን ሲያቅዱ ከርመዋል። እስኪ እነዚህ በእኛ ጸተኝነት ብርታትን ያገኙ አሸባሪዎች ከፈፀሟቸው ጥቂቶቹን እጅግ የታወቁ ክስተቶችን እንጥቀስ፤

1. ሶማልያ 1991
2. የዓለም የንግድ ማዕከል፣ ኒው ዮርክ፣ 1992
3. በሐምሌ ወር 1992 በኒው ዮርክ ታቅዶ የነበረው ጥቃት
4. በሊቀ ጳጳሱ ጆን ፖል ላይ በ 1992 በፊሊፒንስ የታቀደው ግድያ (አሜሪካውያኑ በጳጳሱ የአጃቢዎች ቡድን ውስጥ ነበሩ)
5. በ 1993 በፕ/ት ክሊንተን ላይ ፊሊፒንስ ውስጥ ታቅዶ የነበረው ግድያ
6. በ 1994 በፓሲፊክ ውቅያኖስ ከ 11 እስከ 13 በሚደርሱ አሜሪካውያን ላይ የታቀደው የቦምብ አደጋ
7. በ 1995 በሳውዲ መዲና ሪያድ በግዳጅ ላይ የነበረው የአሜሪካን የወታደር ተሽከርካሪ በቦምብ መጋየቱ
8. በ 1997 ዓ.ም በዳራን ሳውዲ ዓረቢያ በኩባር ታወር ላይ የነበረው የአሜሪካ የአየር ሃይል መኖሪያ በቦምብ መጋየቱ
9. በ 1998 በኬንያ የሚገኘው የአሜሪካ ኤምባሲ በቦምብ መጋየቱ

10. በ 1998 በታንዛኒያ የሚገኘው የአሜሪካ ኤምባሲ በቦምብ መጋየቱ
11. በ 1999 አዲስ ዓመት ላይ የሎስ አንጀለስ ዓለም ዓቀፍ የአውሮፕላን ማረፊያን Y2K በቦምብ ለማጋየት መታቀዱ
12. በ 1999 የኢስት ኮስት Y2K በቦምብ ለማጋየት መታቀዱ
13. በጥር ወር 1999 የአሜሪካን የባሕር ኃይል መርከብ በየመን በቦምብ ለማጋየት መታቀዱ
14. በጥቅምት ወር 2000 በ USS Cole ላይ የደረሰው የቦምብ አደጋ

እናም እነዚህን በጥሞና ተከታትለን፣ ተገቢውን የመልስ ማጥቃትና የማያዳግም እርምጃ በመውሰድ ብንቆይ ኖሮ መስከረም 11 ላይ የመጣውን ልንገምት በቻልን ነበረ:: ሆኖም ቀደም ሲል እንዳልኩት እኛ ማን በሕዝባችን እና በአገራችን ላይ ያንዣበበውን ክፉ አደጋ ይኸው ቸል ብለነዋል:: ለነገሩ «በቅድሚያ ከራስ ነው ትግል» እንደሚባለው በራሳችን ቤት ውስጥ ያለውን ለመግለጽ ያህል በፀረ-ሽብርተኝነቱ ውስጥ የምንገኝ ጥቂት ጓዶች አደጋ ማንዣበቡን ብንገልጽ በደፈናው «ሞት አርጂዎች» ብለው አጣጣሉን:: እናም ከዚህ በበቂ እንግር ዘንድ አሁንም ቢሆን ካለኝ ተሞክሮ ተነስቼ አገርና ሕዝብ የጦርነት አደጋ እንዳንዣበበበት ልገልጽ እወዳለሁ::

ክቡራትና ክቡራን የተከበረው ም/ቤት አባላት፣ ክቡር ሊቀመንበር፣ በግንቦት ወር 1999 በብሔራዊው የፍትህ ኢንስቲቲውት በተካሄደው ኮንፈረንስ ላይ፣ «Terrorism & Technology: Theat and Challenge in the 21st Century» በሚል ርዕስ ባቀረብኩት ጽሁፍ ላይ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰና እያደገ በመጣው ሽብርተኝነት ዙሪያ እንደ አገርና ሕዝብ በቂ ዝግጅት አለማድረጋችንን ጠቁሜ ነበረ:: እስኪ በዚሁ ጽሁፌ ከጠቀስኳቸው ነገሮች ዋቢ አድርጌ አንዳንዶቹን ላቅርብ፣

የሁለተኛው የዓለም ጦርነት በድንገትና ባልተጠበቀ ሁኔታ መጠናቀቅ በዓለም ዓቀፍ ትብብር፣ መንግሥታት እንደ ሽብርተኝነት እና የተደራጀ ወንጀለኝነት ላይ ባሉት ጉዳዮች ላይ የሚያራምዱትን አቋም ላይ ለውጥ ይመጣል ተብሎ ተጠብቆ ነበረ። ነገር ግን በተለይ በዚህ ረገድ አሜሪካ ከጥቂት ስትራቴጂካዊ ጉዳዮች በቀር የተጠበቀውን ለማምጣት ከተሳናቸው ተርታ በማንባር ቀደምትነት ትሰለፋለች። ዛሬም ሽብርተኝነት ትልቅ የተደቀነብን አደጋ ሲሆን አንዳንድ የዚህ አደጋ ምንጮችም ገና ያልታወቁ ናቸው።

በሽብርተኝነት አማካይነት ያንዣበበው አደጋ በሚከተሉት ምክንያቶች ነው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተለወጠና እየተባባሰ የመጣው፣

1. በአገርም ሆነ በዓለም ዓቀፍ ደረጃ የሚንቀሳቀሱ የአሸባሪ ወገኖች ፍልስፍና፣ ዋንኛ ግብ እና መርህ እየተቀየረ መምጣቱ፣
2. አዲስ የምንላቸው የሽብርተኛ ወገኖች በብዛት እንደታየው ጅምላ እልቂትን ማስከተል ዋንኛው ግባቸው አይደለም፣
3. ባሁን ሰዓት አሸባሪዎች የአሜሪካን ዋና ዋና መዋቅሮች፣ ፋሲሊቲዎች እና መ/ቤቶች ጨምሮ በርካታ መረጃ በእጃቸው ይገኛል፣
4. በተለያዩ የዓለም ዓቀፍ የተደራጁ የወንጀል ቡድኖች የሚታገዙት አሸባሪዎች ጅምላ ጨራሽ መሳሪያዎችን በቀላሉ ያገኛሉ።
5. በዛሬ ጊዜ እንተርኔት በመጠቀም አሸባሪዎች የ C31 (Command, Control, Communication and Intelligence) አሠራርን በመጠቀም ፕሮፓጋንዳውን ማሰራጨት ይችላሉ።
6. በአገር ውስጥ የሚገኙ ፀረ-መንግሥት ተቃዋሚ ሃይሎች በተለይም አክራሪዎች ከመቼውም ጊዜ በላይ በመጠናከር ለፌዴራል

መንግስቱም ሆነ በየደረጃው ለሚገኙ የሕግ አስከባሪ አካላት ጋሬጣ በመፍጠር ላይ ይገኛሉ::

የተደራጁ ወንጀለኛ ድርጅቶች በመዋቅራቸውና ባላቸው አቅም ይበልጡኑ ዓለም ዓቀፋዊ ይዘትን እየተጎናፀፉ ሲመጡ የአገራት ድንበሮችም ያን ያህል አያስቸግሯቸውም:: ከዚህም በተጨማሪ በንግዱ ዓለም ልውውጥን እጅግ ቀላልና ቀልጣፋ ለማድረግ ሲባል የተነሱት ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጋሬጣዎች የእነሱን የንግድና የባንክ ንክኪዎችና ሂደቶች ቀላል ያደርጉላቸዋል:: እነዚህ ቡድኖች ከዚህ ቀደም በትብብር አብረዋቸው ሰርተዋቸው ከማያውቋቸው ጋር ለመስራት ያላቸው ተነሳሽነት በእጅጉ የሚደነቅ ሲሆን ለአስተዳደርና ለፀጥታ ግን ችግር እየፈጠሩ የመምጣታቸው ዕድል እጅግ እየተበራከተ ይገኛል::
እነዚህ ሁሉ ድንበር-ተሻጋሪ (trans-national) ቡድኖች ከበፊቱ የበለጠ በሚሰሩት ወንጀል የረቀቁ ዘዴዎችን የሚጠቀሙ፤ በቢዝነስና ፋይናንስም የላቁ ቴክኖሎጂ ውጤቶችን የሚጠቀሙ ሆነዋል:: እንዲያውም አንዳንዶቹ የሚጠቀሟቸው ዘመናዊ የኮምዩኒኬሽን እና መገናኛ ዘዴዎች እጅግ በጣም የረቀቁ ከመሆናቸው የተነሣ አንዳንድ መንግሥታት እንኳ በገዛ አገራቸው ቡድኖቹን አድነው ሊያገኟቸው አልቻሉም::

# አባሪ 7

የመስከረም አንዱን ጥቃት አስመልክቶ በ2004 አሜሪካ ለሕዝብ ይፋ ያደረገችው ሪፖርት የኦሳማ ቢን ላደንን ምስል በተሟላ ሁኔታ አቅርቦታል:: ኮሚሽኑ ኦሳማ ቢን ላደንን እና ዓለምን አስመልክቶ የያዘውን አቋም ከገለፀባቸው ውስጥ የሚከተሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው:: እንደተለመደውም ይህንን የኮሚሽኑን ይፋዊ ሪፖርት በኢንተርኔት አግኝታችሁ ማንበብ ለምትፈልጉት ሁሉ በ:http://www.9-11commission.gov/report/911Report.pdf ላይ ያለላችሁ መሆኑን እገልፃለሁ::

2.2 ቢን ላደን በሙስሊሙ ዓለም ፊት የሚቆምበት ምርኩዝ: በመሠረቱ ይህንን ሰናይ ዋንኛው መታወቅ ያለበት ነገር እጅግ በጣም ብጥብጥ፣ ጥቃት እና ትርምስ በሚበዛበት ሁኔታ ውስጥ ብቻ የሚዳብር ዓላማ ነው:: ታሪካዊ የሚባል ድሉን ለመቀዳጀት ጫፍ ላይ የደረሰ ድርጅትን ነው የምናየው:: ለመሆኑ ኦሳማ ቢን ላደን——አሜሪካውያንን በሙላ ማጥፋት አለብን የሚል ሰው——በሚልዮኖች በሚበልጡ ሕዝቦች ድጋፍና አድናቆትን ሊያተርፍ ቻለ? ቢን ላደን ያለፈባቸው እና መልዕክቱን ሊያስፋፋ የቻለባቸው የአስተዳደግ፣ የባሕል እና ሌሎች የእምነት ሁኔታዎች ለብዙ አሜሪካውያን የማይታወቁ ናቸው:: የእስልምናን ያለፈ በታሪክ የታወቀ ትልቅነት በማንገብ በዛሬው ጊዜ ባንድም ሆነ በተለያዩ ምክንያቶች ራሳቸውን በሌሎች መንግሥታት ቁጥጥር ስር እንደወደቁ አድርገው በሚቆጥሩ ሰዎች ዘንድ ያጣችሁትን ክብርና ዝና እመልስላችኋለሁ ነው የሚለው:: የቁርዓንን ባህላዊ እና ሃይማኖታዊ ጽቁታዎች በማውሳት አንዳንድ ትርጓሜዎቹንም በመጠቀም ላይ ነው ኦሳማ በእልምናው ዓለም ታዋቂ ለመሆን የሚያደርገው ጥረት ያነጣጠረው::

በተለይም ግሎባላይዜሽን እና ዘመናዊነት ከመምጣቱ ጋር ተያይዞ ለውጡ የበዬ-ተመልካች ወይንም አናሳ ተጎጂ ያደረጋቸውን የዓለማችን ድሪዎች መርጦ ነው «ነፃ ሳውጣችሁ» የሚላቸው:: ቢን ላደን ተቀባይነትን ለማግኘት ሕዝብ ፊት የሚያነሳቸው ጉዳዮች የሚከተሉት ናቸው—ታሪክ፣ እስልምና እንዲሁም የክፍለ ዓለሙ የኢኮኖሚ ጉዳት:: ከዚህ በተጨማሪም በሙስሊሙ ዓለም በስፋት የሚታወቀውን እና ተቀባይነት ያገኘውን አሜሪካ ላይ ያለ ቂምና ሮሮ ይጠቀማል:: በሙስሊሙ ዓለም እጅግ ቅዱስ ከተባሉ ስፍራዎች የዋናዎቹ መገኛ በሆነችው ሳውዲ ዓረቢያ ውስጥ የአሜሪካ ወታደሮች በነበሩ ሰዓት በግልጽ ዘለፋ አካሂዶባቸዋል:: የኢራቅ ሕዝብ ከባሕረ ሰላጤው ጦርነት በኋላ በተጣለበት ማዕቀብ እና አሜሪካ ለእስራኤል በምታደርገው ያልተቋረጠ ድጋፍ የተነሳ ለጉዳት መዳረጉን በተደጋጋሚ ተናግሯል::

# እስልምና

እስላም (ቃሉን በቀደመውና ትክክለኛ ትርጉሙ ስናየው *ለአምላክ ፈቃድ ራስን ማስገዛት* ማለት ነው) በቅድስቷ ሥፍራ ለነቢዩ መሐመድ እንደተገለፀላቸው በሙስሊሞች ከሚታመንባቸው የተለያዩ ራዕዮች በኋላ የመነጨ ነው:: ይህች የተቀደሰች ሥፍራ ደግሞ ለአንዱና ለብቸኛው አምላክ ማለትም የአብርሐም እና የኢየሱስ አምላክ መገኛ ናት:: እነዚህ በመላኩ ጅብሪል አማካይነት ለነቢዩ መሐመድ የተገለፁላቸው ራዕዮች በቅዱስ ቁርዓን ላይ ሰፍረው ይገኛሉ:: ሙስሊሞች እንደሚያምኑት ከሆነ እነዚህ በወቅቱ ከነበሩ ነቢዮች ሁሉ ማለት ከአብርሐም ጊዜ ጀምሮ እስከ ኢየሱስ ድረስ ከተፈጠሩቱ ውስጥ የመጨረሻው ለነበሩት ለነቢዩ መሀመድ የተገለፁት ራዕዮች አምላክ ለሰው ልጆች ያስተላለፋቸው የተሟሉ መልዕክቶች ናቸው:: ሌላው እና ሐዲዝ በመባል የሚታወቀው በነቢዩ

ሆነ አሁን ሲታይ ታዓምራዊ ይመስላል:: በመሆኑም የዚያ የእስልምና እድገ አስገራሚ ጥንካሬ ተመልሶ መምጣት ናፍቆት (Nostalgia) ባሁን ሰዓት ብዙውን ሙስሊም የሚያነቃንቅ ጉዳይ ሆኗል::«

እስልምና በማንኛውም ህይወት የእምነት ብቻ ሳይሆን የአኗኗር መመሪያም ጭምር መሆን ችሏል:: ለብዙው የሙስሊም እምነት ተከታይ ጥሩ የሚባለው የመንግሥት አስተዳደር በጠንካራ የእምነታቸው መሠረት ላይ ያተኮረው ነው:: በእርግጥ ይህ ሲባል ግን በኢማሞች የሚገዛ፣ ሙሉ በሙሉ ሃይማኖታዊ መንግሥትን መፈለግ ማለት ላይሆን ይችላል:: ነገር ግን የሙስሊም መንግሥታት በሃይማኖት እና በመንግሥት መሀከል ልዩነት ማድረግ ችለው ቢቆዩም ለአንዳንድ ሙስሊሞች ግን ይህን ዓይነቱን ልዩነት መፍጠር ይከብዳቸዋል:: አክራሪዎችን ብናይ ደግሞ እንደ ፓርላማ እና የሕግ አውጪ መፈጠር የሙስሊም መሪዎችን «ከእግዚአብሔር ስልጣን ቀምተው በስሙ የሚያጭበረብሩ» ያስብላቸዋል:: አክራሪነት ከጊዜ ወደ ጊዜ ራሱን በማስፋፋት በእንግሊዝኛው fundamentalism ወደሚባለው ደረጃ ደርሷል:: አንዳንድ የእስልምና እምነት አራማጆች ደግሞ በምዕመኑ ዘንድ ያለውን ግርምቢጥነት (waywardness) በማውገዝ በቀጥታ ቅዱስ ቁርዓን እና ሐዲዝ በሚሉት መመራት ይሻላል የሚል ሀሳብ ሲሰነዝሩ ይደመጣል:: ለምሳሌም ቢን ላደን አዘውትሮ የሚጠቅሰው አንዱ በ 14ኛው ክፍለ ዘመን የነበረ ምሁር ኢብን ጣይሚያ የሚባል ሲሆን ይህ ምሁርም በወቅቱ በሙስና የተዘፈቁ ገዢዎችንም ሆነ እነሱን የሚታገሷቸውን የሃይማኖት መሪዎች አጥብቆ ይኮንን ነበረ:: ሙስሊሙ እንደ እሱ በተማረው መንገድ ለመተርጎም ብቻ ሳይሆን ቁርዓን እና ሐዲዝን በማንበብ በዕለት ተዕለት ሕይወቱም ሕግጋቱን አንድም ሳያስቀር በማክበር እንዲመራበት መክሯል:: አክራሪ የእስልምና እምነት አራማጆች እንደሚሉን ከሆነ እስልምና ከዚያ በታሪክ ከሚታወቀው የድኅረ-ነቢዩ

መሐመድ የወርቃማ ጊዜ ጥንካሬው እየተዳከመ የመጣበት ዋንኛ ምክንያት በንጉሶቹ እንዲሁም እምነቱን በመሸሽ መሬቱን ሀብቱን ብሎም ነፍሱን ጭምር ለመንጠቅ በመጡት ወራሪ የውጭ ሃይሎች ቁጥጥር ሥር እምነቱ ሲወድቅ ዝምብሎ ያየው ሕዝብ ምክንያት ነው።

# የቢን ላደን የዓለም እይታ

ቢን ላደን ሲናገር ለመላው ዓለም ሙስሊሞች ይሁን እንጂ ዓለምን የሚያይበት መነጽር በጣም ጠበብ ያለ እና ከሙስሊሞች ውስጥ ዓረቦችን እና ሱኒዎችን ብቻ የሚማርክ ነው። ልክ እንደ fundamentalism አራማጆች ቢን ላደንም ካሊፌት የተባለው አመራር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተዳከመ እና እየፈራረሰ ለመምጣቱ ዋንኛ ተጠያቂዎቹ የእስልምናን ዋንኛ እና ጥብቅ መንገድ እየተዉ የመጡ ያላቸው መሪዎች ናቸው። «የጭቆና ግድግዳ በጥይት ናዳና ዝናም ካልሆን አይናድምና» የሚለው ቢን ላደን ተከታዮቹ ሰማዕት ይሆኑ ዘንድ ነው ጥሪ የሚያቀርበው። ብዙዎች የቀደመውን ጊዜ የእስልምና ጥንካሬ፣ የሰፈነውን ሰላም እና ከስጋት ነፃ የሆነ ሁናቴ በማስታወስ ለማናፍቁቱ ቢን ላደንም፣ «ከዛሬዋ ስጋት በተደጋጋሚ ያጫረባት ዓለም የምንገላገለው ካሊፌቱን መልሰን በመጫን ነው» የሚል አማራጭ ይሰጣቸዋል። በሌሎች እይታ ደግሞ የቢን ላደን የዓለም ገለፃ እጅግ የተቃለለ እና ወረድ ያለ ነው። ከዚህ በተጨማሪም ቢን ላደን ሳይድ ቁጥብ በተባለው የግብጽ ፀሀፊ ላይ ይመካል። ይህ በ 1958 ላይ መንግሥት በመገልበጥ ሙከራ ተከስሶ የተገደለው የሙስሊም ወንድማማችነት አባል የነበረው ሳይድ ቁትብ የእስልምናን አስተምህሮት ብዙም ጨብጦ ካልያዘው ነገር ግን ራሱ አመቻችቶ በፈጠረውና ከተረዳው የምዕራብ አስተሳሰብ ጋር ለመቀላቀል ይሞክር ነበረ። በ1940 ግድም በግብጽ መንግሥት ለከፍተኛ ትምህርት ወደ አሜሪካ ተልኮ የነበረው

ቁጥብ ሲመለስ የምዕራባውያንን አስተሳሰብና ባሕል ከምንም በላይ አጥብቆ የሚጠላ ሰው ሆነ። ምዕራቡ ያገኘውን ድልም ሆነ ትልቅ የሚባል ነገር በግልጽ የሚያጣጥለው ቁጥብ፣ «ምዕራቡ የገዛ ሕሊናውን ለማርካት የሚሆንም ሆነ በዚህች ዓለም ላይ የሚኖርበት ዓላማ አለኝ ብሎ ለመናገር የሚያበቃ እንጥፍጣፊ ድፍረት የሌለው ነው» ብሏል።

ከቁጥብ ጽሁፎች ሶስት ዋና ዋና አመለካከቶችን እናገኛለን። የመጀመሪያው ለነቢዩ መሐመድ ራእይ ከመገለፁ በፊት የነበረውን መደዴነት (barbarism)፥ ዝሙተኝነት (licentiousness) እና ኢ-አማኒነት (unbelief) ተዛምዶ የነበረበት ጊዜ ሲሆን ይህንንም ጃሂሊያ ብሎ ይጠራዋል። እንደ ቁጥብ አስተሳሰብ ከሆነ የሰው ልጅ ያለው አማራጭ ወይ እስልምናን መከተል አልያም ጃሂሊያ ውስጥ ገብቶ መጨማለቅ ነው። በሁለተኛ ደረጃ ቁጥብ የሚለን ደግሞ አብዛኛው ሙስሊም ሕዝብ በሚያሳዝን ሁኔታ በጃሂሊያ የሀጢአት ሕይወት ውስጥ ያለው ቁሣዊ ምቾት ስለሚበልጥበት ጃሂሊያ በእስልምና ላይ የበላይነት ይቀዳጃል። በሶስተኛ ደረጃ ደግሞ በቁጥብ አስተሳሰብ አምላክና ሰይጣን በሚያደርጉት ትግል መሀከል አንዱን መምረጥ እንጂ መሀል ሰፋሪነትም ሆነ ሶስተኛ አማራጭ ብሎ ነገር ኩቶ ሊኖር አይችልም። በመሆኑም ሁሉም ሙስሊሞች ጦራቸውን ሰብቀው ይህንን አገዛዝ መፋለም አለባቸው። ይህንን የሱን ጥሪም ሆነ አስተሳሰብ አልቀበልም የሚል ሙስሊም ቢኖር እሱ እምነቱን የካደ እና ውጉዝ ራሱም ጥቃት ሊሰነዘርበት የሚገባ ነው።

እንግዲህ ዋንኛ ትኩረታችን የሆነው ዑሣማ ኢብን መሐመድ ቢን ላደንም ይህን መሰሉን የቁጥብን ጭፍን የዓለም አመለካከት የሚጋራ ሰው ነው። ለዚህ ነው በንጹሀን ላይ እንዲሁ የሚወሰድን የጅምላ እልቂት ሃይማኖትን

እንደመከላከያ እና መጠበቂያ አድርጎ ለማሳየት የሚሞክረው። ብዙ አሜሪካውያን፡

*«ማን ምን አድርገናቸው ነው የሚጠሉን?» ወይንም፣ «ምን ብናደርጋቸው ነው ከዚህ ጥላቻቸው ልናስወጣቸው የምንችለው?»*

ብለው ሲጠይቁ ይሰማሉ።

ቢን ላደን እና ዓል-ቃኢዳ ለነዚህ ሁለት ጥያቄዎች የሚሆኑ ምላሾችን ሰጥተዋል። ለመጀመሪያው ጥያቄ መልስ ሲሰጡ ኦሳማ ቢን ላደን እና ዓል-ቃይዳ አሜሪካ ጥቃት ፈጽማብናለች ይላሉ። ሙስሊሞች በነበሩባቸው ግጭቶች ሁሉ ዋንኛ ተጠያቂ እሷው ራሷ ናት ብለው ይሞግታሉ። እንግዲህ ይህ ማለት እስራኤል ተነስታ ከፍልስጤም ብትጣላ፣ ሩሲያውያኑ ቼቼኒያን ሲወጉ፣ ሕንድና ካሽሚር ሲጫረሱ፣ አልያም የፊሊፒንስ መንግሥት በደቡባዊ ደሴቶች ግድም የሚገኙ እናሳ ብሔሮች ተፋላሚዎቹን ወይንም አማጺዎቹን እጨፈልቃለሁ ሲል ሁሉ፣ «አሜሪካ ናት» ሊሉን ነው። ከዚህ በተጨማሪም የተለያዩ ሙስሊም መንግሥታት ባለም ላይ መኖራቸው ሁሉ በዓል-ቃይዳ አስተሳሰብ «የአሜሪካ ሥራ ነው» ሊባል ነው። እነዚህ መንግሥታትም «እናንተ አሻንጉሊቶች፣ ተላላኪዎች፣ ሞግዚቶች» ተብለው ተዘልፈዋል። ቢን ላደንም በግልጽ ለአሜሪካኖች፡

*«እነዚህን የሙስሊም መንግስታት ስንፋለም*
*እናንተን አሜሪካውያንን ራሳችሁን መፋለም*
*ማለት መሆኑ ይግባችሁ!»*

ብሎ እቅጩን ተናግሯል። ግን የሚያሳዝነው የኢራቅን ሁኔታ፣ ፍልስጠ ,ምን ብሎም አሜሪካ ለጨቋኝ እና አፋኝ መንግሥትታ የምትሰጠው ድጋፍ

እንደምክንያት ተወስዶ ይህ የቢን ላደን አመለካከት በሚልዮኖች የሚደገፍ በመሆኑ ነው፡፡«

ቢን ላደን በአሜሪካ ላይ ቂምና ጥላቻ ማንገብ የጀመረው በጥቂት የአሜሪካ ፖሊሲዎችና እርምጃዎች የተነሳ ቢሆንም አሁን ግን ሥር እየሰደደ መጥቷል፡፡ የሁለተኛውን ጥያቄ ሲመልሱ ደግሞ ቢን ላደን እና ዓል-ቃይዳ አሜሪካ መከከለኛው ምስራቅን እርግፍ አድርጋ መተው፣ ራሷን ወደ እስልምና መቀየር ከዚያም ሲያልፍ የሕዝቧን ቆሻሻ ባሕል እና ከግብረገብነት የወጣ ባሕሪ ማውገዝ እንዳለባት ይናገራሉ፡፡

> *«በጣም ቢያሳዝንም እንደ እናንተ ዓይነት የተዋረደና አስቀያሚ ስልጣኔ በዓለማችን ታይቶ አያውቅም»*

አሜሪካ ይህንን ካላደረግም ብትል ቢን ላደን እና ዓል-ቃይዳ፣

> *«እንግዲያማ እናንተ ለመኖር ከምትፈልጉት በላይ ሞትን ከሚሻው ሙስሊም ጋር ጦርነት ትገጥማላችሁ!»*

ብለዋል፡፡

# ቅጥያ

# አወዛጋቢው ቢን ላደንን የመግደል ዘመቻ

ለበርካታ ዓመታት ቢን ላደንን ፍለጋ የወጡ እጆች በሙሉ ባዷቸውን ለመመለስ ሲገደዱ ቆይተዋል፡፡ በሐምሌ 2010 ታዲያ ለሲአይኤ የሚሰሩ ፓኪስታናውያን በፔሻዋር ጉዳና እንዲት ነጭ ሱዚኪን ተከታትለው የታርጋ ቁጥሯን በመመዝገብ ላይ ነበሩ፡፡

መኪናዋ ውስጥ የነበረው ሰው የቢን ላደን ታማኝ ተላላኪ ነው፡፡ በቀጣዮቹ ወራት የሲአይኤ ሰዎች በመሃል ፓኪስታን ያለማቋረጥ እየተከታተሉት ቆዩ፡፡ ባለስልጣናቱ እንደሚሉት ሰውዬው የመራቸው ከዋና ከተማዋ 35 ማይል ርቀት ላይ ከረዥም የቆሻሻ ክምር ቀጥሎ ወደሚገኝ በደህንነት ሽቦ የታጠረ ቅጥር ነው፡፡

ከስምንት ወራት በኋላ ጨረቃ በሌለችበት አንድ ሌሊት 79 የአሜሪካ ኮማንዶዎች በአራት ሄሊኮፕተሮች ተጭነው ወደግቢው ወረዱ፡፡ የጠበቃቸውም ተኩስ ነበር፡፡ አንደኛዋ ሄሌኮፕተርም ተበላሽታ መነሳት አቃታት፡፡ ስለተልዕኮው ምንም ያልተነገራቸው የፓኪስታን ባለስልጣናት አሜሪካውያኑ ስራቸውን አጠናቀው ለመሄድ ሲጣደፉ ገና ወታደሮችን በማሰማራት ላይ ነበሩ፡፡ ከተገደሉት አምስት ሰዎች መካከል አንደኛው ረዥምና ፂማም ሲሆን አናቱ በጥይት ተበስቷል፡፡ ከባህር ኃይል አባላት አንደኛው ፎቶውን በካሜራ አንስቶ ለተንታኞች ላከላቸው፡፡ እነሱም ወደፊት መለያ ሶፍትዌር አስገቡት፡፡ አዎ እርሱ ነው - ሰውዬው፡፡

በእንደዚህ ዐይነት ሁኔታ ነበር በታሪክ ቀዳሚው ተሰፋፊ፣ ውድና አስጨናቂ ሰው አደን የተጠናቀቀው። የአሜሪካ ቁጥር አንድ ጠላት ሰው አስከሬንም በሄሊኮፕተር ተጭኖ ከእንግዲህ ላይታይና ላይፈራ በባህር ተቀበረ። ከአስር ዓመታት በላይ ከ3,000 በላይ ዜጐቿን በአንድ ቀን የፈጀባትን ሰው አድና መያዝ አቅቷት የነበረች አገር በስተመጨረሻ ቢያንስ የመጀመሪያውን ምዕራፍ በድል ዘግታ ሁለተኛውን ምዕራፍ ገልባለች።

ከደርዘን የሚልቁ የኋይት ሃውስ የደህንነት እና የመከላከያ ባለስልጣናት እንደገለፁት ያለፉት ጥቂት ሳምንታት በስጋትና ፍርሃት የታጀቡ ነበሩ። "ብላክ ሃውክ ዳውን" ሳይጠቀስ የታለፈበት አንድም ስብሰባ አልነበረም" በማለት ነበር አንድ ባለስልጣን ሁለት የአሜሪካ ሄሊኮፕተሮች ተመትተው ወታደሮቹ የተገደሉና የተሰቃዩበት የ1993 የሶማሊያ ጦርነት አጥልቶት የነበረውን ጥላ የገለፁት። ሳይሳካ የቀረውና በ1980 ኢራን ውስጥ ታጋቾችን ለማስለቀቅ የተደረገው ዘመቻም የራሱ ተፅዕኖ ነበረው እንደባለስልጣኑ ገለፃ።

እሁድ ከሰዓት በኋላ ሄሊኮፕተሮቹ የፓኪስታንን ድንበር አቋርጠው ሲገሰግሱ ፕሬዝዳንት ኦባማና አማካሪዎቻቸው በኋይት ሃውስ ቁጭ ብለው ክስተቱን በቀጥታ በመከታተል ላይ ነበሩ። አንድ ረዳታቸው እንደገለፀው የኦባማ ፊት አመድ መስሎ ነበር። የኋይታ ሃውስ ፀረ ሽብር ኃላፊ " ደቂቃዎች የቀን ያህል የረዘሙ ነበሩ" ብለዋል።

የቢን ላደን የኮድ ስም "ገሮኒሞ" ነው። ፕሬዚዳንቱና አማካሪዎቻቸው የሲአይኤው ኃላፊ ሊዮን ኢ.ፓኔታ በዋና መስሪያ ቤታቸው ቁጭ ብለው ፓኪስታን ውስጥ እየኾነ ስላለው ነገር የሚገልፁትን ነበር በቪዲዮ ስክሪን አፍጥጠው የሚከታተሉት።

" ወደ ኢላማው ተጠግተዋል" አሉ ፓኔታ።

ደቂቃዎች አለፉ።

"ገሮኒምን እያየነው ነው"

ከጥቂት ደቂዎዎች በኋላ "ገሮኒም EKIA" አሉ።

EKIA-Enemy Killed in Action /ጠላት በእንቅስቃሴ ወቅት ተገድሏል ማለት ነው። ክፍሉ ውስጥ ፀጥታ ሰፈነ።

በመጨረሻም ፕሬዝዳንቱ ተናገሩ።

"አገኘነው"

# ሂደቱ እንዴት ነበር?

የመስከረሙ አስራ አንዱ ጥቃት ቢን ላደንን ዓለማቀፋዊ እውቅና ከማጎናፀፉ በፊት በነበሩት ዓመታት በሽብር መረቡ ውስጥ ቁልፍ ሚና ያላቸውን ሰዎች ለማወቅ ሲ.አይ.ኤ መረጃ ሲያሰባስብ ነበር። በ2002 የአልቃኢዳ ቅጥረኞችን በማያቋርጥ አስከፊ ምርመራ ማጣያፍ ከመጀመሩ በፊት ግን ስለቢን ላደን የቅርብ ሰዎችም ሆነ የገንዘብ ምንጭ ጠብ ያለለት መረጃ አልነበረም። በአሜሪካ ለፍርድ የቀረቡ እስረኞች ስለ 'ታማኝ ተላላኪው' የተናገሯቸው ታሪኮች ነበሩ። ይሁንና መርማሪዎች የሰውዬውን ስም አንስተው የመስከረም አስራ አንዱን ጥቃት አቀናባሪ ካህሊድ ሼክ ማሐመድንም ሆነ የአልቃኢዳ ኦፕሬሽኖች ኃላፊ አቡ ፋራጅ አል ሊቢን ለማውጣጣት ቢሞክሩ ስሙን ስምተውት እንደማያውቁ በመግለፃቸው መርማሪዎቹ ምናልባትም ይህ ሰው በጣም ወሳኝ መሆን አለበት የሚል ጥርጣሬ ተጫረባቸው።

በ2005 ሲአይኤዎች በቢን ላደን ላይ የጀመሩት አደን መቀዛቀዙን ተመልክተው ጥገናዊ ለውጥ አካሄዱ። በአርምጃውም ተጨማሪ የሲአይኤ መርማሪዎች ወደ ፓኪስታንና አፍጋኒስታን ተላኩ።

በርካታ ወኪሎቹን ያሰማራው ሲአይኤ በመጨረሻ የተላላኪውን የቤተሰብ ስም ደረሰበት። ከዚያም በቤተሰቦቹና ፓኪስታን ውስጥ ባለ ማንኛውም ሰው መካከል የሚካሄዱ የስልክና የኢሜል መልዕክት ልውውጦችን መጥለፍ ጀመሩ። እናም ሙሉ ስሙን ለማግኘት ቻሉ። በሐምሌ ወር 2010 ፓኪስታናዊ የሲአይኤ ወኪሎች ሰውዬው ወደ አቦታባዱ ቅጥር ግቢ ሲገባ ባዩት ጊዜ የአሜሪካ ደህንነቶች አንድ ታላቅ ዒላማ ምናልባትም ቢን ላደንን ራሱን እየተከታተሉ መሆኑ ገባቸው። ለካ አብዛኞቹ ዋሻ ውስጥ መሽጓል ብለው ያመኑለት ሰው በባለ ሶስት ፎቅ ቪላ ውስጥ ሁለት ዙር የደህንነት አጥር አሳጥሮ በጎይት ሃውሱ ባለስልጣን ብሬናን አገላለጽ ፊት ለፊታቸው ተደብቆ ነበር።

ዋሽንግተን ውስጥ ፓኔታ ከኦባማና ባይደን፣ ሂላሪ ሮድሃም ክሊንተን እና ሮበርት ጌትስን ከያዘ ከፍተኛ የደህንነት አማካሪዎች ቡድን ጋር ጥብቅ ስብሰባ ላይ ነበሩ። ስብሰባው በከፍተኛ ምስጢር በመያዙ የተነሳ ባለስልጣናቱ በተላላኪቸው መልዕክቶች ላይ እንኳን አጀንዳውን አልጠቀሱትም። በዚያው ቀን ፓኔት ስለቢን ላደንና ይገኝበታል ስለተባለው ቦታ ሰፊ ማብራሪያ ሰጡ። በስብሰባው የተሳተፈ አንድ የአስተዳድር ባለስልጣን ሁኔታውን ሲገልፀው "ለረዥም ጊዜያት ስንከታተለው አስቸግሮን የነበረን ሰው በድንገት ያውና እንደማለት ነበር የሆነብን። እንደኤሌክትሪክ ነዝሮናል።" ይላል።

ቢን ላደን በተጠረጠረው ቤት ውስጥ የቱ ጋ ሊኖር እንደሚችል የመገመት ስራም ሲሰራ ቆይቷል፡፡ በፓኔታ እና ባልደረቦቻቸው መካከልም ለሳምንታት በርካታ የምክክር ስብሰባዎች ሲካሄዱ ነበር፡፡ ፓኔታ የቢን ላደን በዚያ መኖር በተለያዩ መንገዶች በአሳማኝ ሁኔታ መረጋገጥ አለበት ሲሉ አብዛኞቹ የሲአይኤ ባልደረቦች ግን ምናልባት የቤቱ ጠባቂዎች አካባቢው እየተሰለለ መሆኑን ለአፍታ እንኳን ከተጠራጠሩ ከዓመታት በኋላ የተገኘው ወርቃማ ዕድል ቢን ላደንን በማስመለጥ እንዳይጠቀለል የሚል ስጋታቸውን በተደጋጋሚ ሲያንፀባርቁ ነበር፡፡

ለሳምንታት የስለላ ሳተላይቶች ቤቱን በተደጋጋሚ ፎቶ በማንሳትና ከቤቱ የሚወጡና ወደ ቤቱ የሚደረጉ ግንኙነቶችን በሙሉ በመጥለፍ ሙከራ ተወጥረው ነበር፡፡ ቀላል ስራ ግን አልነበረም፡፡ ግቢው የስልክም ሆነ የኢንተርኔት ግንኙነት አይደረግበትም፡፡ በውስጡ ያሉ ሰዎች ለደህንነት ከፍተኛ ዋጋ በመስጠታቸው ቆሻሻቸውን እንኳን ከግቢ ውጪ አውጥተው አይጥሉም፤ በራሳቸው ያቃጥሉታል እንጂ፡፡

የካቲት ውስጥ ፓኔታ የፔንታጎኑን ልዩ ኦፕሬሽኖች አዛዥ ዊሊያም ኤች ማክራቨንን ወደቢሯቸው ጠርተው በዚያ ግቢ ስለሚካሄደው ጥቃት ዕቅድ ተወያዩ፡፡ አድሚራል ማክራቨን ከሳምንታት ጥናት በኋላ ሶስት የጥቃት አማራጮችን አቀረቡ፡፡ ኮማንዶዎችን ተጠቅሞ በሄሊኮፕተር ማጥቃት፣ በቢ-2 ቦምቦች ግቢውን ማጋየት እና ከፓኪስታን ኃይሎች ጋር በጋራ የሚካሄድ ጥቃት መክፈት የሚሉ፡፡

# ውሳኔው

መጋቢት 14 ላይ ፓኔታ ጉዳዩን ወደ ኋይት ሃውስ ወሰዱት፡፡ ፓኔታ እንደሚሉት በዚያ ወቅት በግቢው ውስጥ የሚኖሩት ሰዎች ልማድ ተጠንቶ ቢን ላደን በዚያው እንዳለ የሚያረጋግጡ ጠቋሚዎች ደረጃ ከፍ ብሏል ፡፡

የሲአይኤው አባል ሬይሞንድ ዴቪስ ጥር ውስጥ በላሆር ከተማ ህዝብ በተሰበሰበበት ሁለት ፓኪስታናውያንን ተኩሶ በመግደሉ በመታሰሩ በአሜሪካና በፓኪስታን መካከል ያለው ግንኙነት ስለሻከረ የተልዕኮው አፈፃፀም ጉዳይ ሰፊ ውይይትና ዝግጅት የሚያስፈልገው ነው፡፡ የኦባማ አማካሪዎች ቢን ላደንን ለመግደል ወይም ለመማረክ የሚደረግ ወታደራዊ ዘመቻ የፓኪስታንን መንግስት ክፉኛ ስለሚያስቆጣ ዴቪስ በታሰረበት እንዲሞት ያደርጋል የሚል ስጋታቸውን ገለፁ፡፡ እንደ አጋጣሚ ግን ዴቪስ መጋቢት 16 መፈታቱ ለባልደረቦቹ የተሻለ ነፃነት ሰጣቸው፡፡

መጋቢት 22 ፕሬዝዳንቱ አማካሪዎቻቸውን ስለተሻለው የጥቃት መንገድ ጠየቁ፡፡ ጌትስ የሄሊኮፕተሩ ጥቃት አደገኛ በመሆኑ ወታደራዊ ባለሙያዎች ከላይ የቦምብ ጥቃት የሚካሄድበትን ዝርዝር እንዲያጠኑ አዘዙ፡፡ ከቀናት በኋላ ባለሙያዎች እያንዳንዳቸው 2,000 ፓውንድ የሚመዝኑ 32 ቦምቦች እንደሚያስፈልጉ አሳወቁ፡፡ ከዚህ ሁሉ ጥቃት በኋላ ግን አሜሪካውያን ቢን ላደንን ስለመግደላቸው እንዴት እርግጠኛ መሆን ይችላሉ፡፡ አንድ የአሜሪካ የደህንነት ኃላፊ ስለዚህኛው አማራጭ "ምንም የሰው አካል ሳናገኝ ትልቅ ጉድጓድ እንፈጥር ነበር" ይላሉ፡፡

በመጨረሻ የሄሊኮፕተሩ ጥቃት የተሻለው አማራጭ ሆኖ ቀረበ። የባህር ኃይል ኮማንዶዎች ከግቢው በሚመሳሰል ቦታ ላይ ጊዜ ወስደው እንዲለማመዱ ተደረገ። ኢላማቸው ማን እንደሆነ ግን እስከመጨረሻው ድረስ አልተነገራቸውም።

ፕሬዝዳንት አባማ ተራ ነገሮች አገሪቱን ትኩረት እያሳጧት ነው ከሚል የብስጭት ንግግር ጋር የልደት ሰርተፊኬታቸውን ይፋ ባደረጉበት ቀን ምሽት ላይ ከከፍተኛ የብሔራዊ ደህንነት ባለስልጣኖቻቸው ጋር ተገናኙ።

ፓኔታ ለተሰብሳቢዎቹ ሲአይኤ በእቅዱ ውስጥ ላልተሳተፉ የተወሰነ አባላቱ ማስረጃዎቹን አሳይቶ ቢን ላደን በአቦታባድ እንደሚገኝ ማረጋገጫ ማግኘቱን አስረዱ። *አሁን ጊዜው የውሳኔ ነው።*

በጠረጴዛው ዙሪያ አሉታዊ ሃሳቦች መንሸራሸራቸውን ቀጠሉ። በመጨረሻ አባማ "ውሳኔዬን አሁን ልነግራችሁ አልችልም። ወደቤቴ ተመልሼ የበለጠ ማሰብ አለብኝ " ካሉ በኋላ " በቶሎ ውሳኔ ላይ እደርሳለሁ" አሉ።

ከአስራ ስድስት ሰዓታት በኋላ ውሳኔ ላይ ደረሱ። በቀጣዩ ቀን ጠዋት አራት የፕሬዝዳንቱ አማካሪዎች በኋይት ሃውስ የዲፕሎማቲክ ክፍል ውስጥ ተሰባስበዋል። ለፕሬዝዳንቱ ማብራሪያ መስጠት ከመጀመራቸው በፊት አባማ ቀድመዋቸው "ወደ ተግባር ይገባ" አሉ። ተልዕኮው ሊፈፀም የሚችልበት ፈጣኑ ቀን ቅዳሜ መሆኑን የገለፁት ባለስልጣናት ነገር ግን ደመናው ለበረራ እንቅፋት ሊሆን እንደሚችል በማሳወቃቸው ዘመቻው ለእሁድ ተቀጠረ።

በቀጣዩ ቀን አባማ የእራት ግብዣቸውን ወደጐን ብለው ለአድሚራል ማክራቨን የመልካም ምኞት የስልክ ጥሪ አደረጉ፡፡

እሁድ እለት ሁሉም ከፍተኛ የብሔራዊ ደህንነት ባለስልጣናት በአንድ ላይ ተሰባስበው የሚኙነውን መጠባበቅ ይዘዋል፡፡

2 ሰዓት ከ5 ደቂቃ ሲሆን ፓኔታ ለተሰባሰበው ቡድን የተልዕኮውን ነድፍ ለመጨረሻ ጊዜ አስረዱ፡፡ በአንድ ሰዓት ውስጥ የሲአይኤው ዳይሬክተር የቪዲዮ መግለጫቸውን መስጠት ጀመሩ፡፡

"የፓኪስታንን ድንበር አቋርጠው ገብተዋል" ሲሉ ጀመሩ፡፡

# ፍጻሜው

ፓኪስታን ውስጥ ከእኩለ ሌሊት ትንሽ አለፍ ያለ ፀጥተኛ ለኞ ምሽት ነበር፡፡ የመጀመሪያዋ ሄሊኮፕተር ዝቅ ብላ እየበረረች ወደ ግቢው ስትጠጋ ጐረቤቶች የጥይት እሩምታዎችን መስማታቸውን ይገልጻሉ፡፡ ከቤቱ ሁለት ማይል ርቀት ላይ የምትኖር አንዲት ሴት በፓኪስታን የጦር ሰፈሮች ላይ የሽብር ጥቃት የደረሰ መስሏት እንደነበር ተናግራለች፡፡ ባለቤቷም ማንም ቢን ላደን በዚያ ይኖራል ብሎ በህልሙ እንኳን ጠርጥሮ እንደማያውቅ ተናግሯል፡፡

የጥቃት ቡድኑ ግቢውን ሲወር ከውስጥ የነበረው ቡድን ነቅቶ ተኩስ ከፈተ፡፡ አንድ ወንድ አንዲትን ሴት እንደከለላ ተጠቅሞ በአሜሪካኖቹ ላይ መተኮስ ጀመረ፡፡ ሁለቱም ተገደሉ፡፡ ሁለት ተጨማሪ ወንዶች ሲገደሉ ሁለት ሴቶችም ቆሰሉ፡፡ የአሜሪካ ባለስልጣናት በኋላ እንዳረጋገጡት ከተገደሉት ወንዶች አንደኛው የቢን ላደን ልጅ ሃምዛ ሲሆን ሌሎቹ ታማኝ ተላላኪና ወንድሙ ናቸው፡፡

የአሜሪካ ባለስልጣናት ቢን ላደን እጁን ለመስጠት ፈቃደኛ ቢሆን ኖሮ ወደፍርድ ለማቅረብ ይፈልጉ እንደነበር ደጋግመው ገልፀዋል። ብሬናንም "ቢን ላደንን በሕይወት መያዝ የምንችልበትን አጋጣሚ ብናገኝና ችግር ባይፈጥር ኖሮ ሰዎቻችን በዚያ መልኩ ተዘጋጅተው ነበር የሄዱት።" ብለዋል።

እንደባለስልጣናቱ ገለፃ የቢን ላደንን ሰውነት የለየችው ከሚስቶቹ አንደኛዋ ናት። በአንደኛው ኮማንዶ የተወሰደና በሶፍትዌር የተካሄደ የፎቶ ትንተናም ቢን ላደን ለመሆኑ የ95 ከመቶ ማረጋገጫ ሰጥቷል። በኋላ ላይ ከዘመዶቹ ጋር የተደረገ የዲኤንኤ ምርመራም 99.9 ማረጋገጫ አስገኝቷል።

አሜሪካኖቹ ሳንካም አጋጥማቸው ነበር። አንደኛዋ ሄሊኮፕተራቸው መነሳት ስላቃታት በተሳሳቱ እጆች ስር ከምትወድቅ በሚል አቃጥለዋታል። በዚያ ሰዓት የፓኪስታን ጦር ገና መንቀሳቀስ መጀመሩ ነበር። "በዚያ ማን እንደነበረ ምንም ፍንጭ አልነበራቸውም።" ያሉት ብሬናን "ከፓኪስታን ኃይሎች ጋር አለመገናኘታችን ተመስገን ነው።" ብለዋል።

አሜሪካኖቹ በቦታው የሰዓት አቆጣጠር 1:10 ላይ ኮምፒዩተሮችንና ጠቃሚ መረጃዎችን ይዘው ዋናዋን ሴትና ከ2 እስከ 12 ዓመት ዕድሜ ያላቸውን ዘጠኝ ልጆች ቤት ውስጥ ትተው ነበር የተንቀሳቀሱት።

የአባማ አስተዳድር የቢን ላደንን አስክሬን ሊቀበል የሚችል ፈቃደኛ አገር ስለማይኖር በ24 ሰዓት ውስጥ በሙስሊም ባህል መሰረት በባህር መቀበር እንዳለበት አስቀድሞ በወሰነው መሰረት እንደዚያ ኾነ። የአሜሪካን ቁጥር አንድ ተፈላጊ ሰው መጨረሻ በዐይን ምስክርነት የተከታተሉ የተባሉት ግን በጣት የሚቆጠሩ የኮማንዶ አባላት ብቻ ናቸው።

# ኦሳማ ቢን ላደንን በፎቶ




ኦሳማ ቢን ላደን ተተኪው ይሆናል ተብሎ ከሚታሰበው

አይማን አልዛዋሃሪ ጋር



ኦሳማ ከልጁና ከልጁ አማት ጋር



ኦሳማ ጋዜጠኛው ፎቶ እንዳያነሳ እየተከላከለ 1998



ኦሳማ በ1998 አፍጋኒስታን ውስጥ ለተከታዮቹ ማብራሪያ እየሰጠ



ከናይሮቢና ዳርኤሰላሙ የአሜሪካ ኤምባሲዎች ጥቃት በኋላ




በ1999 ፓኪስታን ውስጥ ይሸጥ የነበረ የቢንላደንን ምስል የያዘ ፖስተር




በጥቅምት 2001 በአልጀዚራ ቴሌቪዥን የተላለፈ ምስል




በጥቅምት 2001 ‹‹ አሜሪካ የመሐመድን መሬቶች ለቃ እስካልወጣች ድረስ ሰላም አይኖራትም›› በሚል በቪድዮ ተቀርጾ ከተላለፈ መልእክት የተወሰደ



በመጋቢት 2004 በአፍጋኒስታን የሚገኙ ኃይማኖታዊ መሪዎች ያካሄዱት ሰልፍ




በ2005 ፍልስጤማውያን ስደተኞች ካካሄዱት ሰልፍ



በፓኪስታን ዋና ከተማ የሚገኙ ቪዲዮ ቤቶች ከሚያከራዩአቸው
ዲቪዲዎች በአመዛኙ የተዋጊዎችን ታሪክ የሚዘግቡት
ተመራጭ ናቸው



አሳማ ቢን ላደን በ16 ዓመቱ



አሳማ ቢን ላደን በስድስት ዓመቱ



ኦሳማ ቢን ላደን ፓኪስታን አቦታባድ ውስጥ ይኖርበት ነበር የተባለው ቤት



ቢን ላደንን አደን ከወጡት የአሜሪካ ሄሊኮፕተሮች አንደኛዋ
በዚህ መልኩ ተበላሽታ ወድቃ ነበር



የኦሳማ ቢን ላደን አባት መሀመድ ቢን ላደን በ1964



የኦሳማ ቢን ላደን ልጆች

(ፋጢማ፣ሰኢድ፣ኦማር፣መሐመድ፣ኦስማን፣አብዱል እና ራህማን)




ታይም መጽሔት ወሳኝ ሰዎች ሲሞቱ የሚያወጣው ኤክስ ምልክት ያለበት
የፊት ሽፋን



[illegible]

→ የምድራችን ኃያል ሀገራት ከአስር ዓመታት በላይ በአንድ ላይ እስከ የተባበሩበት ቦታ ሁሉ ፈልገው ያጡት የማይጨበጠው የኦሳማ ቢን ላደን ሙሉ የሕይወት ታሪክ ምን ይመስላል? ከኮንስትራክሽንና ከተንደላቀቀ ኑሮስ ይሄንን የመረጠው ለምንድን ነው?

→ አሜሪካንና እስራኤልን ከሁሉም አስበልጦ የጠላበትና ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ የበቀል በትሩን የሚያሳርፍባቸው ለምንድን ነው?

→ አልቃኢዳ እና የመሳሰሉ ድርጅቶች ለምንና እንዴት ተመሰረቱ? በዓለም ዙሪያ ያደረሷቸው ጥቃቶችስ የትኞቹ ናቸው? በተለይ የመስከረም 11ዱን ጥቃት በእንዴት ዓይነት ሁኔታና ዝግጅት አሳኩ? እንዲሁም በመጋቢት 2002 በፓኪስታን ከተካሄደው የአናኮንዳ ኦፕሬሽን ከሞት እንዴት አመለጠ?

→ የኦሳማ ቢንላደን ቀኝ እጅና የአልቃኢዳ ቁልፍ ሰው ዶ/ር አይማን አልዘዋሂሪ ማን ነው?

→ ዓለም ለበርካታ ዓመታት ሲፈልገውና ጭራሽ ተስፋ ወደመቁረጡ የደረሰበትን የቢንላደን ምሽግ ባራክ ሁሴን ኦባማ እንዴትና በምን ሁኔታ አሳኩት?

በተጨማሪም መጽሐፉ በኦሳማ ቢን ላደን አመራር የተፈፀሙ የአጥፍቶ መጥፋት የቦምብ ጥቃቶችና የአውሮፕላን ጠለፋዎችን እውነተኛ ገጽታ በማስረጃዎች ጭምር አስደግፎ የሚያቀርብ ነው። በፎቶ የተደገፉ ማብራሪያዎችም ተካተውበታል።

ዋጋ ብር 35.00

Design & Layout by Thomas Kebede 0911 68 78 39

ንግድ ማተሚያ ድርጅት